የዕንባ ደብዳቤዎች

መቅድም ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከተደረሰ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ አልፎ ታል ። በተለይ ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ ለመ ጨ ፡ ምን ፡ እንደአነሳሳኝ ፤ መቸ ፡ እንደጀመርኩት ፤ በስን ት ፡ ጊዜስ ፡ እንደጨረስኩት ፡ በትክክል ፡ ባላስታውሰው ም ፤ ከውጪኛው ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ በሚገባ ፡ ሳልተ ዋወቅ ፤ የአጻጻፍ ፡ ልምድ ፡ ሳይኖረኝ ፤ ከትምሕርት ፡ ቤት ፡ በመጣሁ ፡ ማግስት ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። ከዚ ህ ፡ ወዲያ ፤ ከትምሕርት ፡ ደብተሮች ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ ለ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ በሳጥን ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ ኖረ ።

እንድ ፡ ቀን ፡ እንደዋዛ ፡ አውጥቸ ፡ በሙሉ ፡ ባንበው ፡ ታሪኩ ፡ ደህና ፡ መስሎ ፡ ተሰማኝ ። እኔም ፤ በግተሚያ ፡ ቤት ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ ብዙ ፡ ደራሲዎች ፡ ሲያማ ርሩ ፡ እሰማ ፡ ነበርና ፤ በቀላሉ ፡ መንገድ ፡ ለአንባቢዎች ፡ ሊያርስ ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ በመፈለግ ፤ ታሪኩን ፡ አሳ ጥሬና ፡ ቀራርጪ ፤ “ንቀዝ ፡ የጣለው ፡ ቤት” ፡ በሚል ፡ አር እስት ፡ በሣሪዱቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጋዜጣ ፡ አስወጣሁት ። ታሪ ኩን ፡ ባጭሩ ፡ አቀራረብ ፡ የተመለከቱት ፡ ጓደኞቸና ፡ ባል ንጀሮች ፡ ጠቅላላውን ፡ ታሪክ ፡ በመጽሐፍ ፡ ጥራዝ ፡ እንዳሳ ትመው ፡ እየደጋገሙ ፡ መከሩኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ ያልደ ረሰ ፡ ሆኖ ፡ አሁንም ፡ እንደገና ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ያህል ፡ ተቀብሮ ፡ ቆይትዋል ።

አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ወደግተሚያ ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ልፈርድበት ፤ በውስጡ ፡ አንዳንድ ፡ ወይንም ፡ ብዙ ፡ የሚ ለዋወጡ ፡ ነገሮች ፡ መኖራቸው ፡ ይሰማኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ እፍላው ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጭንቅላቴ ፡ ያመረተው ፡

ፍሬ ፤ ትምህርት ፥ ቤት፡ ለነበርኩበት ፤ ለዚያ፡ ለመልካሙ፡ ለዚያ ፥ ካለተናትና ፥ ካለፈተና ፥ ሌላ ፥ ሐሳብ ፥ ለሌለበት ፥ ዘመን ፥ መታሰቢያ ፥ እንዲሆነኝ ፥ በማለት ፥ ያለለውጥ ፥ ትቸዋለሁ ። ስለዚህ ፥ አንባቢዎች፡ ድርሰቴን ፥ ስትፈረዱ ፥ በዚሁ ፥ መሠረት ፥ ይሁን ። ቅር ፥ የምትሰኙ ፥ አይመስ ለኝም ። ቅር ፥ ብትሰኙም ፤ ምናልባት ፤ የእግዚአብሔ ር ፥ ፈቃዱ ፥ ቢሆን ፤ የሚተጥለው ፥ መካከሻ ፥ ገጸ ፥ በረከ ቱ ፥ "የቀለም ፥ መከሪ"፡(የዛሬዬቱ ፥ኢትዮጵያን ፥ ጋዜጣ፡ አንባቢዎች ፥ ብታስታውሱ) ፥ የተባለው ፥ ይሆናል ።

ግሀሉ ፥ በሰዓት ፥ ወደቤቱ ፥ ሲመለስ ፤ ካለወትሮው ፥ ደኽዮ ፤ በውጭ ፥ በኩል ፥ ተቆልፎ ፥ ቆየው ። ለመጀመርያ ፥ ጊዜ ፥ ጥርጣሬ ፥ ያዘው ። ልቦናው ፥ ሲጋት ፥ ጭጠረ ። ሰውነ ቱ ፥ ፈራ ፥ የሠረገላውን ፥ ቁልፍ ፥ በተመሳሳይ ፥ መክፈ ቻ ፥ በሚጠመዝዝበት ፥ ጊዜም ፤ እጣቶቹ ፥ እንደመንቀጥ ቀጥ ፥ ሲሉ ፥ ከንፈሮቹ ፥ ደግሞ፤ ድምጽ ፥ አልቦ ፥ ይላወሱ ፥ ነበር ። በራቱን ፥ በርግዶ ፥ ቢገባ ፥ ሕፃኑን ፥ ሲያለቅስ ፥ አገኘው ። ግሀሉ ፥ ወደልጁ ፥ ተጠግቶ ፤ «እይዞህ ፥ —— እረ ፥ ምንድን ፥ ነው?——ባል ፥ ተወው ፥ ይቅር——»እያ ለ ፥ ሊያባብልና ፥ ሲያጽናና ፤ ባንድ ፥ ወገን ፥ ዓይኖቹ ፤ በጭንቀት ፥ ከፍሉን ፥ ሲቃብዙ ፥ በአልጋው ፥ ትራስ ፥ ገደግ ፥ ካንዲት ፥ ብጣሽ ፥ ወረቀት ፥ ላይ ፥ አረፉ ።

"……እንድ ፥ ባለጸጋ ፥ ያቀረበልኝ ፥ የኑርና ፥ የትዳ ር ፥ ምኞት ፤ የመንፈሴን ፥ ብርታት ፥ በምኞት ፥ ትግል ፥ እቆንፎት ፤ የበኩር ፥ ቤቴንና ፥ ትዳሬን ፤ አንተን ፥ የቃል ፥ ኪዳን ፥ ባሌንና ፥ ሕፃን ፥ ልጄን ፥ ትቼ ፥ ከምኞቱ ፥ ጋር ፥ እንድኮበልል ፥ ተገድጀለሁና ፥ መሄዴ ፥ ነው……

"በመጨረሻ ፥ እስከረታ ፥ ድረስ ፤ ይሆንን ፥ ሐሳቤን ፥ ለመግታትና ፥ በያዝኩት ፥ ለመቆም ፤ ምን ፥ ያህል ፥ ተጋ ድሎ ፥ እድርጌ ፥ እንደነበር ፥ ልትገምተው ፥ ባትችልም፤ ልብህ ፥ ቂም ፥ በቀል ፤ እንዳይጽጥርብኝ ፥ እለምንሃለሁ ። ……መደፈት ፥ ምናልባት ፥ በግይን ፥ ሥጋ ፥ እንተያይም ፥ ይሆናልና ፤ እርሳኝ ። በኑርህ ፥ ውስጥም ፥ እንዳልነበርኩ ፥ ቁጠረኝ……

"አበባ"

ግሀሉ ፣ በሕይወቱ ፣ ዘመን ፣ አንዳንድ ፣ ኃዘኖች ፣ ደርሰውበታል ። በዕረፍታቸው ፣ ጊዜ ፣ ሕፃን ፣ ቢሆንም ፣ እንኳ ፣ የወላጆቹ ፣ ሞት ፣ ጉዳት ፣ እያደረና ፣ እየቆየ ፣ ተሰምቶት ፣ ነበር ። የቅርብና ፣ የሩት ፣ ዘመድ ፣ የወዳጅና ፣ የጉረቤት ፣ ሞት ፣ አሳልፎዋል ። የሰው ፣ ልጅ ፣ መከራና ፣ ሥቃይ ፣ አይተዋል ። ነገር ፣ ግን ፣ እንደዚህ ፣ የመርዶ ፣ ደብዳቤ ፣ በኃዘን ፣ ፍላጻ ፣ ልቡን ፣ ጠልቆ ፣ የወጋው ፣ ነገር ፣ ከዚህ ፣ በፊት ፣ በፍጹም ፣ አልገጠመውም ። እንጀቱን ፣ ቁርጥርጥ ፣ ብጥስጥስ ፣ አደረገው ። እርር ፣ ትክን ፣ አለ ። ኑርው ፣ በትካዜ ፣ ቆዳ ፣ ተጠቅልሎ ፣ አዘቅት ፣ ውስጥ ፣ የተጣለ ፣ መሰለው ። ወረቀቱን ፣ በእጁ ፣ እንደጨበጠ ፣ ዕንባው ፣ ሊዝረከረክ ፣ የደብዳቤውን ፣ ጽሑፍ ፣ እያጠበው ይወርድ ። ነበር ።

አእምሮው ፣ ትንሽ ፣ ጸጥ ፣ ሲል ፣ ራሱን ፣ እያወዛወዘ ፣ "አበባ ፣ እርግጥ ፣ በኔ ፣ ጨከነሽ ፣ ልትሄጅ ? በፍጹም ፣ አታደርጊውም ። አትሞክሪውም ። "እያለ ፣ ሲብሰከሰክ ፣ ከአራቱ ፣ ማዕዘን ፣ ግድግዳ ፣ ከጣራውና ፣ ከወለሉ ፣ ከሁሉም ፣ አንፃር ፣ በኩል ፣ »እንተ ፣ ሞኝና ፣ ተላላ ፣ ነህ ፣ አበባ ፣ እንደሆነ ፣ ከሌላ ፣ ጋር ፣ ኮብልላለች ። እንግዲህ ፣ የእንተ ፣ አይደለችም ። «የሚል ፣ ሥውር ፣ ድምጽ ፣ የተሳለቀበት ፣ መሰለውና ፣ "ሐሰት ፣ ነው ፣ አበባዬ ፣ የኔ ፣ የብቻየ ፣ የማሌ ፣ ናት ፣ ምን ፣ ጊዜም ፣ ከኔ ፣ አትለይም ፣ "እያለ ፣ ይጮህ ፣ ጀመር ። ነገር ፣ ግን ፣ ሲታውሩ ፣ ትዝቱ ፣ ሲበርድለት ፣ ደብዳቤውን ፣ እንደገና ፣ ቢመለከተው ፣ ሊከድ ፣ የማይቻለው ፣ ያው ፣ አሲቃቂ ፣ መርዶ ፣ ነበር ። ምነው ፣ ኃያላን ፣ መናፍስት ፣ የዓረፍተ ፣ ነገሩን ፣ ትርጉም ፣ ቢለው ፣ ኖሮ ፣ ግሀሉ ፣ ሰውነቱን ፣ በኃዘን ፣ አኮራምቶ ፣ ራቁን ፣ ፀጉሩ ፣ መካከል ፣ ደበቀና ፣ የፍቅሩን ፣ ትዝታ ፣ ከውጭ ፣ አንስቶ ፣ ትዳሩ ፣ እስከተናደበት ፣ እስከዚች ፣ ሰዓት ፣ ድረስ ፣ እንደሲኒማ ፣ ትርኢት ፣ በዕንባው ፣ መጋረጃ ፣ ላይ ፣ መከነው ።

ከቱንጅናዋ ፣ ይልቅ ፣ ውበትዋና ፣ ደም ፣ ግባትዋ ፣ ይጨልጣል ። ቀይ ፣ ሳትሆን ፣ ጠይም ፣ ዓማ ፣ መሳይ ፣ ናት ። እፍንጯዋ ፣ በጣም ፣ የተገተረ ፣ አልነበረም ። ጊዮርጊስ ፣ ከነፈረሱ ፣ ያለፈበት ፣ የሚመስል ፣ ጉራዳም ፣ አልነበረም ። በመጠኑ ፣ ሰልከክ ፣ ብሎ ፣ የወረደና ፣ መልካም ፣ ቅርጽ ፣ ያለው ፣ ነው ። ዓይኖቿ ፣ የሰጉን ፣ እንቁላል ፣ ያክላሉ ፣ ተብሎ ፣ ትልቅነታቸው ፣ ሊጋነን ፣ ባይችሉና ፣ ከጉድጓዳቸው ፣ ወጥተው ፣ ባይንቧለሉም ፣ መጠነኛ ፣ ሆነው ፣ ጥራታቸው ፣ ያስደንቃል ። አስተያየታቸውም ፣ የሰውነትን ፣ ሕዋሳቶች ፣ የሚያበራጣ ፣ ይመስላል ። ቅንድቦቿና ፣ ሽፋሽፍቶቿ ፣ በምሥራት ፣ አገር ፣ ኩል ፣ የተጠቀሩ ፣ ይመስላሉ ። ነገር ፣ ግን ፣ ተፈጥሮዋቸው ፣ መሆኑ ፣ እይጠረጥርም ። የከንፈሮቿ ፣ አከራከምና ፣ አቀራረጽ ፣ የአፍዋ ፣ አመጣጠን ፣ ተመልካችን ፣ ያስጉመጥል ። እምላክ ፣ በረቂት ፣ እጣቱ ፣ ቀርጾ ፣ ያነሣቸው ፣ የሚመስሉት ፣ በረዶ ፣ ጥርሶቿ ፣ በስለት ፣ ፈለት ፣ ፈለት ፣ ሲሉ ፣ እንኳንስ ፣ ጉልማሳን ፣ ሽማግሌም ፣ ቢሆን ፣ ወከክ ፣ ያደርጋሉ ። እንደመስከረም ፣ ዓደይ ፣ በደም ፣ የፈኩት ፣ ጉንጮቿ ፣ እንደብርቱካን ፣ የጠሩና ፣ እንደጸጠመ ፣ የለሰለሱ ፣ ናቸው ። እሞላላቸው ፣ ሥጋና ፣ ቅቤ ፣ እየተመገበች ፣ በማርና ፣ ፎሎት ፣ እየታጠበች ፣ ፀሐይ ፣ ላያያት ፣ ሐሩር ፣ ላይደፍራትና ፣ ቁር ፣ ላይነካት ፣ በመጋረጃ ፣ ውስጥ ፣ ተጠቅላ ፣

ያደገች ፣ የጌታ ፣ ትምህርት ፣ የዘመናይ ፣ ልጅ ፣ ያስመሰላ ታል ። ቢሆንም ፣ ወፍራም ፣ ዝብተብተ ፣ አይደለችም ።

ትባት ፣ ሳይነካው ፣ የተፈጥሮ ፣ ወዙ ፣ የሚያንጸባር ቀው ፤ ዞግው ፣ እንቍር ፣ ከሕንድ ፣ ጥቁር ፣ ሐር ፣ ጋር ፣ የሚወ ዳደር ፣ ነው ። በረጅሙ ፣ ተሠርቶ ፤ እንደ ፣ እባብ ፣ ግልገል ፣ እየተጉነጉነ ፣ ቢወርድ ፣ እንዲት ፣ ባሳበደ ፣ ነበርነገር ፣ ግን ፣ እናቷ ፣ ባጭሩ ፣ ይከረከሙት ፣ ስለነበር ፣ ዝቅ ፣ ብሎ ፣ አሰካክ ፣ ብርሌ ፣ አንገቷንና ፣ አሠራረቱ ፣ ግሩም ፣ ድንቅ ፣ የሆነውን ፣ ትከሻዋን ፣ በጸጋ ፣ ለማጉናጸፍ ፣ ዕድል ፣ አላገኘም ። ገና ፣ በአስራ ፣ ሁለት ፣ ዓመትዋ ፤ ደረቷ ፣ አበዋ ፣ ብሎ ፤ ጡቶችዋ ፣ ጉጭ ፣ ጉጭ ፣ ግለት ፣ ጀምረዋል ፣ ከወደታች ፣ ሽንጥዋ ፣ ሾጠጥ ፣ ብሎ ፣ ወርዶ ፣ ዳሌዋ ፣ እንደመጒወት ፣ ይታጣዋል ። የእጅዋ ፣ ጣቶች ፣ አለንጋ ፣ ሲመስሉ ፤ የሥራ ፣ ብዛት ፣ ጥቂት ፣ አሻከርዋቸዋል ። የተስተካከለው ፣ ባቷ ፤ ሎሚ ፣ ከመሰለው ፣ ተረከዝዋ ፣ ጋር ፣ ሚጣን ፣ ዋጋ ፣ የሚያሳጣ ፣ ነው ። ጠቅላላ ፣ አትዋ ሻ ፣ ሰሉዎን ፣ በመጋልዩ ፣ የሚጠቅሰው ፣ አርዘ ፣ ሊባኖ ስ ፣ ዓይነት ፣ ናት ። አካልዋ ፣ በሚዛን ፣ ተመጣጥኖ ፤ በትክክል ፣ የተገነባ ፣ የግሪክ ፣ ሐውልት ፣ ይመሰላል ፣ ከዚህም ፣ በላይ ፣ የተቀመመው ፣ ከነጠረ ፣ ደም ፣ ከጠራ ፣ ሥጋ ፣ ነበር ። ስምን ፣ መልአክ ፣ ያወጣዋል ፣ እንደሚባለው በጭቅልነትዋ ፣ ወራት ፣ የተወሰነ ፣ ቅርጽ ፣ ሳይኖራትና ፣ የሚጨረስት ፣ ጭቃ ፣ ትመስል ፣ በነበረበት ፣ ጊዜ ፤ እናትዋ ፣ "አበባ" ፣ ብለው ፣ ሲሰይሟት ፣ እንደነቢይት ፣ ያስቆጥራቸዋል ።

በሁሉም ፣ ልክ ፣ ነች ። ሁለመንተናዋ ፣ ግሩም ፣ ተፈጥሮ ፣ ነው ። የቁንጅና ፣ እንኳ ፣ ባይሆን ፣ የውበት ፣ አምላክ ፣ ነበረች ።

ምዕራፍ ፤ ፪

አባቷ ፣ ሥዩም ፣ ሐዋዝ ፣ ይባላሉ ። አርሳቸውም ፣ በዘራቸው ፣ የካሀናት ፣ ወገን ፣ ነበሩ ። አባታቸው ፣ መሪ ጌታ ፣ ሐዋዝ ፤ ልጃቸውን ፣ የመንበራቸው ፣ ወራሽ ፣ እንዲ ሆኑ ፣ ሳይመኙ ፣ አልተረፉ ። ነገር ፣ ግን ፣ ልጅ ፣ ሥዩም ፣ ጀመድን ፣ እንደጨረሱ ፣ ከቤተክርስቲያን ፣ አካባቢ ፣ መ ሸሸ ፣ አሙ ። አባታቸውም ፣ ምኞታቸውና ፣ ተስፋቸው ፣ እንዳልተሳካ ፣ በመመልከት ፣ ቅር ፣ ቢሰኙም ፤ እንዳንዳ ንድ ፣ ወላጆች ፣ ልጃቸውን ፣ በመወትወት ፣ አላስቀቱም ። ፍላጉታቸው ፣ በሚፈትደው ፣ መስመር ፣ ኑሮዋቸውን ፣ እንዲመሩ ፣ ፈቀዱላቸው ። የልጅ ፣ ሐዋዝ ፣ ዝንባሌም ፣ ንግድ ፣ ነበር ።

በዚህ ፣ አኳኋን ፣ ልጅ ፣ ሥዩም ፤ ከአባታቸው ፣ ትንሽ ቅርስ ፣ ተተብለው ፣ የወጣትነት ፣ ስሜታቸው ፣ ይንጎለት ፣ ወደነበረው ፣ ሥራ ፣ ተጉዳኙ ። አንዲት ፣ በቅሎ ፣ ገዝተው ፣ ሞከሩት ። ዕድላቸው ፣ ቀና ። ንግድ ፣ ከፍላቸው ፣ ሆነ ። የጊዜ ፣ ሁናቴ ፣ ከርሳቸው ፣ ጋር ፣ እንደተመጣጠረ ፣ ሁሉ ፣ በጃቸው ፣ ያለው ፣ ሽቀጥ ፣ ሲወደድ ፣ ሊገዙት ፣ ያሰቡት ፣ ደግሞ ፣ ረከሰ ፣ ይቆያቸዋል ። በጥቂት ፣ ወራት ፣ ውስጥ ፣ ትርፍ ፣ በትርፍ ፣ ሆነው ፣ የገጣ ፣ ከብቶችን ፣ ጨምረው ፣ ገዙ ።

አቶ ፣ ሥዩም ፤ ከብዙ ፣ ጎጋዶች ፣ የሚለዩበትና ፣ የሚመረጡበት ፣ ጠባይ ፣ ነበራቸው ። በጣም ፣ ሐቀኛ ፣ ነበሩ ። የግጭበርበርና ፣ የግታለል ፣ ተግባር ፣ ታይቶባቸው ም ፤ ተሰምቶባቸውም ፣ አያውቅ ። የሸፍጥ ፣ ጥረት ፣ ከንብረታቸው ፣ ጋር ፣ እንዲተላተል ፣ አይፈቅዱም ። ውሸት ፣ አይወዱም ። ከዚህም ፣ በላይ ፣ በጣም ፣ ለጋስ ፣

ርኅሩኅና ፡ ቸር ፡ ነበሩ ። እንደርሳቸውስ ፡ ኢያያዝ ፡ ተዘር ዝሮ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ የሚያልቅ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በየቂጉ ፡ እየዶረጀና ፡ እየበረከተ ፡ ከመሄድ ፡ አላቋ ረጠም ። በገብያ ፡ መለዋወጥ ፡ በጣም ፡ አይሰጉም ። እምነ ታቸውን ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ የሰጡ ፡ ነበሩ ። ቢሆንም ፡ ጸሎታቸው ፡ እንደብዙዎቹ ፡ ግብዝ ፡ ነጋዴዎች ፤ “እባክህ እምላኬ ፡ ገብያ ፡ ከፈትልኝ ፡ ሸቀጤንም ፡ አስወድድ ልኝ” ፡ የሚል ፡ ሳይሆን ፡ “እባክህ ፡ ፈጣሪየ ፡ ጤንነቴን ፡ አታጓድልብኝ ። በግወትም ፡ ሆነ ፡ ባለግወት ፡ ለሠራው ት ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነህና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡” ነበር ይህ ፡ መልካም ፡ ጠባያቸው ፡ በጓደኞቻቸው ፡ መካከል ፡ የተከበሩና ፡ የታመኑ ፤ በገብያተኞች ፡ዘንድም ፡ የተወደዱ ፡ እድርጉዋቸው ፡ ኑሮዋል ።

ለዓቅመ ፡ አዳም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ አባታቸው ፡ የደህ ና ፡ ቤተሰብ ፡ ወገን ፡ አስፈልገው ፡ ለምለም ፡ የምትባል ፡ ቆንጂት ፡ ዳሩላቸው ። ወይዘሮ ፡ ለምለም ፤ ዓመለ ፡ ወርቅ ፡ ልባምና ፡ ባለሙያ ፡ ሴት ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በአግታቸው ፡ ቤት ፡ ሲቀመጡ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በአግትና ፡ በምራት ፡ መካከል ፡ የሚፈጠረው ፡ ቅሬታና ፡ ቅያሜ ፡ ሳይነካቸው ፡ ጉጅ ፡ ወጥተዋል ። አቶ ፡ ሥዩምም ፤ ያመጡ ላቸውን ፡ አግሎቶች ፡ ከግመስገን ፡ ቦዝነው ፡ እያውቁም ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲዝናኑና ፡ ከባለቤታቸው ፡ ጋር ፡ ሲቃለዱ ፤ “ሲባል ፡ የነበረ ፡ አግጭ ፡ ረግጭ ፡ ለኔ ብቻ ፡ አደለኝ ፡ የትዳር ፡ ጣፋጭ” ። እያሉ ፡ በግምስ ፡ ያስቁዋቸው ፡ ነበር ።

በጥቂት ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፤ ከአባታቸው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሲሶ ፡ ደርብ ፡ አደራሽ ፡ ሠርተው ፡ ከማለቤታቸው ፡ ጋር ፡ በተድላ ፡ ደስታ ፡ ተቀመጡ ። ከዚ ህ ፡ በኋላ ፡ የንበረውግ ፡ ምኑ ፡ ተመርቶሲግይ ፡ ተንዶለ ዶል ። ገረድ ፤ አሽከርና ፡ ሎሌ ፡ በቤቱ ፡ ሞላ ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፤ ሀብት ፡ ከደግነት ፤ ዕውቀት ፡ ከአን ደበት ፡ ጋር ፡ ተስተካከልሎ ፡ የተሰጣቸው ፡ አቶ ፡ ሥዩም ፡ ይመጣትነት ፡ ዘመናቸው ፡ የመንደር ፡ አግካሪ ፡ አስታራ ቂ ፡ ሽግግሌና ፡ የተከበሩ ፡ የጉልግሳ ፡ አዛውንት ፡ ሆኑ ። ንጋዲነታቸው ፡ ባጉ ፡ ታወቀ ። ነጋድራስ ፡ ተባሉ—— ለውን ፡ እንኳ ፡ በዚያች ፡ ከተግ ፡ የሚኖሩት ፡ ባልቴቶችና ፡ እርጌዎች ፤ የነጋድራስ ፡ ሥዩምን ፡ ዜና ፡ እያነሱ ፡ እንደተ ረት ፡ በቡናና ፡ በጠላ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ሲጫወቱት ፡ ይሰማል ፡

ነገር ፡ ግን ፤ ከብረት ፡ እየሰፋ ፡ ዕድሜ ፡ እየገፋ ፡ ሲሄ ድ ፡ ትካዜና ፡ ቅሬታ ፡ እንደሸበት ፡ መብቀል ፡ ጀመረ ። ምኑ ፡ ምን ፡ ጉዶል ፣ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሲግይ ፡ ላይ ፤ የፍቅ ሬቸው ፡ ፍሬ ፡ መገለሜና ፡ ግስታወሻ ፤ የደስታቸው ፡ ተካፋይ ፤ ቢያረጁ ፡ የሚጦራቸው ፤ ቢሞቱ ፡ የሚቀብራ ቸውና ፡ የሚወርሳቸው ፡የልጅ ፡ እጋ ፡ ጉደላቸው ። ወይዘሮ ፡ ለምለም ፤ በየአድባራቱና ፡ በየገዳማቱ ፡ እየዞሩ ፤ በመሳለም ፀሎት ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ በመቀበል ፤ ጠበል ፡ በመቅመ ስ ፡ ብዙ ፡ ጣሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምኞታቸው ፡ በጊዜው ፡ አልተፈጸመላቸውም ። ባልና ፡ ሚስቱም ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ቅር ፡ ቢሰኙም ፤ ሳያማርሩና ፡ ተስፋ ፡ ሳይቆርጡ ፤ የፈጣ ሪን ፡ ንፍገት ፡ በትሕትና ፡ ተቀብለው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

መቸም ፡ አምላክ ፡ ችሮታውን ፡ የሚያዘንበው ፡ በፈ ቀደ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ካለፉና ፤ ወይዘሮ ፡ ለምለም ፡ ወደ ፡ እርጅና ፡ ዘመን ፡ በተጠጉ ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ ሳያስቡት ፤ የፅንስ ፡ አበባቸው ፤ የመር ፡ ጉብኙን ፡

አጀረጠ ። ወዲያው ፡ በተከታታዮቹ ፡ ወራት ፡ ወሰየ ፡ ጽንስ ፡ በማኅጸናቸው ፡ ይገላበጥ ፡ ጀመር ። አቤት ፡ የነበረው ፡ ደስታ ! በሥራና ፡ በእንቅስቃሴ ፡ ጠንቅ ፡ ፍጡሩ ፡ ከተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እንዳይጨነግፍ ፡ በመስጋት ፡ ወይዘሮ ፡ ለምለም ፡ ከአልጋቸው ፡ እንዳይወርዱ ፡ ተደረገ ። ንጋድራስ ፡ ሥዩም ፤ እንኳንስ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከፍተኛ ፡ ምክንያት ፡ ለማኅተውና ፡ እንዲሁም ፡ ቢሆን ፡ ባለቤታቸው ፡ ዘመናይ ፡ እንዲሆኑላቸው ፡ የሚሹ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ።

ቤት ፡ ልጅ ፡ በደህና ፡ ተገላገሉ ። ደስታቸው ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ሆነ ።

ልጂቱ ፡ ከርስትና ፡ የምትንጣበት ፡ የአስተርዮ ፡ ማርያም ፡ ለት ፡ ዋለ ። አቤት ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ የተደረገው ፡ ድግስ ፡ ፈረሰ ፡ የሚያስጋልብ ፡ ዳስ ፡ ተጥሎ ፤ ጠጁ ፡ እንደ ውሃ ፡ ሲቀዳና ፡ ሥጋው ፡ ሲቆረጥ ፡ ለአቀራረቡ ፡ መጠንና እንክን ፡ አልነበረውም ። ሰንት ፡ ሰንጋ ፡ እንደታረደ ፡ የሚያስታውሰው ፡ ባይኖርም ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ "የአበባ ፡ ከርስትና ፡ ጊዜ ፣ ምኑ ፡ ተነግሮ ! ሰንቱ ፡ ተቆጥሮ" ፡ እያሉ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያደንቁታል ። የመጠጥ ፡ ስካር ፡ ሞክሯቸው ፡ የማያውቅ ፤ ብዙ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ጠንብዘው ፡ ወደቤታቸው ፡ በደጋፊ ፡ እንደሄዱ ፡ ይወራል ። ወይዘሮ ፡ ለምለምና ፡ ንጋድራስ ፡ ሥዩም ፤ እደግድገው ፡ በተጋባዦቻቸው ፡ መካከል ፡ እየተዘዋወሩ ፤ "ምነው ፡ ብሉልን ፡ ጠጡልን ፡ እንጅ ፡ ካለዛሬ ፡ እንኳ ፡ ወግ ፡ አልያረሰንም" ፣ "እያሉ ፡ ሲያስተናግዱ ፡ ዓለማቸውን ፡ የዘነጉ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ አስመስለዋታል ።

ሕፃን ፡ ሳለች ፡ ከወላጆቿዋ ፡ ሀገድ ፡ የተሰጣት ፡ አከባቢ ፡ ከፍተኛ ፡ እንደነበር ፡ የሚታወስ ፡ ነው ።

እናቷ ፡ ከአትፈ ፡ አትውጭ ፡ በግለት ፤ "አበባዬ ፤ ያይኔ ፡ አበባ" ፡ እያሉ ፡ ሲያቆላምጡዋት ፤ አባትየው ፡ ደግሞ ፤ ፈንታቸውን ፡ ያታብጡዋት ፡ ነበሩ ። ግታ ፤ ባልና ፡ ሚስቱ ከመደብ ፡ ላይ ፡ አረፍ ፡ ብለው ፤ አንዲት ፡ ልጃቸውን ፡ ከመካከላቸው ፡ እያስተላለፉ ፡ በሽሚያ ፡ ሲያጫውቷት ፡ እንዴት ፡ የሚያስቀኑ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ነበሩ !

በዚህ ፡ ሁኔታ ፤ ጥቂት ፡ የተድላና ፡ የፍስታ ፡ ዓመታት እንዳለፉ ፤ የኢትዮጵያን ፡ ቤተሰቦች ፡ ሁሉ ፡ የኃዘን ፡ አጽፍ ፡ ያለበሰው ፡ የፋሽሽት ፡ ግፋዊ ፡ ወረራ ፡ ተጀመረ ። ንጋድራስ ፡ ሥዩም ፡ ግይጪው ፡ ድረስ ፡ በመዝመት ፡ ለሀገራቸው ፡ ያለባቸውን ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ ከፍለው ፡ ተመልሰዋል ። በኋላም ፤ ከአርበኞች ፡ ጋር ፡ ተቀላቅለው ፡ በሚካው ፡ ለመሠማራት ፡ ቆርጠው ፡ ነበር ። ግን ፡ የቤት ፡ ልብ ፡ የያዙት ፡ ባለቤታቸው ፡ በዕንባ ፡ ታጠቡባቸው ። የትዳራቸው ፡ ደዘታም ፡ ካለርሳቸው ፡ እንደማይቆም ፡ በመረዳት ፡ ለልጃቸውና ፡ ለባለቤታቸው ፡ ሲሉ ፡ ቀርተው ፤ ግዳጃቸውን ፡ "በውስጥ" ፡ ሆነው ፡ ለመፈጸም ፡ ወሰኑ ። በንግድ ፡ ስም ፡ በሚያደርጉት ፡ መዘዋወር ፤ ለአርበኞች ፡ መሣሪያና ፡ ስንት ፡ በግቀበል ፡ በጣም ፡ ረድተው ፡ ነበር ።

ከፋሽሽት ፡ ሰላዮች ፡ የሚያመልጥ ፡ ነገር ፡ አልነበረምና ፡ የንጋድራስ ፡ ሥዩም ፡ ግይጪው ፡ መዝመትና ፡ ከአርበኞች ፡ ጋር ፡ የሚያደርጉትም ፡ ሚሥጥራዊ ፡ ግንኙነት ፡ ከጀር ፡ ጠቢው ፡ ደረሰ ። እንድ፡ ጊዜ፡አጋሰሶቻቸውን፡ በሙሉ ፡ የሸቀጥ ፡ ዕቃ ፡ ጭነው ፡ ለንግድና ፡ "ለልዩ-ተግባራቸው ፡ "ከወደ ፡ ጠረፍ ፡ አገር ፡ ደርሰው ፡ ሲመለሱ ፡ የጥቁር ፡ ቸሚዝ ፡ መታደርጎ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ያዘዋቸው ፡ ጓዛቸው ፡ ቢበረበር ፤ ከአንድ ፡ ሽጉጥና ፡ ከጥቂት ፡ ጥይቶ

ች ፣ በተቀር ፣ ሌላ ፣ የወንጀል ፣ ሰንክ ፣ አላገኙባቸውም ። ነገር ፣ ግን ፣ የፋሽሺት ፣ ፍርድ ፤ ማስረጃን ፣ የሚከታተል ፣ ሳይሆን ፤ ሰቡብን ፣ የሚፈልግ ፣ ስለነበር ፤ ወዲያው ፣ ንብረታቸው ፣ ተዘርፎ ፣ እርሳቸውም ፣ መህኒ-ቤት ፣ እንዲ ገቡ ፣ ተደረገ ።

ወሬው ፣ ለዘመዶቻቸው ፣ ደረሰ ። እንዳይጠይቁና ፣ እንዳይጉበኙ ፣ ግን፣ ተከለከሉ ። ቤተ-ሰብ ፣ ሲጨነቅና ፣ ሲታመስ ፣ ሰነበተ ። ከሁለት ፣ ሳምንት ፣ በኋላ ፤ አንድ ፣ ቅዳሜ ፣ ቀን ፣ ነጋድራስ ፣ ሥዩምን ፣ ያሳፈረ ፣ የመህኒ-ቤት መኪና ፣ በመታደሮች ፣ ታጅቦ ፣ ወደ ፣ ገብያው ፣ ሲያመራ ፣ ታዙ ። ተመልካች ፣ ወዲያው ፣ ነገሩ ፣ ገባውና ፤ ወሬው ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ እንደነፋስ ፣ ተዘራ ። የከተማው ፣ ሕዝብ ፣ ተናጠ ። ነጋድራስ ፣ ሥዩም ፤ ተከብረውና ፣ ተወደው ፣ ባደጉበት ፣ አገር ፣ ሲሰቀሉ ፣ ማየትነብያው ፣ ፈረሰ ። መንደሩ ፣ ሁሉ ፣ ተሸበረ ። ፋሽሽቶቹም ፣ ሁኔታውን ፣ በመስጋት፡እንደገና፡ወደእሥር፡ቤት፡መልሰው፡ዶሴዋቸው።

ከዚያች ፣ ሰዓት ፣ ወዲህ ፣ የነጋድራስ፡ ሥዩም ፣ አድራ ሻ ፣ በርገጡ ፣ አልታወቀም ። ወደ ፣ ሚካ ፣ ተመለደው ፣ በጥይት ፣ እንደተደበደቡ ፣ አንዳንድ ፣ ሰዎች ፣ ያወራሉ ። ቤተሰቦቻቸውና ፣ ዘመዶቻቸው ፤ እውነተኛውን ፣ ሁኔታ ፣ ለመረዳት ፣ ጥረት ፣ ሳያንቶች ፣ ያህል ፣ ከተዋለሉ ፣ በኋላ ፤ እንደሞቱ ፣ በግመን ፣ ፍታትና ፣ ልቅሶ ፣ አሰፈደሙ ፣

ይህ ፣ የጋዘን ፣ መብረት ፣ ቤታቸውን ፣ በመታው ፣ ጊዜ ፣ እበባ ፣ የስምንት ፣ ዓመት ፣ ኩብኩባ ፣ ነበረች ። ስለዚህ ፣ የደረሰባቸውን ፣ ጉዳት ፣ በጥልቅ ፣ ለመመራ መር ፣ ባትችልም ፤ እናቷ ፣ ሲጥመነመኑ ፣ በመመልከት ፣ የጋዘኑ ፣ ተካፋይ ፣ ሆናለች ።

እንደዚህ ፣ የመሰለ ፣ አደጋ ፣ በሚወድቅባቸው ፣ ቤተ ፣ ሰቦች ፣ ላይ ፣ የሚደርሰው ፣ የቤት ፣ ጣጣና ፣ ችግር ፣ ፋታ ፣ ሳይሰጥ ፣ ወረደባቸው ። ነጋድራስ ፣ ሥዩም ፤ ብዙው ፣ ንብረታቸው ፣ በሽቀጥ ፣ ላይና ፣ በጓሣ ፣ ውስጥ ፣ እንደነበር ፣ በጠላት ፣ መዘረፉ ፣ ሲታወስ ፤ በቤት ፣ ቀርቶ ፣ የነበረው ፣ ጥቂት ፣ ጥሪት ፣ ደግሞ ፤ ቁርባን ፣ ሲደረግበትና ፣ ተሸካር ፣ ሲወጣበት ፣ ተሟጠጠ ።

ያ ፣ የሞቀ ፣ ቤት ፤ የጋለ ፣ ንብረትና ፣ የሞላ ፣ ንብረ ት ፣ ከነጋድራስ ፣ ሥዩም ፣ ጋር ፣ ብኖ ፣ ጠፋ ። ወይዘሮ፡ ሰምለም ፣ የተረካከቡት ፣ ቅሪት ፤ አንድ ፣ ትልቅ ፣ አደራሽ ፣ ከባዶ ፣ የቤት-ዕቃ ፣ ጋር ፤ ወጀድ ፣ ከናታከልቱ ፤ ከወላጅ ፣ ጥበቃ ፣ ያልወጣች ፣ ሕፃንና ፣ የትዝታ ፣ ጋዘን ፣ ብቻ ፣ ነበር ። በነዚህ ፣ ካርታዎች ፣ ኑሮን ፣ ለመጫወት ፣ እንኳንስ ፣ የሴት ፣ እቅምና ፣ የወንድ ፣ ብርታትም ፣ ቢሆን ፣ እንደሚያመናታ ፣ ሲታመን ፣ የሴት ፣ እልህና ፣ የወንድ ፣ ትእግሥት ፣ ጠባይ ፣ የያዙት ፣ ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ ግን ፣ ጥርሳቸውን ፣ ነክሰው ፣ በድፍረት ፣ ተጋፈጡት ።

ከሥዩም ፣ ወዲያ ፣ ሌላ ፣ ባል ፣ መቸም ፣ አይመኩር ። እንግዲህ ፣ ለሌላ ፣ ወንድ ፣ ምንብ ፣ አዘጋጅቶ ፣ ማትረብ በእንግዳ ፣ እጅ ፣ ደግሞ ፣ መጉረስ! ከሁሉም ፣ ይሳስ ፤ ከሥዩም ፣ በተቀር ፤ "ባሌ-ፍትሬ" ፣ የሚባል ፣ ወንድ ፣ ሊኖር ፣ ይችላል?ዘበት ፣ ነው ። የኑር ፣ ጣዕምም ፣ ሆነ ፣ የሌትነት ፣ ጠባያቸው ፤ ከባለቤታቸው ፣ ጋር ፣ አብር ፣ እንደሞተና ፣ እንደተቀበረ ፣ ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ አረጋገው

ሰራሳቸው ፣ ብቻ ፣ እንኳ ፣ ቢሆን ፣ ቅንጣት ፣ ያህል ፣ ደንታ ፣ ባልነበራቸውም ። የሚያሳስባቸው ፣ ጉዳይ ፣ በቀላሉ ፣ ሊወገድ ፣ ይችል ፣ ነበር ። ገዳም ፣ ገብተው ፣

ለመናር ፣ ቁርጠኛ ፣ ነበሩ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ "የልለት ፣ ልጃቸውን" ፣ ከቁም ፣ ነገር ፣ ማብቃት ፣ ከራሳቸው ፣ መሥዋዕትነት ፣ የሚበልጥ ፣ ግዳጅ ፣ ሆኖ ፣ ተሰማቸው ።

አበባ ፤ በእንጀራ-አባት ፣ ሳትገላመጥና ፣ ሳትሸንቆጥ ፤ በባልንጀሮችዋ ፣ ሳትናቅና ፣ ሳትዋረድ ፤ እርስዋም ፣ በነር ሱ ፣ ሳትቀናና ፣ ሳትበሳጭ ፤ እንደዚሁም ፣ መቀነትዋ ፣ ሳይጐድል ፣ በሚገባ ፣ ለማሳደግ ፣ ታተቀው ፣ ተነሱ ።

ለጠላ ፣ አጠማመት ፣ ሊቁ ፣ ነበሩ ። ግን ፣ "በመሸቶ ች ፣ ከበብ" ፣ መመደብ ፤ የሙዋቹ ፣ ባለቤታቸውን ፣ መን ፈስ ፣ የሚያስቀይም ፣ ከመሆኑም ፣ በላይ ፤ የራሳቸውንና ፣ የልጃቸውን ፣ የሶሺያል ፣ ክብር ፣ የሚያሻግት ፣ ውጤት ፣ እንደሚያስከትል ፣ በመገንዘብ ፤ በዚህ ፣ ዓይነት ፣ ገቢ ፣ ሲመስተዳደር ፣ አልፈቀዱትም ። ስለዚህ ፣ የጉሮዋቸውን ፣ ጣጣ ፤ ከጓሮዋቸው ፣ በሚገኘው ፣ ጥሪት ፣ ለማሸነፍ ፣ እንደሚቻል ፣ ገመቱ ። ግምታቸውም ፣ ስሕተት ፣ አልነ በረም ።

በመጀጻቸው፤ በጠላ፣መጎዛቸው፣የታወቁ፣ ሳባ-አምስት የሚሆኑ ፣ ዩኒቮ ፣ ዛርችና፣ ምስት ፣ መደብ ፣ -ሥር ፣ እንሶሽ ላ ፣ ነበራቸው ። ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ የወይዘሮ ፣ እጣቶቻቸ ው ፣እስኪጐርፁ፣ ድረስ ፣ቅጠሉን ፣ ይሸመጠጡና ፤ በኬሻ ፣ ላይ ፣ አስጥተው ፤ እንዳይጠልዝ፣ በጥንቃቄ፣ እያገለባበጡ ፣ ያደርቁታል ። እንዶሽላውን ፣ ግን ፤ ሳይጠወልግ ፣ በትኩሱ ፣ በስልቻ ፣ ከከተቱ ፣ በኋላ ፤ ሽቀጣቸውን፣አንግበው ፣ ወደ ገብያ ፣ ያመራሉ ። አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ለትርፍ ፣ ከባላገሮ ች ፣ የሽመቱትን ፣ ቅመማ-ቅመም ፣ ዉምረው ፣ ይይዙ ፣ ነበር ።

በትምጥልነት፣ዘመናቸው፣ያውቁዋቸው፣የነበሩትና ፣ ዝናቸውንም ፣ በወሬ ፣ የሰሙት ፣ ሰዎች ፣ ሁሉ ፣ ከወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ ለመገብየት ፣ ይሽቀዳደሙ ፣ ነበር ። ይህ ፣ ከኃዘ ኔታ ፣ የመነጨ ፣ የዕርዳታ ፣ ተግባር ፣ ወይዘርይቱን ፣ አሳስ ደሰታቸውም ። ያፍሩና ፣ ይሰቀቁ ፣ ነበር ። ይልቁንም ፣ ይሱኝታ ፣ ስለሚያበዙ ፣ ዕውቂያ ፣ ላላቸው ፣ ሰዎች ፣ ሁሉ ከገብያ ፣ በላይ ፣ እየጨመሩ ፣ ይሰፍሩላቸዋል ። ቢሆንም ፣ የፈጣሪ ፣ ረድኤት ፣ እየተቀላቀለበት ፣ ነው ፣ መሰል ፣ ማሰሮዋቸው ፣ ጉድሉ ፣ አያውቅም ፣ ነበር ።

አበባ፣ ለእርዳታ፣ በደረሰች፣ ጊዜ፣ የሥራውን፣ ሸክም ከናትዋ ፣ ጀርባ ፣ ላይ ፣ በማቅለል ፣ በቤት ፣ ውስጥ ፣ ጣጣ ፣ ብዙ ፣ ታግዝ ፣ ጀመር ። ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ የገብያው ፣ ሐይ ፣ ሲቀታቸው ፤ ጫጫታው ፣ ራስ-ምታት ፣ ሲሰጣቸ ው ፣ ውለው ፣ በሚመለሱበት ፣ ሰዓት ፤ መልካሟ ፣ ልጃቸ ው ፣ ደግሞ ፤ ቤቱን ፣ ጠርጋ ፤ ወጡን ፣ ሠርታና ፣ የፈረስ ፣ ጭራ ፣ የመሰለ ፣ ቡና ፣ አፍልታ ፣ ትቆያቸውዋለች ። ጥንት ፤ የአሽከርና ፣ የገረድ ፣ መንጋ ፣ ይሯሯጥበት ፣ ቤነበ ረው ፣ አደራሽ ፣ ሁለቱ ፣ ሴቶች ፣ ብቻ ፣ ተቀምጠው ፣ የ ዕለት ፣ እንጀራቸውን ፣ እየቆረሱ ፤ የኑሮን ፣ ጣጣና ፣ ችግር፣ ሲወያዩ ፣ መመልከት ፣ እንዲት ፣ ያስተከዝ ፣ ነበርን የአበባ የሕፃንነት ፣ ዘመን ፣ የተሸኘው ፣ በዚህ ፣ ሁኔታ ፣ ነበር ።

ምዕራፍ ፫ ፣

በንጋድራስ ፣ ሥዩም ፣ አደራሽ ፣ ላይ ፣ የጣለውን ፣ የመከራ ፣ ዝናም ፣ ከካፊያው ፣ እንስቶ ፣ በኃዘን ፣ ዓይን ፣ ከተመለከቱት ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ እንዱ ፣ ግሀሱ ፣ የሚባ ለው ፣ ወጣት ፣ ነበር ። ይህ ፣ ወጣት ፣ ጉረቤታቸው ፣

እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ አባቱና ፡ ኑጋድራስ ፡ ሥዩም ፡ ጥበት ፡ ጓደኞቸች ፡ ነበሩ ። ወላጆቹን ፡ እንደአበባ ፡ በመንከባከብ ፡ ዘመኑ ፡ ተነጥቆዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በቂ ፡ ተንቀሳቃሽና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የወረሰና ፡ ከጠርም ፡ የሚሄንለት ፡ የእርሻ ፡ ምርት ፡ ስለነበረው ፡ የቤት ፡ ችግር ፡ አላጉላቶልውም ። በኋላም ፡ ከመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተቅጥሮ ፡ በበቂ ፡ ደሞዝ ፡ ይተዳደር ፡ ነበር ።

የወይዘሮ ፡ ለምለምን ፡ ችግር ፤ በመገንዘብ ፡ በቤታቸው ፡ ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ለፅርዳታ ፡ ብቅ ፡ ተል ቅ ፡ ይል ፡ ነበር ። ለኑሮዋቸው ፡ ቀረቤና ፡ ተቆርቋሪ ፡ ከሠኑት ፡ ሰዎች ፡ ዓይነተኛው ፤ ግሀሉ ፡ ነበር ። እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ሲሆን ፡ "በመልካሙ-ዜመን" ፡ የተለመደው ፡ እንዳይታጐል ፡ ጠቦት ፤ ሥጋ ፤ ቅቤና ፡ እህል ፡ ይልክላቸዋል ።

አበባን ፡ የሚመሳት ፡ እንደትንሽ ፡ እህቱ ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ የምትመለከተው ፡ እንደትልቅ ፡ ወንድም ፡ ነው ፡ እንደጸሬው ፡ ጥንቡ-እርኩሱ ፡ ሳይወጣና ፡ ብርቅትና-ድንቅ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፤ ለአበባ ፡ ከረሜላ ፡ ያቀመሳት ፡ ግሀሉ ፡ ነበር ። እንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ቀናት ፤ በውድ ፡ ገብያ ፡ ግዙት ፡ ያመጣና ፤ "አበባ-ከረሜላ ፡ እያለ ፡ ሲጠራት ፤ እየረገጸቶች ፡ በመጣት ፤ ወገቡን ፡ ጠምጥማ ፡ በልጅነ ትና-በወንድምነት ፡ መንፈስ ፡ እየሳመች ፡ "ውይ-ጋሽ ፡ ግሀሉ ፡ ይጠፍጣል" ፡ ስትል ፡ ትመርቀውና ፡ ታመሰግነው ነበር ።

ግሀሉ ፡ የአሁት ፡ ትውልድ ፡ ወጣት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቢጋብቻ ፡ ረገድ ፡ የነበረው ፡ አስተያየት ፡ የአባቶቹን ፡ የተቀደሰ ፡ ቅርስ ፡ በጥብቅ ፡ የሚያምን ፡ ነው ። የወንደላ ጤነትን ፡ ኑር ፡ ይነቅፋል ። ትዳር ፡ መያዝና ፤ ቤተሰብ-ማ

ቋቋም ፡ በምድራዊ ፡ በኩል ፡ የግሀበራዊ ፡ ኑር ፡ ግዳጅ ና ፤ በሰማያዊም ፡ የመለኮታዊ ፡ ትዕዛዝና ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑ ን ፡ አልሳተውም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ለዓት-አሳም ፡ በደ ረሰ-ጊዜ ፡ የኑሮ-ባልንጀራ ፡ የምትሆነውን ፡ ከመረጠ ፡ አልዘነጋም ። ሕብሳን ፡ ግን ፡ ከተመራሮች ፡ መደብ ፡ አላስገባትም ። ሁልጊዜ ፡ የሚገምታት ፡ ሕፃን ፡ ሆኖ ፡ እንደምትቀር ፡ ነበር ። የአመራረጥ ፡ ፈተናውን ፡ ልግልፍ ፡ የምትችል ፡ ጥሩ ፡ ቆንጂት ፡ በተሳሱ ፡ ባለግገፍቱ ፡ በፍለጋ ፡ ዘመን ፡ ሲያሳልፍ ፡ አበባ ፡ እየቆነጀች ፡ ሄደች ፤ ደረሰች ።

ቁንጅናዋን ፡ የተገነዘበውና ፡ ያስተዋለው ፤ አስራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከሞላት ፡ በኋላ ፡ ነበር ። የሰውነትዋ ፡ አፈካክ ፡ ለአካለ-መጠን ፡ መብቃትዋን ፡ አጉልቶ ፡ ያስረዳል ። "ታዲያ ፡ እርስዋ ፡ ካልችልኝማ ፤ ይተኛልና ፡ የበለጠ ፡ የት ፡ አገኛ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የምልፋው ! ፡ "ሲል ፡ አሰበ ።

——ባሕሪዋ ፡ ግር ፡ ነው ። ጠባይዋ ፡ የታረመ ፡ ነው አፋራም ። ናት ። ሰው ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ እታይም ። ሥጉ-ሥር ዓትና ፡ አንጋገር ፡ ከተፈጥሮ ፡ ተሰጥቶዋታል ። ከቤተሰቦ ችዋ ፡ በቀዳችው ፡ መልካም ፡ እርሕያንት ፡ አዳብራዋለች ። ልባምነት ፡ ከባቲሌ ፡ እናቷ ፡ አዋንታለች ። እንኳንስ ፡ የሚያውቃትና ፡ ዘናዋንም ፡ የሰማ ፡ ቢሆን ፤ ለቤት ፤ ለትዳር ፡ የሚሎጉዋት ፡ ዓይነት ፡ ናት ። ——ታዲያ ፡ ለምን ፡ እሳልፎ ፡ ይሰጣትመዳርና ፡ ግገባት ፡ ካልተረ ፋት ፡ እርስዋስ ፡ ለምን ፡ ከእንጦሳ ፡ ቤት ፡ ትገባለች? ዘንጎውም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ በፍጹም ፡ እንደማያስከፋት ፡ ዘራቡ ፡ ይተማመናል ። የሁለቱ ፡ ጋብቻ ፤ ለርስም ፤

ልርስዋና ፡ ለናቷም ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ እንደሚሆን ፡ አመነ ።

ግሀሉ ፤ የቤተክህነት ፡ ትምህርትን ፡ ተምሶ ፡ ነበር ። የዜመናዊው ፡ ዕውቀት ፡ ጠቃሚነትንም ፡ ተገንዝቦታል ፡ አበባ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ዲዳ ፡ ነበረች ። "ሁውን" ፡ እንኳ ፡ አልቀጠረችም ። ስለዚህ ፡ ትንሽ ፡ ብትማር ፡ አይከፋም" ሲል ፡ ግሀሉ ፡ አሰላሰለ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከንአበባ ፡ በና ፡ ተጋብዞ ፡ ሲጫወት ፡ "ዛሬት ፡ ትምህርት ፤ ለሴት ፡ ለወንድ ፤ ለትንሹም ፡ ለትልቁም ፡ በጣም፡ አስፈላጊ፡ሆኖ፡ ተገኝተዋል ።——አበባም ፡ ብትሆን ፡ አዲስ ፡ በተከፈተው ፡ ትምሕርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ብትማር ፡ መልካም ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም በማለት ፡ የራሱን ፡ ኅሳግ ፡ ደብቆ ፡ እንደዋዛ ፡ አጫወቻው ። የወይዘሮ ፡ ለምለም፡ አርጌ ፡ ዕምነት ፡ ከአዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጋር ፡ አይወዳጅም ፡ ነበር ። የሚገምቱት ፡ የሞራል ፡ ውድቀት ፡ መንቅ ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡ ጥቅም ፡ እንደማይሰጥ ፡ አድርገው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከግሀሉ ፡ በኩል ፡ ሲቀርብ ፡ ከባድ ፡ መታወሚያ ፡ አልበጉባቸውም ። የዚህ ፡ ወጣት ፡ አስተያየት ፡ ሁልጊዜ ፡ ትክክለኛ ፡ እንደሆነ ፡ ያምናሉ ። ካሁን ፡ በፊት ፡ የሰማቸው ፡ ምክርችና ፤ የሞለላቸው ፡ ውለታዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚጣልባቸው ፡ ሆነው ፡ አግኝተዋቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ወይዘሮ ፡ ለምለም ፡ ጥቂት ፡ ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፡ "ከሆነማ ፡ ምን ፡ ችግር፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቤቱን ፡ ሥራ ፤ ግን ፡ የሚረዳኝ ፡ ይመስልሻልብኝን ፡ አይሆንልኝም ፡ ሰውነቱ ፡ ደክሟል" ፡ እያሉ ፡ አዋዩት ።

ግሀሉ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሳያስበበት ፡ አልቀረምና ፡ "አይ ፡ እሜቴ ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ አያስቡ ። የሚረዳዎት ፡ ገረድ ፡ እንተዋለን" ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ፡

አበባ ፡ ትምሕርት ፡ ቤት ፡ ገባች ። በጥናት ፡ ረገድ ፡ በጣም ፡ ትጉህ ፡ ተማሪ ፡ ሆነች ። አንጉሏም ፡ ነገርን ፡ ለመጨበጥ ፡ በጣም ፡ ቀልጣፋ ፡ ነበረ ። በጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ፊደል ፡ አጠናቀቀች ። ትምሕርት ፡ ቤት ፡ ውላ ፡ ስትመለስ ፤ እየሮጠች ፡ ወደግሀሉ ፡ ዘንድ ፡ ትሄድና ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ስትማረው ፡ የዋለችውን ፡ ትዘረዝርለታለች ።

በኋላም ፡ ታላትን ፡ እያስከካች ፡ ማንበብ ፡ ስትጀምር ፡ ካጠገቡ ፡ ተቀምጣ ፡ ትንተባተብለት ፡ ነበር ። አንዳንድ ጊዜም ፡ ምንባቡ ፡ ሲያቅታት ፤ ከፍተኛ ፡ ወንጀል ፡ እንደፈጸመ ፡ ኃጠአተኛ ፤ ዓይናቹዋን ፡ በግስተዛዘን ፡ እያቁለጨለጨች ፡ ይትርታን ፡ ስትጠይቀው ፤ ግሀሉ ፡ "ፈገግ" ፡ ይልና ፡ ጣትዋን ፡ ይዞ ፡ ይመራታል ። ያስቆጥራታል ። እርሳስን ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ መጫር ፡ ስትሞክር ፤ ከታላት ፡ ሁሉ፡ በፊት፡ እያወለጋገደች፡ የጨንቋረቻቸው ፡ "ግሀለ ፡ አበባ ፡ እግማ" ፡ የሚሉትን ፡ ታላት ፡ ነበር ። ከሕፃንነትዋ ፡ አንስቶ ፤ ግሀሉ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ (የወንድምነት) ፡ ከሥውር ፡ አእምርዋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጾ ፡ ነበር ፡

ግላይ ፡ እንደሚያስመርቅ ፡ አሳኝ ፡ ጸሐፍን ፡ ለግሀሉ ፡ ታበረክትለታለች ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አደጉ ፡ የፍፁ ፡ እግር ፡ የርኅጫውረው ፡ ቢመስልም ፤ ግሀሉ ፡ ከልቡ ፡ እያደነቀ ፡ "እከክ——ግን ፡ ችሎሽ ። ጉብዝሽ ፡ የለም ፡ እንዴ!"እያለ ፡ ሲያሞጋግሳት ፡ በደስታ ፡ እየፈነደቀች ፡ እናትዋን ፡ ደግሞ ፡ ለግብስር ፡ ትሮጥ ፡ ነበር ።

ይመንፈቅ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የአንደኛ ፡ ክፍል ፡ ትምህርትን ፡ ጨርሳ ፡ ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ ተዛወረች ። ባመቱ ፡ ምስተኛ ፡ ገባች ። በጠባይ ፡ በትጋትና ፡ በችሎታ ፡ ተመሰገነች ። በክፍል ፡ ውስጥ ፡ አስተማሪው ፡ አርአያና ፡ ምሳሌ ፡ እያደረገ ፡ የሚጠቅሳት ፡ ሆነች ።

የገሀሉና ፡ የወይዘሮ ፡ ለምለም ፡ ወዳጅነትም ፡ እንደዚው ፡ በበለጠ ፡ እየፋፋና ፡ እየዳበረ ፡ ሄደ ። የቅርብ ፡ ዘመዳሞች ፡ መሰሉ ። የቢታቸውን ፡ አመራር ፡ በቅርብ ፡ እየተከታተለ ፡ በኑሮዋቸው ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ ጉድለት ፡ እንዳይገባ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ በመሙላት ፡ ዋና ፡ አሳቢ ፡ ነበር ።

አበባ ፤ በጊጣጊዋ ፡ ረገድ ፡ ከጎደኞችዋ ፡ እንዳታንስ ፡ ልብሱ ፡ ሜጣው ፡ ጅራቡንቻሹ ——ይገዛላታል ። ይልቁንም ፡ ከጎደኞቿ ፡ ልታኖደምታ ፡ ትታይ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ገሀሉ ፡ ዋና ፡ ግቡን ፡ በሆዱ ፡ ሸምቆ ፡ አቆይቶታል ።

አበባ ፡ ተናት ፡ ባልበዛባት ፡ እርሱም ፡ ሥራ ፡ ባልኖረበት ፡ ቀን ፤ መደግታ ፡ ጊዜ ፡ ሽርሽር ፡ ይዝዋት ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሽርሽራቸው ፤ ዛሬ ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ወንፈርሳና ፡ በቮላ ፡ ጫካ ፡ እንደሚታየው ፡ ዓይነት ፡ አልነበረም ። ንጹሕን ፡ አየር ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ ለመተባል ፡ ነው ። እንኳንስ ፡ የከንፈር ፡ ወዳጅ ፤ የልብ አፍቃሪ ፡ የሚል ፡ ጭውውት ፡ ሊያደርጉ ፡ ‘‘ፍቅር’’ ስለሚለው ፡ አርእስት ፡ ምላሶቸው ፡ ስቶ ፡ አያውቅም ። መረያቸው ፡ ሁሉ ፤ ስለትምህርት ፤ ስለመንደላቂና ፡ ስለተፈጥሮ ፡ ውነው ፤ ቁምነገርን ፡ የያዙ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ሲታዩ ፤ ከሰው ፡ አፍና ፡ ዓይን ፡ መሳቃቸው ፡ አልቀረም ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ከጭራቅ ፡ የባሰ ፡ አውሬ ፡ ነው ። ከፍራፍሬና ፡ ከአብት ፡ ሥጋ ፡ አልር ፡ እርስ-በርሱ ፡ ይባላል ። እኔ ፡ ጎደኛዬን ፡ ቀን ፡ በምላሴ ፡ ስቆረጥመው ፡ አውላለሁ ። ሌሊትም ፡ በሕሊናዬ ፡ ሳመሰኳው ፡ አድራለሁ ። በዓለማችን ፡ ላይ ፡ ከሚደረጉት ፡ ጭውውቶች ፡ አብዛኛው ፡ ሐሜት ፡ መሆኑንና ፤ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ የጊዜ ፡ ድርሻ ፡ እንዳለው ፤ የሶሺያል ፡ ሊታውንት ፡ ያምናሉ ። እያንዳንዳችንም ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ የምናሳልፋቸው ፡ ሰዓቶች ፡ ምስክሮች ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። በተለይም ፡ የቡና ፡ እፍታና ፡ የመሸታ ፡ ጣሙ ፡ የሚታወቀው ፤ ‘‘የእንጨሌና-የእንጨሊት’’ ፡ ጉዳይ ፡ ከንፈር ፡ ሲመጠበት ፡ ይመስላል ።

የገሀሉ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፤ ከሐሜትና ፡ ከሽሙጥ ፡ የንጹ ፡ ፍጹም ፡ ቅዱሳን ፡ አልነበሩም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከሌላው ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ አይለዩም ። ስለዚህ ፡ የጊዜ ፡ ግላለፈያቸውንና ፤ የጨዋታ ፡ ግማሬሟቸውን ፡ ቢፈልጉ ፡ በተለይ ፡ ልንፈርድባቸው ፡ አይገባም ።

‘‘እገሌ ፡ ምን ፡ አደረገ እገሌትስ ፡ ምን ፡ ሆነች?’’ እያሉ ፡ ወሬ ፡ ሲቃርሙ ፡ የገሀሉና ፡ የአበባ ፡ ወዳጅነት ፡ ትኩስ ፡ አርእስት ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። ‘‘——እንዴት ፡ ቢደፍር ፡ ነው ፡ የአጅሬን ፡ ልጅነው ፡ አባት ፡ ያላየው ፡ ጉድ!’’ ቢል ፡ የመንደር ፡ ሙሌ ፡ የመሸታ ፡ ዕውቀቱን ፡ ሲተችበት ፤ የፍቅር ፡ ዘመን ፡ ያለፈባቸው ፡ ባልቲቶችና ፤ ገሀሉ ፡ ተና ፡ ብሉ ፡ ስላላያቸው ፡ የሚቆጩ ፡ ቀነጃጅት ፤ ተበል ፡ አድርገው ፡ ‘‘እርሱ-ምን ፡ ቸገርት ፡ የሴት ፡ ልጅ ፡ ሲያጋጥመው ። ’’በማለት ፡ አስተዋይነታቸውን ፡ እየገለጹ ፡ ይቀናጠው ፡ ነበር ።

የሐሜቱ ፣ ሽውታ ፣ ዙር ፣ ዙር ፣ ከወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ ጀር ፣ ውስጥ ፣ ጥልት ፣ አለ ። በጣም ፣ አዘኑ ። ምንም ፣ እንኳ ፣ ሰው ፣ ያየውንና-ያላየውን ፣ የሰማውንና ፣ ያልሰማውን ፣ የሆነውን ፣ ካልሆነው ፣ ጋር ፣ በማቀጣጠል ፣ እንደሚቀባጥር ፣ ባይስቱትም ፣ ቅር ፣ ከመሰኘት ፣ አልጻ ንም ።

ግሀሉ ፣ ለሥጋ ፣ ፈቃድ ፣ ተሸንፎ ፣ የአባቶችን ፣ ወግና ፣ ሥርዓት ፣ በመጣስ ፣ ከሞራል ፣ ውጭ ፣ የሆነ ፣ ተግባር ፣ ይፈጽማል ፣ በግለት ፣ በጣም ፣ አልሰጉም ። የመንፈሱን ፣ ብርታት ፣ ደህና ፣ እድርገው ፣ ያውቁታል ። በጠባዩ ፣ የተግሙኑ ፣ ናቸው ። አበባም ፣ ብትሆን ፣ ለፍ ቅር ፣ በመገዛት ፣ እስከዚህ ፣ ድረስ ፣ ራስዋን ፣ እንደግታ ዋርድ ፣ የሚጠራጠሩዋት ፣ አልነበሩም ። ግን ፣ አሳድጉ ዋት ? ከየትስ ፣ ተምራውያሳዘናቸው ፣ የሰው ፣ ትችት ፣ ነበር ። እግዚአብሔር ፣ ችግራቸውን ፣ በመመልከት ፣ አንድ ፣ ደጋፊና ፣ አሳቢ ፣ ቢፈጥርላቸው ፣ ደግሞ ፣ ሰይጣን ፣ በሰው ፣ ምላስ ፣ ላይ ፣ አድሮ ፣ ይነሳባቸውን?

ነገሩ ፣ በጣም ፣ ከነከናቸው ። ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ብቻቸ ውን ፣ ካሰላሰሉት ፣ በኋላ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ አበባ ፣ ባልተገኝ ችበት ፣ ቆይታ ፣ ለግሀሉ ፣ እንደዋዛ ፣ አሜወቱት ። በንግግራቸውም ፣ እንዲያስተያይዙት ፣ በመጠንቀቅ ፣ "ካቶ ፣ ሰው ፣ ምን ፣ ሆኖ ፣ ነው ፣ ያለ ፣ ጉዳዩ ፣ የሚቀባጥር ? በሌላው ፣ ላይ ፣ መዘባረቅ ፣ የተፈጥሮ ፣ ዓመል ፣ ሆኖበት ፣ እኮ ፣ ነው" ፣ ሲሉ ፣ የሐሜት ፣ ወሬ ፣ እንግሥተው ፣ ስለርሱና ፣ ስለአበባ ፣ ሕዝቡ ፣ የሚፈተፍተውን ፣ ትችት ፣ በለዘብታ ፣ ገለጹለት ። ግሀሉ ፣ ነገሩ ፣ አስደንቆትና ፣ አሳዝኖት ፣ አገጩን ፣ በጀ ፣ ደግፎ ፣ በትካዜና ፣ በተሞና ፣

ላዳመጠ ፣ በኋላ ፣ "እርግጥ ፤ አብረን ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ እንገፀራቸራለን ። እንደግፈቅራት ፣ ደግሞ ፣ አልቸገ ልዎትም ። በጣም ፣ እመዳታለሁ ። ነገር ፣ ግን ፣ ከሕግ ፣ የ ወጣ ፣ እንዳችም ፣ የብልግናና ፣ የንውር ፣ ተግባር ፣ ፈጽመ ል ፣ ብለው ፣ ተርጣሬ ፣ ቢያድርብዎት ፣ በእምላክ ፣ ስም ፣ ልግልልዎት ፣ ,,አላቸው ። ግሀሉ ፣ እንኳንስ ፣ በሐበት ፣ መዝትና ፣ በውሸት ፣ መቀለድ ፣ የማይወድ ፣ ሰው ፣ ነው ፣ ይህንን ፣ ጠባዩን ፣ መያዘር ፣ ለምለም ፣ ካሁን ፣ በፊት ፣ እማርተው ፣ ያውቁታል ።

"ውይ ፣ ልጄ ! እረ ፣ ምን ፣ ባልከሃየሰውን ፣ ወሬ ፣ አሜወትከህ ፣ እንጅ ፣ የማለተግመንብህ ፣ ሆኘ ፣ ነውን ሲሉ ፣ በግስተባበል ፣ ሐሜተኞችን ፣ ይራገሙ ፣ ቀጠለ

ሐሳቡን ፣ ለመገለጽ ፣ ከዚህ ፣ የተመቸ ፣ ሰዓት ፣ እንደማያገኝ ፣ ግሀሉ ፣ ተረዳ ። ጀግጌል ፣ መላከስ ፣ ልምን ፣ ያሻልሰራሉ ፣ ቢጠይቃቸው ፣ የተሻል ፣ እይሆን ምንከመተመጫው ፣ ብድግ ፣ አለና ፤ እንገቱን ፣ ደፍቶ ፣ መሬት-መሬቱን ፣ እያየ ፣ "———እነሆ ፣ እኔ ፣ ትዳር ፣ ሥያዝ ፣ ከሚገባኝ ፣ ወቶት ፣ ደርሻለሁ ። በጉዳዩም ፣ ካሰብኩበት ፣ ረጅም ፣ ጊዜ ፣ አልፎዋል ። ነገር ፣ ግን ፣ የጋብቻ ፣ ምርጫየ ፣ በአበባ ላይ ከግሪቶአዘለለምና ፈቃድዎስ ፣ ቢሆን ፣ ልጅዎን ፣ ለሚስትነት ፣ እንዲሰጡኝ ፣ እሰምናለሁ" ።

ይህንን ፣ የመሰለ ፣ ተያቂ ከግሀሉም ፣ ሆነ ፣ ከሌላ ፣ ሠንድ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ የሚተርብላቸው ፣ መሆኑን ፣ አላጠኑም ። ነበር ። ቢሆንም ፣ እንደአባቶች ፣ ልማድ ፣ በሥግግል ፣ በኩል ፣ እንጅ ፣ እንደዚህ ፣ ቃል-በቃል ፣ ይደርሰዋል ፣ ብለው ፣ አላሰቡትም ። ግንስ ፣ ከድፍረት ፣ አቀራረብ ፣

የወጻጅነት ፡ ስሜት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አቃንተው ፡ ተርጉ መውታል ። አልተሳሳቱም ።

አበባ ፡ ቁመሀደር ፡ ሆና ፡ እንድትቀር ፡ የማይታለም ፡ ነው ። መጻሯሰ ፡ ካልቀረ ፡ ከማህሉ ፡ የሚመረጥ ፡ ባል ፡ ታገኛለችን?ዘበት?ነው።ልጃቸው፡አስተዳደጓ፡የታረመ፡ነው፡ ሁለቱ ፡ ጠባይ ፡ ለጠባይ ፡ ተኖውቀዋል ። ተግባብተዋል ፡ ሲሆን ፡ ራሳቸው ፡ ፈልገው ፡ ሊያገቡለት ፡ ቀራቢነታቸው ፡ ያስገድዳቸው ፡ ነበር ። ስለውለታውስ ፡ ቢሆን ፡ አበባን፡ በጋብቻ ፡ ቢሰጡት ፡ ይበዛባቸዋልን?እረ ፡ ደስ ፡ እያላቸው!

ማህሉም ፡ ከአማጭ-ረጣጭ ፡ ጋር ፡ ሳይለማመጥ ፡ ጉዳዩ ፡ እንደዚህ ፡ በቀላል ፡ ስለተፈጸመለት ፤ ወደቤቱ ፡ እየተደሰተ ፡ ሄደ ። ዕለቱን ፡ እንድ ፡ አሀያ ፡ የሚያህል ፡ ሙከት ፡ ገጠመ ፡ እጅ-መንሽ ፡ ላከላቸው ።

ግን ፤ ከጠፍር ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ የቤቱን ፡ ጣሪያ ፡ ግርር ፡ እየቆጠረ ፤ ከበነጋው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እርጅናው ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የሚያከናውኑትን ፡ የጉር ፡ ተግባሮች ፡ ሲከልስ ፡ አመሸ ። ገና ፡ ምስት ፡ ጉልኾች ፡ ሳይጣጹ ፡ የትዳር ፡ ወጡን ፡ ይቀምሙ ፡ ጀመር ። “ለአበባ ፡ የሚያደርጓላትን——ለጉጀው ፡ የሚፈጽመውን——ሥየሚወልዱትን ፡ ልጆች ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ “——ሁለት ፡ ወንዶችና ፡ እንዲት ፡ ሴት ፡ ይቢታናል ። ——ሉላ ፡ የተሻለ ፡ ዘመናዊ ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ግሙሪት ፡ አሰብን——ቅሐሳቡ ፡ ብቻ ፡ እንኳ፡ አቢጸሰቱት፡ ብቻውን፡ ይፈግ ፡ ነበር ። አበባን ፡ በማግኘቱ ፡ ራሱን ፡ በማም ፡ ዕድለኛ ፡ እድርጉ ፡ ገመተው ። እርስዋስ“በተቻለኝ ፡ አትሜ ፡ ማስደሰት ፡ አለብኝ” ፡ ሲል ፡ ቃል ፡ ገባ ፡ “ያም ፡ ሆና ፡ እርስዋ ፡ መጀመርያ፡ ማወት፡ ይገባታልን?—

ከጥንቱ ፡ የጋብቻ ፡ ባሕላችን ፡ ውስጥም ፤ እንደዘመናዊው ፡ ዓይነት ፡ ቃል-ኪዳናቸውን ፤ በመግባባትና ፡ በመፈቃቀድ ፡ የሚፈጽሙ ፡ ጉልማሶችና ፡ ኩረጻዎች ፡ ነበሩ ። ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ ማህሉ ፡ አንደኛው ፡ ነው ።

“ቅር ፡ የሚላት ፡ እንደሆንስ?——ትታዘበኝ ፡ ይሆን? ——መሆኑን ፡ እኔ ፡ እንደማፈቅራት ፡ ታፈቅረኛለች? አሻፈረኝ ፡ እስከማለት ፡ ግን ፡ ልትጠላኝ ፡ አትችልም ። ምንም ፡ አይደለም ፤ እየቆየች ፡ ትወደኛለች ። ——ታዲያ ደፍሮ ፡ መናገሩስ?እንዴት ፡ ትገምተኝ?——አንዴ ፡ ከተወ ረድኩትማ ፡ ያበጠው ፡ ይፈንዳ ፡ ማለት ፡ ነው——ነገ ነው ፡ የምጠይቃት——” ፡ ማህሉ ፡ እንደዚህ ፡ በሐሳብና ፡ በመልካም ፡ ምኞት ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሲንሳፈፍ ፤ የዕንቅልፍ ፡ ማዕበል ፡ ሽልብ ፡ አድርጉ ፡ ወሰደው ።

በበነጋው ፡ ግን ፤ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ ሲፎክር ፡ እንዳደረው ፡ እንኳንስ ፡ ሊጠይቃትና ፡ ትክ ፡ ብላ ፡ ስታየውም ፤ ምሥጢሩ ፡ የተገለጸበት ፡ ኃጢአተኛ ፡ ይመስል ፡ ዓይኑን ፡ ያቀረቅር ፡ ነበር ። ብቻውን ፡ ሲሆን ፡ “ነገስ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልፈራም”እያለ ፡ ሲደነፋ ፤ ነገ ፡ ደርሶ ፡ ሲገናኙ ፡ ግን ፡ መላ ፡ ቅጡ ፡ እየጠፋው ፡ አንዲት ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ሳይጥል ፡ ሲለያዩ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አለፈ ፡

ማህሉ ፡ እንደቀድሞው ፡ ተዝናንቶ ፡ መጫወት፡ ተወ፡ አበባ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሆና ፡ ታየችው ። በሕሊናው ፡ ውስጥም ፡ ድንገት ፡ አደገች ። ከትናንት ፡ ወዲያ——ይቃ ለዳት ፡ የነበረችው ፡ ሕፃን ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ በሚሰነዝረው ፡ ዪልት ፡እንደቂል ፡ የምትገምተው ፡ ትልቅ ፡ እመቤት ፡ መ ሰለችው ። ስለዚህ ፡ ግንኙነታቸው ፤ እንደባዳ ፡ የቀዘቀዘ ና ፡ ሽርሽራቸውም ፤ እጅን ፡ ወደኋሊት ፡ አጣምሮ ፡

በጸጥታ ፡ መራመድ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። አበባ ፡ ግን ፡ በኩልዋ ፡ ምሥጢሩ ፡ ስላልገባት ፡ "ምን ፡ በደል ፡ ሠርቸው ፡ ይሆን" ስትል ፡ በጥርጣሬ ፡ መስጋትዋ ፡ አልቀረም ።

የቆጡን ፡ አወርድ ፡ ብላ ፡ የብብትዋን ፡ ጣለች ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ ዓይነት ፤ በደስታና ፡ በጨዋታ ፡ የሚያሳልፉትን ፡ ጊዜ ፡ ከናካቴው ፡ በማደፍረሱ ፡ ሣህሉ ፡ በጣም ፡ ተጸፀተ ።"——ይህ ፡ ሁሉ ፡ እኮ ፡ የይሉኝታ ፡ ፍራቻ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ምን ፡ ነውር ፡ ተገኘበት——እንዲት ሕፃን ፡ ልጅን ፡ መጠየቅ ፡ እሰከዚህ ፡ ድረስ ፡ እንዴት ፡ ያስፈራልኮ በዞችሰ ፡ በኃይል ፡ ነጥቀው ፡ ይወስዳሉ——ዲያ ፡ እስኪ ፡ አንተስ ፡ ወንድ ፡ ይውጣህ!——ነገ ታየኛለህ" ! ሣህሉ ፤ ብዙ ፡ ሌሊቶች ፡ ከራሱ ፡ ጋ ሲሮክከር ፡ ካደረ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ረታ ። ያውም ፡ በሰንት ፡ ጭንቀት ፡ ነበር ።

አበባ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ውላ ፡ ስትመለስ ፤ ከበራፋቸው ፡ አጠገብ ፡ በሚገኘው ፡ የዋርካ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተቀምጠ ፤ ቅጠልና ፡ ሣር ፡ ሲበጣጥስና ፡ ከወፎቹ ፡ ጋር ፡ ሲጫወት ፡ ቆያት ። እንደደረሰች ፡ «እስቲ ፡ ደብተርሽን ፡ »አለና ፡ ገሌን ፡ ያገለባብጥ ፡ ጀመር ። ሐሳቡ ፡ ወዲያው ፡ እንደመ ጣች ፡ ሊነግራት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከፊቱ ፡ ስትቆም ፤ ጉራው ፡ ሁሉ ፡ ጥሎት ፡ ስለሸሸ ፤ በጭንቀት ፤ ፍዝ ፡ የማይ ገባውን ፡ ኤ ፡ ቢ ፡ ሲ ፡ መመራመር ፡ ቀጠለ ። ያው ፡ መከረ ኛ ፡ ዉለማ ፡ ደርሶለት ፤ ጋሻ ፡ ሆኖ ፡ ቢከላከልለት ፡ ይሻለዋል ። ስለዚህ ፡ የሰውን ፡ ፊት ፡ የሚያጋልጠው ፡ የቀን ፡ ብርሃን ፡ ጨርሶ ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ ለሽርሽር ፡ መሔዴን ፡ መረጠ ። ከመንደሩ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አቅጣጫ ፡ በምታመራው ፡ ቀጭን ፡ መንገድ ፡ ጉዝዋቸው ፡

ን ፡ ቀጠሉ ። የምሽቱ ፡ ውጋጋን ፡ ድብዝብዝ ፡ ብሎ ፡ ፊት ፡ ለመሸሸግ ፡ ሲችል ፤ ከእንድ ፡ ቋጥኝ ፡ ላይ ፡ አረፍ ፡ አሉና ፡ ነገራት ። ግን ፡ ነፍስ ፡ ውጭ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ሥቃ ይ ፡ ነበር ። "ሰው ፡ ሆኖ ፡ መቸም ፡ መኳል ፡ መዳር ፡ አይቀርምና——ሚስት ፡ እንድትሆኝኝ ፡ ፈቅጀ ፡ እናት ሽን ፡ ጠይቄአለሁና ፡ እንዳታሳፍሪኝ ፡ »ስንት ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ያጠናው ፡ ዲስኩር ፡ የት ፡ ጠፋከአዳም ፡ እንስቶ ፡ እስከ ፡ ነጋድራስ ፡ ሥዩም ፡ ድረስ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ የጋብቻ ፡ ዜና ፤ እንደሮሜዎ ፤ በስሜት ፡ ሊሰብከላት ፡ ኣልነበረምን?ያም-ሆኖ ፡ እንኳን ፡ እንቅጩ፡ ካፉ ፡ወጣለት፡ እነዚህን ፡ አረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ለመትፋትም ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንዳማጠ ፡ ለመገመት ፡ አያዳግትም ። የሰውን ፡ ገበና ፡ የሚያጋልጠው ፡ ያ ፡ መከረኛ ፡ የቀን ፡ ብርሃን ፡ ኖሮ ቢሆን ፤ ቀዝቃዛ ፡ ላብ ፡ በግንባሩ ፡ ቆረር ፡ ሲልና ፡ አብራኩ ቹ ፡ ሲንቀጠቀጡ፡ ጉድ ፡ በወጣልሱ ፡ ደረቱን ፡ ፈንቅሎ ፡ የሚወጣ ፡ እስኪመስለው ፡ ድረስ ፡ ሲደነፋ ፤ ምላሱም፡ ከተናጋው ፡ ጋር ፡ ተጣብቆ ፡ መናገር ፡ አቅቶት ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ጭንቀት ፡ በከንቱ ፡ ኦሮዋል ። አበባ ፡ እንኳንስ ፡ የመደንገጥና ፡ የመገረም ፡ ስሜት ፡ አሳ ሳየችም ። ለክንስ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እናትዋ ፡ አርድተዋት ፡ ኖሮ ፤ "እማማ ፡ በቀደም ፡ ለት ፡ ነገረችኝ። እኔ ፡ የምመለከትህ ፡ እንደትልቅ ፡ ወንድሜ ፡ መሆኑን ፡ አትስተውም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ መስመር ፡ ስትመጣብኝ ፡ ቅር ፡ መሰኝቴ ፡ ባይቀርም ፡ የምከፋ ፡ አይደለሁም ። በወንድምነት፡ ስተማመንብህ፡እንደኖርኩ፤ በባልነትህም፡ በበለጠ፡ እንደምመካብህ፡ አልጠራጠርም።"

ዝምድናችን ፡ የመቀራረብና ፡ የወዳጅነት ፡ ነው ፡

እንጅ ፣ የዘር ፣ አይደለም ። ስለዚህ ፤ በጋብቻችን ፣ ይበልጥ ፣ ሊጠነክርና ፣ ሊጠቅም ፣ ይችላል ።"

ሣህሉ ፣ ከደስታ ፣ ብዛት ፣ እንጥሩብ ፣ ቢዘል ፣ በወደደ ነበር ።

በጥንቱ ፣ ባሕል ፤ እንደዚህ ፣ የመሰለው ፣ የመተጫጨት ፣ ተግባር ፣ በጣም ፣ ያልተለመደ ፣ መሆኑ ፣ አይዘነጋም ። ነገር ፣ ግን ፣ ሣህሉ ፣ በቀጥታ ፣ ወይዘሮ ፣ ለምለምን ፣ ሲለምን ፤ በተጨማሪ ፣ አበባን ፣ ጠይቋል ። ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ በበኩላቸው ፣ አበባን ፣ ማማከራቸው ፣ የብልህነት ፣ እርምጃ ፣ ነው ። ከሁሉም ፣ ይልቅ ፤ አበባ ፣ የሰጠችው ፣ መልስ ፤ ከዘመናዊው ፣ ወደድኩህ-ወደድኩሽ ፤ የጠለቀ ፣ አስተያየት ፣ ነበር ፣ ለግለት ፣ ያስደፍራል ።

ከዚህ ፣ ጊዜ ፣ ጅምሮ ፣ የሁለቱ ፣ አቀራረብ ፣ የመተፋፈርና ፣ የመሸኩርመም ፣ ጠባይ ፣ ቢታይበት ፣ ቅሉም ፣ የመተዋወቅና ፣ የመግባባት ፣ መንፈስ ፣ ነበረበት ። አበባ ፣ የትምህርቱ ፣ ጉዳይ ፣ በቅርብ ፣ ጊዜ ፣ እንደሚቋረጥ ፣ በመገንዘብ ፤ ዝንባሌዋን ፣ ወደ ፣ ቤት ፣ ባልትና ፣ ማጠናቀቅና ፣ ወደቁንጅና ፣ አከባከብ ፣ አዛወረች ። ግጥግጠሽ ፣ ከተደረገ ፣ በኋላ ፤ ትምሕርት ፣ ቤት ፣ መሔዱን ፣ ፈጽሞ ፣ አቆመች ። ብዙዎች ፣ እማጮችና ፣ ዓይናቸውን ፣ ጥለውባት ፣ የነበሩ ፣ ጉልማሶች ፣ ጣቶቻቸውን ፣ ነክሰው ፣ ቀሩ ። መቸም ፣ አምላክ ፣ ለሣህሉ ፣ መድቦዋት ፣ ኖሮ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እስከዛሬ ፣ ያንቀላፋ ፣ ኑሮዋልን ፣ ወይንስ ፣ ትጠብቀናለች ፣ ብለው ፣ አሰቡ ፣ ሠርጉ ፣ ከመንፈቅ ፣ በኋላ ፣ እንዲፈጸም ፣ ተቀጠረ ። ይህ ፣ የስድስት ፣ ወር ፣ ጊዜ ፣ ለሣህሉ ፣ ዘለዓለም ፣ መስሎ ፣ ታየው ። እንደወጉስ ፣ ቢሆን ፣ ዓመትና ፣ ሁለት ፣ መጠባበቅ ፣ ነበረበት ። በወንድምነት ፣

ስሜት ፣ ተዳፍኖ ፣ የነበረው ፣ ፍቅር ፣ አሁን ፣ ቃጠሎ ፣ እሳት ፣ ሆነበት ። ነበልባሉ ፣ ሰውነቱን ፣ አመድ ፣ አደረገው ፣ አበባ ፣ የአስራ ፣ አምስት ፣ አፍላ ፣ ስለነበረች ፣ የወደዳት ፣ ይቅርና ፤ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ያያትም ፣ መከነፋ ፣ አይጠረጠርም ፣ ሣህሉ ፤ቀኑ ፣ እንደሳምንት፤ወሩ፣እንደዓመት፣ተጐተተበት።

ታላቁ ፣ የሒሳብ ፣ ሊቅ ፣ ዶክተር ፣ አይንስታይን ፣ ስለ ፣ ጊዜ ዝምድና ፣ ሲገልጽ ፤ ፍቅረኛውን ፣ የሚሸኝ ፣ ጉልማሳ ፣ ሰዓቱ ፣ ሲበርበት ፤ የእርኛውን ፣ መመለስ ፣ ለሚጠባበቀው ፣ ወጣት ፣ ደግሞ ፣ ይጐተትበታል ፣ ይላል ። እንደዚሁም ፤ ለሣህሉ ፤ አበባን ፣ ይዞለት ፣ የሚመጣው ፣ የሠርግ ፣ ባቡር ፣ ዳተኛ ፣ ሆነበት ።

እንዳይደርስ ፣ የለም ፣ የቀጠሮው ፣ ቀን ፣ ተቃረበ ፣ ። በሁለቱም ፣ በኩል ፣ ድግሥ ፣ ማሰናዳቱ ፣ ተጀመረ ። ለስሙ ፣ ሁለት ፣ ቤቶች ፣ ይባል ፣ እንጅ፤ ወጭው፣ ገንዘብ፣ የሚዘገነው ፣ ከሣህሉ ፣ ሣጥን ፣ ብቻ ፣ ነበር ። የሴት ፣ ወገን ፣ ድግስ ፣ ከወንድ ፣ ወገን ፣ መሰናዶ ፣ እንዳያንስና ፤ በነጋድራስ ፣ ሥዩም ፣ ቤተ-ዘመዶች ፣ ዘንድ ፣ የችግር ፣ ቅሬታ ፣ እንዳይፈጠር ፣ በማሰብ ፣ አስፈላጊውን ፣ ድርጅት ፣ ከማቅረብ ፣ አላፈገፈገም ። ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ በበኩላቸው ፣ በሴትነት ፣ ሙያቸው ፤ የሁለቱም ፣ ክፍሎች ፣ ድግስ ፣ በሚገባ ፣ መደራጀቱን ፣ ይከታተሉ ፣ ነበር ። እንደዚህ ፣ የተወሳሰበና ፤ የተግሠረ ፣ ጋብቻ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ታይቶ ፣ እንደማይታወቅ ፣ እርግጥ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ በዘመናት ፣ ውስጥ ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ ከተራው-ቤተ ፣ ሰብ ፣ አስደናቂ ፣ ታሪክ ፣ መቀዳቱ ፣ አይዘነጋም ።

ቃል-ኪዳናቸው ፤ የሠርጉ ፣ ዋዜማ ፣ ለት ፣ በሥርዓተ ፣ ተክሊል ፣ ጸደቀ ። ካህኑ ፣ የሙሽሮቹን ፣ ጣቶች ፣ በእንድ ፣

ቀለበት ፣ አጣምሮ ፣ "እግዚአብሔርም ፣ አለ ፤ የምታጫው ተው ፣ የኑሮ ፣ ጓደኛ ፣ ለአዳም ፣ እንፍጠርለት ። እግዚአብሔር ፣ አዳምን ፣ በእንቅልፍ ፣ አስሮ ፤ ከግራ ፣ ጉኑ ፣ አጥንት ፣ አወጣና ፤ ሔዋንን ፣ ሠራለት ። "የሚለውን ፣ ክፍል ፣ ካነበቡ ፣ በኋላ ፣ "እናንተ ፣ አንድ ፣ ሥጋ ፣ ናችሁ ፣ አምላክ ፣ አንድ ፣ ያደረገውን ፣ ሰው ፣ አያሊያየውም ፡" ሲሉ ፣ ጸሎተ ፣ ቡራኬ ፣ ደገሙ ። በሥጋ ፣ ወደሙ ፣ አጸኑዋቸው ። ካለመቃብር ፣ የሚለያያቸው ፣ ይኖር ፣ ይሆን ?

የአበባ ፣ ሠርግ ፣ በክርስትናዋ ፣ ጊዜ ፣ ከተደረገው ፣ ድግስ ፣ ጋር ፣ የሚወዳደር ፣ ባይሆንም ፣ በመጠኑ ፣ የሚያስደስት ፣ ነበር ። ይህም ፣ ሊፈጸም ፣ የቻለው ፣ በግሀሉ ፡ ኪዳራ ፣ ስለሆነ ፣ ሊመሰገን ፣ ይገባዋል ።

ሁለቱ ፣ ቤተሰቦች ፣ ጎረቤት ፣ እንደሆኑ ፣ አመልክተናል ። ስለዚህ ፣ የተጣሉት ፣ ዳሶች ፣ አቅራቢያ ፣ ነበሩ ። ተጋባዦቹ ፣ በመጀመርያ ፣ ከሴት ፣ ወገን ፣ ደርሰው ፣ ከበሉና ፣ ከጠጡ ፣ በኋላ ፣ ወደ ፣ ወንድ ፣ ወገን ፣ ድግሥ ፣ ያመራሉ ። የመጀመርያው ፣ ምግብና ፣ መጠጥ ፣ ሳይንሸራሸር ፣ በላይ-በላዩ ፣ ይታከልበታል። በዚህ፣ ሁናቴ ፣ ሞቅታና ውኪታ፣ የበዛበት ፣ የግሀሉ ፣ ዳስ ፣ ነበር ።

ሙሽራ ፣ ጉዞ ፣ ለማስረዘም ፤ በዙሪያ ፣ መንገድ ፣ ከተጠመዘዘ ፣ በኋላ ፤ "ሆ!ሎጋው ፣ ሽቦ!"እያለ ፣ ከሙሺሪት ፣ ቤት ፣ ደረሰ ። ሴቱ ፣ በልልታና ፣ በእስክስታ ፤ ወንዱ ፣ በሞታና ፣ በጭፈራ ፣ ተቀበለው ። እንደቀበሌው ፣ ወግ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፤ የወንድ ፣ ወገን ፣ "እገባለሁ ፣ "የሴት ፣ ወገን "አላስገባም" ፣ የሚባለው ፣ ግርግር ፣ በተነሣ ፣ ነበር ። በሁለቱ ፣ ቤተሰብ ፣ መካከል ፣ ግን ፣ ይህንን ፣ የመሰለው ፣ አጓጉል ፣ ትርምስ ፣ እንዲደረግ ፣ አልተፈቀደም ። በራፉ ፣

ወዲያው ፣ ተከፈተለትና ፤ ሚዜ ፣ በዳሱ ፣ ውስጥ ፣ ገብቶ ፣ ተገጠገጠ ። የሙሽራና ፣ የሙሽሪት ፣ የነገር ፣ አባቶች ፤ በሽማግሌዎች ፣ እማኝነት ፤ የጋብቻውን ፣ ውል ፣ ተፈራረሙ ። ጥሎሽ ፣ ተደረደረ ። ልጃቸውን ፣ ተቀብለው ፣ በመጡበት ፣ አኳኋን ፣ ተመለሱ ። አበባ ፤ ወደ ፣ ባል ፣ ቤት ፣ ስትሄድ ፣ እንደአንዳንድ ፣ ቅብጢዎች ፣ አላለቀሰችም ። ቅብጠትም ፣ ሳይሆን ፤ ሲዳሩ ፣ ማልቀስ ፣ ወግ ፣ ነበር ።

ማታውኑ ፣ ከሙሽርዬ ፣ ግቢ ፣ ጭፈራው ፣ ሲቀልጥ ፣ አመሸ ።

ሚዜ ፤ "ጫጉላሽ ፣ አብቧል ፣ ዛሬ ፤ ጫጉላሽ ፣ አብቧል ፣ ዛሬ ፤

እቴ ፣ ሽንኩሬ ! "

እያለ ፣ ሲደነክር ፤ ቆንጃጅት ፣ ደግሞ ፣ በመቀባበል ፤

"ይዟት ፣ መጣ ፣ ሲበር ፤

ወንድሜ ፣ ብር፣ ,, በማለት፣ ሰውነታቸው፣ አስኪዝል፣ ድረስ፣ አንገታቸውንና ፣ ቁንጻላቸውን ፣ አሳዩ ። ዘፈኑ ፣ ሳያቋርጥ፣ ሌሊቱ ፣ ወግ ፣ አለ ። እንደምታውቁት ፣ በበነጋው ፣ የብርሃን ፣ ቀን ፣ ይባላል ። እንደሥርዓቱ ፤ ሙሽራው ፣ እንድ ፣ ምንቸት ፣ የበግ ፣ ወጥ ፤ ሞሰብ፣ እንጀራና ፤ አንድ ፣ ትልቅ ፣ ጎብስት ፣ በተመረጡ ፣ ሚዜዎች ፣ አስይዞ ፣ ወደአማቱ ፣ ቤት ፣ ላከ ። ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ ወደ ፣ ጓዳ ፣ ለብቻቸው ፣ ገባ ፣ አሉና ፤ ጓቦውን ፣ ቆርሰው ፣ ቢፈትሹት ፣ በውስጡ ፣ ጥሬ ፣ ብር ፣ አገኙ ። በኩራትና ፣ በደስታ ፣ እየፈነደቁ ፣ ለዘመዶቻቸው ፣ ሁሉ ፣ አሳዩት ።

ይህ ፣ ባሕል ፤ ሙሽራዪቱ ፤ በድንግልና ፣ ከብሯ ፣ እንደተገኘች ፣ የሚያረጋግጥ ፤ ከሙሽራው ፣ የሚላክ ፣

ማሰረጃ ፣ ማለት ፣ ነበር ። ወይዘሮ ፣ ለምለም ፤ ሐሜት ፣ ይነሡ ፣ የነበሩት ፣ ጠላቶቻቸው ፣ ኩም-ይበሉ ፣ በማለት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በልጃቸው ፣ ላይ ፣ ጥርጣሬ ፣ ኑሮዋቸው ፣ አይደለም ። ወዲያው ፣ ሚዜዎቹ ፣ ተነስተው ፣ እያሸበሸቡ ፣

“ጥሩ’ቃ ፣ ሰበረልዎ
ጥሩ’ቃ ፣ ሰበረልዎ

ወንዱ ፣ ልጅዎ” እያሉ ፣ ሲያሜውቱዋቸው ፣ አምሽ ተው ፣ ተመለሱ ።

ፍሬውን ፣ ለመብላት ፣ ያብቃቸው ፣ እንጅ ፤ ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ የልጃቸውን ፣ አበባ ፣ በሚገባ ፣ አዩ ።

ምዕራፍ ፣ ፪ ፩

እነሆ ፣ አበባና ፣ ሣህሉ ፣ የኑሮ ፣ ጓደኝነታቸውን ፣ የጀመሩት፡ ከላይ፡እንደተጠቀሰው፡ ነበር። የጫጉላ፡ ጊዜዋ ፣ እንደተፈጸመ ፣ የቤትዋን ፣ ኃላፊነት ፣ በቀጥታ ፣ ተረከበች። የሚቆጣጠርና ፣ የሚዘልፍ ፣ አማት ፣ አልነበረባትም ። በሥራ ፣ የምታግዝ ፣ ገረድ ፤ ምቾትዋን ፣ የሚከባከብ ፣ ባልና ፤ በማንኛውም ፣ ምክር ፣ በትርቡ ፣ የሚገኙ ፣ እናት ፣ አልጐደለባትም ። የትዳርን ፣ ጣዕም ፣ ወለላ ፣ ወለላውን ፣ ትልስለት ፣ ጀመር ። እንዲት ፣ ይጣፍጣል!ከልብ ፣ የሚያ ፈቅር ፣ ባል ፤ ከበቂ ፣ ሲሳይ ፣ ጋር ፣ ሲገኝ ፤ እንዲያው ፣ መዝመንመንና፡ መፍነሽነሽ፡ነው፡እንጅ፡ምን፡ያስፈልጋል?።

ሣህሉም ፣ በበኩሉ ፣ ደስታው ፣ እንዲህ ፣ አልነበረ ም ። የተመኘውን ፣ አገኘ ። ያሰበውን ፣ ፈጸመ ። የመጨ ረሻው ፣ ግብ ፣ ሕይወትን ፣ ሙሉ ፣ በተድላ ፣ ማሳለፍ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

አበባ ፣ በናትዋ ፣ ብቸኝነት ፣ ቅሬታ ፣ እንዳይገባት ፣ በማሰብ ፣ ከቤቱ ፣ ተዛነብ ፣ አንድ ፣ ከፍል ፣ አስቀጥሎ ፣ አሠራና ፤ ወይዘሮ ፣ ለምለም ፣ መጥተው ፤ አብረዋቸው ፣ ተቀመጡ ።

ቤታቸው ፣ ሞቀ ። ትዳራቸው ፣ ደመቀ ። ምንም ፣ እንኳ ፣ እንደነጋድራስ ፣ ሥዩም ፣ አደራሽ ፣ ባለዝና ፣ ባይሆ ንም ፣ ውስጣቸውን ፣ ለሚያውቅ ፣ ጐረቤት ፣ የሚያስቀ ኑና ፣ የሚያስመጀ ፣ ቤተ ፣ ሰብ ፣ ሆኑ ።

ሣህሉ ፤ በቁንጅና ፣ ረገድ ፣ የሚደነቅለት ፣ ባይሆንም፡ የወንድ ፣ መልክ ፣ ነበረው ። በጠባይ ፣ ባልንጀሮቹን፡ ሁሉ፡ ያራኅፋቸዋል ። በሥራው ፣ ትጉህ ፣ ታታሪ ፣ ነው ። በችሎ ታውም ፣ ተመስግነዋል ። ባሕሪዩ ፣ እንዳቅቤ ፣ የለሰለሰ ፣ ነው ። ንዴትና ፣ ብስጭት ፣ የለበትም ። ስሜቱ ፣ በጥቂቅ ን ፣ ነገር ፣ የሚለዋወጥ ፣ አይደለም ። የኃዘንና ፣ የትካዜ ፣ መልክ ፣ በፍጹም ፣ ታይቶበት ፣ አያውቅም ፣ ነበር ። ምንም ፣ ቢደክመው ፤ ከሥራ ፣ ውሎ ፣ ሲገባ ፣ ፊቱን ፣ አያጠቁርም ። ግንባሩን ፣ አያኮሳትርም ። አበባን ፣ ሁል ፣ ጊዜ ፣ ሲመለከታት ፣ በፈገግታ ፣ ገጽ ፣ ነው ። ብታጠፋም ፡ በለዘብታ ፣ ይመክራት ፣ ነበር ፣ እንጅ ፣ የቁጣ ፣ አለንጋ ፣ አይሰነዝርባትም ። ደግሞ ፣ እንደአንዳንዶቹ ፣ ባሎች ፣ ሲወጡ-ሲገቡ ፣ መነጫነጭ ፣ በፍጹም ፣ ዘበት ፣ ነው ።

ቃል-ኪዳኑ ፣ የጸና፡ ነበር ። ከአበባ፡ በስተቀር ፣ ሌላ ፣ ሴት ፣ ቀና ፣ ብሎ ፣ አያይም ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ በጣም ፣ ስላፈቀ ራት ፣ ነው ፣ በግለት ፣ ትተሻ ፣ ይሆናል ። እርግጥ ፣ ሚስቱን እንደራሱ ፣ ይወዳት ፣ ነበር ። ምናልባት ፣ ከራሱም ፣ ይበልጥ ፣ ይሆናል ። ምክንያቱም ፣ ከራሱ ፣ አልቆ ፣ ይቆረቆርለት ፣ ነበርና ። ነገር ፣ ግን ፣ ፍቅር ፣ ይዘናል ፣

ከሚሉዋቸው ፣ ቆንጆጅት ፣ ጋር ፣ ሲናከሱና ፣ ሲላቀሱ ፣ የሚኖሩት ፣ ጐልማሶች ፣ ስንት ፣ ናቸው ? ባለቤቶቻቸው ንስ ፣ ከቤት ፣ አስቀምጠው ፣ በአደባባይ ፣ ቆንጆ ፣ አይናቻቸውን ፣ ሲያንከራትቱ ፣ የሚውሉ ፣ ሰዎችስ ፣ ሞልተው ፣ የለምንነስለዚህ ፣ ተግባርን ፣ ሊገዛው ፣ የሚችል ፣ የተፈጥሮ ፣ ባሕርይ ፣ ነው ። ከመጥፎ ፣ ልማድ ፣ ለመጠበቅም ፣ የመንፈስ ፣ ብርታት ፣ ያሻል ። ሣህሉ ፣ ሁሉንም ፣ አስተካክሎ ፣ የያዘ ፣ ወጣት ፣ ነበር ።

አበባስ ፣ ቢሆን ፣ ምን ፣ እንከን ፣ ነበረባት!የሚስት ፣ እህት ፤ የሕፃን ፣ ዓዋቂ ፣ ናት ። ዘወትር ፣ የምታስበውና ፣ የምታሰላስለው ፣ የጓዳዋን ፣ ጣጣና ፣ ባሏ ፣ የሚረካበትን ፣ ዘዴ ፣ ነው ። ልባም ፣ ባተሌ ፣ ናት ። ለሣህሉ ፣ ፍቅር ፣ አጸፋውን ፣ ትመልስለታለች ። ከርሱ ፣ በተቀር ፡ ሌላ ፣ ሱሪ ፣ ያጠለቀ ፣ ወንድ ፣ ያለ ፣ አይመስላትም ። ታፈቅረዋለች ። ስትፈራውና ፣ ስታከብረው ፣ በዚያው ፣ ልክ ፣ ነው ። ቢሆንም ፣ ምሥጢር ፣ አትሸሽገውም ፣ ነበር ። ስሕተትዋን ና ፣ ጥፋትዎን ፣ ትናዘዝለታለች ። ሌላው ፣ ቀርቶ ፣ በመንገድ ስታልፍ ፤ እየጠቀሱ ፤ እያኾጨና ፣ ከቤትም ፣ ድረስ ፣ አግላጅ ፣ እየላኩ ፣ ስለሚያስቸግሩዋት ፣ አንዳንድ ፣ ባለጌዎች ፣ ትነግረው ፣ ነበር ። እርሱ ፣ ግን ፣ ነገሩን ፣ እንደቀልድ ፣ ስቆ ፣ ያሳልፈዋል ። ሲያምናት ፣ ከመጠን ፣ በላይ ፣ ስለነበር ፡ የቅናት ፣ ስሜት ፣ ሊያድርበት ፣ አልቻለም ። በሰዎቹም ፣ ላይ ፣ ቂም ፣ በመያዝ ፣ ሊበቀላቸው ፣ አልከጀለም። ይቅር ፣ ባይ ፣ ነበር ።

ይህ ፣ በዕለታዊ ፣ ተግባራትውና ፣ እንቅስቃሴያቸው ፣ ሊገልጽ ፣ የቻለ ፣ ባሕሪያቸው ፣ ነበር ። ከዚህ ፣ በተረፈ ፤ የመንፈስን ፣ ጥልቀት ፣ ሲለካና ፤ ኩላሊትንም ፣ ሊመረም

ር ፣ የሚችል ፣ እንድ ፣ ፈጣሪ ፣ ብቻ ፣ ሲሆን፤ የሰው ፣ልጅ ፣ ውስጣዊ ፣ ባሕርይ ፣ በትክክል ፣ ሊመዘን ፣ የሚቻለው ፣ ደግሞ ፣ በከባድ ፣ ፈተና ፣ ሲነጠር ፣ እንደሆነ ፣ መዘንጋት ፣ የለብንም ።

ችግር ፣ አላጐሳቆላቸውም ። መከራ ፣ አልነካቸውም ፣ እምብዛም ፣ ብልጽግና ፣ አላበሰበሳቸውም ። የምኞት ፣ እንጀራ ፣ እንዳይርባቸው ፤ በአቅራቢያቸው ፣ የለም ። ምኞት ፣ የራስን ፣ ይዞታ ፤ ከሌላ ፣ ሰው ፣ ምኞትና ፣ ብልጽግና ፣ ጋር፣ በማስተያየት፤ "እንደርሱው፣ ልሁን፣ ወይንም ፣ ልብለጥ ፣ "ከሚል ፣ ስሜት ፣ የሚመነጭ ፣ ፍላጐት ፣ ነው ። እነሣሀሉ ፣ የሚኖሩበት ፣ ቀበሌ ፣ የዘመኑ ፣ ሽብርቅርቅ ፣ ያልበዘበዘው ፣ ገጠር-ቀመስ ፣ ከተማ ፣ ነው ። የነዋሪ ዎቹም ፣ የምኞት ፣ ግብ ፤ ከቀበሌው ፣ የኑሮ ፣ ደረጃ ፣ አይዘልም ። የሣህሉ ፣ ቤተሰብ ፣ የኑሮ ፣ ደረጃም ፣ ከአካባቢው ፣ ጋር ፣ ሲመዛዘን ፣ ከፍተኛውን ፣ አቅዋም ፣ የያዘ ፣ ነው ። ለማለት ፣ ያስደፍራል ። ሁለቱም ፣ ተወልደው ፣ ያደጉት ፣ በዚሁ ፣ ከተማ ፣ ነው ።ወጣ ፣ ብለው ፣ ሌላ ፣ የበለጠ ፣ ከተማ አልጐበኙም ። ስለዚህ ፣ በትልልቅ ፣ ከተማዎች ፣ የሚታየው ፣ የኑሮ ፣ ዘበናይነት፣ እከክ ፣ አላሰቃያቸውም ፣ ነበር።

በጠቅላላው ፤ ባገኙትና ፣ ባላቸው ፤ ተደስተውና ፤ ረክተው ፣ ለመኖር ፣ የሚችሉ ፣ ቤተሰቦች ፣ ነበሩ ። እስከጊዜው ፣ ድረስ ፣ በሚገባ ፣ ፈጽመውታል ። ኃዘንና ፣ ትካዜ ፣ በጐጆዋቸው ፣ ላይ ፣ አንጐራብቦበት ፣ አያውቅም ። ምድጃቸው ፣ አልቀዘቀዘም ። ዘወትር ፣ ፍስሐና ፣ ሐሴት ፣ ነበር ። በተጋቡ ፣ በሁለት ፣ ዓመት ፤ ትዳራቸው ፣ በወንድ ፡ ልጅ ፣ ተመረቀ ፤ ተድላቸው ፣ ዕጽፍ-ድርብ ፣ ሆነ ።

ነገር ፡ ግን ፣ በኢዮብ ፣ ላይ ፣ የተነሣ ፣ ሰይጣን ፣ እንደዚህ ፣ ላሉት ፣ ቤተ፣ ሰቦች፣ ስለማያንቀላፋላቸው፤ የፈተና ፣

ወጥመዱን ፣ ዘርግቶ ፤ የውድቀታቸውን ፣ መታብር ፣ ከመማስ ፣ አይቦዝንም ። የመጨረሻውን ፣ ፈተና ፣ የሚያ ልፉት ፣ እንዴት ፣ ኃያላን ፣ ናቸው ?

ምዕራፍ ፣ ፱ ፣

የታሪካችን ፣ እምብርት ፣ የሆነችው ፣ ከተማ ፣ ባሕር ፣ ዳር ፣ ትባላለች ። በተፈጥሮ ፣ አቀማመጥ ፣ ረገድ ፤ በኢትዮ ጵያ ፣ ውስጥ ፤ ውብ ፣ ከሚባሉት ፣ ቀበሌዎች ፣ መካከል ፣ አንዱ ፣ ናት ። በስተሰሜን ፣ በኩል ፣ የተዘረጋው ፣ የጣና ፣ ሐይቅ ፣ ልዩ ፣ ውበት ፣ ይሰጣል ። በተመልካች ፣ ሕሊና ፣ ውስጥ ፤ የጸጥታና ፣ የሰላም ፣ ስሜት ፣ የሚያሳድር ፣ ነው ። በማመላለሻ ፣ ረገድ ፣ ከፍተኛ ፣ ጥቅም ፣ ከመስጠቱም ፣ በላይ ፣ የዓሣ ፣ ሀብት ፣ በሰፊው ፣ የሚያበረክት ፣ ነው ። በምሥራቅ ፣ በኩል ፤ የዓባይ ፣ ወንዝ ፣ ከሐይቁ ፣ ወጥቶ ፣ እየተፍለከለከ ፣ ረጅም ፣ ጉዞውን ፣ የሚቀጥልበት ፣ ታላቁ ፣ ሸለቆና ፣ ሜካ፣ አለ ። አንድ ፣ ሃምሳ፣ኪሎ፣ሜትር፣ዝቅ፣ብሎ እንደነጐድጓድ ፣ የሚያተመው ፣ ስመ ፣ ጥሩ ፣ የጢስ ፣ እሳ ት ፣ ፏፍቴ ፣ ይገኛል ። ወደግታ ፣ ሲሆን ፤ ከፍ፣ከፍ፣ቴው፣ የሚነሣው ፣ እንፋሎት ፣ በቀስተደመና ፣ ሕብረ-ቀለም ፣ በሩቁ ፣ ሲያንጸባርቅ ፤ በሐይቁ ፣ ማዕበል ፣ላይ ፣ የሚደነክረ ው ፣ የጀንበር ፣ ጮራ ፣ አስደናቂ ፣ የሆነ ፣ የውሃ ፣ ነበልባ ል ፣ ይፈነጥቃል ።

የበጋው ፣ ሙቀት ፣ ከሐይቁ ፣ አትጣጫ፣በሚ መጣው፣ ነፋሻ ፣ ዓየር ፣ እየተነጠረ ፣ ይቀዘቅዛል ። የክረምቱ ፣ ወራት በዝናም ፣ የለገሰ ፣ ነው ። ብርድ ፣ ግን ፣ አይበረታበትም ፣ ለምለም ፣ ቀበሌ ፣ ናት ፤ ጋራዎች፣ ሸንተረሮችና ፤ መስኮች ፣ በአረን ጓዴ ፣ ቀለም ፣ የተሸፈኑ ፣ ናቸው ። በተለይም ፣

በጸደይ ፣ ወራት ፤ በአበቦችና ፣ በአዝመራዎች ፣ አሸብርቀ ው ፣ ሲታዩ ፣ ቁንጅናቸው ፣ ይደምቃል ። ወይራ ፤ ዝግባ ፣ ዋርካ ፤ ግራር ፤ ዳቱግና ፣ የመሳሰሉት ፣ ታላላቅ ፣ ዛፎች ፣ በታናናሽ ፣ ቁጥቋጦች ፣ እየታጀቡ፣ ለቀበሌው ፣ ምገስና ፣ ጸጋ ፣ አጐናጽፈውታል ።

በአባይ ፣ ወንዝ ፣ መውጫ ፣ አጠገብ ፤ ወደሐይቁ ፣ ገባ ፣ ብላ ፣ ከርእሰ ፣ መሬት ፣ ላይ፣ የታነጸች፣ የመቤታችን ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አለች ። ይህች ፣ ደብር ፣ ጥንታዊ ፣ ዜና ፣ እንዳላት ፣ ካህናቱ ፣ ይተርካሉ ። የግራኝ፣ የጦር፣ ትጥቅ ፣ ነበ ር ፣ የተባለ ፣ አንድ ፣ ከብረት ፣ የተሠራ ፣ ቀሚስ ፣ ከቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ ግምጃ ፣ ቤት ፣ ውስጥ ፣ ስለሚገኝ ፣ ጥንታዊ ነትዋን ፣ ለማመን ፣ አያስቸግርም ። ጥቂት ፣ ምዕራፎች ፣ ራቅ ፣ ብለው ፣ ታሪካዊ ፣ ስመጥሮቹ ፣ የጻጋ ፣ እስጢፋኖስ ፣ ደሴቶች ፣ ከውሃው ፣ ውስጥ ፣ አንገታቸውን ፣ አሰግገው ፣ የወጡ ፣ ይመስላሉ ። በምዕራብ ፣ በኩል ፤ ለሙ ፣ የዘጌ ፣ መሬት ፣ የቡና ፣ ተክል ፣ ደን ፣ ልብሶ ፣ ይታያል ።

የውጭ ፣ ጉብኝዎችን ፣ ለመሳብ ፤ የተፈጥሮ ፣ ውበት ና ፣ የአቀማመጥ ፣ ስጦታ ፣ አላት ። በማንኛውም ፣ ረገድ ፣ የተመቸች ፣ ከተማ ፣ ናት ። ወደጫካው ፣ ወርደው ፣ የዱር ፣ አውሬን ፣ ማደን ፣ ለሚሹ ፣ ጉበዛዝት ፣ ጥሩ ፣ የማረፊያ ፣ ጣቢያ ፣ ትሆንላቸዋለች ። በጤና ፣ ጉድለት ፣ ምክንያት ፣ ነፋስ ፣ እንዲለውጡ ፣ ለተመከሩ ፣ በሽተኞች ፣ ሐኪሞች ፣ የመሰከሩላት ፣ ቀበሌ ፣ ናት ። ጥንታዊ ፣ የታሪክ ፣ ቅርስን ፣ ለመመራመር ፣ የሚሹ ፣ ሰዎች ፣ መልካም ፣ ውጤት ፣ ይዘው ፣ ሊመለሱ ፣ ይችላሉ ። የውሃ ፣ ጥቅም ፣ የሚያጠኑ ፣ ዓዋቂዎች ፣ ደግሞ ፣ የመጀመሪያ ፣ ውጥናቸውን ፣ የሚጥ ሉት ፣ በአባይ ፣ ወንዝ ፣ አካባቢ ፣ ሆኖ ፣ ይገኛል ። ከሁሉም

ይልቅ፤ የታላላቅ፡ ከተሞች፡ ኖሮ ፡ ጋጋታና ፡ ጩኸት ፡ የመ
ረራቸው፤ የሥልጣኔ፡ ዕድፍ፡ የሰለቻቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፤
የተፈጥሮ ፡ ውበትን ፡ በድግልናዋና ፡ በንጽሕናዋ ፡ ለመመ
ልከትና፡ ለማድነቅ፤ ጥቂት፡ ቀኖችንም፡ በሰላም፤ በጸጥታና፡
በዕረፍት ፡ ለማሳለፍ ፡ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ ይጐርፉ ፡ ነበር ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከደመቀ ፡ ከተማ ፡ ሸሽተው ፡ ከሚመጡት ፡
ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፤ ሕይወታቸውን ፡ አድሰው ፡
በአምላክ ፡ ግሩም ፡ ውበት ፡ ተደንቀው ፡ በሰላም ፡ በመመለ
ስ ፡ ፈንታ ፡ መጥፎ ፡ ተግባር ፡ ከኋላቸው ፡ እየተውና ፤
በሥልጣኔ ፡ ጠረን ፡ እየመረዙዋት ፡ ሲያልፉ ፡ ታይተዋል ።
መከረኛዋ ፡ ከተማ ፤ ለመንገደኞች ፡ በምታቀርበው ፡ መስ
ተንግዶ ፤ በደል ፡ በመከፈሏ ፡ ብዙዎቹ ፡ ነዋሪዎች ፡
መጸጸታቸው ፡ አልቀረም ።

ከእንደዚህ ፡ የመሰሉት ፡ ጉብኝዎች ፡ መካከል ፤
በከተማዋ ፡ ዜና ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የሚተላለፍ ፡ ተረት ፡
ፈጥሮ ፡ የተመለሰ ፡ ተጫን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበር ።
በባሕር ፡ ዳር ፡ ከተማ ፡ በሰነበተባቸው ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፤
አውሬ ፡ ለማደን ፡ አልሞከረም ፡ ነበር ። የታሪክ ፡ ቅርስን ፡
አልተመራመረም ። ወይንም ፡ የጢስ ፡ እሳት ፡ ፏፏቴ ፡
ኃይል ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ አላጠናም ——።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ተጫን ፤ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተምሮ ፡ የመጣ ፡ ወጣት ፡
ነበር ። የመሐንዲስነት ፡ ማዕረግ ፡ አለው ። በሙያው ፡
ታላቅ ፡ የሥራ ፡ ችሎታ ፡ እንዳሳየ ፡ ይነገርለታል ። በአዲስ ፡
አበባ ፡ ውስጥ ፡ ከተመሰገኑት ፡ ዓዋቂዎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ፡
ይላሉ ። ከፍ፡ያለ ፡ ሹመትና ፡ ኃላፊነት ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ።

ተጫን ፤ በመንፈሳዊ ፡ ረገድና ፡ በሃይማኖት ፡ በጣም ፡
የደከመ ፡ ወጣት ፡ ነው ። "የዳርዊንን" ፡ ዕምነት ፡ እንደዓ
ቅሙ ፡ ተቀብሏል ። ሞቶው ፡ (ዓለማው)"ባንድ ፡ ጊዜ ፡
እንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ እንኑር ። ዛሬንም ፡ እንድንደሰትባት ፡
ይገባል ። "የሚል ፡ ነበር ። ከተፈጥሮ ፡ ባሕርይ ፡ የበቀለና ፡
በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የጐለመሰ ፡ የባለጌነት ፡ ጠባይ ፡
አለው ። መጠጥ ፡ ያበዛል ። ዘማዊነት ፡ ያጠቃዋል ።
ያም ፡ ሆኖ ፡ ፡ በመጠኑ ፡ ቢፈጽመው ፡ ኖሮ ፡ ሚስት ፡
ስላልነበረው ፡ በጣም ፡ አይፈረድበትም ፡ ነበር ። ነገር ፡
ግን ፡ "ያየኋት ፡ ቆንጆ ፡ አትለፈኝ ፡ ,,ይላል ። በዚህም ፡
ላይ ፡ ;ንይለኛ ፡ ሞገድና ፡ እልህ ፡ አለበት ። ባይኑ ፡ የገባች
ችውን ፡ ሴት ፡ እስከመጨረሻው ፡ ያሳድዳታል ። ባለትዳር
ም ፡ ትሁን ፡ ወይንም ፡ ሴት ፡ አዳሪ ፡ ልዩነት፡አትፈጥርም።
የወረት፡ ፍቅር፡ በቀላሉ ፡ ይገዛዋል ። ስለዚህ፡ ለሔዋን፡ወነ
ኖች ፡ የነበረው፡ አስተያየት፡ ደግነት፡ የተቀላቀለበት ፡ነው።

ወደባሕር ፡ ዳር ፡ ከተማ ፡ ሲመጣ ፡ ግን ፡ ቆንጆዎችን ፡
ፍለጋ ፡ እንዳልሆነ፡ የሚታመን ፡ነው። ዘመዶቹ ፡ በዚያው ፡
አቅራቢያ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡
ከሰነበተ ፡ በኋላ ፡ እግረ፡ መንገዱን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡
አረፈ ። ከአዲስ ፡ አበባ ፡ አንዲት ፡ መኪና ፡ ይዘ፡መጥቷል ።
ለእንግዶች ፡ ማረፊያ ፡ የተዘጋጀው ፡ ሆቴል ፡ የታነጸው ፡
ከሐይቁ ፡ ዳርቻ ፡ ስለነበር ፤ ዋና ፡ ማዘውተርን ፡ ለሚ
ወዱ ፤ በጀልባ ፡ መንሸራሸር ፡ ለሚፈቅዱና ፡ ወይንም ፡
ከክፍላቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ የማዕበሉን ፡ ጨዋታ ፡
መመልከት ፡ ለሚሹ ፡ እንግዶች ፡ ሁሉ ፡ ፍላጐታቸውን ፡
የሚያረካ ፡ አቀማመጥ ፡ ነበረው ።

ጊዜው፡ከቀትር ፡በኋላ ፡ ወደ፡አስሩ ፡ ሰዓት ፡ ይሆናል ፡

ተጫን ፣ የተሲዓት ፣ እንቅልፉን ፣ ጨረሶ ፣ የግታ ፣ ነፋስ ፣ ለመቀበል ፣ በመኪናው ፣ ይንሸራሸር ፣ ነበር ። በጸጥታ ፣ ሽርሽር ፣ ሐሳብን ፣ ለማቅለለም ፣ ሆነ ፣ በጥልቅ ፣ ለማሰብ ፣ ጥሩ ፣ ጊዜ ፣ ነው ። ድምጽ ፣ አይሰማም ። የሐይቁ ፣ ማዕበል ፣ ጸጥ ፣ ብሎ ፤ ውሃው ፣ ከጀንበሩ ፣ ፀሐይ ፣ የተነሣ ፣ በደም ፣ የተበከ ፣ ይመስላል ። የነፋስ ፣ እንቅስቃሴ ፣ ቁ*ል ። ዛፎች ፣ እንኳን ፣ የሚወዛወዙት ፣ በመጠኑ ፣ ነበር ። የጋራዎች ፣ ጥላ ፣ ያረፈባቸው ፣ ሽሎቆች ፤ በሩቁ ፣ ሲመለከቷቸው ፣ የሚያስፈራ ፣ ግርማ ፣ አላቸው ። ጩኸት ፣ የለም ። አውሬ ዎችና ፣ ወፎች ፣ ተኝተዋል ። ከሚፈናጠቀው ፣ የጀንበር ፣ ሙራ ፣ በስተቀር ፤ ተንቀሳቃሽ ፣ ፍጥረት ፣ አልነበረም ። የከተማው ፣ አደባባይ ፣ እንኳ ፣ ያንቀላፋ ፣ ይመስላል ። ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ሲዘዋወሩ ፣ አይታይም ፣ ነበር ። አልፎ ፣ አልፎ ፣ አንዳንድ ፣ ሕፃናቶች ፣ መልእክት ፣ ለማድረስ ፣ ም ፣ ይሁን ፤ ከብቶችን ፣ ለማሰማራት ፤ በቀስታ ፣ ሲራመዱ ፣ ይታያል ። ሰንበት ፣ ስለሆነ ፣ ሁሉም ፣ በየቤቱ ፣ አርፏል ። በቀበሌው ፣ የሰፈነው ፣ የረጋ ፣ ውበት ፣ ነበር ።

ተጫን ፤ ይህንን ፣ ንጹሕ ፣ አየርና ፣ ፍጹም ፣ ጸጥታ ፤ "ዴትሮት" ፣ በነበረበት ፣ ጊዜ ፣ ከተመለከተው ፤ የጋዝ ፣ ጭስና ፤ የሞተር ፣ ጩኸት ፣ ትርምስ ፣ ጋር ፣ እያመዛዘነ ፣ በማድነቅ ፣ ሽርሽሩን ፣ በቀስታ ፣ ይቀጥል ፣ ነበር ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አበባ ፤ እንዲት ፣ የታመመ ፣ ዘመድ ፣ ጠይቃ ፣ ወደቤትዋ ፣ ትመለሳለች ። ሕፃን ፣ አሽከር ፣ በኋላዋ ፣ ያኩበኩብ ፣ ነበር ። ሁለቱ ፣ እግረኞች ፣ መኪናዋ ፣ ወደምታመራበት ፣ አቅጣጫ ፣ መጡ ። ተጫን ፣ ከመቅጽበት ፣ ገራፊ ፣ ዓይኑን ፣ ጣለባት ። ደም ፣ ግባትዋንና ፣ ቁንጅናዋን ፣ ተመለከተና ፣ ተደሰተ ። በሰውነቷ ፣ ቅ

ርጽም ፣ ጉመጋ ። በቁንጥና ፣ ቡመሸቀርቀር ፣ ብዙ ፣ የከተማ ፣ ቅሬዎች ፣ ይብለጨት ፣ ይሆናል ። ነገር ፣ ግን ፣ ግን ፣ እንደአበባ ! ክብካቤ ፣ ያልተቀላቀለበት ፣ ንጹሕ ፣ ውበት ፣ ነበራት ። በዚህም ፣ ላይ ፣ የአካባቢው ፣ ትርኢት ፣ ውበቷን ፣ በበለጠ ፣ እንደሚያጐላው ፣ የሚታመን ፣ ነው ። እንዲት ፣ የሚጸጸ ፣ ግልገል ፣ ከምድራበጻ ፣ ውስጥ ፣ ይልቅበለመለመ ፣ መስክ ፣ ላይ ፣ ስትፈነጭ ፣ ታምራለች ።

ተጫን ፣ ተደነቀ ። "አርትፊሲየል ፣ ብትጨማምርበት ፣ እንዴት ፣ ልትሆን ፣ ነው ፣ እባካችሁ ፣ ,,ሲል ፣ አሰበ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ከዚህ ፣ ላይ ፣ የተሳሳተ ፣ ይመስላል ። ምክንያቱም ፣ የሥልጣኔ ፣ አርትፊሲየል ፤ ያረፈበትን ፣ ነገር ፣ ሁሉ የተፈጥሮ ፣ ውበቱን ፣ እንደሚያቆሽሸው ፣ የሚታመን ፣ ነው ።

ያ ፣ ለስላሳ ፣ ሰሜቱ ፣ ወዲያው ፣ ተነካ ። በፍላጐት ፣ ተነደፈ ። መኪናውን ፣ እርስዋ ፣ ወደ ፣ ምትሄድበት ፣ አቅጣጫ ፣ ጠመዘዘና ፣ ባጠገቧ ፣ ሲያልፍ ፣ ፣"እ-ሀ-ሀ-ህህ" የሚል ፣ ድምጽ ፣ አሰማ ። ያን ፣ ጊዜ ፣ ዘወር ፣ ብትል ፣ ኖሮ ፣ "ባይን ፣ ጥቅሻ" ፣ ጉዳዩን ፣ ያስረዳት ፣ ነበር ። አበባ ፣ ግን ፣ ድምጹን ፣ ስትሰማ ፣ የባሰውን ፣ አንገትዋን ፣ አቀርቅራ ፣ ጉዞዋን ፣ በጥድፊያ ፣ ቀጠለች ። ተጫን ፣ እንደዚህ ፣ በቀላሉ ፣ መቾ ፣ የሚረታ ፣ ሰው ፣ ነበርና ፤ እንኳንስ ፣ አንዲት ፣ ባላገር ፣ ቢጤና ፣ ሰለጠን ፣ ያሉትም ፣ ቢሆን ፤ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ የንቀት ፣ ዓይን ፣ አሳይተውት ፣ አልቀሩም ። ብቻ ፣ ውርደት ፣ መቀበሉ ፣ አናደድው ። ቢሆንም ፣ ተሰፋ ፣ አልቆረጠም ። በመኪናው ፣ ሆኖ ፣ በኋላዋ ፣ እያደባ ፤ መግቢያዋን ፣ አይቶ ፣ ተመለሰ ።

የሰው ፣ ልጅ ፣ ዕውቀትና ፣ ችሎታ ፤ ለመጥፎና ፣ ለደግ ፣ ተግባር ፣ እንደሚውል ፣ ያለፉት ፣ ታሪኮች ፣ ያስረዱ

ናል ። ሊቃውንት ፣ የአቶሚክን ፣ ኃይል ፣ ለሰላማዊ ፣ አገልግሎት ፣ እንደማዋላቸው ፣ መጠን ፣ የፍጥረት ፣ እልቂት ፣ ጠንቅ ፣ እንዳደረጉት ፣ ደግሞ ፣ የሚሳት ፣ አይደለም ፣ ይህ ፣ ተቃራኒ ፣ ባሕርይ ፣ የሚገኘው ፣ በዓዋቂዎችና ፣ በታላላቅ ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ በማንኛውም ፣ የኑሮ ፣ ደረጃ ፣ የሚጐዳኘው ፣ ሕዝብ ፣ ጠባይ ፣ መሆኑ ፣ አይጠረጠረም ። አንዱ ፤ ቅን ፣ ተግባርን ፣ ለመፈጸም ፣ ሲያስብ ፤ ሌላው ፣ ደግሞ ፣ ተንኰልን ፣ ማሰላሰሉ ፣ አልቀረም ። የማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ ዕድገትና ፣ ውድቀት ፣ የሚመሠረተው ፣ ከዚህ ፣ ተነፃፃሪ ፣ የሐሳብ ፣ ምንጭ ፣ ነው ።

ተጫን ፤ በዚያች ፣ ቀን ፣ የአንጎሉን ፣ ኃይል ፣ ሲያደክም ፣ ያመሸው ፣ ያችን ፣ "የባላገር ፣ ቀብራራ"(አበባን) በእንዴት ፣ ያለ ፣ ዘዴ ፣ ለማሸነፍና ፤ ፍላጐቱን ፣ ለማርካት ፣ እንደሚችል ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የአቀራረብ ፣ መስመሮችን ፣ በመቀየስ ፣ ነበር ። ከሐሳቡ ፣ ጋር ፣ ውጣ፡ውረድ ፣ ሲባባል ፤ እስከሌሊቱ ፣ ዶሮ ፣ ጩኸት ፣ ድረስ ፣ ባይኑ ፣ እንቅልፍ ፣ አልዞረም ። ከወደ ፣ ንጋቱ ፣ ገደማ ፣ ትንሽ ፣ ሽልብ ፣ ሲያደርገው ፣ በሕልሙ ፣ መጥታ ፣ ቀሰቀሰችው ። ተጫን ፣ ያለመው ፤ ግታውኑ ፣ ትራሱንና ፣ እንሶላውን ፣ ሲነክስ ፣ ከመሸበት ፣ ፕላን ፣ የተለየ ፣ አልነበረም ። እንደዚህ ፣ ካለው ፣ ምኞት፡ጋር ፣ የተያያዘውን ፣ ሕልም ፣ ለመግለጽ ፣ አጸያፊ ፣ ቢሆንም ፤ ባጭሩ ፤ ከርሱ ፣ ጋር ፣ ካደረች ፣ በኋላ ፤ ከርሱ ፣ ቀደም ፣ ብላ ፣ በመነሣት ፣ ቁርስ ፣ አዘጋጅታለች ፣ ወደ ፣ ምኝታ ፣ ክፍል ፣ ትገባና ፤ "ቁርስ ፣ ደርስዋል ፣ ፍቅሬ" ፣ ስትል ፣ ከግንባሩ ፣ ላይ ፣ የሳመችው ፣ መስሎት ፣ ብንን ፣ ብሎ ፣ ነቃ ። ነገር ፣ ግን ፣ ዋ ፣ ሕልም ፣ ባዶ ፤ ብቻውን ፣ ስለሆነ ፣ ያለመጠን ፣ ተሳቀቀ ።

ወዲያው ፣ ጺሙን ፣ ተለሜጭቶና ፣ ጸጉሩን ፣ አበጣጥሮ ፤ ቅርጹን ፣ በመስታወት ፣ ውስጥ ፣ እየተመለከተ ፣ ይፎክር ፣ ጀመር ።

እኔን ፣ የመሰለ ፣ ሽጋ ፣ ወጣት ፣ አግኝታ ፣ የምትግደረደር ፣ ማን ፣ ናት ? የኑሮ ፣ ጣዕምን ፣ የማታውቅ ፣ ቂል ፣ ትባላላች" ።

በእውነትም ፣ ተጫን ፣ በመልኩ ፣ የሚመካ ፣ ጐልማሳ ፣ ነበር ። ቆዳው ፣ በምኞት ፣ ያወለወለና ፣ ደሙ ፣ የጠራ ፣ ነው ። የሰውነቱ ፣ አመሠራረትና ፣ የገጹ ፣ አወራረድ ፣ ትክክለኛ ፣ ለመሆኑ ፣ ማንም ፣ ይመሰክርለታል ። አነጋገሩንና ፣ አካሄዱን ፣ በቂንጥ ፣ የሚያጣፍጥ፡ የከተማ፡ ሽጋ ፣ ነው ። ቆንጆነቱን ፣ የሚክድ ፣ ሰው ፣ የለም ።

ነገር ፣ ግን ፣ በቅርብ ፣ አስተውሎ ፣ ለተመለከተው ፣ እንድ ፣ ነገር ፣ የጐደለው ፣ ነው ፤ የሚያሰኝ ፣ ስሜት ፣ ያሳድራል ። ይህ ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ በቀጥታ ፣ ሊጠቀስ ፣ ባይቻልም ፣ በብዙ ፣ የኢትዮጵያውያን ፣ ጐልማሶች ፣ ግምባር ፣ ላይ ፣ የሚነበበው ፣ የወንድነትና ፣ የብርታት ፣ ሐረግ ፣ ጐድሎት ፣ ይሆናል ፣ ወይንም ፣ የውስጥ ፣ መንፈሱ ፣ ደካማነት ፣ በፊቱ ፣ ላይ ፣ እያንጸባረቀ ፣ ነው ፣ የሚል ፣ አስተያያት ፣ ሳይሰጥ ፣ አይቀርም ።

ቁርሱን ፣ በልቶ ፣ ጥቂት ፣ ካረፈፋደ ፣ በኋላ ፣ በመኪናው ፣ ሁኖ ፣ አበባ ፣ ወደምትኖርበት ፣ መንደር ፣ አመራና ፤ ለማለፍ ፣ እንኳ ፣ በሚጸየፍበት ፣ ቀበሌ ፣ ሲንከራተት ፣ አረፈደ ። ነገር ፣ ግን ፣ አበባን ፣ የማየት ፣ ዕድል ፣ አላጋጠመውም ። "ምነው ፣ እንድ ፣ ጊዜ ፣ ብቅ ፣ ብትልና ፣ ያንን ፣ ውበትዋን ፣ እንደጨረታ ፣ ብርሃን ፣ ብትፈነጥቅብኝ"

የገባችበትን ፣ ቤት ፣ አጠናቆ ፣ ተመልክቶ ፣ ነበር ። ቢሆንም ፣ ከሰው ፣ ጓዳ ፣ ዘው ፣ ብሎ ፣ መግባት I ከፍተኛ ፣ ወንጀል ፣ ሲሆን ፣ የሚያስከትለውንም ፣ መዘዝ ፣ አልዘነ ጋውም ። ''እ፡ እ''ብላ፡ ብትጮህና፡ በመንደር፡ ኩበሌ ፣ ብታሲዘውስ!ወይንስ ፣ ባልዋ ፣ ከውስጥ ፣ ቆይቶ ፣ በዱላ ፣ ቢያስተናግደውስ!ይህ ፣ አይሆንም ። ሌላ ፣ ዘዴ ፣ መፈለግ ፣ ነበረበት ።

የራሳቸውን ፣ ትዳር ፣ በግል ፣ ስሕተታቸው ፣ አጨናግ ፈው I ለጥቅም ፣ ሲሉ I ወይንም ፣ በቅናትና ፣ በምቀኝነት ፣ ስሜት ፣ ተገፍተው I የሌሎችንም ፣ ለማሰናከል ፣ ከባድ ፣ የሕሊና ፣ ወቀሳ ፣ የማይሰማቸው I የሞራልና ፣ የሀብት ፣ ምስኪኖች ፣ በየትም ፣ ቀበሌ ፣ አይታጡም ። በሣህሉ ፣ መንደርም I እመት ፣ ተጓዳ ፣ የተባሉ ፣ አሮጊት ፣ መሸ ተኛ ፣ ነበሩ ። እኔህ ፣ ባልቴት I የመሸታ ፣ ሰዓት ፣ እስኪደርስ ፣ ድረስ I ከበራፋቸው ፣ ላይ ፣ ቁጭ ፣ ብለው ፣ ጥጥ ፣ እያባዘቱ፤ የጪት ፣ ፀሐይ ፣ ሲቀቁ I ተጫን ፣ መኪና ውን ፣ ካጠገባቸው ፣ አቆመና ፣ ወደርሱ ፣ ጠራቸው ። መልእክቱን ፣ የሚፈጽመለት ፣ መሆናቸውን ፣ በምን ፣ ዓወቁ!መንፈሱ ፣ ከመንፈሳቸው ፣ ጋር ፣ ምሥጢራዊ ፣ ግኑኙነት ፣ አድርጎ ፣ ይሆን!ወይንስ ፣ ችግረኛ ፣ መሆናቸው ን ፣ በመረዳት ፣ ገንዘብ ፣ ሊገዛቸው ፣ ይችላል ፣ ሲል ፣ በመገመት ፣ ይሆን?ቢሆንም I ''የሰው ፣ ልጅ ፣ በእንጀራ ፣ ብቻ ፣ አይኖርም ። ከእግዚአብሔር ፣ አፍ ፣ ሁሉ፡ወጣው ፣ ቃ ል ፣ ሁሉ ፣ እንጂ'' ፣ የሚለውን ፣ አምላካዊ ፣ ሕግ ፣ በመከተል I ትንሽ ፣ ቅንጣት፡ እንኳ፡ ብትሆን I የተከበረው ን ፣ የሞራል ፣ ሀብታቸውን ፣ በገንዘብ ፣ ሊለውጡ ፣ የማይ ሹት ፣ ጥቂቶች ፣ አይደሉም ።

ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ''የማንን ፣ ቤት ፣ አመልክችኝ ፣ ሊለኝ ፣ ይሆን!የማለት ፣ ትንቢታዊ ፣ ግምት ፣ እያሰላሰሉ ፣ ቀረቡ ። ተጫን ፣ ግን ፣ ምንም ፣ አይነት ፣ ጥያቄ ፣ ሳያስቀድ ም I አስር ፣ ብር ፣ በእጃቸው ፣ አስጨበጠና ፣ ''ለብርቱ ፣ ጉዳይ ፣ እፈልግዎታለሁ ። እመኪናው ፣ ውስጥ ፣ ይግቡ'' አላቸው ። እንደተጫን ፣ በመሰለ ፣ ከፍተኛ ፣ ሰው ፣ (በርሳቸው ፣ ግምት)''ለብርቱ ፣ ጉዳይ ፣ መፈለግ ፣ ''ለወይ ዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ እንደመላእክት ፣ ሙገሰጽ ፣ የመሰለ ፣ እንግዳ ፣ ነገር ፣ ነበር ፣ ከመገረማቸውና ፣ ከመደነቃቸው ፣ ብዛ ት ፣ የተነሣ I ስለጉዳዩ ፣ የሐሳብ ፣ አስተያያት ፣ ለመስ ጠት ፣ አእምሮዋቸው ፣ ተሣስሮ ፣ ነበር ። በዚህ ፣ ላይ ፣ የአስሩ ፣ ብር ፣ ስጦታ ፣ ደግሞ ፣ የደስታ ፣ ድንዛዜ ፣ አሳደረ ባቸው ። ስለዚህ ፣ ምንም ፣ ዓይነት ፣ ጥያቄ ፣ ሳይሰነዝሩ ፣ ፈራ፣ ተባ ፣ በማለት ፣ ከመኪናው ፣ ውስጥ፣ ገብተው ፣ ተሸ ማቀው ፣ ተቀመጡ ።

ተጫን I አንዲት ፣ አሮጊት ፣ አሳፍሮ ፣ ሲሄድ ፣ እንዳይታይ ፣ እንደሆነም ፣ እንጃ ፣ ባራተኛ ፣ ማርሽ ፣ እየከ ነፈ ፣ ከከተማው ፣ ከልል ፣ ወጣ ። እመት ፣ ተጓዳ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ በመኪና ፣ ተሳፍረው ፣ አያውቁም ። ያውም I ከከባድ ጭነት ፣ በታች ፣ ከሰጋር ፣ በቅሎ ፣ በማይፈጥን ፣''ትራ ንታ ፣ ኳትሮ''ነበር ። ይህ ፣ አዲስ ፣ ፍጥነት I በሰውነታ ቸው ፣ ውስጥ ፣ እንቅጥቅጥና ፣ ሽብር ፣ ስለለቀቀባቸው I የጨበጡት ፣ አስር ፣ ብር ፣ ኖት ፣ ከእጃቸው ፣ በመጨው ፣ ወዝ ፣ ርሶ ፣ ነበር ። የተጫን፣ ዝምታም ፣ ፍርኃታቸውን ፣ ይበልጥ ፣ እገነነው። ወደ ፣ ጫካ ፣ ወስዶ ፣ የሚገድል ፣ ወንበ ዴ ፣ (የከተማ ፣ ጭራቅ) መሰላቸው ።

''እይጣል ፣ እኮ ፣ ነው!እበላ ፣ ሲሉ ፣ ይበሉ ፣ የሚባለ

ው ፣ ተረት ፣ በኔ ፣ ሊደርስ ፣ ይሆን ? ''እያሉ ፣ ሲጨነቁ ፣ ተጫን ፣ በእንድ ፣ ዘዋራ ፣ በታ ፣ አቆመላቸውና ፣ ትንሽ ፣ እፎይ ፣ አሉ ። ነፍሳቸው ፣ ገባች ። ከዚያም ፤ ከመኪናው ፣ ውስጥ ፣ እንደሆነ ፣ ፊቱን ፣ ወደርሳቸው ፣ መለስ ፣ አደረገና ፣ ''ከርስዎ ፣ ጐረቤት ፣ የምትኖር ፣ እንዲት ፣ ቆንጆ ፣ ልጅ ፣ ያውቁዋት ፣ የለም?''ሲል ፣ ጠየቃቸው ።

እንዴት ፣ ያል ፣ ጥያቄ ፣ ነው?በርሱ ፣ ሕሊና ፣ ውስጥ ፣ ያለችውን ፣ ቆንጆ ፤ ማንም ፣ ሰው ፤ ''እገሊት ፣ ናት ፤ ያቺ ፣ ናት ፣ ''እያለ ፣ እንደአጥቢያ ፣ ኮከብ ፣ ሊጠቅስለት ፣ የሚችል ፣ ይመስለዋልን ? በቁንጅና ፣ ደረጃ ፣ የሚመደቡ ፣ ሴቶች ፣ በአካባቢው ፣ ሞልተዋል ። በቀጥታ ፣ ባይገልጽላቸውም ፤ ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ የጥያቄው ፣ ዓላማ ፣ ባንዳፍታ ፣ ገባቸውና ፤ ተጫን ፣ ላሰበው ፣ ተግባር ፣ ተገቢ ፣ የሆኑትን ፣ ሴቶች ፣ ዘረዘሩለት ። ፈቶችና ፣ እንዳንድ ፣ ወስላቶች ፣ ባለባሎች ፣ ነበሩበት ። ''አስካለ ፣ ተዋበች ፤ ጌጤ——የል ፍነሽ?''

''ጠይም ፤ ደማም ፤ እግረ ፣ መልካም ? ስትገባ ፣ ያየኋት ፣ ከትልቁ ፣ ቤት ፣ ውስጥ ፣ ነው''

''አበባ?''ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ከዝርዝራቸው ፣ አላስገብ ዋትም ፣ ነበር ።

''እምነእና''

''እርስዋማ ፣ ባል ፣ አላት''? ፣ ብለው ፣ ሲጀምሩ ፤ ''ስለባሏ ፣ ማን ፣ ጠየቅዎት''! አለና፣ በቁጣ ፣ ቢሙህባቸው በድንጋጤ ፣ ከመቀመጫቸው ፣ ዘለሉ ። ተጫን ፤ ከድንጋጤ ያቸው ፣ ለማበረታታት ፣ ሲል ፣ ፈገገና ፤ ፖርሳውን ፣ አውጥቶ ፤ አሰር———ሃያ———ሠላሳ ፣ ብር ፣ በመዳፉ

ው ፣ ላይ ፣ ደረደረላቸው ። ይህን ፣ ያህል ፣ ገንዘብ ፣ ባንድ ፣ ጊዜ ፣ ጨብጠው ፣ የማያውቁት፣ እጣቶቻቸው፣ ተንዘፈዘፉ። ቅዠትም ፣ መሰላቸው ። ዓይኖቻቸው ፣ እንድ ፣ ጊዜ ፣ ወደ ፣ ብሮቹ ፣ እንድ ፣ ጊዜ ፣ ወደተጫን ፣ ይመላለሱ ፣ ጀመር ።

ተጫን ፣ በሙሉ ፣ እንደገዛቸው ፣ ዓወቀ ። ለማንኛውም ፣ መልእክት ፣ እንደማያፈገፍጉ ፣ ተረዳ ። ወይ ፣ እምዬ ፣ ገንዘብ !!

ከመኪናው ፣ መሪ ፣ እንደሆነ ፤ ሰውነቱን ፣ ከወገቡ ፣ በላይ ፣ ጠመዘዘና ፣ ስሜት ፣ በደበቀ ፣ አንደበት ፣ ዲስኩሩን ፣ ጀመረላቸው ። ''ትናንት ፣ በመንገድ ፣ ስታልፍ ፣ ቁንጅናዋን ፣ ተመለከትሁት ። እንደርስዋ ፣ ያለ ፣ ቆንጆ ፣ ሕይወቱን ፣ ሙሉ ፣ ከባል ፣ ጋር ፣ ተጣብቆ ፣ (በተለይም ፣ ከደንቆሮ)ግሳለፍ ፣ አይገባውም ። እኔ ፤ ለምሳሌ ፣ የተማር ኩና ፣ የሠለጠንኩ ፣ ወጣት ፣ ነኝ። የቁንጅናን፣ ግምት፣ ለማ መዛዘን ፣ ስለምችል ፤ ትክክለኛውን ፣ ዋጋ ፣ ልከፍለው ፣ እችላለሁ ። ትናንት ፣ እንኳ ፣ ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ልጠቅስሳት ፣ ሞክሬ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ እርስዋም ፣ እንደአካባቢዋ ያልበሰለች ፣ ጥሬ፣ ውበት፣ ስለሆነች ፣ አንገትዋን ፣ አቀርቅራ ፣ ኩበለለች ። በውነቱ ፣ በጣም ፣ አዘንኩ ። ያንን ፣ የመሰለ ፣ ውበት ፤ በማሰሮ ፣ ውስጥ ፣ እንደተደበቀ ፣ መብራት ፤ ለምን ፣ ያለአንዳች ፣ ጥቅም፣ እንዲባክን ፣ ይደረጋል? ወንጀል ፣ ነው ። የሥነ ፣ ፍጥረት ፣ ድንቅ ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፤ ሊገለጥ ፤ ሊከብር ፣ ሊመለክና ፤ ለሰው ፣ ልጅ ፣ ደስታ ፣ አገልግሎት ፣ ሊውል ፣ የተገባ ፣ ነው ። ይህሉ ፣ ሊሆን ፣ የሚቻለው ፣ ለውበት ፣ ግምትና ፣ ለፍቅር ፣ ጣዕም ፣ ዓዋቂዎች ፣ ሲበረክት ፣ አይደለምን?'' ሲል ፣ አጋኖ ፣ በተቀላቀለበት ፣ ድምጽ ፣ ጠየቃቸው ።

ወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፤ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ፍልስፍና በሕይወታቸው ፡ ሙሉ ፡ ሰምተውም ፡ እያውቁ ። እንኳንስ ሐሳቡ ፡ ሊገባቸውና ፡ ንግግሩንም ፡ በጣም ፡ አልተከተሉ ት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የጨበጡት ፡ ገንዘብ ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ "አዎ-አዎን" ፡ በማለት ፡ መለሱለት ። ተጫን ፡ የፍልስፍናው ፡ ተቀባይ ፡ ደጋፊ ፡ በማግኘቱ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ።

"ያች ፡ ልጅ ፡ አሁን ፤ ስሟን ፡ አበባ ፡ ነው ፡ እንዴ ፡ ያሉኝ ? አዎ-ቁንጅና ፡ ተሰጥቷታል ። ውበት ፡ አላት ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ይዛለች ። ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ባደላት ፡ በዚህ ፡ ጸጋ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ተጠቀመችበት? ለማንስ ፡ አካፈለችው?እንደዚሁ፡ ወደመቃብር ፡ ይዛው ፡ ብትወርድ ፡ እራስዋን ፡ መጉዳትና ፡ የሰው፡ ልጅን፡ መበደል ፡ ይሆንባታ ል ። እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ባሏ ፡ ያሉት ፡ ምን ፡ ሠራተኛ ፡ ነው?"

"እንጃ——ብቻ ፡ ደህና ፡ ደሞዝ ፡ ያገኛል ፡ ይላሉ ፡"

በማፈዝ ፡ ቃል ፡ "ስንት ?" አለና ፡ ጠየቃቸው ።

"አምሳ ፡ ብር ፤ ወደዚያው ፡ ገደማ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀ ርም"ተጫን ፡ ይህንን ፡ ሲሰማ ፡ ከት-ከት ፡ ብሎ ፡ እየሳቀ ፡ "አስር ፡ እጅ ፡ ይበልጥ ፡ የሚያገኘው ፡ ምን ፡ ሊባል ፡ ነው!"በማለት ፡ ተሳለቀባቸው ።

"አሁን ፡ ስለሌላ ፡ ደሞዝ ፡ መከራከር ፡ የኛ ፡ ተግባር ፡ አይደለም ። ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ የአበባ ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለዚች ፡ ልጅ ፡ የሰጠኋት ፡ ግምት ፡ ከፍተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ፡ ነገር፡ ልፈጽምላት፡ አስቤአለሁ። እችላለሁም" አለና፡ ፎከረ። እስካሁን፡ ድረስ፡ ባሰማው፡ ዲስኩር፤ የራሱን፡ ፍላጐ ት ፡ በመሸፈን ፤ የቁንጅና ፡ ፈላስፋ ፤ የውበት ፡ ጠበቃና ፡

ተከራካሪ ፡ መሰሎ ፡ ለመታየት ፡ ሞከሮ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ንግግሩ ፡ ያስረዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ያደካማ ፡ ስሜቱ ፡ ገነፈለበትና ፡ "ትናንት ፡ እንድ ፡ ጊዜ ፡ እይኔ ፡ ሲያርፍባት ፡ በቀጥታ ፡ ወደድኋት ፤ ሰውነቴ ፡ ፍዝዝ ፡ አለ ። ራሴ ፡ ደነዘዘ ። አካላቴ ፡ ሞቀ ። ተቃጠለ ። ሌሊት ፡ እንቅ ልፍ ፡ የሚሉት ፡ ሳላይ ፡ አደርሁ"ተጫን ፡ ከሆዱ ፤ ከእንጀ ቱ ፤ ከልቡ ፤ ከራሱ ፡ የተሰማውን ፡ ሁሉ ፡ ይናዘዝላቸው ፡ ጀመር ። ወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፡ በበኩላቸው ፤ የቁንጅና ፡ ፍልስፍ ና ፤ እያለ ፡ የሚቀባጥረውን ፡ ሊረዱት ፡ ባይችሉም ፡ የሐሳ ቡን ፡ ጠቅላላ ፡ ግብ ፡ ሳይደርሱበት ፡ አልቀሩም ።

"ታዲያ ፡ እርሷ ፡ ኃይለኛ ፡ ናት"ብለው ፡ ንግግር ፡ ሲቃጡ ፤ "ትግል ፡ ይገጥማታል ፡ እንዴ!"ሲል ፡ ጐነባቸ ው ። የወይዘሮ፡ ተጓዳ፡ ሰውነት ፡ በድንጋጤ ፡ ተሸማቀቀ ፡ ድምጻቸው ፡ ደከመ ። "የለም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ አትሞከርም ፡ ማለቴ ፡ ነው ፡ እንጂ" ፡ አሉና ፡ አዋዩት ።

"ለምን ፡ አትሞከርም!ለምን ፡ አትሞከርም!"መሪው ን ፡ በቡጢ ፡ እየደበደበ ፡ "ይህንን ፡ይሰዉት!ይህንን ፡ ደግ ሞ ፡ ያሳይዋት" ! ሰላሳ ፡ ብርና ፡ የራሱን ፡ ፎቶግራፍ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጣቸው ። "እንግዲህ ፤ ቢሆን ፡ ዛሬ ፡ ወይንም ፡ ነገ ፡ መልሱን ፡ ከዚህ ፡ ድረስ ፡ ይዘውልኝ ፡ እንዲመጡ" ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደቤታቸው ፡ አልወሰዳቸውም ። የመኪናው ን ፡ በር ፡ ከፈተና ፡ "ይበሉ ፡ በእግርዎ ፡ ያዝግሙ ። ይቅናዎት ፡ "ሲል ፡ አሰናበታቸው ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሄድ ፤ "ጉልበቴ ፡ ደክሟል" ፡ እያሉ ፡ ያጉረመርሙ ፡ የነበሩት ፡ አሮጊት ፤ ከአምስት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ በላይ ፡ የሚሆነውን ፡ መንገድ ፡ በእግራቸው ፡ ሰጠሰጡት ።

በመቀነታቸው ፣ የተጻጠረው ፣ ገንዘብ ፣ ብርታት ፣ ሰዋታ ቸው ፣ ይሁንም ፣ እንጂ ፣ ወይንም ፣ አበባን ፣ ለማግባባት ፣ የሚችሉበትን ፣ ዘዴ ፣ በማሰላሰል ፤ የጉዳናው ፣ ርዝመት ፣ በፍጹም ፣ አልታወቃቸውም ፣ ነበር ።

ምዕራፍ ፣ ፮

ብዙ ፣ ጊዜ ፣ የመሸታ ፣ ቤት ፤ ሞያተኞችና ፣ ባለሻ ሎች ፣ ጨዋታ ፣ ዓዋቂና ፣ ወሬ ፣ ቀማሚ ፣ መሆናቸው ፣ አይጠረጠርም ። መሸተኛ ፤ የተወደደ ፣ ደንበኛ ፣ ለመሆን ፤ መተቸትን ፤ መቀለድንና ፣ መዳራትን ፣ አዘውታሪ ፣ መሆን ያሻዋል ። የመሸታ ፣ ቤት ፣ ዋናው ፣ ዓለሙ ፣ የጨዋታው ፣ ድምቀት ፣ ነው ። አፋን ፣ እንደተለጉመ ፤ መጠጡን ፣ ብቻ ፣ ለግቶ ፣ የሚወጣ ፣ ሰው ፤ ጣሙን ፣ አላገኘውም ፣ ለማለት ፣ ያስደፍራል ። መሻች ፣ ደግሞ ፣ በበኩሏ ፤ የጥንት ፣ ደንበ ኞች ፣ እንዳይሸሹ ፣ አዲሶችም ፣ እንዲተኩ ፣ ለማድረግ ፣ መሸተኞችን ፣ ሁሉ ፣ በተቻላት ፣ መጠን ፣ ማስደሰት ፣ ዓይነተኛው ፣ ተግባርዋ ፣ ነው ። ወሬና ፣ ጨዋታ ፣ አድማ ጭ ፤ ሲወያዩ ፣ አስተዛዛኝ ፤ ሲተርቡ ፣ ሳቂታ ፤ እንደመሆኗ ፣ መጠን ፤ አታላይ ፤ አሞጋሽና ፣ ትእዛዝ ፣ ፈጻሚ ፣ እንድትሆ ን ፣ አስፈላጊ ፣ ነው ። አንዱ ፣ ዋና ፣ ተግባር ፣ ተፈላጊ—— ግቅረብ ፣ እንደሆነ ፣ አይሸሸግም ።

እመት ፣ ተጓዳ ፤ ለብዙ ፣ ደንበኞቻቸው ፣ ሲፈጽሙት ፣ የኖረ ፣ ተግባር ፣ ስለሆነ ፤ ወይዛዝርትን ፣ ለማግባባት ፣ የሚቻ ልበትን ፣ ዘዴ ፣ ጠላ ፣ መነገድ ፣ ከጀመሩበት ፣ ጊዜ ፣ አንስቶ ፣ በልዩ-ልዩ ፣ ዓይነት ፣ መስመር ፣ አዋንተውታል ። ቢሆንም ፣ የአበባ ፣ ጉዳይ ፣ የተለየ ፣ መልክና ፣ አቀራረብ ፣ ስለነበረው የጥናት ፣ ክለሳና ፤ አዲስ ፣ ማሰብ ፣ ሳያስፈልገው ፣ አልቀረ

ም ። ፈጣሪ ፣ ስንት ፣ ዓይነት ፣ ልመናና ፣ ጸሎት ፣ የሚደርስ ለት ፣ ይመስላችኋል ፣ ?አንዱ ፣ ሰው ፣ ለቅን ፣ ግብ ፣ ሲግጠ ነው ፤ ሌላው ፣ ደግሞ ፣ ለክፉ ፣ ተግባሩ ፣ ይለምነዋል ። የሁሉም ፣ ሐሳብ ፤ ምኞታቸው ፣ እንዲፈጸምላቸው ፣ ግመ ልከትን ፣ እንጅ ፤ ጥያቂያቸው ፣ ተገቢ ፣ መሆኑን ፣ ወይንም ፣ አለመሆኑን ፣ የሚያሰላስሉት ፣ ጥቂቶች ፣ ናቸው ። ሌባ ፤ ሰርቆት ፣ ከመሐዱ ፣ በፊት ፣ ለጊዮርጊስ ፣ ይሳላል ፣ የሚል ፣ ተረት ፣ እንዳለ ፣ እናስታውሳለን ። ወይዘሮ ፣ ተጓዳም ፤ ወደአበባ ፣ ቤት ፣ ጉራ ፣ ከግስታቸው ፣ በፊት ፤ የተላኩበት ን ፣ ጉዳይ ፣ እንዲያቃናላቸው ፣ ለፈጣሪ ፣ የሕሊና ፣ ጸሎት ፣ አድርሰዋል ።

እመት ፣ ተጓዳ ፣ የሚኖሩት ፣ በሣህሉ ፣ አደራሽ ፣ አቅራ ቢያ ፣ መሆኑን ፣ ጠቅሰናል ። ነገር ፣ ግን ፣ ከአበባ ፣ ጋር ፣ የነበራ ቸው ፣ ወዳጅነት ፣ እምብዛም ፣ ነው ። ይዜውም ፤ አበባ ፣ በተፈጥሮዋ ፣ ጉረቤትን ፣ የማታስጠጋ ፣ ሆና ፣ ሳይሆን ፣ የማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ መሰሎቿን ፣ በመፈለግ ፣ በምታሳየው ፣ የምርጫ ፣ አቀራረብ ፣ ምክንያት ፣ ነበር ። ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ትዳራቸውን ፣ የሚመሩት ፣ ከላይ ፣ በተጠቀሰው ፣ ዓይነት ፣ ሲሆን ፤ አበባ ፣ እንደዚህ ፣ ከመሳሰሉት ፣ ሴቶች ፣ ጋር ፣ እንድትዛመድ ፣ አትፈቅድም ፤ ሣህሉም ፣ በበኩሉ ፣ አይወድም ። ስለዚህ ፣ የአበባና ፣ የእመት ፣ ተጓዳ ፣ ዕውቂያ የቅርብ-ሩቅ ፣ ነበር ። ዛሬ ፣ ግን ፣ ነጠላቸውን ፣ አጣፍተው ፣ መቀነታቸውን ፣ አጥብቀውና ፣ ጥርሳቸውን ፣ ነክሰው ፣ “እ ንዴት ፣ አረፈዳችሁ ፣ ከዚህ ፣ ቤት!” አሉና ፣ ከደጃፉ ፣ መድ ረክ ፣ ላይ ፣ ቆሙ ። አበባም ፣ «እግዚአብ፡ሔር ፣ ይመስገን» ስትል ፣ አንገትዋን ፣ ብቅ ፣ አድርጋ ፣ ውይ! ወይዘሮ ፣ ተጓ ዳ ፣ እንደምን ፣ አደሩኽኔ ፣ የየት ፣ እንግዳ ፣ መጣብኝ ፣ ብዬ!

ይግቡ፡እንጂ''-እመት ፣ ተጓዳ ፣ ገብተው ፣ ከመደብ ፣ ላይ ቁጭ ፣ አሉ ።

አበባ ፤ የመጡበት ፣ ጉዳይ ፣ ግራ ፣ ገብቷት ፤ ''ለምን ፣ ይሆን?እያለች ፣ ስታሰላስል ፤ እመት ፣ ተጓዳ ፣ ሐሳቧን ፣ ተረድተውት ፣ ,,በዚህ ፣ ሰሞን ፣ ስላላየሁሽ ፤ ጤንነትሽን ፣ ለመጠየቅ ፤ ከውጭ ፣ እንደነበርኩ ፤ እግረ ፣ መንገዴን ፣ አመራሁ ። ደጉ ፣ አባትሽ ፣ ታሳቅ ፣ ባለውለታየ ፣ ነበሩ ። የኒያ-ብሩክ ፣ ልጅ''በማለት፡ ያሞጋግሷት ፣ ጀመር ። አመጣጣቸው ፣ ለጥየቃ ፣ ብቻ ፣ እንደሆነ ፣ አበባ ፣ ሙሉ ፣ እምነት ን ፣ በመጨበጥ ፤ ''አምላክ ፣ ይመስገን ፣ እኔስ ፣ ደህና ፣ ነኝ ። የዓመት ፣ በዓሉ ፣ ሥራ ፣ እያጣደፈኝ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ወደደጅ የማልወጣ ፣ ሆኜ ፣ ነው ፣ እንጅ ፣ ''አለቻቸው ። መጭው ፣ ዓመት ፣ በዓል ፣ ጥምቀት ፣ ነበር ።

እመት ፣ ተጓዳ ፤ የአቀራረቡና ፣ የአገላለጹ ፣ ጉዳይ ፣ ስለጨነቃቸው ፣ መልእክቱን ፣ በቀጥታ ፣ መዘርገፍ ፣ አደገኛ ፣ እንደሚሆን ፣ በመገመት ፤ በዘዋራ ፣ መስመር ፣ ለማስገባት ፤ ቡና ፣ እስኪፈላላቸው ፣ ድረስ ፣ ብዙ ፣ ሙከራ ፣ አድርገው ፣ ነበር ። ስለወንድ ፣ ስለ ፣ ሴት ፣ ስለወዳጅ ፣ ስለፍቅር ፤ ስለሀብትና ፣ ስለምኞት ፣ ሲቀባጥሩ ፣ ቆይተው ፤ ''አንቺምኮ፡እንደዚሁ፡ ''ብለው ፣ መርበባቸውን ፣ ለመጣል ሲቃጡ ፤ አበባ ፣ ቀና ፣ ብላ፡ በክፉ፡ ዓይን ፣ ብትገርፋቸው ፣ ጨዋታውን ፣ ከናካቴው ፣ እርግፍ ፣ አድርገው ፣ ተውት ።

በኋላም ፣ ቡናው ፣ እስከ፡ በረካው፡ ድረስ፡ ተጠጥቶ ፣ ለመሔድ ፣ ሲነሡ ፤ ለመጡበት ፣ ጉዳይ ፤ እንዳችም፡ ውል ፣ ሳይቋጥሩለት፡በርስዋ፡ኃይለኝነት ፣ በርሳቸው ፣ ፍርሃት፡በመና ድድ ፣ እጃቸውን ፣ እያፋተጉ ፣ ተሰናበቷት ። በትንሽ፡ ዋጋና፡ በጥቂት ፣ ድካም ፣ እንደዚህ ፣ የመሰሉትን ፣ ብዙ ፣ መልእክ

ቶች ፣ የፈጸሙ ፣ ሲሆን ፣ አሁን ፣ ከፍተኛ ፣ ጥቅም ፣ በሚገኝ በት ፣ ጊዜ ፤ ችግሩ ፣ በዚያው ፣ ልክ ፣ ሆኖ ፣ ተደቀነባቸው ። ዕድላቸውን ፣ ይራገሙ ፣ ጀመር ። በገንዘባቸው ፣ ጌታ ፣ በተጫን ፣ እንኳ ፣ ሳይቀር ፣ ተቀየሙበት ። ''ከሞላው ና ፣ ከተረፈው ፣ ቆንጆ ፣ እስቲ ፣ አንዲት ፣ ሞገደኛ ፣ መም ረጡ!የርሷ ፣ ደግሞ ፣ አይብስንሽእንደሔዋን ፣ ከአንድ ፣ ወንድ ፣ ጋር ፣ ሙጥኝ ፣ ብላ ፣ መጣበቋ ፣ ምን ፣ ይሉታል፡ ባለባል ፣ እርሷ ፣ ብቻ ፣ ይመስላታል ፣ እንዴ!,,ይህ ፡ ሁሉ ! ከብስጭት ፣ ስሜት ፣ የፈላ ፣ ሐሳብ ፣ ነበር ፣ እንጅ ፤ አስተ ሞዲ ፣ ልቦናቸውስ ፣ ባንድ ፣ በኩል ፤ ''ተጫን ፣ ምን ፣ አ ጠፋ ? አበባም ፣ ብትሆን ፤ ቃልኪዳኗንና ፣ ዕምነቷን ፣ ስለ ጠበቀች ፣ ያስመሰገናታል ፣ እንጅ ፣ የሚያስነቅፋት ፣ አይ ሆንም ። ይልቁንስ ፣ በራስሽ ፣ ግንባር-ስንኩልነት ፣ ብትግ ሪሪ ፣ ይሻላል''እያለ ፣ ሳያፈዝባቸው ፣ አልቀረም ።

እመት ፣ ተጓዳ ፣ ከቤታቸው ፣ ደርሰው ፣ ንዴታቸው ፣ ጥቂት ፣ ከበረደ ፣ በኋላ ፤ ነገሩን ፣ በልዝብታ፡አስተናተኑት፡ ጉዳዩ ፣ ተጫን ፣ እንደተመኘው ፣ በፍጥነት ፣ ሊከናወንለት ፣ አለመቻሉ ፣ እርግጥ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ በፍጹም ፣ ጨንግ ፏል ፣ ለማለት ፣ ደግሞ ፣ አያስደፍርም ። የመጀመሪያውን ፣ ጥያቄ ፣ ለማቅረብ ፣ ሲሰንዝሩ ፣ አበባ ፤ በአስተያየት ፣ ግልምጫና ፤ በአጭር ፣ መልስ ፤ እንደነበልባል ፣ በሩት ፣ እ የገረፈች ፣ ባታስጠጋቸውም ፤ የመጨረሻውን ፣ ሙከራ ፣ ገና አላደረጉም ። የእሳት ፣ ባሕርይ ፣ የመሰለውን ፣ ይህንን ፣ ብርቱ ፣ መንፈስ ፣ እንደምንም ፣ ጥሰው ፣ ከገቡ ፣ በኋላ፡ ቁርጡ ፣ ይለያል ።

ወይንም፡ ውስጡ፡ ቀዝቃዛ፡ ሆኖ፡ ያገኙት፡ ይሆናል ። ግን ፣ ያውቃል ? ለዚህ ፣ ሁሉ ፣ የሚያስፈልገው ፤ መሞከር ፣

እንደገና ፡ መሞከር ፡ ሲሆን ፡ ለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ያሻዋል ። ይህንን ፡ ተጫን ፡ እንዲረዳው ፡ ይገባል ። ማዋየት ፡ አለባቸው ። አበባን ፡ እንዲያገኝ ፡ ከፈለገ ፤ ጊዜንና ፡ ትዕግሥትን ፡ መሠዋት ፡ አለበት ።

ከተጫን ፡ ጋር ፡ የሚገናኙበት ፡ ጊዜ ፡ ተነግሮዋቸው ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚጓዙት ፡ በእግራቸው ፡ ሲሆን ፤ ድንገት ፡ ሰዓት ፡ ቢያሳልፉ ፡ ተጨማሪ ፡ የመዓት ፡ ቁጣ ፡ እንዳይወርድባቸው ፡ በመስጋት ፡ ከአራት ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ። ከዚያም ፡ የበጋ ፡ ጀንበር ፡ ሲቀታቸው ፡ ዋሉ ።

ተጫን ፡ በአውቶሞቢሉ ፡ እያበደ ፡ ደረሰ ። መኪናዋ እስክትነጥር ፡ ድረስ ፤ ፍሬኑን ፡ በኃይል ፡ ረግጦ ፡ አቆማት ና ፤ "እንዴት ፡ ዋሉ" ፡ ብሎ ፡ ሰላምታውን ፡ ሳያቋርጥ ፤ "ታዲያስ?" ሲል ፡ ጥያቂውን ፡ አስከተለባቸው ። ወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፤ መርዶ ፡ ለማድረስ ፡ እንደመጣ ፡ ዘመድ ፡ ሰውነታ ቸው ፡ በጭንቀት ፡ ሲርበደበድ ፤ ዓይኖቻቸው ፡ በግስተ ዛዘን ፡ ስሜት ፡ ይቁለጨለጩ ፡ ነበር ። በዕዳ ፡ እንደተያዘ ሰው ፤ ነጭ ፡ ወዝ ፡ ከግንባራቸው ፡ ላይ ፡ ችፍ-ችፍ ፡ አለ ። በሕይወታቸው ፡ ሙሉ ፤ እንኳንስ ፡ ሰውና ፤ የዱር ፡ አውሬ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፍርሐት ፡ ሰጽባቸው ፡ እያውቅም ። ምኑ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ የሚያርበደብዳቸው ፤ የወጣቱ ፡ ግርማ ፡ አስደንጋጭ ፡ ሆኖ ፡ ነውን? "አይ ፡ ወሸባየ" የሚዘፈንለት ፤ ጐፈሬው ፡ ደን ፡ የመሰለና ፡ ቆራጥ ፡ አስፈሪ ፡ ጉበዝ ፡ እይተው ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ አልተንዘፈዘፉም ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ የጉርሻው ፡ (የገንዘቡ) ኃይል ፡ ይሆን?

ተጫን ፤ እንዳልተሳካላቸው ፡ በፈታቸው ፡ ላይ ፡ አወቀ ። "እምቢ-አለችዎት ፡ እንዴ?" ሲል ፡ በለሰለሰ ፡ ቃል

ጠየቃቸውና ፡ እመት ፡ ተጓዳ ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ እየተንቀጠ ቀጡ ፤ በቀጥታ ፡ ለመጠየቅ ፡ ያልደፈሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጹለት ፤ "ጊዜ ፡ ስጠኝ ፤ ቀስ-በቀስ ፡ አግባባታለሁ— ብቻ ፡ ጊዜ ፡ ስጠኝ ፡ ,,ሲሉ ፤ የእንጉርጉሮ ፡ ዜማ ፡ የተቀላቀ ለበት ፡ በመሰለ ፡ ድምጽ ፡ ተማጠኑት ። የርሳቸውን ፡ ሐሳብ ፡ ከመደገፍ ፡ በተቀር ፤ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ እን፡ማያገኝ ፡ በመረዳት ፡ በጥያቄያቸው ፡ ተስማማ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጉዳዩ ፡ ላልተወሰነ ፡ ቀጠሮ ፡ ተላለፈ ። ነገር ፡ ግን ፤ ለማን ኛውም ፡ ችግርና ፡ አጋጣሚ ፡ እየመጡ ፡ እንዲያስጠኑት ፡ ያረፈበትን ፡ ሆቴል ፡ አመለከታቸው ።

በዚች ፡ ሌሊት ፡ የወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፡ ጠባብ ፡ አእምሮ ፡ ሊደርስበትና ፡ ሊያርፍበት ፡ የሚችለውን ፡ የብልሃት ፡ ዓይነቶች ፡ ሁሉ ፡ ሲዳስሰው ፡ አድሯል ። በቅናት ፡ ስሜት ፡ ለማሳት ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ አስበውበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ግሀሉ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ፍጹም ፡ የማይጠረጠር ታማኝ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፤ ሚሥጢራዊ ፡ ተንኰላቸው ፡ ምናልባት ፡ በውጥኑ ፡ ጊዜ ፡ የተገለጠባቸው ፡ እንደሆን ፡ መዘዝ ፡ እንደሚያስከትልባቸው ፡ ሰጉ ። ወይንም ፡ አበባ ፡ ወስልታለች ፡ በሚል ፡ የሐሰት ፡ ወሬ ፤ ከባሏ ፡ ጋር ፡ እማ ልተው ፡ ካለያዩ ፡ በኋላ ፤ ተግባራቸው ፡ ሳይቀልላቸው ፡ እይቀርም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ግሀሉ ፡ ሚስቱን ፡ ሲያ ምናት ፡ እንደራሱ ፡ ሲሆን ፤ ነገሩን ፡ ሳያጣራ ፡ በወሬ ፡ የሚፈታ ፡ መስሎ ፡ ስለማይገመት ፤ አጉል ፡ ጠንቅ ፡ መፍ ጠር ፡ ሆኖ ፡ ታያቸው ። ከሁሉም ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ የተ ሰማቸው ፡ ዘዴ ፤ በለዘብታ ፡ መስበክ ፤ ማግባባትና ፡ በጌ ጣ-ጌጥ ፡ ግታለል ፡ ነበር ። ዶሰው ፡ ልጅን ፡ በቀላሉ ፡ ሊያሸንፉት ፡ ከሚችሉት ፡ ስሜቶች ፡ ዓይነተኞቹ ፡ ፍላጐ

ትና ፡ ምኞት ፡ መሆናቸው ፡ የሚሳት ፡ አይደለም ፡ በዚህ መንገድ ፡ ሞክረው ፡ ቢያቅታቸውና ፡ ተጫንም ፡ ሐሳቡን የማይለውጥ ፡ እልከኛ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፤ ምናልባት ፡ ሌላ፡ ዘዴ ደግሞ ፡ ይፈልጉ ፡ ይሆናል ። እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ መፍጨርጨሩን ፡ መረጡ ።

ጉርብትናና ፡ ወዳጅነት ፡ እንዳቀረቡት ፡ ነው ። የሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ ባልንጀርነት ፤ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ መልክ ፡ ያዘ ። በጨዋታቸው ፡ ተዝናኑ ። ቡና ፡ እየተጠራሩ ፡ ይጣጡ ፡ ጀመር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሣህሉ ፡ ከቤት ፡ ባልናረበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በፊት ፡ የማትጠጋቸው ፡ የነበር ፤ አሁን ፤ የወሬያቸው ፡ ጣፋጭነትና ፤ የጫዋታቸው ለዛ ፡ እየጣመ ፡ ያስደስታት ፡ ጀመር ። እመት ፡ ተጓዳም ፡ በበኩላቸው ፡ አበባን ፡ ወደ ፡ ወጥመዳቸው ፡ የሚስብ ፡ ጨዋታና ፡ ወሬ ፡ ከማቅረብ ፡ አይሰለቹም ፡ ነበር ። ቀስ-በቀስ ፡ ያፍርሐታቸው ፡ ሁሉ ፡ እየተወገደ ፤ የወዳጅና ፡ የውሽማ ፡ ወሬ ፤ በግልጽ ፡ ተሰበከ ። የአበባ ፡ አስተዳደግ ፡ አካባቢ ፤ እንደዚህ ፡ ካለው ፡ ነውረኛ ፡ ተረት ፡ የተከለከለ ፡ ስለነበር ፤ ዛሬ ፡ ሳትሰማው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ስለሆነባት ፡ የደስታ ፡ ስሜትን ፡ ይሰጣት ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፤ ዓይናቸውን ፡ በድፍረት ፡ ጨፍነው ፡ የተጫንን ፡ መልእክት ፡ በዝርዝር ፡ አጫወቷት ። ብዙም፡ አልተቆጣችም ። በቁጣ ፡ አላፈጠጠችባቸውም ። ነገር ፡ ግን ፤ “እመት ፡ ተጓዳ ፡ ደህና ፡ ሰው ፡ አልነበሩም ፡ እንዴ” ስትል ፡ በለሰለሰታ ፡ መለሰችላቸው ። ፎቶግራፉንና ፡ ብሩን ፡ አሳይዋትና ፡ በቅዝታ ፡ ተመልክታ ፤ ራሷን፡ ነቅንቃ ፡ መለሰችው ። ወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፡ በልባቸው ፡ አልተና ደዱም ። እንጋገርዋ ፡ የቁጣ ፡ ወይንም ፡ ያለመበገር ፡

ስሜት ፡ ዓይነት ፡ ሳይሆን ፡ የቅሬታ ፡ መንፈስ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ለመሸነፍ ፡ የሚያስተማም ን ፡ ተስፋ ፡ አደረባቸው ። ወደተጫን ፡ ሂደው ፡ ጉዳዩን ፡ ገለጹለት ።

የአበባ ፡ ጥንካሬ ፤ በዚህ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለተጫን ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ። መቸም ፡ ወንድ ፡ ነውና ፤ ሚስት ፡ ማግባት ፡ ኣንደሚገባው ፡ ሳያስብበት ፡ አልቀረም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በከተማ ፡ ካያቸው ፡ ቆንጆዮት ፡ ሁሉ ፤ እምነቱን ፡ ሊጥልባቸው ፡ የሚችል ፡ አላጋጠመውም ። ምናልባት ፤ በራሱ ፡ ጠባይ ፡ ጋር ፡ በማመዛዘን ፤ ዘመናዊ ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ሊረጉ ፡ የማይገባቸው ፡ እየመሰለው ፡ ይሆን፡ ይሆናል ። ቢሆንም ፤ ሚስቱን፡ከሌላ-ወንድ ፡ ጋር ፡ ሊካፈል ከቶ ፡ አይፈቅድም ። ቀናተኛ ፡ ነው ።

አበባ ፡ በቃል ፡ ኪዳኗ ፡ ጽኑ ፡ ትመስላለች ። መጀመር ያ ፡ ካያት፡ቀን፡አንስቶ፤ከሕሊናው፡ውስጥ፡ጠልቃ፡ገብታለች ስለዚች ፡ ልጅ ፡ ያለው ፡ ስሜት ፤ ካሁን ፤ በፊት ፡ በሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ላይ ፡ እንደነበረው ፡ ሥጋዊ-ፍላጐት ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ኖሮ ፡ እስከዛሬ ፡ በመጠኑ ፡ በበረደለት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን፡ በየቀኑ ፡ እየተኰሰ ፡ ይሄዳል ። የለም ። “እውነተኛው ፡ ፍቅር ፡ ”ይዘታል ፡ ማለት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። በቁን ጅና ፡ የምታሳፍር ፡ አይደለችም ። ታዲያ ፡ አዲስ-አበባ ፡ ቢወስዳት ፡ መልካም ፡ ሚስት ፡ ሳትሆነው ፡ ትቀራለችን? በዘህ ፡ አኳኋን ፡ ጉዳዩ ፡ የጋብቻ ፡ መልክ ፡ ወሰደ ።

ከእመት ፡ ተጓዳ ፡ ጋር ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፤ እንደሰሞኑ ፡ የችኰላና ፡ የስስት ፡ ጠባይ ፡ አላሳየም ። ንግግራቸውን ፡ በትዕግሥት ፡ ካዳመጠ ፡ በኋላ ፤ አዲሱን ፡ ሐሳቡን ፡ ገለጠ

ሳቸው ። አሁን ፣ ጉዳዩ ፣ በሦስቱም ፣ ዘንድ ፣ የቀለለ፣ መስሎ ሳይታይ ፣ አልቀረም ። ለተጫን ፣ ከፍተኛ ፣ ወንጀል ፣ ሆኖ ፣ አይሰማውም ። ወይዘሮ ፣ ተጓዳም ፣ የማተጫጨት ፣ እንጅ ፣ የማቃጠር ፣ ተግባር ፣ መስሎ ፣ አይቆጠርባቸውምና ፣ የሕሊና ፣ ወቀሳቸው ፣ አይከብድም ። አበባም ፣ ብትሆን ፤ ከባል ፣ በላይ ፣ ለመወሰለት ፣ የማትፈቅድ ፣ ትሁን ፣ እንጅ ፤ ባላገር-ቢጤ ፣ ባሏን ፣ በባለጸጋና ፣ በዘመናዊ ፣ ሰው ፣ ለመለወጥ ፤ የዘመናይነት ፣ ኑሮ ፣ ምኞት ፣ የሚገፋፍ ትና ፣ የሚያደፋፍራት ፣ ይሆናል ። ተጫንና ፣ ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ይህንን ፣ አስተያየት ፣ በሚያሰሉበት ፣ ጊዜ ፤ ከሣህሉ ፣ በኩል ፣ ያለውን ፣ አንቀጽ ፣ ከሒሳብ ፣ አላስገቡትም ፤ በጭራሽም ፣ አላስታወሱት ።

በእሮጊት ፣ አንደበታቸው ፤ በነገር ፣ ችሎታቸው ፣ እየተመሙና ፣ እያጣፈጡ ፣ መርዛቸውን ፣ በሰፈው ፣ ይግቷት ፣ ጀመር ። ተጫን ፣ ምን ፣ ያህል ፣ እንደሚያፈቅራት ሊፈጽምላት ፣ ያሰበውን ፤ የሚሸልማትን ፣ ጌጣ-ጌጥ ፤ የሚያጉናጽፋትን ፣ ልብስ ፤ የሚያጫማትን ፣ ጫማ ፤ የሚያሳያትንና ፣ የሚያስጠግባትን ፣ ዓለምና ፣ ፈንጠዚያ ፣ ——ዘወትር ፣ በመኪና ፣ መንሸራሸሩን ፣ እንኳ ፣ አያህል ም——ዘረዘሩላት ። በስብከታቸው ፣ በጣም ፣ በረቱ ። ነጋ ፣ ጠባ ፣ መወትወታቸውን ፣ ያለመሰልቸት ፣ ሲቀጥሉ ፤ አበባ ፣ እንደቀድሞው ፣ መንፈሷ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ በዋፊ ፣ አጨላ ፣ ትመልሳቸው ፣ የነበር ፤ ዛሬ ፣ በዝምታ ፣ ታዳምጣ ቸው ፣ ነበር ። ምነው ፣ ምን ፣ ነካት?የለም ። ከመጀመሪያው አንስቶ ፤ በተዘዋሪ ፣ ወሬ ፤ መገፈሏን ፣ አላልተውት ፣ ነበር ፣ ለማለት ፣ ያስደፍራል ።

የሕፃን ፣ አእምሮ ፣ በትምሕርት ፣ እንደሚታነጽና ፣

እንደሚገነባ ፣ ሁሉ ፤ ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ የአበባን ፣ አእምሮ ፤ እንደሸክላ ፣ ሠሪ ፣ ጭቃ ፣ እየጨፈለቁ ፣ አዲስ ፣ ቅርጽ ፣ ያወጡለት ፣ ጀመር ።

ከጊዜ ፣ በኋላ ፤ ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ በአበባ ፣ አእምሮ ፣ ውስጥ ፣ የበተኑት ፣ ዘር ፤ በቅሎ ፣ ፍሬ ፣ ማውጣት ፣ ጀመረ ። ሕሊናዋ ፣ በሁለት ፣ ቦድን ፣ ተከፍሎ ፣ መግትና ፣ ትግል ፣ ይተራመስበት ፣ ቀጠል ። የጥንቱ ፣ ብርቱ ፣ መንፈሷ ፤ የቃል፡ኪዳንን ፣ ክብርና ፣ ቅድስና፡ በመገንዘብ ፤ ‘‘ከሣህሉ ፣ ጋር ፣ በጋብቻ ፣ ስትተሣሠሩ ፤ ጌትነትንና ፣ ድኅነትን ፤ ችግርና ፣ ሀብትን ፤ ተድላንና ፣ መከራን ፣ በእንድ ፣ ላይ ፣ ልትካፈሉ፡ካለሞት፡በተቀር፡ የሚለያያችሁ፡ኃይል፡በመሬት፡ ላይኖር ፣ በሚል ፣ ቃል ፣ ኪዳንና ፣ ውል ፣ አልነበረምን? የአሁኑ ፣ መወላወል ፣ ታዲያ ፣ ምን ፣ ይሉታል?ሣህሉ ፣ እንዴት ፣ ያዝንብሽና ፣ ይበሳጭ ። ሰውስ ፣ እንዴት ፣ ይገምትሽና ፣ ይታዘብሽበሰማይ ፣ ቤትስ ፣ እንዴት ፣ ያለ አቀባበል፡እንደሚደረግልሽ፡ ትገነዘቢዋለሽን?የለም ። ሞት ሽም ፣ ደኅንነትሽም ፣ ከሣህሉ ፣ ጋር ፣ ሊሆን፡የተገባ፡ነው ፣ ››

——እያለ ፣ ሲመክራት ፤ እመት ፣ ተጓዳ ፣ የዘሩት ፣ አዲስ መንፈስ ፣ ደግሞ ፤ ‘‘——የጋብቻ ፣ ዓላማ’’ኮ ፣ ለተደላ ፡ ነው ። ወትሮውንም ፣ ቢሆን ፣ የሣህሉ ፣ ውለታና ፣ የናቴ ፣ ቃል ፣ ገፋፍቶኝ ፡ ነው ፣ እንጅ ፤ ትምሕርቴን ፣ አቋርጬ ፣ እንደዚህ ፣ ባጭሩ ፣ ለመቀጨት ፣ ምኞቴ ፣ አልነበረም ። እውነት ፣ ነው ፤ ከሣህሉ ፣ ጋር ፣ ሆኜ ፣ አልተከፋሁም ። ችሎታችንና ፣ አካባቢያችን ፣ በሚፈቅድልን ፣ መጠን ፣ ደህና ፣ ኑሮ ፣ እናሳልፋለን ። ’’የወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ስብከት ፤ የትዳሯን ፣ ሙቀትና ፣ ድምቀት ፣ እንደዚህ ፣ በቀላሉ ፣ ለመገመት ፣ አበቃት!‘‘——አሁን ፤ ተጫን ፣ የተባለው ፤

የተሻለና ፣ የበለጠ ፣ ለማበርከት ፣ ደጅ ፣ ይጠናል ።——ዘመ
ናዊ ፣ የተማረ ፣ ነው ። ሀብት ፣ የተረፈው ፣ ይመስላል ።
አዲስ ፣ አበባን ፣ ለማየት ፣ ትጓጓ ፣ አልነበረምን?እነሆ ፣
ዕድል ፣ ወረደልሻ!ሲኒማ ፣ የሚባለውን ፣ አስደናቂ ፣ ትርዕ
ይት ፣ ለማየት፣ አትጓጉምን? በዘመናዊ ፣ ቅርስና ፣ ምቾት ፣
ለመንቀባረርና ፣ ለመደሰት ፣ አትፈልጊምን?በውነቱ ፣
ቂል ፣ አትሁኝ!ይህንን ፣ የመሰለ ፣ አጋጣሚ ፣ ዕድል ፤
ሁለተኛ ፣ በሕይወትሽ ፣ ሙሉ ፣ አይመጣልሽም ። ተይ ፣
ወርውረሽ ፣ እንዳትጥይው!የዘመናዊ ፣ ኑሮ ፣ ጣዕም ፣
ለመቅመስ ፣ ብትፈቅጅ ፣ የዛሬው ፣ አያምልጥሽ ። ሣህሉ ፣
ይወድሻል ፣ እርግጥ ፣ ነው ። ስትሄጅበትም ፣ ቢያዝ
ን ፣ እውነት ፣ አለው ። ቢሆንም ፣ ሌላ ፣ ከማግባት ፣ የሚ
ያግደው ፣ ነገር ፣ የለም ። ነገር ፣ ግን ፣ ግን ፣ እንደተጫን!
ካንቺ ፣ ፍቅር ፣ የተነሣ ፤ እንዴት ፣ እንደሚንሰፈሰፍና ፣
እንደሚጨነቅ ፣ ወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ አልነገሩሽም ? ታዲ
ያ ፣ ከመጠን ፣ በላይ ፣ የማያፈቅርሽ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፤
ስንት ፣ የከተማ ፣ ቆንጆጅት ፣ ተርፎለት ፣ የለም ፣ እንዴ !
ለምን ፣ አንችን ፣ ይማጠናል!——"በሕሊናዋ ፣ ውስጥ ፤
የሚታገሉት ፣ እነዚህ ፣ ሐሳቦች-ሰውነቷን ፣ በሥቃይ ፣
ያንገላቱት ፣ ነበር ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ "በፍጹም ፣ አይሞከ
ርም ። ባሌም ፤ ትዳሬም ፣ ሣህሉ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ "በማለት ፣
የቀሩትን ፣ አስተያየት ፣ ከአእምሮዋ ፣ ለማሽማለል ፣
ስትሞክር ፣ ባልቴቲቷ፣ ይመጡና፤ የሠራችውን፣ በማፍረስ፣
አዲስ ፣ እጡብ ፣ አስቀምጠውበት ፣ ሲሄዱ ፣ እንደገና ፣
ትዋልላለች፣ ። ይህ ፣ አዲስ ፣ ምኞት ፣ ስትጥለው ፣ ሲጥላት ፣
ስትወድቅ ፣ ስትነሣ ፣ በብዙው ፣ ተንገላታች ። በፍጹም ፣
ሞክሯት ፣ የማያውቅ ፣ የነበር ፤ መጥፎ ፣ ቅዠቶች ፣ በእን
ቅልፏ ፣ እየመጡ ፣ ይቀጠቅጧት ፣ ጀመር ።

በቀድሞው ፣ ሁኔታ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፤ አንድ ፣ ሰው ፣
እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ችግር ፣ ሲፈጥርባት ፣ በቀጥታ ፣ ለሣህሉ ፣
ከመንገር ፣ ባላመነታችም ፣ ነበር ። በተጫን ፣ ላይ ፣ ግን ፣
አፍዋን ፣ የለጎመውን ፣ እንጂ ፤ በፍጹም ፣ አልተነፈሰ
ችለትም ። ከመጀመሪያው ፣ አስታውቃው ፣ ቢሆን፤ ምናል
ባት ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፣ ፈውስ ፣ ሳይደረግለት ፣ አይቀርም ፣
ነበር። እመት ፣ ተጓዳን ፣ ቢቆጣቸውና ፤ ከአበባ ፣ እንዳይደ
ርሱ ፣ ቢገስጻቸው ፣ ኖሮ ፤ ከዚህ ፣ ሁሉ ፣ ሥቃይ ፣ ለመገላገ
ል ፣ ትችል ፣ ነበር ። ተጫንንም ፣ ቢሆን ፣ በተግሣጽ ፣
ወይንም ፣ በዛቻ፣ ቃል፣ አስፈራርቶ፣ ለማስተው ፣ ሳይቻል፣
አይቀርም። ነገር ፣ ግን ፣ እመት፣ ተጓዳ፣ የመሠረቱት፣ ቀስ-
በቀስ ፣ ስለ ፣ ነበር ፣ ሕንፃው ፣ እስከአደገ ፣ ድረስ ፣ አስጊነ
ቱና ፣ አደገኛነቱ ፣ በፍጹም ፣ አልታወቃትም ። አሁንማ ፣
ምኑን ፣ ትንገረው!ሕሊናዋ ፣ በመዋዠቅና ፣ በማመንታት ፣
ላይ ፣ አይደለም ፣ እንዴ ፣ የሚገኘው ?

የወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ስበከትና ፣ ውትውታ ፣ እንደመቀ
ጠሉ ፣ መጠን ፤ የአበባ ፣ ብርታት ፣ እየደከመና ፤ በሕሊናዋ
ውስጥ ፣ በሚደረገው ፣ ሙግት፣ የአዲሱ፣ ምኞት፣ ሚዛን፣እየ
ደፋ፣ሄደ፤እርሷም፣ወደዚሁ ፣ክፍል፣እንድታደላ ፣ተገደደች ።

ሁለቱ ፣ ሴቶች ፣ ስለዚህ፣ ጉዳይ፣ መጨዋወት፣ የተለመ
ደ ፣ ተግባር፣ ፣ አድርገው ፣ ያዙት ። አበባ ፣ እንደበፊቱ ፣
ቅር ፣ በመሰኘት ፣ ፈንታ ፣ ነገሩን ፣ራሷ፣ በግልጽ ፣ እየገፋፋ
ች ፣ "ታዲያ ፣ ተጫን ፣ ይበልጥብሻል ፣ ነው ፣ የሚሉኝ?
ስትል ፣ ትጠይቃዋለች ። እንዲያው ፣ መጨነቅ ፣ ሆኖባት ፣
ነው ፣ እንጅ ፤ እርሳቸውም ፣ የሚጥሩት ፣ ለዚሁ ፣ ግብ ፣ መሆ
ኑን ፣ ልቧ ፣ ያውቀዋል ። ብቻዋን፣ በምትሆንበት፣ ጊዜም ፤
በሐሳብ ፣ ውዝዋዜ ፣ ትንጓለል ፣ ነበር ።

በነዚህ ፡ የማዕበልና ፡ የፈተና ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፤ ተጫን ፡ ወደ ፡ እዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፤ ብዙ ፡ ጌጣጌጦችና ፡ በግምት ፡ የተሰናዳ ፡ ልብስ ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ ። እመት ፡ ተጓዳ ፡ ይህንን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በጉጉትና ፡ ሽተጠው ፡ አመጡና ፡ አበረከቷቅ ። ነገር ፡ ግን ፡ አበባ ፡ ቅር ፡ እያላት ፡ ሳትቀበል ፡ መለሰችው ። መረታቷ ፡ ገና ፡ አልተረጋገጠም ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ ሁኔታው ፡ እንደሚያስረዳው ፤ ፍርድ ፡ ወደተጫን ፡ በኩል ፡ መዝኖ ፡ መታየቱ ፡ አያጠራጥርም ።

እመት ፡ ተጓዳ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልሰለቹም ። ጉዳዩ ፡ ተፈጽሞ ፡ ዋጋቸውን ፡ እንደሚያገኙ ፡ ተስፋቸው ፡ በየቀኑ ፡ እያደገ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። ተጫን ፡ በበኩሉ ፤ ምኞቱ ፡ እንደሚሳላለት ፡ እምነቱን ፡ አላጓደለም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፤ አበባ ፡ እየተዳከመች ፡ መሔዷን ፡ ተረድታው ፡ ነበር ። እንዳንድ ፡ ጊዜ ፤ ፈጣሪ ፡ ብርታት ፡ እንዲሰጣት ፡ ጸሎት ፡ ጎታደርግ ፡ አልቀረችም ። ቢሆንም ፡ ወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፤ የዘሩት ፡ የምኞት ፡ መርዝ ፡ አንጎሏን ፡ በመጠኑ ፡ በልቶት ፡ ስለነበር ፡ መዳኗ ፡ የሚያወላውል ፡ ነው ።

በተፈጥሮ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይንም ፡ በአጋጣሚ ፡ ዕድል ፡ ከከበቻቸው ፡ የተጋጩት ፡ እነዚህ ፡ ምስት ፡ ፍጡሮች ፡ ያረፉበት ፡ የሐሳብ ፡ አቅዋም ፡ ሁናቴ ፡ የየግል ፡ መሥመሮች ፡ የተከተሉ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

ተጫን ፤ አበባን ፡ ከተመለከታት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ ያደረበት ፡ የፍላጐት ፡ መንፈስ ፤ የጋብቻ ፡ መልክ ፡ ይውሰድ ፡ እንጅ ፤ ከመጀመሪያው ፡ ግለት ፡ የተቀነሰ ፡ አይመስለም ። ስለዚህ ፡ ምኞቱ ፡ እንዲረካ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በላይ ፤ "የሐሳብ ፡ ውጥንን ፡ ከግብ ፡ ማድረስ ይገባል" ፤ የሚለው ፡ ዘመናዊ ፡ ትምሕርቱ ፤ እልህ

ስለጨመረበት ፤ በማንኛውም ፡ ዘዴ ፡ አበባን ፡ ካላሸነፈ ፡ በተቀር፤ ታላቅ፡ ውርደት፡ የደረሰበት፡ መስሎ ፡ ይሰማዋል ።

እመት ፡ ተጓዳ ፡ በዚህ ፡ ተማባር ፡ (መልእክቱ)በተለይ የጠኑበት ፡ የሣህሉን ፡ ትዳር ፡ ለማፈናቀል ፡ ፍላጐት ፡ ኑሮዋቸው ፡ ሳይሆን ፤ የብሩ ፡ ምትሐት ፡ እያንቀሳቀሳቸው ፡ እንደሆነ ፡ የሚታመን ፡ ነው ። አበባ ፡ በበኩሏ ፤ ከሣህሉ ፡ ሰመለየት ፤ በፊት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ እንዳልነበራት ፡ ሲታወስ ፤ በእመት ፡ ተጓዳ ፡ አማካይነት ፡ የተመረዘችበት ፡ ምኞት ፤ እሷንታን ፡ አሳዮቷት ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ተጫን ፤ በአውቶሞቢሉ ፡ ይሆንና ፤ ለመታየትም ፡ ሆነ ፡ ለማየት ፡ እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመንደሯ ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። የመኪና ፡ ድምጽ ፡ ስትሰማ ፤ በመስኮት ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ትመለከት ፡ ነበር ። ይሄውም ፡ እንዳችም ፡ ዓይነት ፡ የጉጉት ፡ ስሜት ፡ አድሮባት ፡ ሳይሆን ፤ ያንን ፡ ያህል ፡ የሚያፈቅራትንና፡ የሚፈልጋትን ፡ ሰው ፡ ለማየትና ፡ ለማወቅ ፡ ነው ። በመኪናይቱ ፡ ሳትደሰት ፡ አልቀረችም ። የተጫንም ፡ የልብሱ ፡ ማማርና ፤ የሰውነቱ ፡ ጥዳት ፡ አስደንቋታል ፡ ቢሆንም ፡ የምትወደው ፡ አልመሰላትም ። ነገር ግን ፡ ለጉዱ ፤ በዚያን ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ በሕልሟ ፡ መጥቶ ፡ አየችዋ !

አሰራ ፡ አምስት ፡ ቀኖች ፡ አለፉ ። አበባን ፡ ያ ፡ መጥፎ ፡ ምኞት ፡ ሊጥላት ፡ ያንገደግዳት ፡ ጀመር ። ማነው ፡ የሚደግፋት ? ኧረ ፡ ትንሽ ፡ ኃይልና ፡ ዓቅም ፡ የሚያበድር ? የሚረዳ ፤ የሚያጽናና ፡ ያለህ ! —— ግንም ፡ አልተገኘም ። አልነበረም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፡ አኳኋኗን ፡ ተመልክተው ፤ አቅዋሟንና ፡ ሰውነቷ

ን ፣ የምታመዛዝንበት ፡ ሩቃ ፣ ሳይሰጡ ፤ በዚያ ፣ ብርቱ ፣ የነገር ፣ ጉልበታቸው ፣ ይደቁሲት ፣ ጀመር ።

በቃ ፣ ተከተተ ፤ አበባ ፣ ተሸነፈች——ተረታች ። ዋ ፣ እወዳደቅ ፤አቤት ፣ ታላቅ ፣ ውድቀት፤በውነቱ ፣ በጣም ታግላ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ፈተናው ፣ በጣም ፣ ከበደባት ፣ እንኳንስ ፣ የወጣት ፣ መንፈስና ፣ ሊጋ ፣ እእምሮ ፤ በዕድሜ ፣ የበሰሉትና ፣ በመንፈሳዊ ፣ ትምሕርት ፣ የረቀቁትንም ፤ ከጓርና ፣ ከኅዳም ፣ እየመነጠቀ ፣ እንደሚያመጣቸው ፣ አይሳትም ። ስለዚህ ፣ እኛም ፣ ይወንኑ ፣ የመሰለ ፣ ፈተና ፣ ለግለፍ ፣ መቻላችንን ፣ ስለማናረጋግጥ ፣ በጣም ፣ ልንፈር ድባት ፣ እውነት ፣ ያለን ፣ አይመስልም ። እንደዚህ ፣ የመሰ ለውን ፣ ማዕበል ፣ ለመቯገር ፣ የሚችሉት ፣ ጥቂቶች ፣ ሲሆኑ ፤ እነርሱም ፣ በጣም ፣ የሚመሰገኑ ፣ ናቸው ።

ምዕራፍ ፣ ፯ ፣

አበባ ፤ ሃያ ፣ ቀኖች ፣ ያህል ፣ ተፈራግጣ ፣ በመርታት ፣ እሽታዋን ፣ ስትገልጽ ፤ እመት ፣ ተጓዳ ፣ ያደረጉት ፣ መፈን ደቅ ፤ ከተጫን ፣ ደስታ ፣ ጋር ፣ የሚወዳደር ፣ ነበር ። የርሱ ፣ ምኞቱ ፣ ስለሞላለት ፣ ሲሆን ፣ የርሳቸው ፣ ደግሞ ፤ የመል እክታቸውን ፣ ዋጋ ፣ ለመቀበል ፣ ባደረባቸው ፣ የጉርሻ ፣ ተስፋ ፣ መሠረት ፣ ነበር ። ቢሆንም ፣ ተጫን ፤ ያሰቡትን ፣ ያህል ፣ ስላላበለጸጋቸው ፤ ደስታቸው ፣ በመጨረሻ ፣ ወደ ቅሬታና ፣ ጸጸት ፣ ተለውጧል ።

አበባና ፣ ተጫን ፣ የሚገናኙበት ፣ ቀንና ፣ ሰዓት ፣ ተወሰነ ። ግንኙነታቸው ፣ በበነጋው ፣ ሊሆን ፣ ሌሊቱን ፤ አበባ ፣ እንቅልፍ ፣ ባይኗ ፣ ሳይዞር ፣ ነጋ ። ተጫን ፣ መጀመሪ ያ ፣ ቀን ፣ እንደደረሰበት ፣ ያለ ፣ የሐሳብ ፣ ውዝዋዜ ፣

ሲያላጋት ፣ አደረ ። ነገር ፣ ግን ፣ የርቧው ፣ እንደርሱ ፣ በፍላጐት ፣ በመቃጠል ፤ ሰሚቱን ፣ ለማርካት ፣ በመቸኰ ል ፣ ሳይሆን ፤ ማህሉ ፣ የሚደርስበትን ፣ ኃዘንና ፣ ትካዜ ፤ ልጇዋ ፣ የሚያድርበትን ፣ ናፍቆት ፣ በማስታወስና ፣ ቅር በመሰኘት ፣ ነበር ። እርቧም ፣ ወደፊት ፣ የምታገኘውንና ፣ የምታየውን ፣ ዘመናዊ ፣ ምኞትና ፣ ፈንጠዝያ ፣ በሕሊና ፣ አሰላስላዋለች ። እንዳይነጋ ፣ የለም ፣ ነጋ ። ጥዋት ፣ ማህሉ ፣ ወደ ፣ ሥራው ፣ ለመሔድ ፣ ሲነሣ ፤ ቁርሱን ፣ አቅርባለታ ለች ። ነገር ፣ ግን ፣ የተሰናዳው ፣ በግማሽ ፣ ልብ ፣ ስለነበር ፣ እንደተንቁ ፣ አልጣፈጠም ፤ የርቧ ፣ ጨዋታና ፣ ለዛ ፣ በተጨማሪ ፣ ካለቃመመው ፤ ጣፋጭም ፣ ቢሆን ፣ ጣዕሙ ፣ አይሰማውም ፣ ነበር ። ዛሬ ፣ ጧት ፣ ግን ፣ እንኳንስ ፣ ያንን ለኽት ፣ ያለውን ፣ ጨዋታዋን ፣ ልታስቀርሰው ፣ ይቅርና ፣ በግንባሯ ፣ ላይ ፣ ትካዜና ፣ ቅሬታ ፣ ይነበብበት ፣ ነበር ። ‘‘ደህና ፣ ዋሉ’’ብሎ ፣ ሲወጣ ፤ እንደገና ፣ እንደማይተያዩ ፣ ስታውቅ ፣ ለምን ፣ የመጨረሻውን ፣ ፈገግታዋን ፣ እንኳ ፣ ነፈገችውማህሉን ፣ ለማስከፋትና ፣ ለማስቀየም ፣ ብላ፣ አይደለም ። ነገር ፣ ግን ፣ ከፊቷ ፣ ላይ ፣ የተደቀነው፣ አዲ ሱ ፣ የኑሮ ፣ መልክ ፤ አይኗን ፣ አሳውሮ ፣ የምታደርገውን ፣ ሁሉ ፣ አሳጥቷት ፣ ስለነበር ፤ ማሰብ ፣ አልቻለችም ።

አበባ ፣ ሰሞኑን ፣ ያሳየችው ፣ የጠባይ ፣ መልክ ፣ የጥንት ፣ ባሕሪዋ ፣ አለመሆኑን ፣ ማህሉ ፣ ሳይገነዘበው ፣ ባይቀርም ፤ ምክንያቱን ፣ ሊረዳው ፣ አልቻለም ፣ ነበር ። ሊመራመረውም ፣ አልፈለገም ። ስለዚህ ፣ የዚች ፣ ቀን ፣ ጧት ፣ ወደሥራው ፣ ሲሄድ ፣ ጉዳዩን ፤ ከፍተኛ፣ አስተያየት ባይሰጠውም ፣ ቅሉ ፣ በመጠኑ ፣ አሰላስሎት ፣ ነበር ። ይሄውም ፣ አበባን ፤ በመጥፎ ፣ ግምት ፣ ላይ ፣ (በትክክለኛ

ው)በመጣል ፣ ሳይሆን ፤ "በምን ፣ ተከፍታብኝ ፣ ይሆን?" በሚል ፣ ቅን ፣ መንፈስ ፣ ነው ።

የመጀመሪያ ፣ የትዳር ፣ ቤትዋን ፣ ለመጨረሻ ፣ ጊዜ ፣ በቅሬታ ፣ ዓይን ፣ እየተገላመጠች ፣ ተመለከተችውና ፤ ከአልጋው ፣ ላይ ፣ የተኛውን ፣ ሕፃን ፤ ሦስት ፣ አራት ፣ ጊዜ ፤ በከንፈሯና ፣ በዕንባዋ ፣ ከሳመች ፣ በኋላ ፣ ቤቱን ፣ የኋሊት ፣ ዘግታ ፣ ወጣች።ከውጨኛው ፣ በር ፣ አቅራቢያ ፣ ስትደርስ ፣ ደግሞ ፤ እንደገና ፣ ዘወር ፣ ብላ ፤ "የጫጉላ ፣ ጉጆዬ ፣ ደህና ፣ ሁኚ ፣" በሚል ፣ መንፈስ ፣ ተሰናበተችና ፤ ወደቀጠሮዋ ፣ ሥፍራ ፣ ኳተነች ። ከተጫን ፣ ጋር ፣ የተገናኙት ፣ ግታ ፣ ሲሆን ፣ ቀኑን ፣ ሙሉ ፣ የዋለችው ፣ ከወይዘሮ ፣ ተጓዳ ፣ ጋር ፤ በአንድ ፣ ዘመዳቸው ፣ ቤት ፣ ነበር ። ጀንበር ፣ ከጠለቀች ፣ በኋላ ፤ እመት ፣ ተጓዳ ፣ አውሬ ፣ ገድሎ ፣ እንደተመለሰ ፣ አዳኝ ፤ አበባን ፣ አስከትለው ፣ ወደ ፣ ተጫን ሆቴል ፣ አመሩ ። ተጫን ፤ ቀኑ ፣ አልመሸልህ ፣ ብሎት ፣ ሲንቆራጠጥ ፣ ከዋለ ፣ በኋላ ፤ በመስኮት ፣ አንቱቱን ፣ ብቅ ፣ እድርጐ ፣ ወደ ፣ መምጫቸው ፣ አቅጣጫ ፣ ይመለከት ፣ ነበር ። በምሽቱ ፣ ብርሃን ፣ የሁለቱን ፣ ወይዛዝርት፣ ቅርጽ፣ ለየና ፤ በድል ፣ አድራጊነት ፣ ስሜት ፣ ፈገግ ፣ አለ ።

አበባ ፤ ገላዋ ፤ በጭንቀትና ፣ በፍርኃት ፣ ወዝ ፣ እየታጠበ ፤ በአሮጊቷ ፣ እየተመራች ፣ ገባች ። አንገቷን ፣ አቀርቅራ ፤ የእግሯን ፣ መቆሚያ ፣ ከመከታተል ፣ በተቀር ፤ ተጫንንም ፣ ሆነ ፣ ክፍሉን ፣ እንድም ፣ ጊዜ ፣ ቀና ፣ ብላ ፣ አልተመለከተችውም ። ተጫን ፣ በዘመናዊ ፣ ትሕትና ፣ ተቀብሎ ፣ አስተናገዳቸውና ፤ ሁለቱ ፣ ወይዛዝርት ፣ ከቀረ በላቸው ፣ ወንበር ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ አሉ ።

አበባ ፤ ራሷን ፣ ደፍታ ፣ ከነጠላዋ ፣ ጠርዝ ፣ ጋር ፣

ትጫወታለች ። ወይዘሮ ፣ ተጓዳም ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ቀና ፣ እያሉ ፣ ተጫንን ፣ በመግባባት ፣ ዓይን ፣ ከመመልከት ፣ በተቀር ፣ አንዳችም ፣ ቃል ፣ አልተናገሩም ። ክፍሉ ፤ እንኳንስ፣ ሦስት ፣ ሰዎች፣ ያረፉበትና ፤ የሕይወት ፣ ምልክት ፣ ያለበት ፣ አይመስልም።ተጫን፤ ሲጋራውን፣ አቀጣጥሎ፣ጢሱን፣አንድ ጊዜ ፣ ተጕለል፣ አደረገና ፣ ጸጥታውን፣ ለማደፍረስ፣ ያህል፣ እህህ—ታዲያስ ፣ ''አለ ። አበባ ፣ ለቅጽበት ፣ ያህል ፣ ስርቅ ፣ አድርጋ ፣ አየችውና ፣ ተመልሳ ፣ ነጠላዋን ፣ ማፍተልተል ፣ ቀጠለች ። ለእንግዶቹ ፣ ቢራ ፣ ቀረበላቸው ። ነገር ፣ ግን ፣ የሚጋበዘው ፣ አላገኘም ፣ ነበር ። እመት ፣ ተጓዳ ፤ ለጠላና ፤ ለሀገር ፣ አረቂ ፣ ነው ፣ እንጂ ፤ ከሚሎቲ ፣ ቢራ ፣ ጋር ፣ እውቂያ ፣ ስላልነበራቸው ፣ መራር ፣ ሆኖ ፣ አገኙት ። አበባ ግን ፣ በከንፈሯም ፣ አላዞረችው ፣ ነበር ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ሁሉ ፤ ተጫን ፣ በሲጋራው ፣ ጢስ ፣ ውስጥ ፣ አበባን ፣ ከእግር ፣ እስከራሷ ፣ ይገመግማት ፣ ነበር ። ያ ፣ የፈካው ፣ ገላዋና ፣ የመሸኮርመም ፣ ሁኔታዋ ፣ በጕልማሳው ፣ ወጣት ፣ ሰውነት ፣ የፍላጐት ፣ ቃጠሎ ፣ ለቀቀበትና ፤ "ጉዳይዎ ፣ ተፈጽሟል ። እንግዲህ ፣ ወደቤትዎ ፣ ይሂዱ" በሚል ፣ የትእዛዝ ፣ ዓይን ፣ ወይዘሮ ፣ ተጓዳን ፣ ገላመጣቸው ። እርሳቸውም ፣ ጥቂት ፣ ቃላት ፣ ከራሳቸው ፣ ጋር ፣ ብቻ ፣ ካጉረመረሙ ፣ በኋላ ፣ "ደህና ፣ እደሩ" ብለው ፣ ወጡ ።

አበባ ፤ አገጯን ፣ ከመዳፍዋ ፣ ላይ ፣ በማንተራስ ፣ እንደግሪክ ፣ የቁንጅና ፣ ሐውልት ፣ ደርቃ ፣ ቁጭ ፣ አለች ። ተጫን ፣ በክፍሉ ፣ ውስጥ ፣ እየተንጐራደደ ፤ ሲጋራውን ፣ በሲጋራ ፣ እያቀጣጠለ ፣ ይምገው ፣ ጀመር ። አንገቱን ፣ ዘቅዘቅ ፣ እያደረገም ፣ ይመለከታት ፣ ነበር ። የትምባሆው ፣ መዓዛ ፣ ልቧን ፣ አቅለሸለሻት ። የጢሱ ፣ እፍናት ፣

ራቢን ፣ አዘረፈው ። ማን ፣ ከጣጉላ፣ ቤት ፣ እንዳለች፣ ሙሽራ፣ የሕመሟን ፣ ሥቃይ ፣ ሁሉ ፣ ሟጭ፣ እድርጋ ፣ ዋጠችው ። ከሁሉም ፣ የበለባት ፣ የነፍረቁ ፣ ጭንቀት ፣ ነበር ።

አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ከሚሰማው ፣ የእግር ፣ ኩቲ ፣ በትቀር ቀበሌውን ፣ የጨለማው ፣ ጸጥታ ፣ ውጠት ፣ ነበር ። ከመካ ከላቸው ፣ በተዘራጋው ፣ የጸጥታ ፣ ዓይል ፣ አሸባር ፣ ሁለቱ አዲስ ፣ ባልንጀሮች ፣ በብዙ ፣ ምሰራፎች ፣ ርቀት ፣ የተለያ ዩ ፣ ይመስላል ።

በአበባ ፣ ልቦና ፣ ምንም ፣ ዓይነት ሐሳብ ፣ አይላወስ ም ፣ ነበር ። ይህ ፣ ድንገተኛ ፣ ይዘታ ፣ የማሰብ ፣ አእምሮዋ ን ፣ አደንዝዘታል ። ተጫን ፣ ማን ፣ በበኩሉ ፣ ግንኙነታቸው ን ፣ የሚያሞቅና ፣ የሚያደምቅ ፣ ጨዋታ ፣ ለማቅረብ ፣ ሳያሰላሰል ፣ አልቀረም ፣ ነበር ፤ ነገር ፣ ግን ፣ ለአሁኑ ፣ አቀራረብ ፣ ተስማሚ ፣ የሚሆን ፣ ዓይነት ፣ ሊፈጥር ፣ አልቻለም ። ከጠፉ-ጨረቃ ፣ በታች ፣ ቁጭ ፣ ብሎና ፣ የፍቅረኞን ፣ እጅ ፣ ጨብጠ ፤ በስሜትና ፣ በመዚቃ ፣ ቃና ፣ የፍቅርን ፣ ታሪክ ፣ ማውራት ፣ ባላቃተውም ፣ ነበር ። ቢሆንም ፣ ይህ ፣ ዓይነት ፣ ጭውውት ፤ በሥለጠኑና ፣ በተለማመዱ ፣ ፍቅረኞች ፣ መካከል ፣ የሚያስደስት ፣ ሲሆን ከአሁኑ ፣ ሁኔታ ፣ ጋር ፣ በፍጹም ፣ የማይጣጣና ፣ የማይጋጠም ፣ እንደሚሆን ፣ ግጦት ። ወይንም ፣ እንደውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ ልማድ ፣ ስለዓየሩ ፣ ጠባይና ፣ ስለአሰፈው ፣ ሳምንት ፣ ፊልም ፣ እንዳያጫውታት ፣ ምኑ ፣ ሊገባት ? እንዲያውም፣እንደአቀማመጥዋስ ፣ ማንኛውንም ፣ ድምጽ ፣ የምትሰማ ፣ አይመስልም ። ስለዚህ ፣ ከሁሉም ፣ አቀራረብ የተሻለ ፣ መስሎ ፣ የታየው ፤ በጥሞናና ፣ በጊዜ ፣ ብዛት ፣ ማስለመድና ፣ መላመድ ፣ ሲሆን ፣ መልካሙን ፣ ጸጥታ ፤

በትብጠት ፣ ለማሸበር ፣ ሳይሞክር ፤ ይህች ፣ ያልተግራችው ን ፣ ውብ ፣ እንሰሳ ፣ በአድናቆት ፣ መመልከትን ፣ መርጠ ፣ ነበር ።

በቀዝቃዛው ፣ ሌሊት ፣ የተጫን ፣ ሰውነት ፤ ትኩሳት ፣ ግለት——ቃጠሎ ፣ ተሰማው ። ከመቀመጫው ፣ ጋር ፣ ይተሻሸና ፣ ይንቀራጠጥ ፣ ጀመር ። ሰዓቱ ፣ ማን ፣ የማይን ቀሳቀስ ፣ ሆነበት ። የምሽቱ ፣ ሌሊት ፣ የረጋ ፣ መሰለ ። ትሰማሥቱ ፣ እየተዋገደ ፣ ሄደ ። በመጨረሻ ፤ ሥስት ፣ ሰዓት ፣ ገደማ ፣ ላይ ፣ ሲሆን ፤ ልብሶቹን ፣ አወላልቆ ፣ ካልጋው ፣ ላይ ፣ ጋደም ፣ አለና ፤ "አትተኛም ፣ እንዴ?" አበባ ፣ አልመለሰችለትም ። ጥቂት ፣ ካጉረመረመ ፣ በኋላ ፣ ኃፍረት ፣ እንደያዛት ፣ በመገንዘብ ፣ መብራቱን ፣ አጠፋላት አበባ ፣ በማመንታትና ፣ በፍርሃት ፣ ትንሽ ፣ ከተርበደበደች ፣ በኋላ ፤ ውድቀቱን ፣ ጨለማ ፣ ጋሸ ፣ በማድረግ ፣ ወደአልጋ ው ፣ ስትጠጋ ፤ ተጫን ፣ ሲያደባ ፣ እንደቆየ ፤ ስሜት ፣ በተቀላቀለበት ፣ ኃይል ፣ ጉትቶ ፣ ከላይ ፣ አሳረፋት ። ልብሶቿን ፣ ስታወጣ ፣ አካልዋ ፣ በሙሉ ፣ ይንዘፈዘ ፍ ፣ ነበር ።ከዚህ ፣ በኋላ ፤ ለማይቀረው ፣ የሔዋንነት ፣ ግዳጅ ፣ ሰውነቷን ፣ መሠዋት ፣ እንዳለባት ፣ በመገንዘብ ፤ ፈቃዱን ፣ ለመሙላት ፣ ተዘጋጀች ። ስሜትዋን ፣ እ ንኳ ፣ ባይሆን ፣ አካሏን ፣ ሰጠችው——ተጫን ፣ ከግለዋ ፣ ተመገበ ። የሃያ ፣ ቀን ሪ ስሜትና ፣ የፍላጐት ፣ ራቡን ፣ ሲያረካ ፣ አደረ ። የአበባ ፣ ሰውነት ፤ የመጫት ፣ ጠረን ፣ ገና ፣ በሙሉ ፣ ያልወጣለት ፣ ቢሆንም ፤ በሽቶ ፣ ብዛት ፣ ከቀረናው ፣ የከተማ ፣ ሴቶች ፣ መዓዛ ፣ በብዙ ፣ እጅ ፣ የሚያስመርጥ ፣ መስሎ ፣ ተሰማው ። ከሙሉ ፣ በከፊሉ ፣ ውሃ-ውሃ ፣ መሽተት ፣ እንየደሚያሸ ፣ የሚታመን ፣ ነው ።

ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፤ የነላዋ ፡ ልስላሴ ፡ በጣም ፡ ሳያስደስተ ው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ።

በበነጋው ፡ ጠዋት ፡ ተጫን ፡ ሚስቱን ፡ ከጮኑ ፡ አስቀምጠ ፡ ወደ ፡ አዲስ፡ አበባ ፡ ኩበለለ።"ባልና-ሚስት" እንበላቸው ፡ እንጅ ፤ ይህንን ፡ ስያሜ ፡ የሚያጸድቅ ፡ ማንኛውም ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ በመከላላቸው ፡ አልተደረገ ም ። ቃል-ኪዳን ፡ አልተሣሠሩም ። በወግ ፡ በሥርዓት ፡ በሽማግሌ ፡ አልተፈጣጠሙም ። እርሱ ፡ ፈቀዳትና ፡ ሚስቱ ፡ እንድትሆን ፡ አባበላት፤ እርሷም ፡ ተከተለችው ፡ ዘግለት ፡ በተቀር ፤ በምን ፡ ዓይነት ፡ ስምምነት፡በእንዴት ፡ ያለ ፡ ይዞታ፡በሰማንያ ፡ ነውን ፡ ወይንስ ፡ በቅጥር፡አልተለ የም ። ተጫን ፡ በበኩሉ ፡ ያሰበው ፡ የፍቅሩንና ፡ የፍላጐቱ ን ፡ ስሜት ፡ መኾላት ፡ እንጅ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መፈጸም ፡ እንደሚገባ ፡ አላስታወሰም፡ ለማለት ፡ ሲቻል ፡ አበባ ፡ ግን ፤ ከፊትዋ ፡ ላይ ፡ የተደቀነው ፡ ብርቅና ፡ ዕንግዳ ፡ የኑሮ ፡ መልክ ፤ ልቧን ፡ በአድናቆት ፡ ያስደነፋ ው ፡ ስለነበር ፤ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለማሰላሰል ፡ ፋታ ፡ አላገኘችም

አዲሶቹ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኞዋች ፤ በመካከላቸው ፡ የተዘረ ጋውን ፡ የመተፋፈር ፡ አምባ ፡ በጉዞዋቸው ፡ ጊዜ ፡ በመጠ ኑ ፡ ለማፈራረስ ፡ ችለዋል ። ተጫን ፤ መኪናውን ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ ሲመራ ፤ የሚያልፏቸውንና ፡ በሩቅ ፡ የሚታዩትን ፤ መንደሮች ፤ ተራሮች ፡ ወንዞችና ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎች ፤ በሌላው ፡ እጁ ፡ እየጠቀሰ ፡ በማመልከት ፡ ስማቸውንና ፡ ዜናቸውን ፡ ያወራላት ፡ ነበር ። አበባ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሐሳቧና ፡ አይኗ ፡ እንደመኪናው ፡ ፍጥነት፡ ቢቃብዝ ም ፡ ንግግሩን ፡ ከማዳመጥና ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቂዎችን ፡ ከመሰንዘር ፡ አልታገደችም ። የእንግዲሁ ፡ መግደርደር ፤

ተጫንን ፡ ማበሳጨትና ፡ ራሷንም ፡ መበደል ፡ እንጅ ፡ አንዳችም ፡ ጥቅም ፡ እንደማይሰጥ ፡ በመገንዘብ ፤ ዕረፍት ፡ ለማድረግ ፡ በአስደሳች ፡ ሥፍራዎች ፡ በትንንሽ ፡ ከተሞች ሲቆሙ ፡ የሚጋብዛትን ፤ ቢስኩት ፤ ፍራፍሬና ፡ ቀላል ፡ መጠጥ ፡ እየተቀበለች ፡ እንከታዋለች ። በጀመረችው ፡ መግፋት ፡ እንጅ ፡ ማፈግፈግ ፡ እንደማይገባት ፡ ልትገነዘብ ፡ በተፈጥሮዋ ፡ አስተዋይ ፡ እንደነበረች ፡ እንረዳለን ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በመጠኑ ፡ የተላመ ዱ ፡ የተዋወቁና ፡ በመዝናናት ፡ የሚጨዋወቱ ፡ ጓደኞዋች ፡ ሆነው ፡ ነበር ።

በተወለደችበት ፡ መንደር ፡ ብቻ ፡ ተወስና ፡ ያደገችው አሸባ ፤ የመናገሻ ፡ ከተማ ፡ ትዕይንት ፡ ከፍተኛ ፡ አድናቆት ን ፡ ፈጠረባት ። የሕዝቡን ፡ መሳት ፤ የመኪናውን ፡ ዓይነትና ፡ ብዛት ፡ በመመልከት ፡ ፈዛ ፡ ቀረች ። የአድናቆ ቱም ፡ ስሜት ፡ አዲስ ፡ ዓይነት ፡ ደስታ ፡ ሳይሰጣት ፡ አልቀ ረም ፡ ነበር ። ከወዲያ-ወዲህ ፡ እየተቅበዘበዘች ፤ "ያ ፡ ደግ ሞ ፡ ምንድን ፡ ነው?እየው-እየውማ!,,እያለች ፡ በመፈንደ ቅ ፡ ስትወተውተው ፤ ተጫን ፡ እንደቆንጆ ፡ አሻንጉሊት ፡ በገርነትዋ ፡ እየሳቀና ፡ እየተደሰተ ፡ ወደቤቱ ፡ ወሰዳት ።

መኖርያ ፡ ቤቱ ፡ በጉለሌ ፡ ቀበሌ ፡ አንድ ፡ መጠነኛ ፡ ቪላ ፡ ነበር ። የአውቶሞቢሉ ፡ ጥሩምባ ፡ ሲነፋ ፡ እንድ ፡ እሽከር ፡ እየተጣደፈ ፡ መጥቶ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ቆመና ፤ ከጌታው ፡ መኪና፡ውስጥ ፡ አበባ፡ስትወጣ ፡ በማየቱ ፡ ተገ ርሞ፡እንደጉድ ፡ ከግር፡እስከራሷ፡ይቃኛት፡ ጀመር።"ነገር፡ግን ወዲያው ፡ ተጫን ፡ ያዘውና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቁጣ ፡ ዓይን-ጅራፍ ፡ ቢሸነቁጠው ፡ እየተሽቆጠቆጠ ፡ ወደግድቤቱ ፡ ሮጠ ።

በውጭው ፣ ማማር ፣ ስትደነቅ ፤ በቀደም ፣ ተከተል ፣ እየተማሩ ፣ ከሣሎኑ ፣ ከፍል ፣ ዘው ፣ ብለው ፣ ሲገቡ ፣ አበባ ፣ በድንጋጤ ፣ አፍን ፣ ከፍታ ፣ ቀረች።ዘመናዊው ፣ የቤት ፣ ዕቃና ፣ ዜማ-ጌጥ ፣ ላልተላመደው ፣ የግጠር ፣ ዓይን ፣ እንደ ፣ ቤተ ፣ መቅደስ ፣ ያሸበረቀ፣ እንደሚሆን፣ አይሳትም። ግና ፣ ስትገባ ፣ ባያስጠነቅቃትና ፣ ስትራመድ ፣ ባይደግፋት ፣ ኖሮ ፤ በሰም ፣ የተወለወለው ፣ ወለል ፤ አሻልጦ ፤ ከመራት ፣ ሊዶበልቃት ፣ ነበር ። ፎቁው ፣ የሰው ፣ መቀመጫ ፣ መሆኑ ን ፣ በፍጹም ፣ አላሰበችም ። ''ከዚህ ፣ አረፍ ፣ በይ'' ፣ ሲል ፣ ከመለከታት ፣ በኋላ ፣ እንኳ ፣ ለጥቂት ፣ ደቂቃውም ች ፣ አመናታለች ፤ የፎቁው ፣ ምቾት ፤ ወደ ፣ ፊት ፣ የምታሳልፈ ውን ፣ ዘመናይ ፣ ኑሮ ፣ ሲያስታውሳት ፤ ''የዚህ ፣ ቤት ፣ እመቤት ፣ መሆኔ ፣ እኮ ፣ ነውኮከዚህ ፣ የበለጠ ፣ ምን ፣ ዓለ ም ፣ ይገኛል!''ኢያለች ፣ በማሰላሰል ፣ ከፍሉንና ፣ ዕቃዎቹ ን ፣ ሁሉ ፣ በደስታ ፣ ዓይን ፣ ትቀላውጠው ፣ ጀመር ። በመኝታ ፣ ቤት ፣ ውስጥ ፣ የሚገኙትም ፤ የአልጋው ፣ ማማር ፤ ቁም ፣ ሣጥኑ ፤ መስታወቱና ፣ የቀሩትም ፣ የከፍሉ ፣ ዕቃዎች ፣ በጣም ፣ አስደንቅዋትና ፣ አስደሰትዋት ፣ ነበር ።

የሰማችውንና ፣ የተወራላትን ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ እገኘ ችው ፣ ደረሳት ። ነገር ፣ ግን ፣ ከልጅነት ፣ ያልተዋወቀችው ፣ ዘመናይነት ፣ አስከተቂት ፣ ወራት ፣ ድረስ ፣ ያደናግራት ፣ ነበር ። ከአሊጋው ፣ ላይ ፣ ወጥታ ፣ እንደ ፣ ልቧ ፣ ለመንከባ ለል ፣ ይቀሩት ፣ ነበር ። ከፎቁው ፣ ላይ ፣ ዘርፈጥ ፣ ስትል ም ፣ ሰቅጠጥ ፣ ኢያሰኛት ፣ ነው ። የቤቱ ፣ ሙሉ ፣ እመቤት ፣ ለመሆን ፣ መብቱ ፣ የተፈቀደላት ፣ መሆኑ ፣ ቢታመንም ፣ ፍጹም ፣ ሥልጣንን ፣ ለማሳየት ፣ ትሔት ፣ ተፈጥሮዋ ፣ አልተናፈረም ። አሽከርዋ ፣ እንኳ ፣ ተጭን ፣ ከልኖረ ፣

በተቀር ፣ ተግቢውን ፣ የመታዘዝ ፣ መልክ ፣ አይሰጣትም ፣ ነበር ። ያም ፣ ሆኖ ፣ ቅፈታ ፣ አልገባትም ። እስከጊዜው ፣ ድረስ ፣ በአፍላ ፣ ስሜት ፣ ልቧ ፣ ረከቶ ፣ ነበር ።

ተጫን ፣ በበኩሉ ፣ ከግባላት ፣ ቃል ፣ አንጻችም ፣ እንዲባያል ፣ አላደረገም ። በየመደብሩ ፣ እያዞረ ፤ ልብሱን ፣ ጫማውን ፤ ጌጣ-ጌጡን ፤ አይኗ ፣ በመረጠውና ፣ ልቧ ፣ በከጀለው ፣ ግዛላት ። ሰጣት ። አስረከባት ። እርሱም ፣ ተቀባበላት ። እሜጭሩ ፣ ቀሚስ ፤ ምንም ፣ እንኳ ፣ እርሷ ፣ የማትፈቅደው ፣ ብትሆንም ፤ ከአወጣጠ ፣ መልካሙ ባትሞና ፣ ተረከዝዋ ፣ ጋር ፣ በደንብ ፣ ሳይስማማት ፣ አል ቀረም ። የጀሮ ፣ ጉትቻውና ፣ ያንባቱ ፣ ሐብል ፤ መቸስ ፣ ተግቢ ፣ ቦታውን ፣ ለመያዙ ፣ አይጠረጠርም ። እጅ ፣ አም ባሩና ፣ ቀለበቱ ፤ ወደር ፣ ከሌለው ፣ ከንዲና ፤ ከአለንጋው ፣ እጣቷ ፣ ጋር ፣ በጠና ፣ ተወዳጅተው ፣ ነበር ። ያ ፣ ሽንቅጥ ፣ መገብ ፣ በጉልህ ፣ የሚገለጽበትን ፣ ዘመናዊ ፣ ቀሚስ ፣ አገኘ ። ዘማው ፣ ጠጉር ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ቅባት ፣ ሲታሽ ፣ ጊዜ ፣ የሚሆነውን ፣ አጣ ። (ነገር ፣ ግን ፣ ወደፊት ፣ እንደም ናገኘው ፤ ሲበዛበት ፣ መበላሸቱ ፣ አለቀረም)ተረከዘ ፣ ስንዝር ፣ የሆነው ፣ ጫማ ፣ ግን ፣ ቁርጭምጭሚትዋን ፣ እያጋጨ ፣ በወለምታ ፣ ከማስቸገሩም ፣ በላይ ፣ አረማመዱ ን ፣ እስከጣዙ፣ ወራት፣ድረስ ፣ ልታውቅበት፣ አልቻለችም ።

ከዚህ፣በተቀርየውስጡ፣ዕውቀትዋ፣በዝቅተኛ፣ደረጃ ፣ የተወሰነው ፣ የገጠሬቱ ፣ አበባ ፤ በውጭ ፣ መልክ ፣ ረገድ ፣ ከከተማው ፣ ጥራዝ ፣ ነጠቅ ፣ ሥልጣኔ ፣ ጋር ፣ በቀላሉ ፣ ለመላመድ ፣ የምትችል ፣ መስላ ፣ ትታያለች ። እንዶርሷ ፣ ውስጠ-ባዶ ፣ ከሆኑት ፣ ከተማ ፣ አደግ ፣ ወይዛዝርት ፣ ጋር ፤ በአለባበስ ፣ በአካሄድና ፣ በቄንጥ ፣ ለመወዳደር ፣ ረጅም ፣

ጊዜ ፡ አልወሰደባትም ። እንደጀግሪ ፡ ተማሪ ፤ ይህ ፡ የውድድር ፡ ስሜት ፡ እስኪበርድላት ፤ ድንገት ፡ ያገኘችው ፡ ዘመናይነትና ፡ እመቤትነት ፡ እስክትጠግበውና ፤ የጫጉላ ፡ ቤትዋ ፡ አፍላ ፡ እስኪወጣላት ፡ ድረስ ፤ አዲሱ ፡ ኑሮዋ ፡ በርግጡ ፡ የሚያስደስት ፡ ሆኖ ፡ ተሰምታት ፡ ነበር ። ቅሬታ ፡ ኑሮበት ፡ ቢሆንም ፡ በጥሞና ፡ ለማሰላሰል ፡ ፋታ ፡ አልሰጣትም ።

በቁም ፡ ሳጥኑ ፡ አግዳም ፡ ላይ ፡ ከተንዠረገገው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሞድና ፡ የሀገር ፡ ልብሶች ፤ ዓይኗ ፡ ያረፈበትን ፡ አውጥታ ፡ ታጠልቅና ፤ ሽንጧን ፡ ሰበቅ ፤ ራሷን ፡ ንቅንቅ ፤ ሰውነቷን ፡ ሽኮርኮር ፡ እያደረገችና ፡ በልዩ-ልዩ ፡ ውዝዋዜ ፡ አካልዋን ፡ እየሞከረች ፡ ቅርጽዋን ፡ በትልቁ ፡ መስተዋት ፡ ስትመለከት ፡ በራስዋ ፡ አዲስ ፡ ቁንጅና ፡ ከመደሰትዋ ፡ የተነሣ ፡ በመስትዋት ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ አምሳያዋ ፡ ጋር ፡ ትፈግ ፡ ነበር ። መልኳንም ፡ ትወደው ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ቁንጅናዋ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ ቢሆንም ፡ እንደዚህ፡ ደምቆ ፡ በግዙፍ ፡ ለማየት ፡ ዕድል ፡ አልነበራትም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፤ በቤቱ ፡ አቅራቢያ ፡ ሲያልፉ ፡ የተመለከተቻቸውን ፡ የወይዛዝርት ፡ ዜንጥ ፡ ለመቅዳት ፤ በዚሁ ፡ መከረኛ ፡ መስታወት ፡ አማካይነት ፤ ከወዲያ-ወዲህ ፡ ስትንጐራደድ ፡ የምታሳልፋቸው ፡ ብዙ ፡ ደቂቃዎች ፡ ራስን ፡ የመፈተንና ፡ የማፍቀር ፡ ደስታ ፡ ይሰጡዋት ፡ ነበር ።

ንብረትነቱና ፡ እመቤትነቱ ፡ የራሷ ፡ እንደሆነ ፡ በመሰማት ፡ የቤት ፡ ዕቃዎችን ፡ መጻበስ ፡ መፈተሽና ፡ መመልከት ፡ ደስታን ፡ ይሰጣት ፡ ነበር ። ተጫን ፡ በመጀመሪያዎች ፡ ቀኖች ፡ እንዳስጠናት ፤ ራዲዮኑን ፡ ከፍታ ፡

የጣቢያ ፡ መፈለጊያውን ፡ ስትጠመዝዘው ፡ ብትውል ፡ አይደክማትም ። ከፎቷው ፡ ላይ ፡ መገለባበጥ ፡ የቁም ፡ ሳጥኑን ፡ ልብሶች ፡ ማተራመስ ፡ የፎቶግራፉን ፡ አልቡም ፡ መገላለጥ ፤ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ መደንከር ፤እንዴት ፡ ጥሩ ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያዎች ፡ነበሩ! ነገር፡ግን፡ ይህ ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ ለሁልጊዜ ፡ የሚጸና ፡ አለመሆኑ ፡ ከፋ ፡ ምክንያቱም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተለዋዋጭና ፡ አዳዲስ ፡ ጨዋታ ፡ ከአላገኘ ፡ በተቀር ፡ መሰልቸት ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ ነውና ።

አበባ ፡ ዓመት ፡ በማይሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከአዲሱ ፡ ኑሮዋ ፡ ጋር ፡ በመጠኑ ፡ ስትላመድ ፤ ከአድናቆትና ፡ ከአፍላ ፡ መንፈስ ፡ የተነሣ ፡ ይሰማት ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ እየጠወለገና፡በፈንታው፡የቀድሞ፡ተዝታ፡እያቆበቆበት፡ሄደ።

ውጭ ፡ መውጣት ፡ አላዘወተረችም ። የምትውለው ፡ ከቤት ፡ ዕቃዎች ፡ ጋር ፡ ስትጫወት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደመሰልቸት ፡ ሲላት ፡ ብቸኝነት ፡ ይሰማት ፡ ጀመር ። ጐረቤታ ፡ ሴቶች ፡ አልታጡም ። ሞልተው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የባላገር ፡ ዘርና ፡ የገጠር ፡ ቡቃያ ፡ መሆኗን ፡ በማወቅና ፤ ከሥልጣኔያቸው ፡ ጋር ፡ ለመስተካከል ፡ እንደማትችል ፡ ቆጥረው ፡ በመናቅ ፤ ከሰሸያል ፡ ከበባቸው ፡ ውስጥ ፡ እንድትገባ ፡ የሚፈቅዱ ፡ መስለው ፡ አልታዩም ። እርሷም ፡ ብትሆን ፡ ባልተፈለገችበት ፡ ቦታ ፡ ለመግኘት ፡ መቸስ ፡ ይሉኝታን ፡ ፈሪ ፡ ነች ፡ ያ ፡ መናጢ ፡ አሽከርዋ ፡ እንኳ ፡ ከንቀቱ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ለማነጋገር ፡ ይጀነን ፡ ነበር ።

እንግዲህ ፡ የተመኘችው ፡ ሁሉ ፡ ፍላጐት ፡ ሲሞላላት ፡ ያሰበችው ፡ ደስታ ፡ ግን ፡ ቅዠት ፡ ብቻ ፡ ናሮ ፡

ከእንግድነት ፣ ዕንቅልፍዋ ፣ ስትነቃ ፣ በኖ ፣ የሚጠፋ ፣ መሰለ ።

እንደቀድሞው ፣ ትዳርዋ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ አጋማሹን ፣ የብሞኝነት ፣ ኑሮ ፤ አጣዳፊው ፣ የቤት ፣ ሥራ ፣ ያሳልፍላት ፣ ነበር ። አሁን ፣ ግን ፣ ማንኛውም ፣ ነገር ፣ የሚዘገጀው ፣ በዘመናዊ ፣ ምድጃና ፣ በቤት ፣ አገልጋር ፣ ሲሆን ፣ ከየምግቡ ዓይነት ፣ እየለካከፈ ፣ መጐራረስ ፣ የለመደው ፣ የወጥ ፣ ቤት ፣ ግድቤቱን ፣ እንድትረግጥበት ፣ የማይፈቅድ ፣ ነበር ። ስለዚህ ፣ እጅዋን ፣ አጣምራ ፣ ቁጭ ፣ ብላ ፣ ስትውል ፤ የጉንቱ ፤ የቀድሞው ፣ ትወሳ ፣ እየመጣ ፤ አዲሱን ፣ ኑሮዋን ፣ ያደፈርስባት ፣ ጀመር ። የቡናው ፣ ገበታ ፣ ጨዋታና ፣ ወሬ ፣ ትዝ ፣ አላት ፣ ጐረቤት ፣ ተሰብስቦ ፤ ቁርሱ ፣ እየተቆረጠመ ፣ ቡናው ፤ ከእቦል ፣ እስከበረካ ፣ ሲጠጣ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ወግና ፣ ሥርዓት ፣ ነበረው !!የመንደር ፣ ሴቶችን ፣ የዕረፍት ጊዜን ፣ በደስታ ፣ የሚያሳልፍላቸው ፣ ይሄው ፣ የቡና ፣ ማህበር ፣ ሲሆን ፤ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ ከመጠን ፣ እያለፈ ፣ ቤት ፣ መፍታቱ ፣ አይካድም ። በተጫን ፣ ቤት ፣ ግን ፣ እንኳንስ ፣ መንደረና ፣ ሊታደምበትና ፣ ድጋሚ ፣ አልነበረ ውም ።

ልጅዋን ፣ ፈጽሞ ፣ አልዘነጋችውም ፣ ነበር ። ከመጣች ፣ አንስቶ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ በሕሊናዋ ፣ ውስጥ ፣ ሳይመላለስ ፣ አልቀረም ። ነገር ፣ ግን ፣ ናፍቆቱና ፣ ትዝታው ፣ የተሰማት ፣ አሁን ፤ ነበር ። እንዴት ፣ ይሆን ፣ ዓይኑን ፣ ለማየትና ፣ በእናትነት ፣ ፍቅር ፣ እቅፍ ፣ አድርጋ ፣ ለመሳም ፣ ጓጓች ። ቢሆንም ፣ እንግዲህ ፣ ከልጅዋ ፣ ጋር ፣ ለመገናኘት ፣ መመኘት ፣ የሕልም ፣ እንጀራ ፣ ብቻ ፣ መሆኑን ፣ ሕሊናዋ ስለተገነዘበ ፣ ብርቱ ፣ ትካዜ ፣ መታት ። ለወላጆች ፣ ደስታ

ና ፣ ኩራት ፣ ዋና ፣ አብነት ፣ የሆነው ፤ የሕፃናት ፣ ጨዋታ ፣ ርግጫ ፤ ዝላይ ፣ ሜጫታና ፣ ረብሻ ፣ ከሞንት ፣ ቤትዋ ፣ በራፍ ፣ ተነሥት ፣ በመንፈስ ፣ እየመጣ ፣ ያሳድጓት ፣ ጀመር ። የመጀመርያው ፣ ጊዜ ፣ ፈንጠዝያና ፣ ፍንደቃ ፣ ቀርቶ ፤ ከትዝታ ፣ ጋር ፣ ስትጥመነመን ፣ መዋል ፣ መጣ ። ከፊትዋ ፣ ላይ ፣ የሚነበበው ፣ የትካዜ ፣ መልክ ፤ ቀን-ወደ ቀን ፤ እየጐላ ፣ ይቀረጽ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ችግሩ ፣ በዚህ ፣ ብቻ ፣ ቢወሰን ፣ እንዴት ፣ ቀላል ፣ ነበር ።

ተጫን፣ አበባን፣ ሲአገባ፣ቢቃል፣ ኪዳን፣ ግዳጅ፣ ሳይሆን፣ በፍቅር ፣ ስሜት ፣ ብቻ ፣ መሆኑን ፣ ተመልከተናል ። ተከሊልና ፣ ቁርባን ፣ የሚባሉት ፣ መንፈሳዊ ፣ ደንቦች ፣ አይቀበልም ፣ ነበር ። ሚስቱ ፣ እንዳትወሰልት ፣ ይጠይቃል እንጅ ፤ ራሱም ፣ እንዲሁ ፣ በእንዲት፣ ሴት ፣ መወሰን ፣ እንደሚገባው ፣ አያምንም ። ቢሆንም ፣ የሌሎቹን ፣ ሚስቶች ፣ በሚያባልግበት ፣ ጊዜ ፣ የራሱን ፣ ሕግ ፣ እንኳ ፣ መጣሱን ፣ አዝሮ ፣ አይገነዘበውም ። የሥጋ ፣ ፍላጐቱ ፣ በእንድ ፣ ሴት ፣ ብቻ ፣ የመርካት ፣ አመል ፣ የለበትም ። ስለዚህ ፣ ሚስት ፣ ተብየዋ ፣ ከቤቱ ፣ ተቀምጣም ፣ ቢሆን ያን ፣ መጥፎ ፣ ጠባዩን ፣ ሊተወው ፣ አልቻለም ፤ አልሞከረም ። ምክንያቱም ፣ እንደወንጀል ፣ አይቆጥረውም ፣ ነበርና ። ብዙ ፣ ጊዜ ፤ ከሥራ ፣ እንደወጣ ፣ ወደዚሁ ፣ ተግባር በማምራት ፣ ወደቤቱ ፣ ሳይመጣ ፣ ይውላል ። እንደዚሁም ፣ እስከውድቀት ፣ ሌሊት ፣ የሚያመሽበት ፣ ጊዜ ፣ ነበር። ውጭ ፣ ያደረበት ፣ ጊዜም ፣ አለ ።

ይህ ፣ ልማዱ ፣ አበባን ፣ እምብዛም ፣ አላስከፋትም ። ስለተጫን ፣ ያላት ፣ ፍቅር ፣ ቃጠሎ ፣ ሳይሆን ፤ በኑሮ ፣ ምቾት ፣ ዓላማ ፣ የተወዘተ ፣ ለብታ ፣ ስለነበር ፤ ብዙ ፣

ጊዜ ፣ ሰብዓዊ ፣ ፍጡርን ፣ ሲያሳርርና ፣ ሲያነድ ፣ የሚታየው ፣ የቅናት ፣ ነበልባል ፣ በጣም ፣ አላሰቃያትም ። ቅሬታ ፣ ሳይገባት ፣ አልቀረም ። ነገር ፣ ግን ፣ በሌላ ፣ በኩል ፣ የሚበድላት ፣ ካለሆነ ፣ በተቀር ፤ የብዙ ፣ ወንዶች ፣ ባሕርይ ፣ በሆነው ፤ በዚሁ ፣ ጉድለት ፣ "ቡራ-ከረዩ" በማለት ፣ ከትዳርዋ ፣ ለመፈናቀል ፣ ፍላጐት ፣ የላትም ። ሁሉም ፣ ነገር ፣ ተሟልቶ ፣ ሊገኝ ፣ ስለማይቻል ፣ አንዳንዱን ፣ መሠዋት ፣ ያሻል ። ከዚህ ፣ በተቀር ፣ ተጫን ፤ ባለቤቱን ፣ የሚያስከፋ ፣ ተግባር ፣ ፈጽሞ ፣ አያውቅም ። ነበር ። ስለዚህ ፣ አበባ ፣ በልቧ ፣ ውስጥ ፣ የነበረውን ፣ ትንሽ ፣ የቅናት ፣ ረመጥ ፣ በትግሥት ፣ አመድ ፣ አዳፍና ፣ ለመኖር ፈቃደኛ ፣ ነበረች ።

የሁለተኛው ፣ ትዳርዋ ፣ ግዕዘን ፣ የተዛባው ፤ ሁሉም ፣ ያልተጠነቀቁበት ፣ በድንገተኛ ፣ የውጭ ፣ ግዕበል ፣ ነው ፣ ለማለት ፣ ያስደፍራል ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ፤

አበባ ፤ በአዲሱ ፣ ቤትዋ ፣ ውስጥ ፣ ትካዜ ፣ ይሰማት ፣ የጀመረው ፣ ከሥልጣኔ ፣ ጋር ፣ በመጠኑ ፣ ኩተዋወቀች፣ በኋላ ፣ መሆኑን ፣ እናስታውሳለን ። በአሁኑ ፣ ጊዜ ፣ የገጠር ፣ ሣላዋን ፣ ከሙሉ ፣ በከፊል ፣ አራግፋ ፣ የከተማ ፣ ዘለላ ፣ ማቆብቆብ ፣ ጀምራ ፣ ነበር ። በአደባባይ ፣ ለማስመረቅ ፣ የምታሳፍር ፣ መስላ ፣ አትታይም ። ከዚህ ፣ በፊት ፣ ጥቂት ፣ ቀናች ፣ ያህል ፣ ወደሲኒማ ፣ ቤት ፣ መስደዋት ፣ ኖሮ ፣ በትርኢቱ ፣ ደስ ፣ እየተሰኘች ፣ ተመልሳ ፣ ኑበር ። በዚሁ ፣ አስተያየት ፣ ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ "ከፓርቲ"ችሎት ፣ ፈት ፣ ሊያቀርባት ፣ ሲፈቅድ ፤ መልካም ፣ የፈንጠዝያ ፣

ሰዓቶች ፣ እንደምታሳልፍና ፤ ዘገየም-ፈጠነ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ሳይደርስባት ፣ የማይቀረውን ፣ የትችት ፣ ፈተና ፣ በደህና ፣ እንደምታልፈው ፣ በመተማመን ፣ ነበር ። ዋ-ምነው ፣ በተላለፈ!በቀረ!

ተጫን፣ የተሳሳተው፤ በውጭ፣ አገር፣ ተምረው ፣ከተመለሱትና ፣ በአገር፣ ውስጥም፣ ከፍተኛ፣ ትምህርት ፣(ሁለተኛ ደረጃ)ከጨረሱት ፣ ወይዛዝሪትና፣ ወይዛዝርት፣ ተጋባጮች፣ ጋር ፣ አበባ ፣ ለመወዳደርና ፣ ለመፎካከር ፣ ትችላለች ፣ ሲል ፣ መገመቱ ፣ ነበር ። ገና ፣ ከመግቢያው ፣ መድረክ ፣ ላይ ፣ ቆማ ፣ የፓርቲው ፣ ድምቀት ፣ ሲገርፋት ፣ አመዷ ፣ ቡን ፣ አለ ። እጅ ፣ አነሣሱ ፤ ሰላምታ ፣ አሰጣጡ ፤ አካሄዱና ፣ ፕርስ፣ አፈላለቁ፣ ሁሉ፣ መላ፣ ቅጡ፣ ጠፋት።ከሰዎች፣ ጋር ፣ ለመተዋወቅ ፣ ከወዲያ ፣ ወዲህ ፣ ስትዘዋወር ፣ እግሮቿ ፣ ያደናቅፏዋት ፣ ነበር ። ከሴቶች ፣ ቡድን ፣ በተቀለቀለች ፣ ጊዜ ፣ ከባድ ፣ ፈተና ፣ ገጠማት ። ሆነ ፣ ብለው ፣ የሚነጋገሩት ፣ በእንግሊዝኛ ፣ ወይንም፣በፈረንሳይኛ ፣ ቋንቋ ፣ ነበር ። አማርኛ ፣ የሚያስቸግራቸው ፣ ይመስላል ። አበባ ፣ ዋን ፣ በፈረንጅ ፣ ቋንቋ ፣ ለመጫወት ፣ ዕውቀትዋ ፣ ስለማይፈቅድላት ፣ እንደተደገመበት ፣ ሰይጣን ፣ እኟን ፣ ለጉማና ፤ አገጭዋን ፣ በመዳፍዋ ፣ ደግፋ ፣ ለብቻ ፣ መቀመጥ ፣ ግድ ፣ ሆነባት ። በኩክቴሉ ፣ ግብዣ ፣ አቀራረብ ፣ ላይ ፣ ያሳየችው ፣ ሥነ ፣ ሥርዓትም ፣ በጣም ፣ የተበላሸ ፣ ነበር ።

ከመጀመርያውም ፣ ቢሆን ፣ "——ከባለቤትዎ ፣ ጋር እንዲመጡ ፣ ተጋብዘዋል——"የሚል ፣ የጥሪ ፣ ደብዳቤ የደረሰው ፤ ከገጠር ፣ ሚስት ፣ ይዞ ፣ መምጣቱን ፣ የሰሙ ፣ ተንኰለኞች ፣ ሊዛበቱበት ፣ አስበው ፣ ያደረጉት ፣ ይመስል ነበር ። ከገቡ ፣ አንስቶ ፤ የብዙዎቹ ፣ ተጋባጮች ፣ ዓይን ፣

ያረፈው ፡ በአበባ ፡ ላይ ፡ ነው ። ምስኪን ፡ አበባ ፤ ከድንጋጤና ፡ ከፍርሐት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፤ ሹካው-ማንኪያው ፡ ሲወድቅባት ፤ ጥብሱ ፡ ሥጋ ፡ ልትቆራርጠው ፡ ስትሞክር ፡ እየተፈናጠረ ፡ ሲበርባት ፡ መጠጡ ፡ ሲከነበል ፤ በተለይ ፡ ከወይዛዝርቶች ፡ ዘንድ፡ የሚገለጸው፡ የፈዝ ፡ አስተያየት ፤ ይበልጡን ፡ እያደናገራት ፡ ሄደ ። አንዳንዶቹም ፡ ምግብ፡ ከአፋቸው፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ሳቃቸውን ፡ ለመዋጥ፡ ሲሞክሩ ፡ "ትን-ትን" ያሰኛቸው ፡ ነበር ።

የምትይዘውን ፤ የምትጨብጠውን ፡ የምታደርገውን ፡ አጣች ። ተጫን ፡ አስጠንትዋት ፡ የነበረውን ፡ ሥነ-ሥርዓት ፡ በሙሉ ፡ ዘነጋችው ፡ ሰውነትዋ ፡ በጭንቀት ፡ እየተርበደበደ ፤ ሴቶቹ፡ ሲቆናጠጡባትና፡ ወንዶች፡ ሲጣቀሱባት ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ የግብጣውን ፡ መዓት ፡ በትዕግሥት ፡ ትቀበለው ፡ ነበር ። ጥቂቶቹም ፡ ኀይን ፡ አውጣዎች ፡ የገጠር ፡ ዘየዋን ፡ ለመቅዳትና ፡ አቃቂር ፡ ለማውጣት ፡ በመፈለግ ፡ ሳትወድ ፡ ለማነጋገር ፡ ሲጣደፉ ፡ ከወንዶች ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ እየተመላለሱ ፡ ለዳንስ ፡ የሚጠይቋት ፡ ነበሩ ። አበባ ፤ ከሙዚቃው ፡ ስልት ፡ ጋር ፡ ለመወዛወዝ ፡ በቤት ፡ ትንሽ ፡ ሙከራ ፡ ያያረገች ፡ ቢሆንም ፡ በዚህ ፡ ድንፋታ ፡ ውስጥ ፡ ለመገምገም ፡ የምትችል ፡ አልነበረችም ለይስሙላ ፤ የዳንስ ፡ ግብዣ ፡ የሚጠይቋትን ፡ ፊዘኞች ፡ "አዝናለሁ" ፡ እያለች ፡ መመለሱ ፡ ትዕግሥቷን ፡ ጨረሰባት ። በጥፊ ፡ እያላሰች ፡ ብታባርራቸው ፡ እንዴት ፡ ቁጭትዋ ፡ በወጣላት ፡ ነበር!ነገር ፡ ግንስ ፡ በግብጣ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ ምን ፡ ይደረግ ። በጠቅላላው ፤ ብዙዎቹ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ባጠገብዋ ፡ መተላለፍን ፡ ያዘወትሩ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተጫን ፡ በአሻገር ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በመመልከት ፡ ከንፈሩን ፡ እየነከሰ ፡ ሲናደድ ፤ ይባሰው ፡ በማለት ፡ አንዳንድ ፡ ዕብሪተኞች ፡ ወደርሱ ፡ እየተጠጉ ፡ በልግጫ ፤ "ባለቤትህ ፡ የፓሪቲው ፡ ኮከብ ፡ አልሆነችም ፡ እንዴ!" እያሉ ፡ ትከሻውን ሲጠበጥቡት፡ እየተነሳ፡ ቢተናነቃቸው፡ ባልጠላም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁኔታውን ፡ ማባባስ ፡ እንጅ ፡ ጥቅም ፡ እንደማይሰጥ ፡ በመረዳት ፡ የምሪት ፡ ፈገግታ ፡ እያሳየ ፡ ይሸኛቸው ፡ ነበር ።

በመጨረሻ ፡ ገደማ ፤ የመዓቱና ፡ የጭንቀቱ ፡ ማዕበል ከቀመሰችው ፡ ጥቂት ፡ መጠጥ ፡ ጋር ፡ ራሷን ፡ አዙሮት ፤ ከተቀመጠችበት ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ዘለፍ ፡ ብላ ፡ ወደቀች ፡ የተከተለው ፡ ግርግርና ፡ ረብሻ ፡ እንዲህ ፡ አልነበረም ። ወዲያው ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ እንደቀለበት ፡ ዙርያውን ፡ ከበው ወደታች ፡ ይመለከትዋት ፡ ነበር ። ግማሾቹ ፡ ለማዳነቅ ፡ ያህል ፡ ውሃ ፡ በጠርሙስ ፡ እየያዙ ፡ ሲሯሯጡ ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደመደገፍና ፡ እንደ ፡ ማስታመም ፡ ሲሞክሩ ፤ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ በጓድ-በጓድ ፡ ቁመው ፡ ሲያወካኩ ፤ ከልብ ፡ በመነጨ ፡ የኃዘን ፡ ስሜት ፤ ከንፈራቸውን ፡ የመጠጡላትና ፡ ራሳቸውን ፡ ያነቃነቁላት ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ። እንደገና ፡ ነፍስ ፡ ከዘራች ፡ በኋላ ፡ ተጫን ፡ ደግፎ ፡ ወደመኪናው ፡ ሲወስዳት ፡ የፖርቲው ፡ ስላቅና ፡ ውካታ ፡ እያተመመ ፡ በስተኋላው ፡ ሲከተለው ፡ ይሰማ ፡ ነበር ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ተጫን ፡ እንደብስጭት ፡ አነዳዱ ፡ ምንም ፡ አደጋ ፡ ሳያገኘው ፡ በደኅና ፡ ወደቤቱ ፡ መድረስ ፡ የአምላክ ፡ ጥበቃ፡ ነበር፡ ለማለት፡ ያስደፍራል።

አበባ ፡ "የኔ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ የኔ ፡ የደንቆሮይቱ ፡ ጉድለት ፡ ነው" ስትል ፡ የይቅርታ ፡ ልመናዋን ፡ በልቅሶ ፡ ተንሰቅስቃ ፡ ለመግለጽ ፡ ስትፈቅድ ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡

የአበተዳደግና ፣ የሴትነት ፣ ኩራት ፣ ስሜትዋን ፣ እየገታው
ዕንባዋን ፣በግነት ፣ ‘‘ሰው ፣ በሁለት ፣ እግሩ የሚራመድ ፣
አውሬ ፣ ነው ፣ ከአውሬም ፣ ጨካኝ ፣ ነው ። ለፍጡር ፣
መሰሉ ፣ ኃዘኔታ ፣ የለውም ፣ ፓርቲ ፣ የሚሉት ፣ ስብሰባም ፣
አረመኔ ፣ ሕዝቦች ፣ የሚዶልቱበት ፣ በረት ፣ ነው’’ ፣
በሚል ፣ የዝምታ ፣ ሐሳብ ፣ ጸናች ። ደም ፣ የለበሰው ፣
የተጫን ፣ ፊት ፣ (ቆዳ)በውነቱ ፣ የቱን፣ ያህል ፣ እንዳፈረና ፣
እንደተዋረደ ፣ ያሳይ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ሲጋራውን ፣
እያከታተለ ፣ ከመግማ ፤ ግምባሩን ፣ በእጁ ፣ እያሸ ፣ ጥርሱ
ን ፣ ከግፋጨትና ፣ ከግድግዳው ፣ ጋር ፣ ከመፋጠጥ ፣ በተቀ
ር ፣ ከቶም ፣ ሆነ ፣ በጎ ፣ ቃል ፣ ከንፈሩን ፣ አላለፈም ።

ከወንድ ፣ በኩል ፣ በሥጋዊ ፣ ፍቅርና ፣ ፍላጐት ፤
ከሴት ፣ በኩል ፣ በምኞት ፣ ሐሳብ ፣ ብቻ ፣ በቸኩላ ፣ ተጠር
ዞ ፤ መንፈሳዊ ፣ ሙሻዘር ፣ የጐደለው ፣ የአበባና ፣ የተጫን ፣
ጎብረታዊ ፣ ኑሮ ፤ ከዚች ፣ ቀን ፣ እንስቶ ፤ ሊጠገን ፣ በማይ
ቻል ፣ አኳኋን ፣ እየተሰነጠቀ ፣ ሄደ ።

ከዚህም ፣ በኋላ ፣ ቢሆን ፤ ከአሁን ፣ አሁን ፣ ምናልባት
ሳይሻል ፣ አይቀርም ፣ በማለት ፣ እንደገና ፣ በሁለቱ ፣ ፓርቲ
ዎች ፣ ላይ ፣ ሙከራ ፣ አድርጉ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ የሚያ
ጸናና ፣ ተስፋ ፣ የሚሰጥ ፣ ው ጤት ፣ አልተገኘም ። አበባ ፣
በመጀመርያው ፣ ፓርቲ ፣ ላይ ፣ የቆሰለችው ፣ ውርደት ፤
የፍርሐት ፣ ነቀርሳ ፣ ተክሎባት ፣ አልፎ ፤ ከጥቂት ፣ ሰዎች ፣
መካከል ፣ በተደባለቀች ፣ ጊዜ ፣ እንደልብ ፣ ለመዝናናት ፣
ፍጹም ፣ ድፍረት ፣ አጣች ። ሰውነቷ ፣ ይርበደበድ ፣ ጀመር ።

ዘመናዊው ፣ የተጫን ፣ ሶሽያል ፣ ክበብ ፣ አበባን ፣
እንደዚህ ፣ አድርጉ ፣ በጠና ፣ የተጠናወተበት ፣ በድንቁር
ናዋ ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ ሌላ ፣ ዓይነተኛ ፣ ምክንያት ፣ ነበረው

ተጫን ፣ በጠቅላላው ፤ ስለሔዋን ፣ ወገኖች ፣ የሚመ
ራውን ፣ ፖሊሲ ፣ እናስታውሳለን ። በቁንጅና ፣ ደረጃ ፣
(በርሱ ፣ ግምት)የሚመደቡት ፣ ሴቶች ፣ ሁሉ ፣ ቢጻረሱት ፣
አይጠላም ፣ ነበር ። ሙከራውንም ፣ የሚያጸርጥ ፣ አይመስ
ልም ። ብዙ ፣ የወንድ ፣ ሚስቶች ፣ እባልጓል ፤ የባልጀር
ቹን ፣ የጓደኞቹን ፣ እመኞች ፣ ወዳጆች ፤ ውሽሞችና ፣
ቅምጦች ፣ አላተረፈም ። ስለዚህ ፤ በየደረሰበት ፣ አካባቢ ፣
በሌላ ፣ እንኳ ፣ ባይሆን ፤ በዚህ ፣ ጠባዩ ፣ የተጠላ ፣ የተጠረ
ጠረና ፣ ዘወትር ፣ የማይታመን ፣ ነበር ። ብዙ ፣ ተበዳዮች ፣
ቂም ፣ ይዘውበታል ። በቅናት ፣ መንፈስ ፣ ጠምደው ፣ የያዙ
ት ፣ ብዙዎች ፣ ነበሩ ። ወንዶች ፤ ሚስቶቻቸውንና ፣ ወዳጆ
ቻቸውን ፣ ስለተካፈለባቸው ፣ ሲሆን ፤ ሴቶች ፣ ደግሞ ፣
ለጥቂት ፣ ቀኖች ፣ ያህል ፣ እያባበለ ፣ ከተወዳጀ ፣ በኋላ ፣
እንደሸሚዝ ፣ ወዲያው ፣ ስለሚለዋውጣቸው ፣ ነበር ።
እነዚህ ፣ ሲናደዱና ፣ ሲበሽቁ ፣ የኖሩ ፣ ሰዎች ፣ ሁሉ ፣
የሚበቀሉበትን ፣ ዘዴ ፣ ያገኙ ፣ መስሎ ፣ ተሰማቸው ።
በተጫን ፣ ወንጀልና ፣ ኃጢአት ፣ ምስኪን ፣ አበባ ፣
መሥዋዕት ፣ እንድትሆን ፣ ተፈረደባት ።

‘‘ከክብርት ፣ ባለቤትዎ ፣ ጋር ፣ እንዲመጡ ፣ ተጋብዘ
ዋል——’’የሚለው ፣ የጥሪ ፣ ደብዳቤ ፣ ከዚያም ፣ ከዚያ
ያም ፣ ይጐርፍለት ፣ ጀመር ። ይዝዋት ፣ ሲሄድ ፤ የሴቶች ፣
መላጣና ፣ መዘባበቻ ፣ ሆነች ። እንደዚሁም ፣ አንዳንዶቹ ፣
ወንዶች ፣ የቅናት ፣ ብድራቸውን ፣ ለመመለስ ፣ ሲሉ ፤
ከአበባ ፣ ሰውነት ፣ መጠጋት ፣ መተሻሸትና ፣ በጀርዋ ፣
ማሾክሾክን ፣ ይሞክሩ ፣ ነበር ። ይህ ፣ ሳይሳካላቸው ፣ የቀረ
እንደሆነ የበቀል ፣ ጦራቸውን ፣ በትችት ፣ ደም ፣ ይበከሉት
ነበር ። እንደዚህ ፣ የመሰለውን ፣ የግፍ ፣ ፈተና ፣ ለማለፍ ፤

እንኳንስ ፡ የወጣት፤ የሴት ፡ አቅምና ፤ ብርቱ ፡ ጀግና ፡ ነኝ ፡ ያለውንም ፡ ቢሆን ፡ እንደሚያጠራጥረው ፡ አይካድም ።

ተጫን ፡ ብቻውን ፡ ወደፓርቲው ፡ ሲሄድ "አቶ— ተጫን ፡ ባለቤትዎ ፡ የት ፡ ቀሩ?"

"ባለቤትህን ፡ እኮ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለመተዋወቅ ፡ ይሻሉ!ለምን ፡ አላመጣሃቸውም——?"

"ባለቤትዎ ፡ ከተማውን ፡ ለመዱት ፡ እንዴ!,, የሚሉ ፡ አሽሙሮችና ፡ ጥያቄዎች ፡ ናላውን ፡ ይበጠብጡት ነበር ። በዚሁ ፡ አሽሙርና ፡ ፊዝ ፡ ሰቀቀን ፡ ወደፓርቲ ፡ ከመሔድና ፤ ባልንጀሮቹንም ፡ ወደቤቱ ፡ እየጠራ ፡ ከመጋበዝ ፡ አቋረጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ፡

ተጫን ፡ ፓርቲንና ፡ ግብዣን ፡ በጣም ፡ ይወድና ፡ ያዘወትር ፡ እንደነበርው ፡ መጠን ፡ አሁን ፡ ተካፋይ ፡ ሲሆን ባለመቻሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትካዜ ፡ ገባው ። ልምድ ፡ በቀላሉ ፡ የማይወገድ ፡ ቁራኛ ፡ ነውና ፡ በጣም ፡ አንፈርድ በትም ። ነገር ፡ ግን ፡ በደሉን ፡ ሁሉ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ መጫኑ ፡ አገባብ ፡ አልነበረም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ በርሱና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ መካከል ፡ ጠልቃ ፡ ገብታ ፡ የተደቀንችበት ፡ አበባ ፡ መሆኗ ፡ አይጠረጠርም ። እርስዋን ፡ ባያገባ ፡ ኖሮ ፤ ከሶሺያል ፡ ክበቡ ፡ አይፈናቀልም ፡ ነበር ። ከደመቀው ፡ ዘፍኖ እንዳሻው ፡ ፈንድቆ፡ተጫውቶና ፡ ተዝናንቶ ፡ ለመኖር ፡ የሚያደናቅፈው ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ቢሆንም ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ከመጀመርያው ፡ ማሰብና ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ማሰላሰል ፡ የራሱ ፡ ተግባር ፡ ነበር ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንደሚፈጠር ፡ አበባ ፡ አላወቀችም ። ያመጣት ፡ እርሱ ፡ ለምኖ ፡ ነበር ፡ እንጅ ፡ እርሷ ፡ ጠይቃ ፡ አልተከተለችም ። ሲያባብላትም ፤ ሁለቱ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ሙሉ ፡ በደስታ ፡ እንደሚያሳልፉ ፡ በመስበክ ፡ እንደነበር ፡ ይታወሳል ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የኃዘኑ ፡ ተካፋይ ፡ ነች ። ሰቀቀኑና ፡ ትካዜው ፡ የጋራቸው ፡ ነው ። ተጫን ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ አስተያየት ፡ ጠልቆ ፡ አላመዛዘነውም ። እርስዋን ፡ እንደማጽናናት ፡ ራሱንም ፡ እንደማበረታታት፡ ፈንታ ፡ ብስጭት ፡ ያሸንፈው ፡ ጀመር ።

ሲወጣና ፡ ሲገባ ፡ መናጨትና ፡ መጐማጀት ፡ አመጣ። ከውጭም ፡ በሚደርስበት ጉዳትና ፡ በሕሊናው ፡ ለሚሰማው ፡ ትካዜ ፤ ንዴቱን ፡ የሚያበርደው ፡ በአበባና ፡ በቤት ፡ አሽከሩ ፡ላይ ፡ ሆነ ። በጭቃቅን ፡ ምክንያቶች ፡ ቁጣውን ፡ ያወርደዋል ። ጠባዩ ፡ ተብሰከሰከ ። ከቀን ፡ ወደቀን ፡ እየባሰና ፡ ለአስታማሚ ፡ የማይቻል ፡ እየሆነ ፡ ሄደ ፡ አበባን ፡ በመልካም ፡ ዓይን ፡ ከመመልከት ፡ አቋረጠ ። ለተግሣጽ ፡ ካልሆነ ፡ በተቀር ፤ በወዳጅነት ፡ መንፈስ ፡ መጨዋወት ፡ ቀረ ። ከሥራ ፡ ውሎ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፤ ሬዲዮኑን ፡ ከፍቶ ፡ የውጭ ፡ አገር፡ ወሬዎችን ፡ ያዳምጣል ፡ ወይንም ፡ ወደመጻሕፍቱ ፡ ያቀረቅራል ። የምግብ ፡ ፍላጐቱ ፡ እየተቀነሰ፡ ከመጠጥ ፡ ጋር ፡ መሻረኩን ፡ ቀጠለ ። ውጭ ፡ ማምሸትን ፡ አዘወተረ ። ወደቤቱ ፡ ሳይገባ ፡ የሚያድርባቸው ፡ ሌሊቶች ፡ ተደጋገሙ ። የአበባ ፡ ኑሮም ፡ እንደዚሁ ፡ ነየደነገዘባትና ፡ እየጨለመባት ፡ ሲሄድ ፡ ይታይ ፡ ነበር። በዚህ ፡ አንፃርማ ፡ የቀድሞ ፡ ቤትዋ ፡ ፋሲካ፡ አልነበረም ፡ እንዴ!

ሁለቱን፡ በክፉ ፡ ቀን ፡ ያጋጠመ ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡

እንካንስ ፣ የወጣት፤ የሴት ፣ አቅምና ፤ ብርቱ ፣ ጀግና ፣ ነኝ ፣ ያለውንም ፣ ቢሆን ፣ እንደሚያጠራጥረው ፣ አይካድም ።

ተጫን ፣ ብቻውን ፣ ወደፓርቲው ፣ ሲሄድ "አቶ— ተጫን ፣ ባለቤትዎ ፣ የት ፣ ቀሩ?"

"ባለቤትህን ፣ እኮ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ለመተዋወቅ ፣ ይሻሉ!ለምን ፣ አላመጣሃቸውም——?"

"ባለቤትዎ ፣ ከተማውን ፣ ለመዱት ፣ እንዴ!,, የሚሉ ፣ አሽሙሮችና ፣ ጥያቂዎች ፣ ናላውን ፣ ይበጠብጡት ነበር ። በዚሁ ፣ አሽሙርና ፣ ፊዝ ፣ ሰቀቀን ፣ ወደፓርቲ ፣ ከመሔድና ፤ ባልንጀሮቹንም ፣ ወደቤቱ ፣ እየጠራ ፣ ከመጋ በዝ ፣ አቋረጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ፡

ተጫን ፣ ፓርቲንና ፣ ግብዣን ፣ በጣም ፣ ይወድና ፣ ያዘወትር ፣ እንደነበርው ፣ መጠን ፣ አሁን ፣ ተካፋይ ፣ ሲሆን ባለመቻሉ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ትካዜ ፣ ገባው ። ልምድ ፣ በቀላሉ ፣ የማይወገድ ፣ ቁራኛ ፣ ነውና ፣ በጣም ፣ አንፈርድ በትም ። ነገር ፣ ግን ፣ በደሉን ፣ ሁሉ ፣ አበባ ፣ ላይ ፣ መጫኑ ፣ አገባብ ፣ አልነበረም ። እርግጥ ፣ ነው ፣ በርሱና ፣ በማኅበራዊ ፣ ኑሮው ፣ መካከል ፣ ጠልቃ ፣ ገብታ ፣ የተደቀነችበት ፣ አበባ ፣ መሆኗ ፣ አይጠረጠርም ። እርስዋን ፣ ባያገባ ፣ ኖሮ ፤ ከሶሺያል ፣ ክበቡ ፣ እይፈናቀልም ፣ ነበር ። ከደመቀው ፣ ዘፍኖ እንዳሻው ፣ ፈንድቆ፣ተጫውቶና ፣ ተዝናንቶ ፣ ለመኖር ፣ የሚያደናቅፈው ፣ ነገር ፣ አልነበረም ። ቢሆንም ፣ ይህንን ፣ ሁኔታ ፣ ከመጀመርያው ፣ ማሰብና ፣ የሚያስከትለውን ፣ ውጤት ፣ ማሰላሰል ፣ የራሱ ፣ ተግባር ፣ ነበር ።

እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ችግር ፣ እንደሚፈጠር ፣ አበባ ፣ አላወቀችም ። ያመጣት ፣ እርሱ ፣ ለምኖ ፣ ነበር ፣ እንጅ ፣ እርሷ ፣ ጠይቃ ፣ አልተከተለችም ። ሲያባብላትም ፤ ሁለቱ ፣ ሕይወታቸውን ፣ ሙሉ ፣ በደስታ ፣ እንደሚያሳልፉ ፣ በመስበክ ፣ እንደነበር ፣ ይታወሳል ። አሁንም ፣ ቢሆን ፣ የኃዘኑ ፣ ተካፋይ ፣ ነች ። ሰቀቀኑና ፣ ትካዜው ፣ የጋራቸው ፣ ነው ። ተጫን ፣ ግን ፣ ይህንን ፣ አስተያየት ፣ ጠልቆ ፣ አላመዛዘነውም ። እርስዋን ፣ እንደማጽናኛት ፣ ራሱንም ፣ እንደማበረታታት፣ ፈንታ ፣ ብስጭት ፣ ያሸንፈው ፣ ጀመር ።

ሲወጣና ፣ ሲገባ ፣ መኖጨትና ፣ መጐማጀት ፣ አመጣ። ከውጭም ፣ በሚደርስበት ፣ ጉዳትና ፣ በሕሊናው ፣ ለሚሰማው ፣ ትካዜ ፤ ንዴቱን ፣ የሚያበርደው ፣ በአበባና ፣ በቤት ፣ አሽከሩ ፣ላይ ፣ ሆነ ። በጥቃቅን ፣ ምክንያቶች ፣ ቁጣውን ፣ ያወርደዋል ። ጠባዩ ፣ ተብሰከሰከ ። ከቀን ፣ ወደቀን ፣ እየባሰና ፣ ለአስታማሚ ፣ የማይቻል ፣ እየሆነ ፣ ሄደ ፣ አበባን ፣ በመልካም ፣ዓይን ፣ ከመመልከት ፣ አቋረጠ ። ለተግሣጽ ፣ ካልሆነ ፣ በተቀር ፤ በወዳጅነት ፣ መንፈስ ፣ መጨዋወት ፣ ቀረ ። ከሥራ ፣ ውሎ ፣ በተመለሰ ፣ ጊዜ ፤ ሬዲዮኑን ፣ ከፍቶ ፣ የውጭ ፣ አገር፣ ወሬዎችን ፣ ያዳምጣል ፣ ወይንም ፣ ወደመጻሕፍቱ ፣ ያቀረቅራል ። የምግብ ፣ ፍላጐቱ ፣ እየተቀነሰ ፣ ከመጠጥ ፣ ጋር ፣ መሻረኩን ፣ ቀጠለ ። ውጭ ፣ ማምሸትን ፣ አዘወተረ ። ወደቤቱ ፣ ሳይገባ ፣ የሚያድርባቸው ፣ ሌሊቶች ፣ ተደጋገሙ ። የአበባ ፣ ኑሮም ፣ እንደዚሁ ፣ ነየደነገዘባትና ፣ እየጨለመባት ፣ ሲሄድ ፣ ይታይ ፣ ነበር። በዚህ ፣ አንፃርማ ፣ የቀድሞ ፣ ቤትዋ ፣ ፋሲካ፣ አልነበረም ፣ እንዴ!

ሁለቱን፣ በክፉ ፣ ቀን ፣ ያጋጠመ ፣ መጥፎ ፣ ዕድል ፣

አጣምሮ ፡ በሥቃይ ፡ አለንጋ ፡ ይሸነቁጣቸው ፡ ጀመር ። ግርፋቱ ፡ ከቀን ፡ ወደቀን ፡ ከሰዓት ፡ ወደ ፡ ሰዓት ፡ እየጠነከረባቸው፡ ይሄድ ፡ ነበር በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ተቆራኝተው ፡ የሕይወት ፡ ዘመናቸውን ፡ ለመዝለቅ ፡ ከቶ ፡ ዘበት ፡ መሆኑን ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ሕሊና ፡ የተገነዘበው ፡ ቢሆንም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ፡ ተያይዘው ፡ መንገድገዳቸው ፡ አልቀረም ።

አበባ፡ በምኞት ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ለመቆናጠጥ ፡ ስትሞክር ፡ የሶሺያል ፡ እርካብ ፡ ጠልፎ ፡ በመጣል ፡ ከኃዘን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሲጐትታት ፡ እግሮቿን ፡ ማሰለቀቅ፡ እንዳለባት ፡ አልዘነጋቸውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መድረሻዋ ፡ እንደማያምር ፡ በመፍራት ፡ ተጫን ፡ ውጭ ፡ ብሎ ፡ እስኪያሰናብታት ፡ ድረስ ፡ ተኩራምታ ፡ ለመታገስ ፡ ቆረጠች ። ቢሆንም ፡ የመሰደጃዋ፡ዘመን፡ሩቅ፡ እንደገይሆን፡ ታምን ፡ ነበር ።

ተጫንም ፡ በበኩሉ ፡ በዚሁ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ነበር ። የሕይወቱን ፡ ዘመን ፡ ከግዕበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ገለልተኛ ፡ ለሆነ፡ብቸኝነት፡ ሊሰዋው ፡ ከቶ ፡ አይፈቅድም።

የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ በአበባና ፡ በተጫን ፡ ብቻ ፡ አልተጀመረም ። አልፎ-አልፎ ፡ በቤተሰቦች ፡ ላይ ፡ ሲደርስባቸው ፡ ይታያል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜን ፡ ለትዕግሥት በመሸጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በዘመናት፡ ብዛት ፡ የሚሽርላቸው ፡ ሞልተዋል ። ተጫን ፡ እንደዚህ ፡ እርቆ ፡ አላስተዋለውም ። እርሱ ፡ የተጨነቀበት ፤ የተከታታይ ፡ ቀኖች ፡ ብቻ ፡ መጪለምን ፡ እንጅ ፤ ከዓመት——ከሁለት ፡ ዓመት——በኋላ ፡ ይነጋ ፡ ይሆን?ሲል ፡ አርቶ ፡ አልተመለከተውም፡ ። ምክንያቱም ፡ ዛሬን ፡ ብቻ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ነበርና ። ያምሆኖ ፤ ከአበባ ፡ ጋር ፡ መለያየት ፡ የቀድሞ ፡

ነፃነቱን፡ የሚመልስለት ፡ መሆኑን ፡ ሲያምን ፤ የማሰናበቱ ነገር ፡ አእምሮውን ፡ ያስጨንቀው ፡ ነበር ።

ተጫን ፡ በጠባዩ ፡ የማይመሰገን ፡ ይሁን ፡ እንጅ ፡ ተፈጥሮው ፡ ጨካኝ ፡ አልነበረም ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ የአዘኔታ ፡ ስሜት ፡ አለው ፡ እንዲያውም ፡ ደካማ ፡ መንፈሱ ፡ ደግነት ፡ የተቀላቀለበት ፡ ነው ። ከመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የጽሕፈት ፡ ጠረጴዛ ፡ ከንዱን ፡ አንተርሶ ፡ በመዳፉ ፡ አገጩን ፡ ደግፎ ፡ ጉዳዩን ፡ በሕሊናው፡ ውስጥ ፡ በሚያገለባ ብጥበት ፡ ጊዜ ፡ አበባን ፡ በመጀመርያ ፡ ቀን ፡ ዓይኑን ፡ ሲያሳርፍባት ፡ እንዴት ፡ ችላ ፡ ብላው ፡ እንዳለፈችና ፤ በኋላም ፡ በወይዘሮ ፡ ተጓዳ ፡ ጥረትና፡ ብርታት ፡ እንዴት ፡ ሊያሸንፋት ፡ እንደቻለ ፡ ሊያስታውስ ፤ የሰጣት ፤ ተስፋና ፡ የገባላት ፡ የቃል ፡ ውል ፡ ይመጣበታል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የበደለኛ ፡ ወቀሳ ፡ ሕሊናውን ፡ ሲፈርደው ፡ "በደሀና ፡ ጉጀ ፡ እንደአትምዋ ፡ ከምትኖርበት ፡ ትዳር ፡ በልመና ፡ አፈናቅየ ፡ አምዋቾ ፡ አሁን ፡ እንደገና ፡ ባባርራት ፡ ትልቅ ፡ ግፍ ፡ አይደለምን?" በማለት ፡ ሊፈጽም ፡ የቆረጠውን ፡ ሐሳብ ፡ ያፈራርሰው ፡ ነበር ።

አበባን ፡ ለማሰናበት፡ ካሰበበት፡ቀን፡አንስቶ፡የተጫን ፡ መንፈስ ፡ በተጨማሪ፡ የርኅራሄ፡ ስሜት ፡ ይንጣላታ ፡ ነበር ። የገጹ ፡ መጠውለግ ፤ የአእምሮውን ፡ ትግል ፤ እንግልትና ፡ ሥቃይ ፡ ያሳይ ፡ ነበር ። በሥራው ፡ ላይም ፡ እየደከመ ፡ ሄደ ።

በመጨረሻ——በመጨረሻ ፡ ግዴታ ፡ ሆነ ። አበባ ፡ ከኑሮው ፡ ሸግሎ ፡ እንድትልለት ፡ ተቆረጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ የግርዳቱ ፡ ነገር ፡ ምጥ ፡ ነበር ። ውጭ ፡ በቆየበት ፡ ሰዓት ፡ አሁን ፡ ስሄድ፤ ሁኔታውን ፡ እንድትረዳው ፡ አድርጌ ፡

ውጤት ፡ ተፈጠረበት ። የሁለታችንም ፡ ኑሮ ፡ የትካዜና ፡ የኃዘን ፡ ባሕር፡ ሆነ ። ፍቅርና ፡ ጋብቻ ፡ ለደስታ ፡ እንጅ ፡ ለሥቃይ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋልን?በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በኩል ፡ የደረሰብኝን ፡ መከራ ፡ ታውቂዋለሽ ። የሰው ፡ መዘባበቻና ፡ መሣለቂያ ፡ ሆንኩ”

አበባ ፡ አእምሮዋን ፡ ሁሉ ፡ አንቅታ ፡ በጥሞና ፡ ታዳምጠው ፡ ነበር ። ሲቃ ፡ እንደያዘው ፡ ሰው ፡ ድምጹ ፡ እየተሰባበረ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፤ አበባ ፡ የራስዋን ፡ ሥቃይ ፡ ሁሉ ፡ በመርሳት ፤ ስለተጫን ፡ የተሰማት ፡ ኃዘን ፡ እስከ ፡ አልነበረውም ። በሁለቱም ፡ ላይ ፡ ለደረሰባቸው ፡ መከራ ሁሉ ፡ ራስዋን ፡ ብቻ ፡ በደለኛ ፡ አድርጋ ፡ ቆጠረችው ።

ተጫን ፡ ከሲጋራው ፡ ጢስ ፡ ጋር ፡ ትንሽ ፡ ተንፈስ ፡ አለና ፤ እኔ ፤ ፈከሶሽያል ፡ ክበብ ፡ ወጥቶ ፤ በብቸኝነት ፡ ለመኖር ፡ የምችል ፡ ሰው ፡ አይደለሁም ። የሕይወቴ ፡ ሰዓቶች ፡ በፈንጠዝያና ፡ በጭዋታ ፡ እንዲያልፉ ፡ እወዳለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሁለታችንም ፡ ጋብቻ ፤ ለዚህ፡ ዓላማየ ፡ ዕንቅፋት ፡ እንደሆነብኝ ፡ አትስችውም ፡ ይሆናል ።—— ስለዚህ ፤ የሁለታችንም ፡ ኑሮ ፡ በጨለማ ፡ ከሚዋዥቅ ፡ ተለያይተን ፡ ብንሞክረው፡ የሚከፋ፡ መስሎ፡ አይታየኝም ። እርግጥ ፡ ነው ፤ በደለኛ ፡ መሆኔ ፡ ይሰማኛል ። ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ቅያሜ ፡ ከመጸጠርሽ ፡ በፊት ፤ ሁኔታውን ፡ በልዝብ ታ ፡ ብታመዛዝኝው ፤ ምናልባት ፡ ይቅርታ ፡ ልታደርጊልኝ ፡ ትችይ ፡ ይሆናል ።”

ንግግሩን ፡ እንደፈጸመ ፡ በአረጋገጠች ፡ ጊዜ ፤ አበባ ፡ ቃሏን ፡ አለስልሳ ፤ የእንጉርጉሮ ፡ ዜማ ፡ በተቀላቀለበት ፡ ድምጽ ፤ “ያንተ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ለማለት፡ አያስደፍርም ። የሚሳካ ፡ መስሎህ ፡ ሞክረህ ፡ አትቶሃል ። ምናልባት

ብዙው ፡ የኔ ፡ ጉድለት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። በጠቅላላው ፡ ግን ፡ የተፈጥሮ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ ሐሳብህን ፡ ሰምኑን ፡ አስቢበት ፡ ነበር ። ሌላ ፡ መውጫ ፡ መንገድ ፡ የለንም ። ፍጻሜዬ ፡ ባለግማሩ ፡ ባዝንም ፡ እስግማበታለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ መጠጊያየን ፡ እስከአዘጋጅ ፡ ድረስ ፡ ቀን ፡ እንድትሰጠኝ ፡ እለምንሃለሁ” ፡ አለችው ።

ተጫን ፡ በዚህ ፡ አመላለስዋ ፡ በጣም ፡ ተደሰተ ። እንደዚሁም ፡ ተሳቀቀ ። እንደርሱ ፡ ግምት ፤ በቁጣ ፡ ደንፍታ ፤ “ስለቁንጅናየ ፡ ያደረብህን ፡ የፍላጐት ፡ ታጠሎ ፤ በገላየ ፡ ማገዶነት ፡ ለመማገብ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ልመናና ፡ ጥረት ፡ አሳየህ ። አሁን ፡ ግን ፡ ስሜትህን ፡ ካረካህና ፤ ነበልባሉም ፡ በመሰልቸት ፡ ከበረደልህ ፡ በኋላ ፡ አስፈላጊህ ፡ ሆኘ ፡ አልተገኘሁምና ፡ እንደልብስ ፡ አውልቀህ ፡ ትጥለኛለህ! ያሁሉ ፡ ጉራና ፡ ተስፋ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ኑሮዋልን!——”ስትል ፡ በቮለ ፡ ምላስ ፡ የምትቀበለው ፡ መስሎት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደበትዋ ፡ ልዝብ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፤ በደሉን ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ ስትጥለው ፡ መስማት ፡ አንጀትን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ ነበር ።

ከርስዋ ፡ ጋር ፡ የተያየበትን ፡ ሰዓት ፡ ረገመ ።“በውነቱ ፡ ታላቅ ፡ ግፍ ፡ እንድሠራ ፡ ተገደድሁ ። የንጹሕና፡ የደግ ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ አጉሳቆልኩ ። በአበባ ፡ ምትክ ፡ የምለውጠው ፡ በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ እንደማላገኝ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ——”ሲል ፡ ካሰበ ፡ በኋላ ፤ “እርሱ ፡ ምንም ፡ አይደል ። በችኰላ ፡ እንዲፈጸም ፡ አያሻም ። ቀስ ፡ ብለሽ ፡ ልትፈልጊ ፡ ትችያለሽ ፡ አሳት ።

ከዚች ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ አበባ ፡ ለታ ፡ እስከወጣችበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፤ የሁለቱ ፡ ኅብረታዊ ፡ ኑሮ ፡ እንደባል ፡

ዓይነት ፣ ነበር ። አበባ ፣ ጋብቻቸው ፣ እንደፈረሰ ፣ ካረጋገጠች ፣ በኋላ ፣ ልትጠጋው ፣ አልፈቀደችም ። ተጫንም ፣ በበኩሉ ፣ የሕሊናው ፣ ወቀሳ ፣ ከፊትዋ ፣ እያሸሸው ፤ ቀንም ፣ ሆነ ፣ ሌሊት ፣ ወደቤቱ ፣ የሚገባባቸው ፣ ሰዓቶች ፣ እንደከብረ-በዓል ፣ በጣም ፣ የተወሰኑ ፣ ነበሩ ።

የስንብቱ ፣ ተግባር ፣ የጭንቀት ፣ ማጥ ፣ ነበር ። የመጨረሻ ፣ ሰላምታ ፣ በሚሰጣጡበት ፣ ጊዜ ፤ የተጫን ፣ ሕዋሳቶች ፣ መሪር ፣ በሆነ ፣ የስሜት ፣ ቃንዛ፣ ተቆረጣጠሙ ሰውነቱ ፣ እንደመርበድበድና ፣ እንደመንዘፍዘፍ ፣ ይቃጣው ፣ ነበር ። ዕቃዎችዋን ፣ አስጭና ፤ በመኪናው ፣ መንገድ ከዓይኑ ፣ እስክትሰወር ፣ ድረስ ፣ ከተመለከተ ፣ በኋላ ፤ ወደክፍሉ ፣ ገብቶ ፤ ከከንፈሩ ፣ ላይ ፣ የነበረውን ፣ ሲጋራ ፣ በኃይል ፣ እሽቀነጠረና ፤ ዕንባ ፣ የሌለበት ፣ ልቅሶ ፣ አለቀሰ ፣ አበባ ፣ ግን ፣ ድንገት ፣ ከባሕር ፣ ውስጥ ፣ እንደተጣለ ፣ ዋና ፣ የማያውቅ ፣ ሰው ፤ ያለ ፣ ሁኔታ ፣ ቢገጥማትም ፤ የመሸበር ፤ ወይንም ፣ የድንጋጤና ፣ የፍርሐት ፣ መልክ ፣ አልታየባትም ። መከራውን ፣ ከአምላክ ፣ እንደታዘዘ ፣ ቅጣት ፣ በመቁጠር ፤ በቆራጥነትና ፣ በርጋታ ፣ ለመቀበል ፣ የተዘጋጀች ፣ ትመስል ፣ ነበር ።

"ደህና ፣ ሁን" ፣ ብላ ፣ የተጫንን ፣ እጅ ፣ ስትጨብጥ ፣ በዞደዋ ፣ ቂም ፣ አልያዘችበትም ። እንዲያውም ፣ መልካም ፣ ዕድል ፣ ተመኝታለታለች ። ብቻ ፣ ልቧ ፣ እንደትልቅ ፣ ሸክም ፣ ከብድዋት ፣ ነበር ።

አበባ ፣ ከተጫን ፣ ቤት ፣ ይዛው ፣ የወጣች ፣ ጥሪት ፤ ጌጣ - ጌጥና ፣ ልብስ ፣ በሙሉ ፤ አልጋ ፣ ከነምንጣፉና ፣ ከነልባሱ ፤ ሁለት ፣ ጠረጴዛዎች ፣ ከነወንበሮቻቸው ፤ አንድ ፣ ትንሽ ፣ ራዲዮን ፤ በጠቅላላው ፤ ለአንዲት ፣ ሴት ፣ ቤት ፤

በቂ ፣ የሆነ ፣ ዕቃና ፣ ፎመቶ ፣ ብር ፣ ነበር ። ከዚህ ፣ በተረፈ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ በቆየችባቸው ፣ ወራት ፣ ስለከተማ ፣ ሴቶች ፣ የመስተዳደሪያ ፣ ጉልት ፣ ጉዳይ ፤ አንዳንድ ፣ ጠቃሚ ፣ አንቀጾችን ፤ በወሬና ፣ በዝና ፣ ጫፍ-ጫፉን ፣ ሰምታለች ።

ምዕራፍ ፤ ፤

አበባ ፣ በዚህ ፣ ንብረት ፣ የመጠጥ ፣ ቤት ፣ ከፈተች ። ብታውቅበት ፣ ኖሮ ፤ የሴት ፣ አዳሪነት ፣ ሙያ ፣ ባላጐሳቆለውና ፣ ባላረካከሰው ፣ የወጣትነት ፣ ውበቷ ፤ አፍላ ፣ ገብያ ፣ ልታገኝበት ፣ ትችል ፣ ነበር ። ንግዱ ፣ አልቀዘቀዘም ። ነገር ግን ፣ ማስተናገዱንና፣ መቃበጡን፣ እስክትለምደው ፣ ድረስ ጊዜ ፣ ወስዶባታል ። ወደሴት፣መጠጥ፣ቤት፣ጐራ፣ የሚሉት ፣ ብዙዎቹ ፣ ወጣቶች ፤ የመጠጥ ፣ ፍላጐትን ፣ ለማርካት ፣ ሳይሆን ፤ ለመጫወት ፤ ለመደሰትና ፣ ጊዜን ፣ ለማሳለፍ መሆኑ ፣ ሲታመን ፤ አበባ ፣ ይህንን ፣ ግብ ፣ ለመሙላት ፣ አልቻለችም ። ሰውነቷን ፣ ለጠያቂዎቹ ፣ ሁሉ ፣ ፈቃድ ፣ ለማስገዛት ፣ መንፈስዋ ፣ ከቶ ፣ ሊገራላት ፣ አልቻለም ። የሴት ፣ አዳሪነት ፣ ትዳር ፤ ጥቅሻን ፣ በፈገግታ ፣ መመለስ ፤ ቀልድን ፣ በሳቅ ፣ ማዳነቅ ፤ ውይትን ፣ በጋዘን ፣ መልክ ፣ መቀበልና ፣ ሰበካን ፣ በሽንገላ ፣ መቀባት ፤ የሚጠይቅ ፣ ሙያ ፣ ሲሆን ፤ የኣበባ ፣ የተፈጥሮ ፣ ከፍተኛ ፣ ጠባይ ፤ ለዚህ ፣ ተግባር ፣ ክብሩን ፣ ለማዋረድ ፤ ረጅም ፣ ጊዜ ፣ ጠይቋል ። ለጊዜው ፣ ግን ፣ የሚበገር ፣ መስሎ፣ አልታየም፣ ነበር ።

መልክ-መልካም ፣ በሆኑ ፣ ወጣቶች ፣ ከመጋበዝ ፤ ከመለመን ፣ ከመኳሸም ፤ ወይንም ፣ በስስታም ፣ ዓይን ፣ ከእግር-እስከራስ ፣ ከመገምገም ፤ ሥራውን ፣ ለገረድ ፣ ትታ ፣

በምኽታ ፣ ክፍልዋ ፣ ውስጥ ፣ መደበቅን፣ ፣ ትመርጣለች ። ስለዚህ ፣ የሚገኘው ፣ የንግድ ፣ ገቢ ፣ ዝቅተኛ ፣ ከመሆኑም ፣ በላይ ፣ ከአሽከር ፣ ቅሸሻ ፣ ከኩሊ ፣ ኪራይና ፣ ከቤት ፣ ጣጣ ፣ ወጪ ፣ ተደርሶ ፣ ትራፊው ፣ የዚያን ፣ ያህል ፣ ነበር ። እንዲያውም ፣ ከተቀማጩ ፣ ጥሪት ፣ እየቆነጣጠሩ ፣ ማኻላ ት ፣ ግዴታ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ እምላክ ፣ ይመስገን ፣ ችግሩ ፣ በጣም ፣ አልተሰማትም ። ካለበለዚያስ ፣ በመጀመ ሪያዎቹ ፣ ወራት ፣ ከፍተኛ ፣ ችግር ፣ ገጥሟት ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ እንጉሏ ፣ ተናውጦ ፣ ወፈፌ ፣ ሆና ፣ በቀረች ፣ ነበር ።

አበባ ፣ የመናር ፣ ፍላጐትዋን ፣ ለመጠበቅ ፣ ከፈለገች ዕድልዋ ፣ ከሰጣት ፣ ትዳር ፣ ጋር ፣ ተመሳስላ ፣ መተዳደር ፣ እንደሚገባት ፣ እየተገነዘበችው ፣ ሄደች ። በሴት ፣ አዳሪ ነት ፣ ሙያ ፣ እንዲተዳደሩ ፣ ተገዶ ፣ ከብርን ፣ መሻት ፣ ከንቱና ፣ የማይሰካ ፣ ግብ ፣ መሆኑን ፣ የገንዘቡ ፣ ጣጣ ፣ አስረዳት ። ስለዚህ ፣ በአሁኑ ፣ ጊዜ ፣ ጠቀሜታ ፣ ሊሰጥ ፣ የማይችለውን ፣ መንፈሳዊ ፣ ኩራት ፣ በመጠኑ ፣ እየሞረደ ች ፣ ከአካባቢው ፣ ሁኔታ ፣ ጋር ፣ ታስተካክለው ፣ ጀመር ።

የተጫን ፣ ማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ ክበብ ፣ እንደቆሻሻ ፣ ነገር እየተፋ ፣ ያስወጣት ፣ የነበረውን ፣ ያህል ፣ አዲሱ ፣ አካባቢ ፣ ግን ፣ ወዲያው ፣ የሚቀባበላት ፣ ሆኖ ፣ ተገኘ ። የሴት ፣ አዳሪዎች ፣ ማኅበር ፣ ውስጣዊ ፣ ተንኰል ፣ ይበዛበታል ። የሥራይና ፣ የመድኃኒት ፣ ተግባር ፣ ይዘወትርበታል ። ነገር ፣ ግን ፣ ባይተዋርን ፣ በአላልነት ፣ ለማስተናገድ ፣ ከሌሎቹ ፣ የማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ ክበቦች ፣ የተሻለ ፣ ሳይሆን ፣ አይቀርም ። የቡናው ፣ ማኅበር ፣ በደንብ ፣ ይካሄዳል ። ጨዋታው ፣ የደመቀ ፣ ነው ፤ ወሬው ፣ አያባራም ። ከቤት ፣ ወደቤት ፣ እየተጠራሩ ፤ ለመጠጥና ፣ ለምግብ ፣ ግብግ ፣

በሚሰበሰቡበት ፣ ጊዜ፡ ወዳጅነታቸውና፡ ባልንጀርነታቸው አብሮ ፣ አደግ ፣ ይመስላል ። አበባ ፣ በቀላሉ ፣ እንደአንዱ ፣ ሆነች ። ከመንደሩ ፣ ጋር ፣ ተቀላቀለች ። የመሠሪነት ፣ ጠባ ይ ፣ የሌለባት ፣ ገራም ፣ ስለነበረች ፣ የቅርብ ፣ ወዳጆችና ፣ የጉዳይ ፣ ሚስጢረኞች ፣ ለማትረፍ ፣ ቻለች ። (ቢሆንም ፣ ከሌላ ፣ ዕርዳታን ፣ ሳትጠይቅ፡ ራሷን ፣ በራሷ ፣ ለመጠበቅ ፣ እስከቻለች ፣ ጊዜ ፣ ብቻ ፣ ነበር)በነዚሁ ፣ ጓደኞችዋ ፣ አማካይነት ፣ ብዙ ፣ ነገሮችን ፣ ተማረች ። ጠቃሚ ፣ ሙያ ዎችን ፣ አጠናች ።

እንደመሰሎችዋ ፣ ሁሉ ፤ ፊትዋን ፣ ወላውላ ፤ ጸጉሯን ፣ አሳምራ ፤ ቅርጽዋን ፣ አስተካክላና ፣ ሁለመንተናዋን ፣ አቆንጅታ ፣ ወደጢያሳ ፣ ወጣ ፣ ማለት ፣ ለመደች ። ይህ ፣ ጉዞ ፣ በስሙ ፣ ሽርሽር ፣ ነው ፣ ይባላል ፣ ነገር ፣ ግን ፣ አይደለም ። አንዳንዶቹ ፣ ሠርክ ፣ ወደማታ ፣ ሲፈጅሙት ፣ ይታያል ። ሌሎቹም ፣ ቅዳሜና ፣ እሁድ ፣ አያስታጉሉትም ፣ በብዙዎቹ ፣ ሴት ፣ አዳሪዎች ፣ ዘንድ ፣ ዋና ፣ ዕለታዊ ፣ ተግባ ር ፣ ሆኖ ፣ የሚቆጠር ፣ ነው ። የሚስጢር ፣ ስሙ ፣ ግን ፣ ድለላ ፣ ,,ይባላል ። እንግዲህ ፣ የዚህ ፣ ሽርሽር ፣ ዓይነተኛ ፣ ግቡ ፤ የውጭ ፣ ዓየርን ፣ ለመቀበል ፤ ወይንም ፣ ሰውነት ን ፣ በእንቅስቃሴ ፣ ለማፍታት ፣ ሳይሆን ፤ ቁንጅናን ፣ (መጥፎም ፣ ሆነ፡ ደግ፡ እንደ የደረጃውና ፣ እንደአቀራረቡ) በአደባባይ ፣ መካከል ፣ እያስመረቁ ፤ የወንድን ፣ ፍላጐታ ፣ ዊ ፣ ስሜት ፣ አነሳስቶ ፤ እስከቤት ፣ ድረስ ፣ ሱክ-ሱክ ፣ እያለ ፣ እንዲከተል ፣ ለማድረግ ፣ መሆኑ ፣ አይካድም ።

አበባ ፤ ዘወትር ፣ እንኳ ፣ ባይሆን ፤ አንዳንድ ፣ ቀን ፣ ለድለላ ፣ እንድትወጣ ፤ የገንዘብ ፣ ፓርሳዋ ፣ ያስገድዳት ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ነውርን ፣ እየጠበቀች ፣ ነው ። ሰው ፣ ምን

ይለኛልን ፣ አትዘነጋም ። ኃፍረትዋን ፣ ሽጣ ፣ አልበላችም ፣ ነበር ። ለምሳሌ ፤ ስትራመድ ፣ ዳሌዋን ፣ ሆነ ፣ ብላ ፣ አታወዛውዝም ። ወገቧን ፣ አትሰብቅም ። አንገትዋን ። አትነቀንቅም ፤ ዓይንዋን ፣ አታቀብዘብዝም ፤ ወይንም ፣ አታስመነምንም ። እንደሲኒማ ፣ አርቲስቶች ፣ ቅጅ ፣ ልሁን አትልም ። በጣም ፣ ጉልህ ፣ በሆነ ፣ አስተያየት ፣ ሰውን ፣ ለመማረክ ፣ አትፈቅድም ። አንዳንድ ፣ ጐረምሳ ፣ በተከተላ ት ፣ ጊዜም ፤ በመጋበዝና ፣ በማበረታታት ፣ አስተያየት ፤ እየተገላመጠችና ፣ ወደኋላ ፣ ቀረት ፣ ሲል ፣ እየጠበቀች ፣ ወደቤትዋ ፣ ለመምራት ፣ በፍጹም ፣ አትሞክረውም ።የእን ጀራ ፣ ማዳጅ ፣ ሆናባት ፣ ነው ፣ እንጅ ፣ የሚከተላትን ፣ ጉልማሳ ፣ ሁሉ ፣ እያዋረደች ፣ ብትመልሰው ፣ አትጠላም ። ሌላው ፣ ቀርቶ ፣ ኩታ፣ሳትደርብ፣ መውጣትን ፣ አትወድም ፣ ነበር ።

የወንድ ፣ ጥላ ፣ ሲያርፍባት ፣ ይቀፋታል ። እንኳንስ ፣ ነክተዋትና ፣ ሲጠጉዋትም ፣ ቢሆን ፣ መንፈሷ ፣ ይሸከፍ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ አታላይ ፣ አልነበረችም ። ‘‘ወደድኩህ ፣ ሞትኩልህ!’’እያለች ፣ መሸንገልን ፣ አታውቅበትም ፣ ነበር ። ያለ ፣ አግባብ ፣ የሰው ፣ ገንዘብን ፣ ለመውሰድ ፣ አትዳፈርም ።

ያም ፣ ሆኖ ፤ ከዘመናዊው፣ የሴት፣ አዳሪነት ፣ ፖሊሲ ፣ ጋር ፣ የማይጋጠመው ፣ ይህ ፣ ጠባይዋ ፣ በጣም ፣ አልጉ ዳትም ። ከቅሬዎች ፣ ይልቅ ፣ ተሽከርማሚዎችን ፣ የሚመርጡ ፤ ከትብጢ ፣ ይልቅ ፣ አንገተ ፣ ሰባራን ፣ የሚፈልጉ ፣ አንዳንድ ፣ ወንዶች ፣ ይጐበኙዋት ፣ ነበር ። ከጥቂቶች ፣ በተቀር ፣ ብዙዎቹ ፣ ይለግሱላታል ። የወንድ ፣ መወደድ ፣ ነበራት ።

በጠቅላላው ፤ ገብያው ፣ በጣም ፣ የቀዘቀዘ ፣ ነበር ፣ ለግለት ፣ አያስደፍርም ። እርሷ ፣ ነቃ-ነቃ ፣ ስትልበት ፣ እየተሻለው ፣ ይሄድ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ የገንዘቡ ፣ ጣጣ ፣ ከልኩ ፣ አልፎ ፣ እያውቅም ። ወጭው ፣ በዚያው ፣ መጠን፣ ነበር ። ‘‘ለክሬም’’ይባላል ፣ ‘‘ፓውደር’’ ፣ ይከተላል ። የሰውነትና ፣ የጸጉር ፣ ቅባት ፣ ያስፈልጋል ። ሽቶው ፣ የማይቀር ፣ ነው ። ጸጉሩ ፣ መተኰስ ፣ አለበት ። ቡና ው ፣ ቢያንስ ፣ ሦስት ፣ ጊዜ ፣ ይፈላል ። ዕጣኑ ፣ አስር ፣ ጊዜ ፣ ይጨሳል ። እንደጐረቤቶቿ ፣ መምሰል ፣ ካለባትማ ፣ ስንቱ ፣ ተቆጥሮ!ሚማውና ፣ ልብሱ ፣ በየወሩ ፣ እንዲተካ ፣ የውድድር ፣ አስፈላጊ ፣ ነው ። የተላላኪ ፤ የጠራጊ ፣ የኩሊ ፣ ደሞዝ ፣ አለ ። የምግቡ ፣ ነገር ፣ ግዴታ ፣ ነው ። ለዚህና ፤ ለቀረውም ፣ ለስንቱ ፣ መቶ ፣ ወጭ ፣ ባከኖ ፣ የሚተርፈው ን ፣ መከረኛው ፣ የቤት ፣ ኪራይ ፣ ሙጥኖ ፣ አድርጉ ፣ ይጠርገዋል ። በዚሁ ፣ ላይ ፣ ገቢው ፤ የማያስተማምንና ፣ እንደጊዜው ፣ ሁናቴ ፣ ተለዋዋጭ ፣ ነው ።

ምዕራፍ ፣ ፲፩ ፣

በባል ፣ አስተዳደርና ፣ ኃላፊነት ፣ ሥር ፣ ሆኗ ፣ የሰጡዋትን ፣ አዘጋጅታ ፣ ማቅረብና ፤ በጐደለ ፣ ‘‘ይህ ፣ ያስፈልገኛል’’ስትል ፣ ችግርዋን ፣ በባለቤቷ ፣ ትከሻ ፣ ላይ ፣ ጭና ፣ መኖር ፣ የለመደችው ፣ አበባ ፣ ‘‘ነገ’’ ፣ ሁልጊዜ ፣ ጨለማ ፣ እየሆነ ፣ ይታያት ፣ ነበር ። ዛሬን ፣ እንደምንም ፣ አሳለፈች ፣ ነገስ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ቀን ፣ ይሆን ? በአን ድ ፣ ዓይነት ፣ መሰናክል ፣ ወይንም ፣ ተንኰል ፣ ገብያው ፣ ቢዘጋስ ? ታማ ፣ ብትተኛስ ? መጠባበቂያ ፣ ተቀማጭ ፣ ገንዘብ ፣ የላትም ፣ ምን ፣ ይበጃት ፣ ይሆን?እነዚህን ፣ ጥያቄዎች ፣ ሰታሰላስል ፣ የሚያጽናናት ፣ መልስ ፣ አታገኝ

ም ፣ ነበር ። የምታዋየው ፤ የሚረዳትና ፣ አይዞሽ ፣ አለሁል ሽ ፣ የሚላት ፣ ሁነኛ ፣ ዘመድና ፣ ጥብቅ ፣ ወዳጅ ፣ በአቅራቢ ያው ፣ የለም ። ይህ ፣ በቋፍ ፣ የቆመና ፤ ከቀን-ወደቀን ፣ ይብስ ፣ ይሆናል ፣ እንጅ ፣ ይሻላል ፣ የማይባል ፣ ተስፋ-ቢስ ፣ ኑሮ ፤ አበባን ፣ ያጠራጥራትና ፣ ያስጨንቃት ፣ ነበር ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ሁኔታውን ፣ ፣ በጥልቅ ፣ ስታስበው ፤ አእምሮዋ ፣ ይታወክ ፣ ነበር ። ራሷንም ፣ እስከመጥላትና ፣ እስከመጸየፍ ፣ ትደርሳለች ። ከሙያው ፣ ነውረኛነት ፣ ይልቅ ፤ የአላፊ-አግዳሚውን ፣ ዓይንና ፣ እጅ ፣ ተጠባብቆ ፣ መኖርን፣አበባን ፣ ያንገፈግፋት ፣ ነበር ።

ይህን ፣ የሐሳብ ፣ ጭንቀትና ፣ ውዝዋዜ ፣ በመጠኑ ፣ የሚያሽልላት ፣ ፈውስ ፣ መጠጥ ፣ ነበር ። ጐረቤቶጀ ፣ የሰጡዋት ፣ ጠቃሚ ፣ ምክርና ፣ ያስተማሩዋት ፣ ልምድም ፣ ይሄው ፣ ነው ።

አበባ ፤ ዊስኪውን ፤ ኩኛኩን ፤ አኒሹን ፤ ስቶኩን ፤ ቪርኖውን ፣ ቢራውን—የተገኘውን ፣ ትከለትው- ትከለትውና ፤ ሰውነቷ ፣ ሞቅ ፣ ሲል ፣ ብስጭቱ ፣ ይሻላታል ። ትካዜዋም ፣ ይቀልላታል ። ወይንም ፣ መጠጡ ፣ በዝቶ ፤ አእምሮዋ ፣ በስካር ፣ ደብዝብዝ ፣ ያለ ፣ እንደሆነ ፤ መከራውንና ፣ ችግሩን ፣ በጭራሽ ፣ ትረሳው ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ከስካር ፣ ሲነቁ ፣ እንደገና ፣ መታወሱ ፣ የማይቀር ፣ ስለሆነ ፣ መጠጡ ፣ መከታተል ፣ ያስፈልገዋል ።

መጠጡ ፣ በጨዋታ ፣ እየተጣፈጠ ፣ በሲጋራ ፣ ሲማግ ፣ (በእሁኑ ፣ ጊዜ ፣ ማጤስ፣ ለምዳለች) ፣ ትንሽ ፣ የደስታ ፣ ትኩሳት፣ ይሰማት ፣ ነበር ። ስለዚህ ፤ ከሌላው ፣ እንኳ ፣ ባ ይሆን ፣ ከምግቡ ፣ ወጭ ፣ እየቀነሱ ፣ የአልኩሱን ፣ ጠርሙዝ ፤መሙላት ፣ አስፈላጊ ፣ ነበር ።

የአበባ ፣ ዕድሜ ፣ በዚሁ ፣ ሁኔታ ፣ ተገፋ ። ዓመት ፣ ሁለት ፣ ——ሦስት——አራት——አምስት ። የወጣትነት ፣ ዘመንዋ ፣ ተገባደደ ፤ ሰውነቷ ፣ በረደ ። ብርቱካን ፣ ይመስሉ ፣ የነበሩት ፣ ጉንጮችዋ ፤ ደማቸው ፣ ተመጠ ፤ በፓውደርና ፣ በክሬም ፣ ብዛት ፣ ወዛቸው ፣ ጠፍተዋል ። ገርጥተዋል ። አልፎ ፣ አልፎ ፣ እንደማዲያት ፣ የመሰለ ፣ ጥቋቁር ፣ ነጥብ ፣ ተንጠባጥቦባቸው ፣ ይታያል ። ዓይኖጀ ፣ በጥላት ፣ ኩል ፣ ተብላሽተዋል ። ወደውስጥ ፣ ተሰርጉደው ፣ ገብተው ፣ ነበር ። ጥራታቸውም ፣ ደፍርስዋል ። ቅንድቦችዋ ፣ ተነቃቅለዋል ። ያ ፣ ጸጉር-ያዘማ ፣ ጸጉር ፣ በኮሬንቲ ፣ ካውያ ፣ ሳስቶ ፣ ነበር ። በብስጭት ፣ ምክንያት ፣ ይሁንም ፣ እንጃ ፣ አንዳንድ ፣ ነጮች ፣ (ሽበቶች)ተፈናጥቀውበታል ። ከንፈሮጀ ፣ በሲጋራ ፣ ቅርጣን ፣ መብለዝ ፣ ጀምረው ፣ ነበር ። ጥርሶችዋም ፣ የጥንት ፣ ፍልቃታቸው ፣ ጠፍተዋል ። የትንፋሽዋ ፣ መዓዛ ፣ እንኳ ፣ በመስቲካ ፣ እንኳ ፣ ካልተጣፈጠ ፣ በተቀር ፣ የተባላሸ ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። ገላዋ ፣ በአልኮል ፣ ቃጠሎ ፣ ደርቆዋል ።

ጠዋት ፤ ሳትወላወልና ፣ ሳትቀባባ ፤ ፊትዋን ፣ በመስታወት ፣ ስተመለከተው ፤ በመጀመርያ ፣ ከተሜን ፣ ቤት ፣ በትልቁ ፣ መስታወት ፣ ውስጥ ፣ ካየችው ፣ ውበት ፣ ጋር ፣ በማነፃፀር፣ፈያቺ ፣ የጥንቲቱ ፣ አበባ ፣ ነኝን፣አይደለሁም ፣ ያች ፣ አበባ ፣ ሞታ ፣ ተቀብራለች ። አሁን ፣ እኔ ፣ ከክብር ፣ ከብር ፣ የሌለው ፤ የሚንቀሳቀስ ፣ በድንና ፣ የንግድ ፣ ዕቃ ፣ ግለት ፣ ነኝ ። የምናረው ፣ ሰውነቴን ፣ እየሸጥኩ ፣ በመብላት ፣ ነው ። ከዚህ ፣ የበለጠ ፣ ግምት ፣ የሚሰጠኝ ፣ ለው ፣ የለም ። ወይኔ ፣ ወይኔ» ፣ እያለች ፣ ራሷን ፣ በጸጸት፣ ታወዛውዝ ፣ ነበር ። ቢሆንም ፣ ይህንን ፣ ኑሮ ፣ እርግፍ፣አድርጋ ፣ በመተው ፣ ለመመነን ፣ አልቆረጠችም ።

አበባ ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ በምትገኝበት ፡ ዘመን ፤ አንድ ፡ ወጣት ፡ ጐልማሳ ፤ በኑሮዋ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ ገብቶ ፤ ጨለማ ፡ ሕይወትዋን ፡ ለጥቂት ፡ ወራት ፡ ያህል ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ ፈንጥቆበት ፡ ነበር ። የተዋወቁት ፡ በተለመደው ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ነው ። ብቻ ፡ አቀራረቡ ፡ ከሌሎቹ ፡ የተለየ ፡ ነበር ።

በመጀመሪያ ፡ ቀን ፡ መለኪያ ፡ ኩኾክ ፡ ይዞ ፡ በቤት ዋ ፡ ውስጥ ፡ ሲቀመጥ ፡ እንደብዙዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ ዜንጥና ፡ ጉራ ፡ አላሳየም ። አበባንም ፡ እንደሺያጭ ፡ ዕቃ ፡ አልተመ ለከታትም ። ራሱን ፡ አቀርቅሮ ፡ እንደማፈር ፡ ሲቃጣው ፤ ከሴት ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ የመጀመርያው ፡ ጊዜ ፡ እንደሆ ነ ፡ ያስገምት ፡ ነበር ። አንዳንዶቹ ፡ ወንዶች ፤ ገብተው ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ የሚያሳዩትን ፡ ቁንጥ ፤ የሚፈጽሙትን ፡ ብልግና ፡ ፈቱን ፡ በማጥቆር ፡ ሲመለከት ፡ የነቀፈው ፡ ይመስላል ። አበባንም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ሲመለከታት ፡ ኃዘኔታ በተቀላቀለበት ፡ መልክ ፡ ነው ። ለሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ የጠየቃ ት ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ ደጅ ፡ ጥናትና ፡ ምልልስ ፡ በኋላ ፡ ነበር ። ይሄውንም ፡ ጥየቃ ፡ ሲያቀርብላት ፤ በደንበኛው ፡ የትሕ ትና ፡ አንደበት ፡ ሲሆን ፤ ስለተዳፈራት ፡ ይቅርታን ፡ እየለመነ ፡ ነበር ።

ሰውነቷን ፡ ገንዘብ ፡ እንደከፈለበት ፡ ነገር ፡ አድርጐ ፡ አልቆጠረውም ። ለሰበአዊ ፡ ገላዋ ፡ ተገቢውን ፡ ጥንቃቄና ፡ አክብሮት ፡ ይፈጽም ፡ ነበር ። ሥጋዊ ፡ ፍላጐቱ ፡ የሰሰት ፡ ባሕርይ ፡ አልነበረበትም ።

አንደበቱ ፡ ጠፈፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ንግግር ፡ ያውቃል ። ጨዋታው ፡ ቀልድ ፡ የሞላበትና ፡ የሚያስደስት ፡ ሲሆን ፡

ከብልግና ፡ ቃላት ፡ የነጣ ፡ ነው ። እንደብዙዎቹ ፡ ራሱን ፡ ከፍ-ከፍ ፡ በማድረግ ፡ እያሞጋገሰ ፡ አያወራም ። አበባን ፡ በሚወድስበት ፡ ጊዜም ፤ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ሽንገላ ፡ እንዳይመስልበት ፡ እየቆጠበና ፡ እየገመተ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ወጣት ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅ ፡ ዕድል ፡ የገጠመው ፡ ማንኛ ውም ፡ ሰው ፤ ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ጭውውት ፡ በኋላ ፤ የሚሰጠው ፡ ግምት ፤ አስተዋይ ፡ ብልሀና ፡ ደግ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። ስሙ ፡ ይላቅ ፡ ይባላል ።

ይህ ፡ ወጣት ፤ ወደ ፡ አበባ ፡ ቤት ፡ መምጣትን ፡ አዘወተረ ። አበባ ፤ ከመጀመርያው ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፤ ከሌሎ ቹ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አግኝታው ፡ ስለነበር ፡ መመላለሱን ፡ እምብዛም ፡ አልጠላችም ። እንዲያውም ፡ ወደመውደዱ ፡ ሳይቃጣት ፡ አልቀረም ። ወጣቱም ፡ ጠጋ ጠጋ ፡ ያላት ፡ ይህንን ፡ ስሜትዋን ፡ በመረዳት ፡ ይሆን-ይሆናል ።

እየተለማመዱ ፡ ሄዱ ። ወዳጅነታቸው ፡ ጠበቀና ፡ ስለፍቅር ፡ ያወሩ ፡ ጀመር ። አበባ ፡ በሴት ፡ አዳሪነት ፡ ሙ ያ ፡ መስተዳደር ፡ ከጀመረችበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፤ በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ወንዶች ፡ ፈቃድ ፡ የሞላች ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፤ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ የወዳጅነት ፡ ዝንባሌ ፡ ሲያድርባት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የተሰማትን ፡ ፍቅር ፡ ቢጤ ፤ በአቀራረብም ፡ ሆነ ፡ በቃል ፡ ከመግለጽ ፡ አልሸሸገችም ። እርሱም ፤ ጓደኞቹ ፡ "ፍቅር ፡ ያዘን" ሲሉት ፡ ይዛበትባቸው ፡ እንደነበርና ፤ አሁን ፡ ግን ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑን ፡ ሲነግራት ፤ ከልቡ ፡ የመነጨ ፡ እየመሰላት ፡ ትቀበለው ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ በመግ ባባት ፡ መንፈስ ፡ ይሳሳቁና ፤ ዕቅፍቅፍ ፡ ብለው ፡ ይሳሳማሉ ።

አበባ ፤ በራቱዋን ፣ በውስጥ ፣ እየሸጉረች ፣ ከአዲሱ ፣ ፍቅረኛዋ ፣ ጋር ፣ ስትጫወት ፣ መዋል ፣ ማምሸትና ፣ ማደር ፣ ደስታን ፣ ይሰጣት ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ይላቅ ፣ በገንዘብ ፣ በኩል ፣ እጁ ፣ ያጥራል ። ቢሆንም ፣ በጣም ፣ ካልቸገራት ፣ በተቀር ፣ ልታስከፋው ፣ አትሻም ። አንድ ፣ ቀን ፤ ፈራ-ተባ ፣ ስትል ፣ ነገሩን ፣ አነሣችለትና ፤ ይላቅ ፣ በዚያ ፣ ልዝብ ፣ አንደበቱ ፤ "ይህንን ፣ ጉዳይ ፣ ካንቺ ፣ በፊት ፣ እኔው ፣ ሳላስብበት ፣ አልቀረሁም ። ችግርሽን ፣ የማልገነዘበው ፣ ይመስልሻልን?እንግዲያውስ ፣ ነገሩን ፣ ካነሳሽው ፤ ሐሳቤን ፣ ለመግለጽ ፣ ከአሁን ፣ የተመቸ ፣ ጊዜ ፣ አላገኝም ። በመጀመሪያ ፣ ካየሁሽ ፣ ምሽት ፣ እንስቶ ፤ ይህ ፣ ሙያ ፣ የሚስማማሽ ፣ ዓይነት ፣ እንዳይደለሽ ፣ ለመገመት ፣ ችየ ፣ ነበር ። በቅርቡ ፣ ለመተዋወቅ ፣ ከበቃን ፣ ወዲህ ፣ ደግሞ ፣ ይህንኑ ፣ ዕምነቴን ፣ አረጋግጫለሁ ። አንቺ ፣ የትዳር ፣ ሴት ፣ እንጅ ፣ የሌላ ፣ አይደለሽም ። እንደግፈቅርሽም ፣ ታውቂያለሽና ፣ መልካም ፣ ፈቃድሽ ፣ ቢሆን ፣ እንጋባ ፤ ሚስቴና ፣ እመቤቴ ፣ ሆነሽ ፣ ተቀመጭ ። አሁን ፣ በገንዘብ ፣ በኩል ፣ ልረዳሽ ፣ ያልቻልኩት ፤ አንቺን ፣ ከመጠየቄ ፣ (በጋብቻ) በፊት ፣ በቤት ፣ ዕቃና ፣ መሰናዶ ፣ በኩል ፣ ያለውን ፣ ዝግጅት ፣ በማከናወን ፣ ላይ ፣ ስለአለሁ ፣ ነው ። ፍቅሬ ፤ እምቢ ፣ እንደማትይኝና ፤ እንደግታስከፈኝ ፣ ተስፋ ፣ አደርጋለሁ ፣ ,,አላት ።

"በሞቴ ፣ እንጋባ" "ሚስት፣ የማገባ ፣ ከሆነ ፣ ካላንቺ ፣ ሌላ ፣ አላገባም" የሚል ፣ የቀልድም ፣ ሆነ ፣ የፈዝ ፣ ንግግር ፤ ካሁን ፣ ቀደም ፣ ብዙ ፣ ወጣቶችና ፣ ጐረምሶች ፣ የቀባጠሩላት ፣ ሲሆን ፤ ከይላቅ ፣ አንደበት ፣ ሲወጣ ፤ የውተኛነት ፣ ጣዕምና ፣ ልዩ ፣ መዓዛ ፣ ነበረው ። ወይ ፣

እምቢታ ! ታዲያ፣ ከዚህ ፣ ኖሮ፣ የሚደነላግል፣ ሲገኝ፣ ዓይን፣ ማሸት ፣ ይገባል ፣ እንዴ!ከሰማይ ፣ የወረደ ፣ የምሕረት ፣ ስጦታ ፣ ነው ። አበባ ፤ ደስታዋንና ፣ ምስጋናዋን ፣ በቃላት ፣ ልትገልጽለት ፣ ስላልቻለች ፤ ፊትዋ ፣ በውስታ ፣ እየፈገገ ፤ ወገቡን ፣ ጥምጥም ፣ አድርጋ ፣ በክንፈርዋ ፣ መለሰችለት ። ሰውነትዋ ፣ በተስፋ ፣ እየፈካና ፣ እየሞላ ፣ ሄደ ።

ወሬውን ፣ ለመንደረኛው ፣ ሁሉ ፣ አዳረሰችው ፤ አንዳንድ ፣ ባልንጀሮችዋ ፣ "አንቺ ፣ እንዳያሞኝሽ" ፣ ሲሉ ፣ ለሚያቀር ቡላት ፣ የማስጠንቀቂያ ፣ ምክር ፣ "ማን ? ይላቅ ፣ ሰው ! አታውቁም" ፣ በማለት ፣ ትመልስላቸውና ፤ በልቧ ፣ የቅና ት ፣ ወሬ ፣ ነው"ስትል ፣ ታማቸው ፣ ነበር ።

አበባና ፣ ይላቅ ፣ ስለትዳራቸው፣ በሰፈው፣ ይጫወቱና ይማከሩ ፣ ነበር ። የቤት ፣ ዕቃ ፣ ዓይነትና ፣ የአቀማመጥ፣ ድር ጅት ፣ ምርጫቸው ፣ ተመሳሳይ ፣ ሆኖ ፣ ስላገኙት ፣ በማባ ባት ፣ ይደሰታሉ ፤ ቀኑን ፣ ሙሉ ፣ ከአልጋ-ላይ ፣ ተጋድመ ው ፤ የባሙን-የቆጡን፣ ሲቀባጥሩ፣ የሚውሉበት፣ ጊዜ፣ አለ። ይላቅ ፣ ከአበባ ፣ ጋር ፣ የሚያሳልፈው ፣ ሰዓት ፣ ሲገመት ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ እንደሚገባ ፣ ለመረዳት ፣ ያስቸግራል ። ሥራ ፣ ይኑረው ፤ ወይንም ፣ አይኑረው ፣ አላረጋገጠችም ። እንዳለው ፣ ግን ፣ ነግሮዋት ፣ ነበር ። የይላቅ ፣ ዝግጅት፣ተጉተተ ። "ይህ ፣ ጉድሉኝ፣ ነው ፤ "እንድ ፣ የምፈጽመው፣ መሰናዶ ፣ ይቀረኛል ፣ "ካሳምንት በኋላ ፤ ከዚህ ፣ ነውረኛ ፣ ሥፍራ ፣ ልትለቂ ፣ ነው! "እያለ ፣ ቀጠሮውን ፣ ይቀጣጥል ፣ ነበር ። ቢሆንም ፤ እንዳችም ፣ ጥርጣሬ ፣ በሆድዋ ፣ አልገባም ።

የወር ፣ እንግዳዋ ፣ በተወሰነው ፣ ጊዜ ፣ ሳይጐበኛት ፣ ቀረ ። ወዲያው ፣ ጢት-ጢት ፣ ያማትና ፣ ያስታውካት ፣

ጀመር ። አበባ ፤ የደስታ ፣ ጥርጣሬ ፣ ያዛትና ፣ ለማረጋገጥ ፣ ያህል ፤ ወደሐኪም ፣ ዘንድ ፣ ሄዳ ፣ ተመረመረች ፤ ሐኪሙ ፤ “በማኅጸንዎ ፣ ውስጥ ፣ ጽንስ ፣ ይዘዋል ፡” ሲል ፣ በመሰከረላት ፣ ጊዜ ፣ የተሰማት ፣ ደስታ ፣ እስከ ፣ አልነበረውም ። “አምላክ ፣ በምሕረቱ ፣ ቢቃሽ ፣ ሲል ፣ ምሕረት ፣ አድርጉልኝ ፣ ይላትን ፣ አወረደልኝ ። አሁን ፣ ደግሞ ፣ በልጅ ፣ ጸጋ ፣ ሊመርቀኝ ፣ ነው ። በማለት ፣ ጥልቅ የሆነ ፣ ምስጋና ፣ ለፈጣሪ ፣ አቀረበች ። “እንግዲህ ፣ ይላት፣ በጣም ፣ ይደሰታል ። የትዳር ፣ ይዞታየም ፣ የሚያስተማምን ፣ ይሆናል ፣ ›› ስትል ፣ አሰበች ።

ይህንን ፣ ዜና ፣ ለእሙኛዋ ፣ ለማብሰር ፣ ቸኩለች ፤ በጣም ፣ ጓጓች ። ይላቅም ፣ ካለወትሮው ፣ የዘገየ ፣ መሰላት ።

ሲመጣ ፤ ከአንገቱ ፣ ላይ ፣ ተጠመጠመችና ፤ “የምሥራች-የምሥራች” ፣ አለችው ። ይላቅም ፣ በዚያ ፣ ለሰሰ ፣ ባለ ፣ አነጋገሩ ፤ “ምሥር ፣ ብይ ፤ ምንድነው?›› ሲል ፣ ጠየቃት ። አበባ ፤ ከይላቅ ፣ በተቀር ፣ ከወንድ ፣ ጋር ፣ እንደዚህ ፣ ተዝናንታ ፣ አታውቅም ። ጉንጩን ፣ ሳም ፣ አደረገችውና ፣ እየፈነደቀች ፣ “አረገዝኩልህ-አረገዝኩልህ ፣ እኮ,,! አለችው ። ይላቅ ፣ ሰውነቱን ፣ ሰቅጠጥ ፣ አደረገና “አይደረግም!,,ሲል ፣ ከአንገቱ ፣ ላይ ፣ የጠመጠመችውን ፣ እጅዋን ፣ ፈርቅቆ ፣ አስለቀቀው ። ከሐኪም ፣ ዘንድ ፣ ሄዳ ፣ እንደአረጋገጠች ፣ ከነገረችው ፣ በኋላ ፣ ይበልጡን ፣ ቅዝዝ ፣ ብሎት ፣ አመሸ ። አበባ ፣ ግን ፤ ነገሩን ፣ በክፉ ፣ ሳትተረጉም ፤ “ባሎች ፣ እኮ ፣ በጣም ፣ ደስ ፣ የሚላቸው ፤ ወልደው ፣ ሕፃኑን ፣ ባስታቀፋዋቸው ፣ ጊዜ ፣ ነው ፡,,በማለት ፣ አሰባ ፣ ተወችው ። ሌሊትም ፣ ቢሆን ፤ ካለወትሮው ፣ ጀርባውን ፣ ወደርሷ፣ አዙሮ ፣ ካደረ ፣ በኋላ፣ በዚት ፣ ተሰናብ

ቷት ፣ ወጣ ። ቀን ፣ አልተመለሰም ። ማታም ፣ ሳይመጣ ፣ ቀረ ። አበባ ፤ በመጀመርያ ፣ “ምን ፣ እንከን ፣ ገጥሞት ፣ ይሆን ? የቤቱን ፣ ሥራ ፣ በትሎ ፣ ፈጽሞ ፣ እኔን ፣ ለመውሰድ ፣ እየተጣደፈ ፣ ይሆናል” ፣ በማለት ፣ ስትጽናና ፤ ባንድ ፣ በኩል ፣ ደግሞ ፣ “አደጋ ፣ አግኝቶበኝ ፣ ይሆን” ? እያለች ፣ ትሰጋ ፣ ነበር ።

በሁለተኛው ፣ ቀን ፣ ጥርጣሬ ፣ ገባት ፣ ወንድኮ ፣ አይታመንም—በሦስተኛው ፣ ቀን ፤ እንዲት ፣ ጐረቤትዋ ፣ ይላቅን ፣ በጥያሳ ፣ ሲንጐራደድ ፣ ያዩት ፣ መሆናቸውን ፣ ሲነግሩዋት ፣ እንጀቷ ፣ ብጥስ ፣ ቁርጥ ፣ አለ።በእንዳንድ፡ ሴቶች ፣ ላይ ፣ ደረሰ ፣ ሲባል ፣ የሰማችው ፣ በራሷ ፣ ላይ፣ እንደተፈጸመባት ፣ ተረዳች ። ያ-ሁሉ ፣ ተስፋ-ዋ-ያሁሉ፣ አለኝታ ፣ እንደበጋ ፣ ዳመና ፣ በኖ ፣ ጠፋ ። ኑሮዋን ፣ አንዴ ፣ ጨለማ ፣ አለበሰው። ከተጫን፡ቤት፡ በወጣች ፣ ጊዜ፡ እንኳ ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ድንገተኛ ፣ ኃዘን ፣ አልመታትም ፣ ነበር ። ከዚህ ፣ አሰቃቂ ፣ የኑሮ ፣ ሙያ ፣ ለማምለጥ ፤ እንዴት ፣ ትተማመነው ፣ ነበር!ዋዋ፡ ከንቱ ፣ ተስፋ! ፡ በጣም ፣ እርር ፣ ትክን ፣ አሰኛትና ፣ በዚሁ ፣ ድንጋጤና ፣ ብስጭት፡ ሁለት ፣ ቀን ፣ ያህል ፣ ታመመች ። የይላቅ ፣ እድራሻ ፣ የውሃ ፣ ሽታ ፣ ሆነ ።

ምዕራፍ ፲፫ ፡

የዚያ ፣ ከሃዲ ፣ ፍጥረት ፤ በግኅጸኗ ፣ ውስጥ ፣ መላወስ ፣ መገለባበጥ ፣ ጀመረ ። የንፍሰ-ጡር ፣ ሕመምና ፣ ድካም ፤ እየተሰማት፣ ብዙውን፡ ጊዜ፡ከአልጋ፡ ላይ፡ ስትውል፤ሙያው ተቋረጠ ። ወጭ ፣ እንጂ ፣ ገቢ ፣ ገንዘብ ፣ በስለት ፣ ሆነ ። ዓይነተኛው ፣ መከራና ፣ ችግር ፤ ጓዙን ፣ ጫጭኖ ፣ የገባው ፣

አሁን ፣ ነው ፣ ለማለት ፣ ይቻላል ። ችግር ፣ ያቀራምዳት ፣ ነበር ። በዚህ ፣ የነፍሰ-ጡርነትዋ ፣ ወራት ፣ የደረሰባት ፣ ከባድ ፣ ችግር ፤ ከተጫን ፣ ቤት ፣ ያመጣችውንና ፣ በኋላም ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ በደህና ፣ ጊዜ ፣ እየገፋች ፣ ያጠራቀመቻቸውን ፣ የቤት ፣ ዕቃዎች ፣ እንድትሸጥ ፣ አስገዳደት ። ኮመዲኖ ፤ ራዲዮን ፤ ጠረጴዛዎች ፣ ወንበሮች ፤ ቆይታም ፣ ቁም ፣ ሣጥኑን ፣ በየተራ ፣ አስረከበች ። ማግኘትን ፣ እንጅ ፣ ማጣትን ፣ እምብዛም ፣ የማይጠጋው ፣ የሴት ፣ አዳሪዎች ፣ ባልንጀርነት ፣ ይሸኻት ፣ ጀመር ። እንዳንዶቹ ፣ ጓደኞቿ ፣ የነበሩት ፤ ጥቃቅን ፣ ምክንያት ፣ እየፈለጉ ፣ ሲቀያየሟት ፤ ሌሎቹ ፣ እንዲሁ ፣ አይቀርቡዋትም ፣ ነበር ።

ሰውነትዋ ፣ ደንበኛውን ፣ ክብካቤ ፣ ሳያገኝ ፣ በእል ኮል ፣ የደረቀ ፣ በመሆኑ ፤ የወሊድ ፣ ምጥ ፣ በጣም ፣ አየለባ ት ። በቤትዋ ፣ ውስጥ ፣ ለመገላገል ፣ ምስት ፣ ቀን ፣ ሙሉ ፣ በሥቃይ ፣ ከተጨነቀች ፣ በኋላ ፤ በመጨረሻ ፤ የማይሳካና ፣ እደኛ ፣ ሆኖ ፣ ስለታየ ፤ አልጋዋ ፣ በጉረቤት ፣ ብድር ፣ ተይዞ ፣ ሆስፒታል ፣ እንድትገባ ፣ ተደረገ ። ከዚያም ፣ በደህ ና ፣ ተገላግላ ፣ የሚያምር ፣ ልጅ ፣ ታቅፋ ፣ ወጣች ።

መቸስ ፣ እንዳይኖር ፣ የለም ፤ አልጋም ፣ ቤትም ፤ ተከራይታ ፤ በዘዋራ ፣ ሠፈር ፤ ሥራዋን ፣ እንደገና ፣ ለመቀ ጠል ፣ ሞከረች ።

የክፍልዋ ፤ ስፋት ፤ አንዲት ፣ መጠነኛ ፣ አልጋ አዘርግታ ፤ የሁለት ፣ ወንበሮች ፣ ማስቀመጫ ፣ ሥፍራ ፣ ይተርፋታል ። ስለዚህ ፤ አልጋውን ፣ ለስሙ ፣ ያህል ፣ የሚጋርደው ፣ አሮጌ ፣ ሹት ፤ ከደጃፉ ፣ ግማሽ ፣ ሜትር ፣ ብ ቻ ፣ የራቀ ፣ ነው ። ወደላይ ፣ ከፍታዋ ፣ የረጅም ፣ ሰው ፣ እጉር ፣ ልትነካ ፣ ትቃርባለች ። ወለሉ ፣ አፈር ፣ ነው ።

ጣራው ፣ በኬሻ ፣ መሳይ ፣ ተሰብጂል ። ግድግዳው ፣ ኖራ ፣ ተቀብቶ ፣ ነበር ፣ ይባል ፣ እንጅ ፣ ግማሹ ፤ ጭቃውና ፣ ገለባው ፣ ብቻ ፣ የቀረ ፣ ነው ። የኩራንቲ ፣ መብራት ፣ የለውም ።

አበባ ፤ በዚያ ፣ የመጫት ፣ ጉስቁልናዋ ፣ ላይና ፤ በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ አካባቢ ፣ ውስጥ ፣ የሚጉበኙዋት ፣ ወንዶች ፣ ጥቂቶች ፣ ሲሆኑ ፤ ዓይነታቸውም ፣ የኔ-ቢጤ ፣ መናኛዎች ፣ መሆናቸው ፣ አይሳትም ፣ ስለዚህ ፣ የዕለት ፣ ገቢዋ ፤ የእርስዋንና ፣ የልጅዋን ፣ ሕይወት ፣ ለመጠበቅና ፤ ወጭውን ፣ ሁሉ ፣ ለመመከት ፣ በጣም ፣ ዝቅተኛ ፣ ነበር ። ምስኪን ፣ አበባ ፤ በዚሁ ፣ ሁኔታ ፣ ኑሮን ፣ ልትገፋ ፣ ትንገላታለች ።

ቀኑ ፣ የቅዱስ፣ ዮሐንስ፣ ዋዜማ፣ ነው።የቤቱ ፣ ባለቤት፤ በዓመት፣ በዓል፣ ምድር፣ በቂት፣ መዋተው ፤ ሲጮሁባት ፣ አርፍደው ፤ ኪራዩን ፣ በሙሉ ፣ በበንጋው ፣ ካልከፈለች ፣ በማግሥቱ ፣ በፖሊስ ፣ አስገድደው ፣ የሚያስወጡዋት ፣ መሆናቸውን ፣ አስጠንቅቀዋት ፣ ሂደው ፣ ነበር ። ሰሞኑን ፣ ገብያው ፣ ተዳፍኖ ፣ ነው ፣ የሰነበተው ።

የታቀፈችው ፣ ሕፃን፣ (ምነው፣ ይላቅ፣ ቢያየው፣ ኖሮ፣ መቸስ፣ አባቱን፣ መስሎ፣ ነበር፣ የወጣው) የፍርኖ ፣ ጹቱት ፣ ሙቅ ፣ እንጅ ፤ በዕጦት ፣ ምክንያት፣ የደረቀው ፣ የናቱ ፣ ጡት ፣ አልጠቅመው ፣ ስላለ ፤ ርቦት ፣ ያለቅሳል ። የርስዋ ፣ ሆድም ፣ ባንድ ፣ በኩል ፣ ይቦረቡራታል ። ግታ ፣ አብርታ ፣ የምትጠባበቅበት ፣ የሻማ ፣ መግዣ ፣ እንኳ ፣ የላትም ።

ከአሥር ፣ ዓመት ፣ በፊት ፣ ነውን ? የጊዜው ፣ ቁጥር ፣ እንኳ ፣ ጠፍቷታል ፤ የመጀመርያ ፣ ልጅዋን ፣ አርሳ ፣ ሳለች ፣

የዶሮ፡ ዓይን፡ የመሰለ ፡ ጠላ፡ ተጠምቆ ፤ ቀንዱ ፡ የዘረ፡ መ ክት፡ ታርዶ ፤ የማር ፡ ሰፈፍ፡ የመሰለ ፡ እንጀራ፡ ተጋግሮና፡ ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ ተሰብስቦ ፤ በዚች ፡ ቀን ፤ በድሮ ፡ ቤትዋ ፤ ከማህሉ ፡ ጋር ፡ ያሳለፈችውን ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ አስታወሰችና ፤ ዕንባዋ ፡ ወርዶ-ወርዶ ፤ ደረትዋን ፡ እስኪያ ጨተየው ፡ ድረስ ፡ ምርር ፡ ብላ ፡ ከልቧ ፡ አለቀሰች ።

አበባ ፡ ልብዋ ፡ የሚፈርጥ ፡ እስኪ ፡ መስል ፡ ድረስ ፡ ከተንሰቀሰቀች ፡ በኋላ ፤ ሲታዋ ፡ ጥቂት ፡ ተግ ፡ ሲልላት ፡ ልጅዋን ፡ በልዩ ፡ የኃዘኔታ ፡ ፍቅር ፡ ወደጉኗ ፡ ሽጥ ፡ አድርጋ ፡ አቀፈችና ፤ "እሹሩሩ-እሽሩሩዬ ፡" እያለች ፡ በጸጸት ፡ ትካዜ ፡ ትቆዝም ፡ ጀመር ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የጥንቱ ፡ ቤትዋ ፡ መልክ ፡ ቅርጽና ፡ አቀማመጥ ፤ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ደብዝዘብዝ ፡ ብሎ ፡ በረቂቅ ፡ ይታያት ፡ ጀመር ። ትዳርዋን ፡ እንዴት ፡ ትመራ ፡ እንደነበር ፡ በማስታወስ ፤ ከገረድ ፡ እንኳ ፡ ተርፎ ፡ ያድር ፡ የነበረው ፡ ሲማይ ፡ ትዝ ፡ አላት ።

በቤት ፡ ዕቃ ፡ ረገድ ፤ እርግጥ ፡ ባላገር ፡ ቢጤዎች ፡ ነበሩ ። አልጋው ፡ ከጠፍር ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ምንጣፋቸው ም ፡ ጀንዲ ፡ ነበር ። ፎቴ ፤ ቁም ፡ ሣጥን ፤ ራዲዮን ፤ የመሳሰሉትን ፡ ዘመናዊ ፡ የቤት ፡ ዕቃዎች ፡ በዓይናቸ ው ፡ እንኳ ፡ አይተውት ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እርሷ ፡ በረሃብ ፡ በምትቆራመድበት ፡ ጊዜ ፤ ከማህሉ ፡ ቤት ፡ ምግቡ ፡ ከውሻ ፡ ዳረጉት ፡ እንኳ ፡ ተርፎ ፡ ማደሩ ፡ ይቀራልን ? በማለት ፡ ስታስብ ፤ ሕፃን ፡ ሆና ፤ በትምሕርት ፡ ቤት ፡ ሳለች ፤ የአባቱን ፡ የውርስ ፡ ድርሻ ፡ ተካፍሎ ፡ ወደሌላ ፡ ቀበሌ ፡ በመኰብለል ፤ በብልግና ፡ ጨዋታ ፡ አባክኖ ፡ በረሃብ ፡ ከተሰቃየ ፡ በኋላ ፤ ከአሽከርነቱ ፡ እንደአንዱ ፡ እንዲሆን ፡ አባቱን ፡ ይቅርታ ፡

ጠይቆ ፡ ስለተመለሰው ፡ ልጅ ፤ "የጠፋው ፡ ልጅ" ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የሞራል ፡ አስተማሪዋ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እየጠቀሰ ፡ የነገራት ፡ ታሪክ ፡ ትውስ ፡ አላት ። ከርቧ ፡ ሁኔታ ፡ ጋርም ፡ ተመሣሣይ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘችው ፡ ገረማት ።

"እርሱስ ፡ ንስሐ ፡ ገብቶ ፡ ተመለሰ ። እኔስ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ፈውስ ፡ ይገኝልኛል ? „እያለች ፡ ስታሰላስል ፤ „የኔ ፡ ወንጀል ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ነው ።ያከሰርኩት ፡ እኮ ፡ ያባቴን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይሆን ፡ ጋብቻን ፡ ነው ። የፈረሰ ፡ ታል ፡ ኪዳን ፡ እንደገና ፡ ሊጠገን ፡ ይችላልን ? „ቢሆንም ፡ ማህሉ ፡ ይቅርታ ፡ እንደሚያደረግላት ፡ ትተማመናለች ፡ አሁን ፡ ጠባዩ ፡ ባይለወጥስ ፡ በተፈጥሮው ፡ ደግና ፡ ርኅሩኅ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠባዩ ፤ ጊዜ ፡ የማይለዋውጠው ፡ ቀዋሚ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እንኳ ፡ በአበባ ፡ ችግር ፡ ይጨክናል ፡ ተብሎ ፡ አይገመትም ። አበባ ፡ ከዚህ ፡ የሞት ፡ ኑሮ ፡ በኃሰሐ ፡ ለመነሣት ፡ በምታሰላስል በት ፡ ጊዜ ፤ ምናልባት ፡ ወደአገርዋ ፡ ብትመለስ ፤ መንደረ ኛው ፡ የሚያደርግላትን ፡ አቀባበል ፡ ስታስበው ፡ እንገሸገ ሻት ። "ቸርሙጣ""አገር ፡ አሳደድ ፡ ጋለሞታ" ፡ የሚለው ስድብ ፡ ፊት-ለፊት ፡ እንኳ ፡ ባይጋፈጣት ፡ በስተጀርባዋ ፡ እንደሚያሳድጣት ፡ ዕውቅ ፡ ነው ። በየደረሰችበት ፡ የሐሜት እፍታ ፡ መሆኗ ፡ አያጠራጥርም ። ከማንም ፡ ጉረቤት ፡ ጋር ፡ እንደልብ ፡ ተዳፍራ ፡ መነጋገርዋ ፡ ይቀራል ። በእደባባይ ፡ መካከል ፤ ራስዋን ፡ በኃፍረት ፡ አቀርቅራ ፤ የምትራመድ ፡ ትሆናለች ። በጠቅላላው ፤ የተዋረደች ፡ የተናቀች ፡ የተጠላች ፡ መዘባበቻ ፡ መሆኗ ፡ የማይቀር ፡ ንግርት ፡ ነው ። ማህሉ ፡ እንኳ ፡ እንደጥንቱ ፤ ሊኮራባት ፡

ሊፎክርባት ፣ ሊመካባት ፣ አይችልም ። እርሱም ፣ ራሱ ፣ የሚያፍርባት ፣ ይሆናል ። አሁን ፣ እርሷ ፣ ተላምጣ ፣ የተ
ተፋች ፣ ምግብ ፣ ማለት ፣ ናት ። ምን ፣ ይበጃታል ?

አበባ ፤ የወደፊት ፣ ዕድሏን ፣ ለመወሰን ፤ በጉውንና ፣ ክፋውን ፣ እያነፃፀረች ፣ ለማመዛዘን ፣ ብዙ ፣ ደቂቃዎች ፣ በሐሳብ ፣ ባሕር ፣ ዋኘቀች ። በመጨረሻ ፣ "ምንም ፣ አይደል ። ሕሜቱን ፣ የዘመን ፣ ብዛት ፣ ይደመስሰዋል ፤ ውርደቱ ፣ ይረሳል ። ሁሉም ፣ ቢቀር ፣ በሞትኩ ፣ ጊዜ ፣ ደህና ፣ ቀብር ፣ ሳይደረግልኝ ፣ አይቀርም ። ምንም ፣ ቢሆን ፣ የወንዜ ፣ ልጆች ፣ ናቸውና ፣ እስከዚህም ፣ ድረስ ፣ አያሳድዱኝም ። "በሚለው ፣ አስተያየት ፣ ላይ ፣ ቆመች ። ነገር ፣ ግን ፤ በቀጥታ ፣ ለመሔድና ፣ "ግሀሉ ፣ ተመለስኩልህ ፣ "ኮ ፣ ,,ብላ ፣ በቀላሉ ፣ የቀድሞ ፣ ትዳርዋን ፣ ለመቀጠል ፣ የምትችል ፣ መስሎ ፣ አልታያትም ። አንደኛ ፤ የመጓጓዣው ፣ ነገር ፣ ችግር ፣ ነው ። ሁለተኛ ፤ ግሀሉ ፣ ይቅርታ ፣ አድርጉ ፣ እንደሚተበላት ፣ መቶ በመቶ ፣ እርግጠኛ ፣ አልነበረችም ። ወይንም ፣ "ይቅርታ ፣ የኔ ፣ ለመቤት ፣ እኔ ፣ የማንም ፣ ትራፊ አልሰዘሰብም" ሲል ፣ ቢመልሳትስ ? ግን ፣ ያውቃል ? ግንስ ፣ አያድርስ ። ብቻ ፣ ከሁሉም ፣ የሚሻለው ፣ መጀመር ያ ፣ ደብዳቤ ፣ ጽፎ ፣ መላክ ፣ ሆኖ ፣ ታያት ።

እንግዲህ ፣ ሐሳቧን ፣ ከወሰነች ፤ ጉዳዩን ፣ ለበጎጋታው ፣ እንኳ ፣ ለማስተላለፍ ፣ ተጣደፈች ። ወዲያው ፣ ከእርጌው ፣ ሳጥን ፣ ውስጥ ፤ ከግዜ ፣ ብዛት ፣ የበሰበሰ ፣ ደብተርና ፣ የደመደመ ፣ እርሳስ ፣ አውጥታ ፤ መልእክትዋን ፣ ታሰፍር ፣ ቀጠለች ።

የደረሰባትን ፣ መከራና ፣ ችግር ፤ ሥቃይዋንና ፣ እንግልትዋን ፣ አሁን ፣ ያለችበትን ፣ ሁኔታ ፤ ከሕሊናዋ ፣ በ

ሚሰማት ፣ አካኋን ፤ ከወረቀቱ ፣ ላይ ፣ ለማስፈርገ ፣ ቃላቶች ፣ እየተቃወሱ ፤ እያጠሩና ፣ እየተጣመሙ ፣ ያውኩዋት ፣ ነበር ። በመጀመርያ ፤ ሁለት ፣ መስመሮችን ፣ ያህል ፣ እንደጻፈች ፣ ቀደደችው ፤ ቀጥላ ፣ በአጋማሽ ፣ ላይ ፣ ደገመችው ።

በመጨረሻ ፤ ጽሑፉ ፣ ሐሳቧን ፣ በመጠኑ ፣ የሚያረካ ፣ መስሎ ፣ በተፈጸመ ፣ ጊዜ ፤ ሰዓቱ ፣ ድብዝዝዝ ፣ ብሎ ፣ ነበር ።

አበባ ፤ ደብዳቤውን ፣ አጣጥፋ ፤ በአንድ ፣ አሮጌ ፣ ፖርሳ ፣ ውስጥ ፣ አጉረችና ፣ ልጅዋን ፣ በፎጣ ፣ ጠቅላላ ፣ ከቤትዋ ፣ ወጣች ። በበነጋው ፣ ጧት ፣ ወደጉጃም ፣ የሚሄድ ፣ አውቶቡስ ፣ አለ ፣ እንግዲህ ፣ በሐሳቧ ፣ ተሳፋሪ ፣ መንገደኛ ፣ ብታገኝ ፣ ለርሱ ፤ ወይንም ፣ ለነጅው ፣ "አደራ ፣ አድርስልኝ" ፣ ብላ ፣ ለመስጠት ፣ ነበር ።

ጥቂት ፣ መንገድ ፣ እንዳዘገመች ፣ ድንገተኛ ፣ የጸጉሚ ፣ ዝናም ፣ ይጥል ፣ ጀመር ። አበባ ፤ አረማመድዋን ፣ በማፋጠን ፣ ጉዞዋን ፣ ስትቀጥል ፣ ዝናሙ ፣ እየበረታ ፣ ሄደ ። ነገር ፣ ግን ፣ ሐሳቧ ፣ በደረቅ ፣ አገር ፣ ላይ ፣ ስለነበር ፣ ርጥበቱ አልተሰማትምና ፤ ብቻ ፣ ልጅዋን ፣ ቅዝቃዜ ፣ እንዳይገባው ፣ ስትል ፣ ሽፍንፍን ፣ አድርጋ ፣ በጉኛዋ ፣ ውስጥ ፣ ሸጐጠችውና ፤ ዝናሙ ፣ እየወረደባት ፣ መንደገድዋን ፣ ቀጠለች ። ወዲያው ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ የመኪና-መንገድ ፣ ለማቋረጥ ፣ ከመካከል ፣ ስትደርስ ፤ አንድ ፣ ዕብድ ፣ አውቶሞቢል ፣ እየከነፈ ፣ መጣባት ፤ ወደኋላ ፣ ለመመለስም ፣ ሆነ ፣ ወደፊት ፣ ለማምለጥ ፣ ጊዜ ፣ አልነበራትም ። አውቶሞቢሉም ፣ ለመቆም ፣ የሚችል ፣ መስሎ ፣ አልታየም ። "ውይ!" ብላ ፣ ጩኽትዋን ፣ ሳትጨርስ ፣ ለግቶ ፣ ጣላትና ፤ እናትና ፣ ልጅ ፣ ተፈናጥረው ፣ ወደቁ ። ነጅው ፤ ፍሬኑን ፣

ለዓመል ፡ ያህል ፡ ያዝ፡ አድርጐ ፡ በመስኰቱ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ጥፋቱን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፤ "ነፍሴ ፡ አውጭኝ" ፡ ሲል ፡ በቁልቁለቱ ፡ በረረ ።

በዝናሙ ፡ ምክንያት ፡ እግረ ፡ መንገደኛ፡ አልነበረም። ነገር ፡ ግን ፡ በአሻገር ፡ ተጠልለው ፡ የነበሩ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች አደጋውን ፡ ተመልክተው ፡ ሳለ ፤ ድንገተኛነቱና ፡ ድንጋጤው ፡ አደናግሮዋቸው ፡ ስለነበር ፤ የመኪናውን ፡ ሰሌዳ ፡ ለመመዝገብ ፡ ፋታ ፡ አላገኙም ። ለመርዳት ፡ በከበቡ ፡ ጊዜ ፤ ሕፃኑ ፡ ሞቶ ፤ አበባም ፡ በብርቱ ፡ ቆስላና ፡ በግጭቱ፡ ስሜት ፡ በደን ፡ ሆና ፡ ነበር ። ሰዎቹ ፡ የአደጋውን ፡ አሰቃቂነት ፡ እየተወያዩ ፤ የሁለቱን ፡ ፍጡሮች ፡ አካላት ፡ በጅባጅንቦሽ ፡ አንስተው ፡ ወደመንገዱ ፡ ዳር ፡ አሳረፉት ። የፈሰሰው ፡ ደማቸው ፡ ግን ፤ ከጕርፉ ፡ ጋር ፡ በመቀላቀል ፤ የአውቶሞቢሉን ፡ ፋና ፡ ተከትሎ ፡ በቁልቁለት ፡ እየተውዘገዘገ ፡ ሲወርድ ፡ ሲታይ ፤ ደመኛውን ፡ አሳድዶ ፡ ለመበቀል ፡ የቆረጠ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ የፖሊስ ፡ ተራፊክ ፡ ክፍሎች ፡ ደርሰው ፤ ሥፍራውን ፡ መተሩና ፤ ቁስለኞችን ፡ (አንዱ ፡ ሬሳ)በአምቡላስ ፡ መኪና ፡ አሣፍረው ፤ ለሕክምና ፡ ለምርመራ ፡ ወደሆስፒታል ፡ ላኩዋቸው ።

አበባ ፤ የግጭቱ ፡ ኃይል ፡ አንጐልዋን ፡ ነክቷት ፡ ኖሮ ፡ አእምሮዋን ፡ ስታ ፡ ነበር ። ያተደረገላት ፡ ሕክምና ፡ ሁሉ ፡ አልተሰማትም ። ነፍስዋን ፡ ያወቀችው ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ከሕመም ፡ እንቅልፍዋ ፡ ነቅታ ፡ አይኖቿን ፡ በገለጠች ፡ ጊዜ ፡ ያለችበት ፡ ክፍል ፡ ተለዋውጦ ፡ አገኘችውና ፡

በመጀመርያ ፡ ግራ ፡ ገባት ። ጣራውን ፡ ግድግዳውንና ፡ ወለሉን ፡ ቃኘችው ። በኋላ ፡ ግን ፡ በአካባቢዋ ፡ የተቀማመጡትን ፡ የሕክምና ፡ ዕቃዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ተመልክታ ሁኔታውን ፡ በማስታወስ ፤ "መኪና ፡ ገጭቶኝ ፡ በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ተኝቻ ፡ ነውና ፡ ያለሁት ፡ "ስትል ፡ ነገሩ ፡ ገባት ። ወዲያው ፤ የደረሰባትን ፡ ጉዳት ፡ ለማወቅ ፤ በኖራና ፡ በሻሽ ፡ የተለበደውን ፡ ሰውነቷን ፡ በቀስታ ፡ እያንቀሳቀሰች ፡ ስትመራመር ፤ የአንድ ፡ እግርዋ ፡ አገዳ ፡ ልዩ ፡ ስሜትና ሚዛን ፡ ሰጣት ። በመጥፎ ፡ ጥርጣሬ ፤ ሰውነቷ ፡እን ደመዛልና ፡ እንደመሸማቀቅ ፡ ሲል ፤ እንደተጋደመች ፡ ራሷን ፡ ትንሽ ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፡ ቁልቁል ፡ ብትመለከት ፡ በአልጋው ፡ ልባስ ፡ ጕልቶ ፡ የሚለየው ፡ የገላዋ ፡ ቅርጽ ፡ ከወደታች ፡ ትክክል ፡ አልነበረም ። እውነትም ፡ አንድ ፡ ቅልጥሟ ፡ ያጠረ ፡ ነው፡ድንገት ፡ ታዋር፡ እንደሆን፡ በማለት ፡ ልትዘረጋው ፡ ሞከረች ። የለም ፡ አልታጠፈም!

አበባ ፡ ወከክ ፡ አለች ። በቃ ። ተከተተ ። የመጨረሻው ፡ ተስፋ ፡ ምዕራፉን ፡ ዘጋ ። "እንግዲህ ፡ የኔ ፡ ፍጻሜ ፡ ይሄው ፡ ሆኖ ፡ ቀረ!,,እያለች ፡ በሕመምተኛ ፡ ሲቃ ፤ ትንሽ ፡ መንሰቅሰቅ ፡ እንደጀመረች ፤ የደከመው ፡ ሰውነቷ የኃዘን ፡ ክብደት ፡ ለመሸከም ፡ የሚችል ፡ ስላልነበረ ፤ የሽልብታ ፡ ሰመመን ፡ መልሶ ፡ ወሰዳት ።

ነርሶችና ፡ ሞግዚቶቹ ፡ ሊያጽናኑዋት ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ የሚያጽናና ፡ ነገር ፡ ይገኝላታል? የሴት ፡ እግረ ፡ ቆራጣ ፡ ምን ፡ የኑሮ ፡ ተስፋ ፡ ሊኖራት ፡ ይችላል!እንዲያው ፡ ከንቱ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፤ ወደሣህሉ ፤ ለመመለስ ፡ ማሰቡ ፡ ተደመደመ ። የሴት ፡ አዳሪነትን ፡ ተግባር ፡ ለመቀጠል ፡ ከቶ ፡ ዘበት ፡ ነው ። በጅርም ፡ አልተ

ሰግ ፤ በዓይንም ፡ አልታየ ። ለጉድ ፡ ባልተባለም ፡ ነበር ፡ እንዴ ! ጪሪና ፡ ቀባሪ ፡ ሕልም ፡ ነው ። አበባ ፡ ይሆንን ፡ በምታስብቡት ፡ ጊዜ ፡ የሰይጣን ፡ ልክፍት ፡ እንደ ፡ ሚያመ ታየው ፡ ሰው ፡ ገጽዋ ፡ ስብርብር ፡ ይል ፡ ነበር ።ጭፍግግ፡ ስትጥጥ ፤ ኩምትር ፡ ዘርጋ ፡ ያሰኛታል ።

የልጅዋ ፡ ሞት ፡ መርዶ ፡ በጣም ፡ አሳስለቀሳትም ። የናት ፡ አንጀት ፡ ነውና ፡ ማዘኗ ፡ አልቀረም ። ቢተርፍስ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ ነበረውስእንዴት ፡ ለማሳደግ ፡ ይቻላል ? ቢሆን ከቀድሞው ፡ ባልተፈጠረ ፡ ይሻለው ፡ ነበር ። ያም ፡ ሆኖ ፤ አባቱ ፡ ቢከዳው ፡ እንኳ ፡ ጪናማ ፡ እናት ፡ ትኖረውና ፡ ተከባክባው ፡ አድጉ ፡ ራሱን ፡ ይችልልኛል ፡ ሲባል ፡ ይጠበቃል ። ነገር ፡ ግን ፤ አባቱ ፡ ለጠፋ ፤ እናቱም ፡ እያለ ች ፡ ለሞተች ፡ ሕፃን ፤ በዚሁ ፡ ዓለም ፡ ምን ፡ ቢታና ፡ ተስፋ ፡ አለው ። ከሁሉም ፡ የቆጫት ፤ የወላጅ ፡ ኃጢአት ፡ ለልጅ ፡ እንደሚባለው ፤ በርሰዋ ፡ ኃጢአት ፡ የግፍ ፡ ዘር ፡ መውለድዋና ፡ በኋላም ፡ ማስቀጨትዋ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ራሷም ፡ ቢሆን ፡ ድርሻዋን ፡ እንደተቀበለች ፡ አይሳት ም ። በትዝትም ፡ ሆነ ፡ በውንዋ ፡ "የእግዚአብሔር ፡ ቁጣ ፡ በላየ-ላይ ፡ ወረደ ። በቁመናየም ፡ ሊቀጣኝና ፡ ሊአሰቃየኝ ፡ ቆረጠ ፡ ,,እያለች ፡ ትለፈልፍ ፡ ነበር ። ምስኪን ፡ አበባ አንዲት ፡ ደካማ ፡ ፍጡር ፡ ይሆንን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ መሸከ ም ፡ ይገባታልን ?

ያ ፡ ዓመጸኛ ፡ ነጅ ፤ ያመለጠ ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅም ፡ አበባ ፡ በነፃ ፡ እንድትታከም ፡ የትራፊክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፤ ፈቃድ ፡ አስወጥተውላት ፡ ነበር ። የሐኪሙ ፡ ቤቱ ፡ ኃላፊም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ረድተዋታል ። በጠቅላላው ፤ የሆስፒታሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ደጉችዋ ፡

ነበሩ ። በሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ መከራ ፡ ወርዶ ፡ ሲታይ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የማይራራ ? እንዴትስ ፡ ያለ ፡ ድፍን ፡ ልብ ፡ ነው ፡ የማይ ነካ ? ቁስሎችዋ ፡ ሻሩ ። ሰውነቷ ፡ በረታና ፤ ካልጋው ፡ ላይ ፡ እየወረደች ፤ በሦስት ፡ እግር ፡ ያንካሳ ፡ ቢስክሌት ፡ መሽከ ርከር ፡ ጀመረች ። ከዚህም ፡ የምትኖር ፡ ቢሆን ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ነበር ። በጣምም ፡ ባልተከፋች ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የበሽተኞች ፡ ብቻ ፡ ሠፈር ፡ ስለሆነ ፤ ከዳንች ፡ ቦታ ፡ መልቀቅ ፡ የማይቀርላት ፡ ነው ።

አንድ ፡ ቀን ፤ አንድ ፡ ደግ ፡ ዶክተር ፤ በደንብ ፡ የተሠ ራ ፡ የአንካሳ ፡ ምርኩዝ ፡ ገዝቶ ፡ አመጣና ፡ ሰጣት ፤ አበባ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያሳየችው ፡ ጠባይ ፡ የሚመሰገን፡ አልነበረም። ቢሆንም ፡ የብስጭት ፡ ስሜት ፡ ስለሆነ ፡ አይፈረድባትም ። ስለአሳቢነቱና ፡ ስለውለታው ፡ ሰውየውን ፡ በማመስገን ፡ ፈንታ ፡ በቁጭት ፡ ከንፈርዋን ፡ እያንቀጠቀጠች ፡ ተቀበለ ችው ። እንዲያውም ፡ ወርውረሽ ፡ ስበሪው ፡ አሰኝትዋት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለተኛ ፡ እግርዋ ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘ በችና ፡ ስሜቷን ፡ ገታች ።

መቸስ ፡ እንደዚች ፡ ምርኩዝ ፡ የጠላችው ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ዘወትር ፡ የምትመለከታት ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ነው ፤ ስታነሳትም ፡ በንዴትና ፡ በበቀል ፡ መልክ ፡ ነበር ፡ ያም ፡ ሆኖ ፡ ቆሞ ፡ መሄድ ፡ የማይቀር ፡ ነበርና ፡ ልምምድ ፡ ታደርግባት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሐኪሞቹና ፡ ነርሶቹ ፡ እንዳሳይዋት ፡ ምርኩዟን ፡ ከብብትዋ ፡ ሽጉጥ ፡ አድርጋ ፡ ዝል-ዝል ፡ ለማለት ፡ ስትሞክር፡ ሰውነቷ ፡ ሁሉ፡ በብስጭት እሳት ፡ ይቃጠላል ። ያደናቀፋት ፡ እንደሆነማ ፤ ዕንባ ፡ ይተ ናነቃት ፡ ነበር ።

ከሆስፒታል ፣ መውጫ ፣ ቀን ፣ ደረሰ ። ነርሶቹ ፣ የል ጅዋን ፣ ልብስ ፤ በአደጋው ፣ ጊዜ ፣ ጨብጣው ፣ የነበረው ን ፣ ፖርሳና ፣ቅባጥርስ ፣ በፎጣ ፣ ጠቅልለው ፤ አንድ ፣ አሮጌ ፣ ብርድ ፣ ልብስ ፣ ጨመሩላትና ፣ አስነገቡዋት፣ እንደዚሁም ፣ ጥቂት ፣ ገንዘብ ፣ በመካከላቸው ፣ አዋጥተው ፤ ለስንቅ ፣ እንዲሆናት ፣ በግለት ፣ ሰጡዋት ።

አዲስ ፣ አበባ ፤ ከተማ ፣ ከመጣች ፣ ጊዜ ፣ ጀምሮ ፤ እንደነዚህ ፣ ነርሶች ፣ ልባዊ ፣ ወዳጆችና ፣ አዛኝ ፣ ፍጥረቶ ች ፣ አላጋጠማትም ። መከራዋንና ፣ የሥቃይዋን ፣ ስሜት ፣ ለማቃለል ፣ በጣም ፣ ተቸግረውላታል ። በምርኩዝ ፣ ቁማ ፣ ለመሔድ ፣ የቻለችው ፤ በነርሱ ፣ ብርታትና ፣ ምክር ፣ ነበር ።

ሲሰነባበቱ ፣ ዕንባ ፣ አፍስሰውላታል ። እያንዳንዳቸ ውም ፣ ‘‘ግዴለም ፤ በጣም ፣ አይዘኑ ። በርስዎ ፣ አልተጀመ ረም ። ይልቁንስ ፣ ነፍስዎን፣ ስላዳነልዎት፣ እግዚአብሔርን፣ ያመስግኑት ። መንፈስዎን ፣ ብስጭት ፣ አያሸንፈው ። በትዕግሥት ፣ ይበርቱ ። ረድኤቱ ፣ ከርስዎ፣ ጋር፣ ይሁን’’፣ እያሉ ፣ የሰጡዋት ፣ የማጽናኛ ፣ ቃል ፤ እግር ፣ እንኳ ፣ ባይሆንላት ፣ ሁለተኛ ፣ ምርኩዝ ፣ ሆኖ ፣ ረድትዋታል ። ከለበለዚያስ ፤ ከሆስፒታሉ ፣ በራፍ ፣ ላይ ፣ ወድቃ ፣ ተሰባብ ራ ፣ በቀረች ፣ ነበር ።

አበባ ፤ መልኳ ፣ እንዳይለይ ፣ ፊትዋን ፣ ሸፋፍና ፤ ጓዝዋን ፣ አንጠልጥላ ፤ ወልከስ-ወልከስ ፣ እያለች ፣ ከዓይና ቸው ፣ እስክትሰወር ፣ ድረስ ፣ ከመድረኩ ፣ ላይ ፣ ከምችች ፣ ብለው ፣ ተመለከትዋት ።

እንግዲህ ፣ የቁም ፣ ሙት ፣ ሆናለች ። ከደመቀው ፣ ዓለም ፣ አደራሽም ፣ ወጥታ ፣ ተሰውራለች ። ስለዚህ ፣

አበባን ፣ ከዚሁ ፣ ላይ፣በመተው ፤ ወደሣህሉ ፣ ዘንድ ፣ ሂደን ፣ ኑሮውን ፣ በመጠኑ ፣ እንመልከት ።

ምዕራፍ ፤ ፲፬ ፣

ሣህሉ ፤ አበባ ፣ በላዩ-ላይ ፣ ከኮበለለችበት ፣ ጊዜ ፣ አንስቶ ፣ በትዳሩ ፣ ሌላ ፣ ሚስት ፣ አልተካበትም ።

በውበት ፤ በቁንጅና ፤ በባሕርይና ፣ በባልትና ፤ የአበባን ፣ ሥፍራ ፣ ሊወስድለት ፣ የሚችል ፣ ሴት ፣ ከቶ ፣ ያለ ፣ አልመሰለውም ። ሊፈልግም ፣ አልሞከረም ። በሔዋን ፣ ልጆች ፣ ላይ ፣ የነበረው ፣ እምነት ፣ ፈጽሞ ፣ ደርቋል ። አገር ፣ የመሰከረላት ፣ አበባ ፣ እንኳ ፣ ስትከዳው፤ እንግዲህ ፣ ሴት—እያለ ፣ ይተች ፣ ነበር ። ከዚህም ፣ በላይ ፣ የፍቅሩ ፣ ቁስል ፣ አልሻረለትም ፣ ይመስላል ። ምንም ቢሆን ፣ ከሕሊናው ፣ ሊያስወግዳት ፣ አልቻለም ። ይህንን የትዝታ ፣ ኑቀርሳ ፣ ለመንቀል ፣ ችሎታ ፣ ያላት ፣ የቁንጅና ፣ ወጌሻ ፣ በአካባቢው ፣ አጣ ። ስለዚህ ፣ ሕይወቱን ፣ በብቸኝ ነት ፣ ለማሳለፍ ፣ ቆረጠና ፣ ገረድ ፣ ቀጥሮ ፣ ተቀመጠ ።

ልጁን ፤ በሕፃንነቱ ፣ ዘመን ፣ አንዲት ፣ አክስቱ ፣ ተቀብለው ፣ በጥንቃቄ ፣ እየተከባከቡ ፣ አሳንደጉለትና ፣ በእግሩ ፣ ማኮብኮብ ፣ ሲጀምር ፣ ግን ፣ ከአባቱ ፣ ጋር ፣ ሆነ ።

ሣህሉ ፤ የቅዝታው ፣ ቁስል ፣ በጊዜ ፣ ሕክምና ፣ ልያገግም ፣ ሲቃጣው ፤ እንደገና ፣ የሚያገርሹበት ፤ ይሄው ፣ ልጁና ፤ የዓመት ፣ በዓል፣ቀኖች ፣ ነበሩ ።

ልጆች ፤ ወላጆቻቸው ፣ የሚያወሩት ፣ ምሥጢር ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ አያመልጣቸውም ። እንደዋዛ ፣ ያጻምጣሉ ። እነርሱ-በነርሱ ፣ በሚጨዋወቱበት ፣ ጊዜ ፤ ክቶም ፣ ሆን ፣

ደግ ፣ ነገር ፣ አይደባበቁም ። ከአባታቸው ፤ ከእናታቸው ፣ ወይንም ፣ ከገረድ ፣ አፍ ፣ የለቀሙትን ፣ ምሥጢር ፣ ይዘካዘካሉ ። የኩታራ ፣ ሆድ ፣ ጥሬ ፣ አይጥጥርም ፣ እንደሚባለው ፤ ስለአበባ ፣ ከየቤታቸው ፣ የሰሙትን ፣ ጭምጭምታ ፣ እያመጡ ፣ ለልጁ ፣ ይነግሩት ፣ ነበር ። ስለዚህ ፣ የመንደር ፣ እናቶች ፤ ለልጆቻቸው ፣ በማድላት ፤ የተቆጡት ፤ የነሡት ፣ ወይንም ፣ የበደሉት ፣ እንደሁ ፤ ወደአባቱ ፣ ዘንድ ፣ እየሮጠ ፣ ይመጣና ፤ ከጉልበቱ ፣ ላይ ፣ ተደግፎ ፣ “የእንትና ፣ እናትኮ ፣ ዛሬ—አደረገችን ፣ የኔ ፣ እናትም ፣ ብትኖር ፣ ኖሮ ፣ እንደዚሁ ፣ ታብርልኝ ፣ ነበር ። አለች ፣ ይላሉ ፣ እኮ ፣ አበባየት ፣ ነው ፣ ያለችው ፣ ለምን ፣ እንደሌሎቹ ፣ እናቶች ፣ ከኛ ፣ ጋር ፣ አትቀመጥም?,,እያለ ፣ ሲያዋየው ፤ የሚሀሉ ፣ ቅሰም ፣ ሰብርብር ፣ ይል ፣ ነበር ። ከእንደዚህ ፣ ያለ ፣ ቀበሌ ፣ ትኖራለች ፣ ሲል ፣ እንዳይነግረው ፣ ወስዶ ፣ ሊያሳየው ፤ ወይንም ፣ ሊያናግረው ፣ አይችልም ። ሞታለች ፣ ሲል ፣ እንዳያስታውቀው ፤ መርዶ ፣ አልደረሰውም ። ወይንም ፣ ጉዱን ፣ ዘርዝሮ ፣ እንዳያስረዳው ፤ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ የእናት ፣ ገመና ፣ ለልጅ ፣ ማውራት ፣ ተገቢ ፣ አይደለም ። “ዝምበል ፣ ”ሲል ፣ እንዳይቆጣው ፤ ልጁ ፣ ጥፋተኛ ፣ ሆኖ ፣ አልተገኘም ። ስለዚህ ፣ የሚመልሰው ፣ ሲጨንቀው ፤ ነገሩን ፣ በማደባበስ ፤ ሌላ ፣ እየደነጉረ ፣ ለማረሳሳት ፣ ይሞክር ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ሕፃኑ ፣ በዕድሜ እየጐለመሰ ፣ ሲሄድ ፤ ስለእናቱ ፣ የሚያቀርበው ፣ ጥያቄ ፣ እየተደጋገመ ፣ ሄደ ። በዚሁ ፣ አኳኋን ፤ ልጁ ፣ ያለማሰብ ፣ የሚያሰማው ፣ የእናት ፣ ጥሪ ፤ በሚሀሉ ፣ ልብ ፣ የተጻፈን ውን ፣ ትዝታ ፣ እየቆሰቆሰ ፣ የሚያሰቃይ ፣ ነበር ።

እንደዚሁም ፣ የዓመት በዓል ፣ ቀን ፤ ብትኖው ፣

ሚሀሉ ፣ የሞቀ ፣ ትዳርን ፣ የሚያዘክርበት ፣ ቀን ፣ ነው ። ከፈንጠዝያ ፣ ይልቅ ፤ የትዝታ ፣ ትካዜን ፣ ጭናለት ፣ ይመጣል ።

ሚጥኑ ፣ ባዶ ፣ እልሆነም ። ጓዳው ፣ አልጐደለም ። ተገቢው ፣ የዓመት ፣ በዓል ፣ ዝግጅት ፣ ተዳፍኖ ፣ አያውቅም ። በጐረቤቶቹ ፣ ቤት ፣ የሚሰናዳው ፣ ሁሉ ፤ እንዲያውም ፣ በርሱ ፣ ጐጆ ፣ የበለጠ ፣ ሆኖ ፣ ሳይሰናዳ ፣ አልቀረም ።

ነገር ፣ ግን ፣ ፍጹም ፣ ደስታ ፣ ማለት ፣ ከነፍስ ፣ የሚመነጭ ፣ የመርካት ፣ ስሜት ፣ እንደሆነ ፣ ሲታመን ፣ የነፍስ ፣ ምግብ ፣ ደግሞ ፣ የጋራ ፣ ፍቅር ፣ ነው ። እንጀራና ፣ መጠጥ ፣ ሥጋን ፣ ያዳጉላል ፣ እንጅ ፤ መንፈስን አያጠግበውም ። ግማሽ ፣ ጉኑ ፣ የተገነጠለ ፣ የቤተሰብ ፣ ትዳር ፣ ምን-ጊዜም ፣ ሊሞቅና ፣ ሊደምቅ ፣ የማይችል ፤ ዘወትር ፣ የቀዘቀዘ ፣ ነው ።

ስለዚህ ፤ ሚሀሉ ፣ የሚያስታምመው ፣ ነጠላ ፣ ትዝታ ፣ ብቻ ፣ መሆኑ ፣ ሲታወቅ ፣ ሙክቱ ፣ ቢሰባ ፤ ጠላው ፣ ቢያምር ፤ ወጡ ፣ ቢጣፍጥ ፤ ቅንጣት ፣ ያህል ፣ ደስታ ፣ አይሰጠውም ፣ ነበር ። ደንታም ፣ አልነበረው ። ለምኑ ፣ ነው፤ከማንስ ፣ ጋር ፣ ሊጫወትበትና ፣ ሊደሰትበትነረድ ፣ አቅርባለት ፣ ከሕፃን ፣ ልጁ ፣ ጋር ፣ ለመጫወት ፣ ነውን?ለዚህም ፣ ምን ፣ ዓመት ፣ በዓል ፣ እዘቦትስ ፣ ያሰኛል?ይልቁንስ ፣ መልካሙን ያለፈ ፣ ጊዜ ፣ ማስታወሱ ፣ ይብሳል ። ጥንት ፣ አበባ ፣ ሳለች ፣ ልጃቸውን ፣ በመከከላቸው ፣ አድርገው ፣ እየተከባከቡና ፤ እንርሱ-በነርሱ ፣ እየተቆለማመጡ ፣ የሚያሳልፉት ፣ ዓመት በዓል ፣ ነበር ። ደስታቸውን ፣ የሚከፋፈሉበት— አሁን ፣ እነዚያ ፣ ቀናት ፣ አልፈዋል ። ሞተዋል ። ድግሱም ፣ እንደተዝካር ፣ የሚቆጠር ፣ ነበር ።

ቀኑ ፣ አበባ ፣ ደብዳቤ ፣ ለመላክ ፣ ስትንከወከው ፣ በመኪና ፣ ተገጭታ ፣ አካልዋን ፣ ያጣችበት ፤ የቅዱስ ፣ ዮሐንስ ፣ ዋዜማ ፣ ነው ። ያአሰቃቂና ፣ ጨለማ ፣ ዕለት—

ሣህሉ ፣ ከውጭ ፣ ቆይቶ ፣ መደ ፣ ቤቱ ፣ ሲመለስ ፤ ልጁ ፣ የመንደር ፣ ጨዋታውን ፣ አቋርጦ ፣ እየሮጠ ፣ ደረሰበትና ፣ ከዚያም ፤ ባንድ ፣ እጁ ፣ ያባቱን ፣ ክንድ ፣ ጨብጦ ፤ በሌላው ፣ ችቦውን ፣ እያወዛወዘ ፣ "አባባ ፣ ችቦ የን ፣ እኮ ፣ አሰርኩት" አለው ፣ አባቱም ፣ ቀበል ፣ አደረገና፣ "መልካም-መልካም' ሲል ፣ ከተዛነቡ ፣ ላይ ፣ አስደግፎ፤ ተያይዘው ፣ ወደቤቱ ፣ ገቡ ። ሣህሉ ፣ ከድንክ ፣ አልጋ ው ፣ ላይ ፣ ሲቀመጥ ፤ ሕፃኑ ፣ ከጉልበቱ ፣ ላይ ፣ ተደ ግፎ ፣ ዓይኑን ፣ ወደላይ ፣ ያቁለጨልጭ ፣ ጀመር ። እሽ ፣ እንደዚህ ፣ ያለው ፣ አስተያየት ፣ ለደግ ፣ አይደለም ። "ምን ድን ፣ ነው ፣ አሰረስ ? ,,ሲል ፣ አባቱ ፣ ጠየቀው ።

አስረስ ፤ ለማስተዛዘን ፣ የሕፃናት ፣ ልዩ ፣ ስጦታ ፣ በሆነው ፣ መዓዛዊ ፣ ልሳን ፣ "ዛሬ ፤ ከበደ ፣ ችቦዮን ፣ ሊሰርቅብኝ ፣ሲል ፣ ብመታው፤ እናቱ ፣ አብራ፣ ልትመታኝ ፣ መጣች ። ከዚያም ፣ ሩጫ ፣ ባመልጣት ፣ ሙልጭ ፣ አድርጋ ፣ ሰደበችኝ ፣ አለው ። አባትየውም ፤ የሰድቡን ፣ ዓረፍተ ፣ ነገር ፣ ለማወቅ ፣ በመሻት ፣ ሳይሆን ፣ ሕፃኑን ፣ ለማጽናናት ፣ "ደግሞ ፣ ምን ፣ ብላ ፣ ነው ፣ የምትሰድብሀ"አለና ፣ ጠየቀ ው ። መቸስ ፣ የልጅ ፣ ነገር ፣ ነውና ፤ ሣህሉ ፣ ለመስማት ፣ የማይፈቅደውን ፣ ሁሉ ፣ ዘረከቀለት ። "ይህ ፣ የናቱ ፣ አድራሻ ፣ የማይታወቅ ፤ የከርታታ ፣ ልጅ—በቀርማ ፣ የዚያች ፣ አገረ ፣ ፈት ፣ ልጅ ፣ ሆነህ ፣ ልትረባ—ልጆቻች ን ፣ ከዚህ ፤ ከሚበጠብጥብን ፤እንደናቱ፣ ወጥቶ፣ አይቀርም ነበር" ፣ አለችኝ ፣ የምታስ ፣ እናት ፣ ግን ፣ ሳለቅስ ፣ አይታ ፣

ጠራችኝና ፣ "ዝም ፣ በል ፤ አይዞህ ፣ እታልቅስ—ያንተ ፣ እናት ፣ መዋር ፣ ዕድል ፣ ጥሎባት ፣ ነው ፣ እንጅ ፣ ከግንዴ ፣ ሴት ፣ አታንስም ፣ ሲሆን ፣ ትበልጥ ፣ ነበር ። ብቻ ፣ የከበደ ፣ እናት ፣ ያለችህን፣ ለአባትህ፣ አትንገረው ። ይልቁንስ ፤ ነገ ስታሚውተውና ፣ ስታስደስተው ፣ እንድትውል" ፣ አለችኝና ፤ እንጀራ ፣ በወተ ፣ ሰጠችኝ ። አበባ ፤ እናቴ፣ ያለችው ፣ እዲስ ፣ አበባ ፣ ከሚባል ፣ አገር ፣ ነው ፣ ይላሉ ። ለምን፣ እናመጣትምና፣ ከኛ ፣ ጋር፣ አትቀመጥም፣ዛሬ፣ከዚህ፣ ብትኖር ፣ ኖሮ ፣ እንደሌሎቹ ፣ ልጆች ፣ "ጎሮ ፣ ገባሽ ፣ እማማ"እላት ፣ ነበር ።"

የሕፃኑ ፣ እንጋገር ፤ የሣህሉን ፣ ልብ ፤ እንደጦር ፣ ሰርስሮ ፣ ወጋው ። የእስር ፣ ዓመት ፣ ቁስሉን ፣ ነካበት ። ቀሰቀሰበት ። ስሜቱ ፣ ልክ ፣ እንደተኩስ ፣ ድርጊት ፣ ገነፈለበት ። ከብስጭትና ፣ ከመሳቀቅ ፣ የተነሣ ፣ ጸጉሩን ፣ ለመንጨት ፣ እየጉተተ ፤ ገጹን ፣ ሲያጨማድደው ፣ ልጁ ፣ አየና ፣ በዚህ ፣ ድንገተኛ ፣ መለዋወጥ ፣ ደንግጦ ፣ "ምንድን ነው ? ምንድን ፣ ነው ፣ አባባ!"ሲል ፣ ጠየቀው ። ሣህሉ ፣ ግን ፣ ምሳውን ፣ ሊበላ ፣ የነበረውን ፣ አቋርጦ ፣ በመነሳት ፣ "ምንም ፣ አይደል-ራሴን ፣ አሞኝ ፣ ነው"እያለ ፣ ወደ ምኝታ ፣ ክፍሉ ፣ አመራ ። ከዚያም ፤ ከአልጋው ፣ ላይ ፣ ተደፍቶ ፤ ተጥመነመነ ። ዕንባ ፣ አውጥቶ ፣ ግን ፣ አላስቀሰም የኃዘን ፣ ስሜት ፣ ይቀላቀልበት ፣ እንጅ ፣ አብሣኛው ፤ የሐሳብ ፣ ማዕዛበል ፣ ነበር ። ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻላል? የልጁ ፣ የናት ፣ ጥማት ፣ ከቀን ፣ ወደቀን ፣ እየባሰበት ፣ እንደሚሄድ ፣ አይጠረጠርም ። በእንጀራ ፣ እናት ፣ ሊረካ ፣ አይችልም ። ከዚህም ፣ በላይ ፤ ሌላ ፣ ሴት ፣ ለማግባት ፤ ሣህሉ ፣ በፍጹም ፣ ምኞት ፣ የለውም ። ታዲያ ፣ አበባን ፣

ያስባል፤አልቀረም ። ግሀሱ ፤ ነገሩን ፣ በውሉም ፣ እንፃር ፣ እያመዛዘነ ፣ ተመለከተው ።

አበባ ፣ በጣም ፣ ጥፋተኛ ፣ እንደሆነች ፣ ባይካድም ፤ መኩብለል ፣ በር፧ ፣ አልተጀመረም ። ውድቅትዋ ፤ ሙሉ ፣ ‘ይቅርታ ፣ ሊደረግላት ፣ ባይችልም ፣ ፈተናው ፣ በጣም ፣ ከባድ ፣ ስለነበረባት ፤ አስተያየት ፣ ሊሰጠው ፣ የሚገባ ፣ ነው ።

ከባሏ ፣ ጋር ፣ ተፋታ ፣ በሴት ፣ አዳሪነት ፣ እንደምትኖ ር ፣ ሽውታ ፣ ደርሶታል ። ቢሆንም ፣ ተገዳ ፣ እንጅ ፣ ይሆንን ፣ ዓይነት ፣ ሙያ ፣ ወዳው ፣ እንደማይሆን ፣ ግሀሱ ፣ ያምን ፣ ነበር ። ያ ፣ የተፈጥሮ ፣ ጠባይዋ፤ ለእንደዚህ ፣ ያለው ፣ ርኩስ ተግባር ፣ በቀላሉ ፣ እንደማይተታ ፣ ገመተ ። ስለዚህ ፣ ምናልባት ፤ ጊዜ ፣ ካልወጣት ፣ በተቀር ፤ ባለፈው ፣ ጥፋት ፣ ተጸጽታ ፤ ትዳርዋን ፣ ሰጥ-ለጥ ፣ ብላ ፣ ትይዝ ፣ ይሆናል ። እርግጥ ፣ ነው ፤ አበባ ፣ አሁን ፣ ተላምጣ ፣ የተተፋ ፣ ነገር ፣ ግለት ፣ ናት ፣ ቢሆንም ፤ ለልጁ-ለልጁ ፣ ሲል ፣ እንኳ ፣ የተተፋ ፣ ነገርን ፣ መልሶ ፣ ለመዋጥ ፣ አሰበ ። ግሀሱ ፤ ከዚህ ፣ ውሳኔ ፣ ላይ ፣ ለማረፍ ፣ ብዙ ፣ ደቂቃዎች ፣ ተጨን ቆ ፣ ነበር ። በዚህ ፣ አስተያየቱ ፣ ላይ ፣ ተቃራኒ ፣ ሚዛን ፣ ሆኖ ፣ ያስቸገረው ፣ የሕዝቡ ፣ ይሉኝታ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ የሞንቱ ፣ ፍቅር ፣ ትዝታ ፣ ደገፈለትና ፤ “ልጃችንን አበባንና ፣ እኔን ፣ ደስ ፣ ካለን ፣ አዳሜ ፣ የፈለገውን ፣ ቢቀባጥር ፣ ምን ፣ ቸገሮን ፣ ,,ሲል ፣ ቆረጠ ። ሐሳቡን ፣ በመወሰኑም ፣ ደስ ፣ አለው ። ሕሊናውንም ፣ ቀለለው ። የበነጋታው ፣ ዓመት ፣ በዓልም ፤ ካለፉት ፣ አሥር ፣ ዓመታት በዓላት ፣ ሁሉ ፤ በተሻለ ፣ መንፈስና ፣ ስሜት ፣ አሳልፎት ፣ ዋለ ።

ሰሞኑን ፤ ስንቁን ፣ አሰነቱና ፣ አስፈላጊውን ፣ የመንገ ደኛ ፣ ግዝ ፣ አዘጋጅቶ ፣ ወደ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ ገሰገሰ ። አውቶቡሱ ፣ አምጥቶ ፤ ከአቡነ ፣ ጴጥሮስ ፣ ሐውልት ፣ አትራቢያ ፣ ከሚገኘው ፣ ጣቢያ ፣ ላይ ፣ ሲያራግፈው ፤ ለጊዜው ፣ ያከተማው ፣ ትርምስ ፣ አደናገረውና ፤ በአዲስ ፣ ከተማ ፤ ከአንድ ፣ ነጋዴ ፣ ብራንዳ ፣ እንዲያድር ፣ ተገደደ ። በኋላ ፣ ግን ፤ ጥንት ፣ ያባቱ ፣ ባልንጀራ ፣ የነበሩ ፣ እንድ ፣ ትልቅ ፣ ሽማግሌ ፣ ነጋዴ ፣ መኖሪያ ፣ ሠፈር ፤ ጠያይቆ ፣ ደረሰ ። ሽማግሌውም ፤ የአባቱን ፣ ፍቅርና ፣ ውለታ ፣ በማስታወስ ፤ በደንብ ፣ ተቀብለው ፣ ካስተናገዱት ፣ በኋላ ፤ ግሪፊያ ፣ ከፍል ፣ እንዲዘጋጅለት ፤ በምንብም ፣ ረገድ ፣ እንዳያስጠበና ፣ እንዳይሳቀቅ ፣ አደረጉ ። ግሀ ሱ ፤ የመጀመርያው ፣ እርምጃ ፣ ቀናው ፤ አሁን ፣ እንግዲ ህ ፤ የመጣበትን ፣ ዋና ፣ ዓላማ ፣ መፈጸም ፣ ነው ፣ የቀረው ።

አዲስ ፣ አበባ ፣ ውስዋ ፤ እድራሻው ፣ ያልታወቀ ፣ ሰውን ፣ ፈልጉ ፣ ለማግኘት ፣ መሞከር ፣ በከምር ፣ ድርቆሽ ፣ ውስዋ ፣ አንዲት ፣ መርፌን ፣ እንደመሻት ፣ ይቆጠራል ። በተለይም ፣ ፈላጊው ፣ ለከተማው ፣ እንግዳ ፤ ተፈላጊዋ ፣ በኪራይ ፣ ቤት ተንከራታች ፣ ሴት ፣ አዳሪ ፣ ስትሆን ፤ አፈላለጉ ፣ ውል ፣ የሌለው ፣ ቋጠሮ ፣ ግለት ፣ ነው ። መምሪያ ፣ አይገኝለትም ። ከተማውን ፣ በሙሉ ፣ ግዳሪስና ፤ መንደሮችን ፣ በዝርዝር ፣ ግበጠር ፣ ይኖርበታል ። ወይንም ፣ ድግግት ፣ በቶሎ ፣ ይተናው ፣ ይሆናል ። ወይንም ፣ እስከነጭራሹ ፣ ሳይሳካ ፣ የሚቀርበት ፣ ጊዜ ፣ አለ ።

ለምሳሌ ፤ ፈላጊው፣ አንድ፣ መንደርን፣ መርምሮ፣ ከጨረ ሰ ፣ በኋላ ፣ እንደአጋጣሚ ፣ ተፈላጊው ፣ ወደዚሁ ፣ መሬር ፣ ይዛወር ፣ ይሆናል ። ፈላጊው ፤ የቀረውን ፣ ከተማ ፣ አዳርሶ ፣

ወደዚሁ ፡ ሠፈር ፡ መጠያየቅ፡ሲጀምር፡ደግሞ፡ሰውየው፡ሠፈሩን ፡ይሰውጣል።በዚሁ ፡ አኳኋን፡ልውውጡ ፡ ሳያቋርጥ ፤ ቢደጋገም፡ፍለጋው፡ፍጻሜ፡ ያገኛል፡ለማለት፡አያስደፍርም ። ነገር ፡ ግን ፡ በአጋጣሚ ፡ ወይንም ፡ በጠቋሚ ፡ ተግባሩ ፡ የተቃለለ ፡ ሲሆን ፡ ይችላል ።

ግሀሱ ፤ ምስት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ሺህ ፡ ከሚሆን ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ አንዲት ፡ ፍጡር ፡ መርጦ ፡ ለማውጣት ፡ የጨበጠው፡መሣሪያ፡መጠሪያ ፡ ስም፡ብቻ፡ነበር።የአስር፡ዓመታት ፡ ጊዜ ፡ ታሳቅ፡ የመልክ፡መለዋወጥ ፡ ሊያደርስ ፡ መቻሉ ሲገመት ፤ ምናልባት ፡ በእደባባይ ፡ መካከል ፡ ቢያገኛት ፡ እንኳ ፡ ሊያውቃት ፡ አይችልም ፡ ይሆናል ።

ፍለጋውን ፡ በብርቱ ፡ ትጋት ፡ ቀጠለ ። ቀበሌውን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ዞረው ። የውቤ ፡ በረሃን ፡ በዝርዝር ፡ አዳረሰው ። ገዳም-ሠፈርን ፡ በብጥር ፡ ፈተሸው ። በዶሮ-ማነቂያ ፡ ጠያየቀ ። ሠራተኛ-ሠፈር ፤ እራበከንቱ ፤ ሀኪም-ቦራ ፤ አዲስ ፡ ከተማ ፡ ቸርችል ፡ ጉዳና የሴት ፡ አዳሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ የተባለው ፡ መንደር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አልቀረውም ፡ ነበር ። በየጉራንጉሩ ፡ ተንከራተተ ። አበባ ፡ ግን ፡ አልተገኘችም ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደተለመደው ፤ ከሰፈር ፡ ገብቶ ፤ “አበባ ፡ ሥዩም ፡ የተባሉ ፡ ሴት ፡ አታውቁልኝምን? ከአገር ፡ ቤት ፡ የመጣሁ ፡ ዘመዳቸው ፡ ነበርኩ ። ,,እያለ ፡ ሲጠያየቅ ፤ አንድ ፡ የሰፈር ፡ ሰው ፤ “ይምጡ ፡ ላሳይዎት” አለና ፡ ይመራው ፡ ጀመር ። ግሀሱ ፡ በደስታ ፡ እየተቅበጠበጠ ፤ “እግዛኢአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ጌታ ። አስቸገርኩዎት ፡ መሰለኝ ፡ ,,እያለ ፡ ተከተለው ። መንገዱ ፡ ረዘመበት ፡ ቸኩሉ ፡ እንዲት ፡ እንደሚገናኛትና ፡ እንደሚያነጋግራት ፡

ደግሞ ፡ ፈራ ። ሰውየው ፤ ወሰዶ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ግቢ ፡ አመለከተው ።

ግሀሱ ፡ በወሬ ፡ የሰማው ፤ ሴት ፡ አዳሪ ፡ ሆናለች ፡ ግለትን ፡ ነበር ። ይህ ፡ እደራሽ ፡ ግን ፡ የቤተ ፡ ሱበና ፡ የትልቅ ፡ ሰው ፡ መኖርያ ፡ ይመስላል ። ጨነቀው ። ግራ ፡ ገባው ። ምናልባት ፡ እንደገና ፡ ሌላ ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ ይሆን? ሲል ፡ አሰበና ፤ “ይህግ ፡ ከሆነ ፡ የኔው ፡ ጉዞና ፡ ድካም ፡ መና ፡ ቀረ ። ይህንን ፡ የመሰለ ፡ እደራሽ ፡ ትታ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ትመለሳለች ፡ ግለት ፡ ዘበት ፡ ነው ፡,, ሲል ፡ ሐሞቱ ፡ በስጋት ፡ ፈሰሰ።መሪውን፡እንኳ፡ሳያመሰግነው ፤ ተመልሶ ሊሮጥ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግንስ ፤ ግን ፡ ያውቃል!ከመናገር ፡ ደጃዝማችነት ፡ ይቀራል፡እንደሚባለው ፤ ጠይቄ ፡ ቁርጡን ፡ ባውቀው ፡ አይከፋም፡ ፡ ሲል ፡ ተዳፈረና ፤ ገብቶ ፡ ጠየቀ ።

ባለቤቲቱ ፡ ወጡና ፤ “ምንውን ፡ ምን ፡ ይፈልጋሉ?,,

አሉት ፡ “ወይዘሮ ፡ አበባ ፡ ሥዩም ፡ የሚባሉ ፡ ዘመዴ ፡ ነበሩ”ሲል ፡ ጠየቀ ።

“አበባ ፡ ሥዩም ፡ ግለት ፡ እኔ ፡ ነኝ ”ጉድ ፡ ፈላ! እንኳንስ ፡ እሱ ፡ የሚያውቃት ፡ አበባ ፡ ሊሆኑና ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አይመሳሰሏትም ፤ ውፍረታቸው ፡ የርቢን ፡ ሁለት ያህላል ። ቅላት ፡ ይኑራቸው ፡ እንጅ ፡ ጉርድርድ ፡ ያሉ ፡ ትልቅ ፡ ወይዘሮ ፡ ቢጤ ፡ ነበሩ ። የርሱይቱ ፡ አበባ ፡ እንዳይደሉ ፡ ቢያምንም ፡ ለማረጋገጥ ፡ ያህል ፡ ከእግር ፡ እስከራሳቸው ፤ ከተመለከታቸው ፡ በኋላ ፤ ራሱን ፡ በቅሬታ ንቅንቆ ፡ ሊወጣ ፡ ሲል ፡ ወይዘሮይቱ ፡ አገሩን ፡ ጠየቁትና ፡ ሲነግራቸው ፡ “እንግዲያውስ ፡ የስም ፡ ሞክሸንት፡ይሆናል,, በማለት ፡ አሰናበቱት ። ግሀሱ ፡ በመሳቀቅ ፡ ተመለሰ ።

ምንም ፣ ቢሆን ፣ ተስፋ ፣ አልቆረጠም ። እስከብዙ ፣ ወራትም ፣ ቢሆን ፤ ፍሊጋውን ፣ ለመቀጠል ፣ ወሰኖ ፣ ነበር ። አንዳንድ ፣ ቀን ፣ በምሽት ፣ ይንከራተት ፣ ነበር ።

በቀን ፣ ብርሃን ፣ ሰው ፣ የሚኖርበት ፣ የማይመስለው ፣ የሴት ፣ አዳሪዎች ፣ ሠፈር ፣ የሌሊት ፣ ድምቀቱን ፣ በሚገል ጥበት ፣ ጊዜ ፤ ማህሉ ፣ በየበራቱ ፣ እየቆመ ፤ ተሸሞንሙነው በወንበሩ ፣ ላይ ፣ የተዘረጉትን ፣ ወይዛዝርት ፤ አንገቱን ፣ እደሰገገ ፣ ይመለከት ፣ ነበር ። ሰሌላ ፣ ተመልካች ፤ ቁንጅና ን ፣ እያማረጠ ፣ የሚያሳድብ ፣ የማታ ፣ መንገደኛ ፣ ወንደላ ጤ ፣ ሳይመስል ፣ አልቀረም ። በእውነትም ፣ አንዳንዶቹ ፣ ቤቶች ፤ ይሆንኑ ፣ የመሰለ ፣ ግምት ፣ በመውሰድ ፤ የማበረታ ቻና ፣ የግብኛ ፣ አስተያየት ፣ ሲሰነዝሩለት ፤ .....ማህሉ ፤ ዓይኑን ፣ ቱሱ ፣ ሰበር ፣ ያደርግና ፤ "ወይ ፣ ግሩም ፣ ፈተና"ኮ,, ነው ፣ ሲል ፣ መንገዱን ፣ ይቀጥላል ። ከዚያም ፤ የሴቶቹ ፣ ልብስ፣የሚቱቡት፣የውበት፣ቅመም፤የከሬንቲው፣ መብራት፣ ቀለም ፤ የሚፈጥረውን ፤ አሳሳች ፣ ቅዠታዊ ፣ ትርኢት ፣ እያደነቀና ፣ በሴቶቹ ፣ የነውር ፣ ሙያ ፣ ድፍረት ፣ እየተገረ ም ፤ እንደዚሁም ፤ አበባ ፣ ከነዚህ ፣ ቱራ ፣ በመመደቧ ፣ እያዘነ ፣ ወደግረፊያው ፣ ያዘግማል ።

ማህሉ ፣ በተፈጥሮው ፣ የቤተ ፣ ክህነት ፣ ቤተሰብ ፣ ነው ። አበባ ፣ ከሰዳችው ፣ አንስቶ ፣ ይበልጡን ፣ ወደመንፈ ሳዊ ፣ ሕሳብ ፣ በማዘንበል ፤ በጾምና ፣ በጸሎት ፣ ሰውነቱን ፣ ለፈጣሪው ፣ ያስገዛ ፣ ነበር ። አዲስ ፣ አበባ ፣ በቆየባቸው ፣ ወራት ፣ ሁሉ ፤ ከቤተ፣ክርስቲያን ፣ ተለይቶ ፣ አያውቅም። ዘውትር ፣ ጠዋት ፤ ዕለታዊ ፣ ተግባሩን ፣ ከመጀመሩ ፣ በፊት ፣ ወደአራዳው ፣ ጊዮርጊስ ፣ ይሄድና ፤ ለፈጣሪው ፣ ጸሎት ፣ ያቀ ርባል ። በዚው ፣ አካኋን ፣ በጾብሩ ፣ ከሚገኙት ፣ ካህናት ፣

ጋር ፣ ለመተዋወቅና ፣ ለመለማመድ ፣ ችሎ ፣ ነበር ።

አንድ ፣ ሌሊት ፣ መጥፎ ፣ ቅዠት ፣ ሲያታዝው ፣ አደረ ። ከዚያ ፣ በፊትም ፣ ቢሆን ፤ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ስለአበባ ፣ ያልም ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ይሄኛው ፣ የተለየ ፣ በጣም ፣ የሚያስፈራ ፣ ነበር ።

ማህሉ ፤ በአንድ ፣ ረግረግ ፣ ጫካ ፣ ውስጥ ፣ ሲዘዋወር ፤ በሩቅ ፣ የአበባን ፣ ድምጽ ፣ ይሰማና ፣ እየፈለገ ፣ ወደዚያው ፣ ሲሄድ፤ አበባን፣ እስከአንገትዋ፣ ድረስ፣በእዘቅት፣ተውጣ፣ እጅዋን ፣ ለዕርዳታ ፣ ስታርገበግብ ፣ ያገኛታል ። ማህሉ ፣ እየተንቀጠቀጠና ፣ "አይዞሽ ፣ አይዞሽ!"ሲል ፣ እየጠራ ፤ ካጠገቡ ፤ አንድ ፣ የዛፍ ፣ ሐረግ ፣ መሥ ፣ ወረወረላት ። አበባ ፣ ሐረጉን ፣ ጨብጣ ፤ እርሱ ፣ ጉትቶ ፣ ሊያወጣት ፣ ሲል ፣ ይቢጠስባቸዋል ። እንደገና ፣ ሌላ ፣ ሐረግ ፣ ቆርጦ ፣ ሊልክላት ፣ ሲል ፣ የአበባ ፣ ራስ ፣ በሙሉ ፣ ይዋጥና ፤ እጣቶችዋ ፣ ብቻ ፣ ወደርሱ ፣ እንዳመለክቱ ፣ ይቀራሉ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ማህሉ ፤ ልብሱን ፣ እወላልቆ ፣ ሊደረጉስ ፣ ሲል ፣ በድንጋጤ ፣ ብንን ፣ አለ ። በአርአያ ፣ ሥላሴ ፣ አማተበ ና ፣ ተመልሶ ፣ ተኛ ። ቢሆንም ፣ የጸጥታና ፣ የጠለቀ ፣ እን ቅልፍ ፣ ላይወስደው ፣ ነጋ ። ጠዋትም ፣ ወደቤተ፣ክርስቲያ ን ፣ ሲሄድ ፤ ሰውነቱን ፣ ከፉኛ ፣ ቀፎት ፣ ነበር ።

ጊዮርጊስ ፣ እንደደረሰ ፤ ካህናቱና ፣ ጥቂቶች ፣ ምዕመ ናን ፣ ከአንድ ፣ ዓጸድ፣ ሥር፣ከበው፣ ቆመው፣ሲተራመሱ፣ አገኘ ። ማህሉ ፣ ምክንያቱን ፣ ለማወቅ ፣ ጠጋ ፣ ብሎ ፣ ቢጠይቅ ፤ አንዲት ፣ የእግዚአብሔር ፣ ምስኪን ፣ አርፋ ፤ ሰዎች፣ ስለቀብሩ ፣ ይነጋገራሉ ፤ ጥቂቶቹ ፣ አካፋና ፣ ዶማ ፣ ለማምጣት ፣ ሄደዋል ። ማህሉ ፤ ለሰበእዊና ፣ ለክርስቲያና ዊ ፣ አገልግሎት ፣ ቀልጣፋ ፣ ነውና ፤ ወዲያው ፣ ዕርዳታውን

ለማበርከት ፣ ቀረብ ፣ አለና ፤ “ታዲያ ፣ ምን ፣ እንጠብቃለ
ን ፣ እስፈላጊውን ፣ የአስከሬን ፣ ዝግጅት ፣ ማድረግ ፣
አይሻልምን ? ሲል ፣ ጠየቀ ። ሰዎቹ ፣ እነርሱ ፣ በነርሱ ፣
ተያዩ ። ብዙዎቹ ፣ በድን ፣ ለመንካት ፣ የሚጸዩሩ ፣ አለመሆ
ናቸው ፣ በአስተያየትታቸው ፣ ይታወቅ ፣ ነበር ። ሚሀሉ ፣
“እንደኛው ፣ የእግዚአብሔር ፣ ፍጡር ፣ ነበረች ። ምኑ ፣
ያስፈራል ፣ ”ሲል ፣ ነጠላውን ፣ ወለቅ ፣ አድርጉ ፣ ተጉነበ
ሰና ፣ ሬሳውን ፣ ያደራጅ ፣ ጀመር ። ምንው ፣ ልዩ ፣ ስሜት ፣
ተሰማውበደን ፣ ማገለባበጥ ፣ የመጀመርያ ፣ ጊዜው ፣
አልነበረም ። ይልቁንም ፣ የሬሳው ፣ ገጽ ፤ እንደሥውር ፣
ኃይል ፤ በሰውነቱ ፣ ውስጥ ፣ እንድ ፣ ዓይነት ፣ የትዝታ ፣ ቅዝ
ቃዜ ፣ ስለለቀቀበት ፣ አተኩሮ ፣ ሊመለከተው ፣ አልፈቀደም
ና ፣ በአርጌ ፣ ልብስ ፣ ጋርዶ ፤ ለማጠቢያ ፣ የሚሆን ፣
ውሃ ፣ እስኪመጣ ፣ ድረስ ፣ ስለከፋት ፣ ይነጋገሩ ፣ ነበር ።
ገንዘብ ፣ እዋጥተው ፣ ለመግዛት ፣ አሰቡና ፤ “ምንም ፣
እንኳ ፣ ለማኝ ፣ ብትሆን ፣ ጥቂት ፣ ገንዘብ ፣ አይጠፋትም ፣
ይሆናልና ፣ ፈቅሹ”ሲል ፣ አንዱ ፣ ታዛቢ ፣ አስተነዘበ ።
ለሥራ ፣ ቀደምት ፣ የሆነው ፣ ሚሀሉ ፣ መዲያው ፣ ጓዟን ፣
አነሳና ፣ ሲበዘብዝ ፤ አንድ ፣ ፎቶግራፍና ፣ ደብዳቤ ፤
ጹብ ፣ ብለው ፣ ወደቁ ። ሁሉን ፣ ነገር ፣ ለማወቅ ፣ መሻት ፣
የሰው ፣ ተፈጥሮ ፣ ባሕርይ ፣ ነውና ፤ ደብዳቤውን ፣ አንስቶ ፣
እያነበባበጠ ፣ ሲመረመር ፣ “ለክቡር ፣ ውድ ፣ ወንድሜ ፣
አቶ ፣ ሚሀሉ ፣ መሸኛ ፣ ,,የሚል ፣ አድራሻ ፣ አነበበ ።
ውስጡን ፣ ገለጠና ፣ ቢመረምረው ፤ እውነትም ፣ ለርሱ ፣
ነው ፣ የተጻፈለት ። በመዉረሻ ፣ ላይም ፣ የአበባ ፣ ስም ፣
ሰፍሮበት ፣ ነበር ። ፎቶግራፉን ፣ እንደገና ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ቢ
መልከተው ፣ አበባ ፣ ቁልጭ ፣ ብላ ፣ ተገለጸችለት ፣ እንደሥ
ውር ፣ ነገር ፣ ይሰበው ፣ የነበረው ፣ የሬሳው ፣ መልክም ፤ በር

ተግራፉ ፣ ላይ ፣ እንደመስታወት ፣ ወጣ ። ተከሰተ ።

“ለክቡር ፣ ውድ ፣ ወንድሜ ፣ አቶ ፣ ሚሀሉ ፣ መሸኛ ፤
ከተለያየንባት ፤ ከዚያች ፣ ውድቀት ፣ ቀን ፣ አንስቶ ፣
ለጤናህ ፣ እንደምን ፣ ትሆናለህ ። እኔ ፣ ግን ፤ የእግዚአብሔ
ር ፣ ምስጋና ፣ መጓደል ፣ አይገባውም ፣ እንጅ ፤ ደህና ፣ ነኝ ፣
ብል ፤ ከንቱ ፣ ትምክህት ፣ ያስኝብኛል ። ቁሜአለሁ ። ።
እንቀሳቀሳለሁ ። ነገር ፣ ግን ፣ ሕያው ፣ ነኝ ፣ ማለት ፣ በሕተ
ት ፣ ነው ። መንፈሱና ፣ ነፍሱ ፣ የሞተ ፣ ሥጋ ፤ መቃበርም ፣
የተፋው ፣ በድን ፣ ነኝ ።

“ይህንን ፣ ደብዳቤ ፣ ስጽፍልህ ፣ የቱን ፣ ያህል ፣
እንደምትታዘበኝ ፣ አውቃለሁ ። ልትንቀኝና ፣ ልትጸየፈኝ ፣
ይገባኛል ። ብትሸሸኝም ፣ አይፈረድብህም ። ጥፋቴን—
ያንን ፣ ከፍተኛ ፣ ጥፋቴን ፤ የሊአል ፣ ጨለማ ፣ እንኳ ፣
ሊደብቀው ፣ ይችላልን?አይመስልኝም ።

“እንደዚያ ፣ ስትወደኝ ፣ ከዳሁህ ። ከራስህ ፣ አብልጠ
ህ ፣ ስታስብልኝ ፣ በደልኩህ ። እምነቴን ፣ አጓደልኩ ። ምን
እምነቴን ፣ ማጓደል ፣ ብቻ ፤ ቤቴን ፣ ዘግቸ ፣ ወጣሁ ፣
የተክሊል ፣ ግዳጇን ፣ በመጣስ ፣ ከሌላ ፣ ጋር ፣ ከበለልኩ ።

“ነገር ፣ ግን ፣ ምን ፣ ተጠቅምኩበእንተ ፣ ዘንግተሃት ፣
እንደሆን ፣ እንጅ ፤ እኔ ፣ ዘወትር ፣ በማሰታውሰት ፣ በዚያች ፣
በሰንብት ፣ ደብዳቤየ ፣ እንዳገለጽኩልህ ፤ በለው ፣ ነገር ፣
ተመርዠ ፤ የተሻለ ፣ ለማግኘት ፣ በምኞት ፣ ፈረስ ፣
ሲጋልብ ፤ ወድቄ ፣ ተሰበርሁ ፣ የራሴንና ፣ እራሴን ፣ አጣሁ ።

“በመጀመርያዎቹ ፣ ወራት ፤ የትዠት ፣ ደስታ ፣ አግኝ
ቸ ፣ እንደነበር ፣ አልሸሽግህም ። ዘመኖቼው ፣ ተድላ ፣
ከፈቲ ፣ ተዝርግቶልኝ ፤ የተራበው ፣ ምኞቴ ፣ በማየት ፣ ብቻ

ተመግበሽታል ። በሆንም ፣ ለብዙ ፣ ጊዜ ፣ አልነበረም ። ከአዲሱ ፣ ትዳሬ ፣ ጋር ፣ መዲያው ፣ ተፋታን ። በሰውየው ፣ (ባል ፣ ተብየው)አልፈርድበትም ። በተቻለው ፣ መጠን ፣ ሞክር ፣ ፈንታውን ፣ ተሸንፎዋል ።

"ኑሮውና ፣ ኑሮየ ፣ የተመጣጠነ ፣ አልሆነም ፤ የኔ ፣ የሥልጣኔ ፣ ደረጃ ፣ ከማህበራዊ ፣ ክበቡ ፣ ጋር ፣ ተጋፍሮ ፣ ለመወዳደር ፣ አልቻለም ። በዚሁ ፣ ምክንያት ፣ ከባልንጀሮቹ ፣ እንዲለይ ፣ ሲገደድ ፣ በብቸኝነት ፣ ከኔ ፣ ጋር ፣ በደስታ ፣ ለመኖር ፣ የሚችል ፣ ሰው ፣ አልነበረም ።

"ከርሱ ፣ ቤት ፣ ከወጣሁ ፤ የወደቅሁበትን ፣ የውርደት ት ፣ ተግባር ፣ ብገልጽልህ ፣ ምን ፣ ይጠቅማል!ይቀፍፃል ፣ ያንገሽግሽሃል ። ያስባጭሃል ። እኔንም ፣ በበለጠ ፣ እንድት ጠላኝ ፣ ያደርግሃል ። እንደተሸፈነ ፣ ቢኖር ፣ መልካም ፣ ነበር ፣ ነገር ፣ ግን ፣ የውስጡን ፣ ርኩሰት ፣ በዝርዝር ፣ እንኳ ፣ ባታውቀው ፤ ላይ-ላዩን ፣ ሳትሰማው ፣ እንደማትቀ ር ፣ የሚታመን ፣ ነው ።

"አሁን ፣ የምገኘው ፣ በችግር ፣ ማጥ ፣ ተውጬ ፣ ነው ። ይሆንን ፣ ደብዳቤ ፣ ስጽፍልህም ፤ በጥንቱ ፣ ዓለሜ ፣ ቤት ፣ በዓመት ፣ በዓል ፣ ቀን ፣ የነበረውን ፣ ፍሥሐ ፣ በማስታወስ ፣ ፅንባዬ ፣ እንደጉርፍ ፣ ይፈሳል ።

"መቸም ፣ ሙሉ ፣ ይቅርታ ፣ በማድረግ ፣ እጅህን ፣ ዘርግተህ ፣ ልትቀበለኝ ፣ አልተግመንም ፤ ልጠይቅህም ፣ መብት ፣ የለኝም ። ነገር ፣ ግን ፤ ምናልባት ፣ ያ ፣ ርኅሩኅ ፣ ልብህ ፣ ባይጨክንና ፤ እኔን ፣ ምስኪኒቱን ፣ ለመርዳት ፣ ቢፈቅድ ፤ በጭንቅ ፣ እጠባበቃለሁ ። ከዚህም ፤ ያንተን ፣ የጥንቱን ፣ ፍቅርህን ፣ የሚያሸንፍና ፣ የሚደመስስ ፣ ወንድ ፣ እንዳልተወለደ ፣ ስገልጽልህ ፣ በኃፍረት ፣ ነው ።

"ልጄን ፣ ናፍቄአለሁና ፤ ስለኔ ፣ አትፈህ ፣ ሞጭሙ ጭልኝ ። አድራሻየ—መንገድ ፣ ነው ።

"የአምላክ ፣ ፈቃድ ፣ ቢሆን ፤ በዓይነ-ሥጋ ፣ ለመገና ኘት ፣ ያብቃን ።

"እህትህ ፤ አበባ ፣ ሥዩም"

ግሀሉ ፣ ደብዳቤውን ፣ ጨርሶ ፣ አሳነበበውም ። ከግግሹም ፣ አልደረሰ ። ሁለት-ሦስት ፣ መስመሮች ፣ እንዳሞገደ ፣ ዘሎ ፣ ተደፋና ፣ እራሳውን ፣ እየዳበሰ ፣ ይንሰቀ ሰቅ ፣ ጀመር ። መራቱ ፣ ጠበበው ፤ ተወራጨ ። እእምሮውን ስቶ ፣ የሚሆነውን ፣ አጣ ። "አበባ!አበባ" ፣ እያለ ፣ ሲጮህ ፤ ሰምቹ ፣ ተደናግጠው ፣ ትንሽ ፣ ደቂቃዎች ፣ ከቆሙ ፣ በኋላ ፤ ጉትተው ፣ አስነሱትና ፤ እንቅልፍ ፣ እንደያዘው ፣ ሰው ፣ እየነቀነቁ ፣ "ምን ፣ ሆኑ! ምን ፣ ነካዎት! ሲሉ ፣ጠየቁት።ግሀሉም፣"ልቀቁኝ፣ ልቀቁኝ፣ እንጅ" እያለ ፣ በዋይታ ፣ ከተፈራገጠ ፣ በኋላ ፣ ትንሽ ፣ ትግ ፣ ሲልለት ፤ ትንፋሹን ፣ እየቆራረጠ ፤ "ሚስቴ—ሚስቴ ፣ እኮ ፣ ነች—ከአገር ፣ ቤት ፣ የመጣሁት፣እርሷን ፣ ለመፈለግ ፣ ነበር—" አሳቸው ።

ምዕራፍ ፲፩ ፤

ግሀሉ ፤ በአበባ ፣ ሞት ፣ የተሰማውን ፣ ኃዘን ፤ ለመግ ለጽ ፣ መሞከር ፤ በከንቱ ፣ ቀለምን ፣ መጨረስ ፤ ወረቀቶችን መፍጀት ፤ ጊዜን ፣ ማባከን ፣ ይሆናል ። ቃላት ፣ በቂ ፣ ስሜት ፣ አይኖራቸውም ፣ ዓረፍተ ፣ ነገሮችም ፣ ትክክለኛው ን ፣ ፍቺ ፣ ሊያስተላልፉልን ፣ አይችሉም ። ረቂቅ ፣ ስሜቶ ችን ፣ በጽሑፍ ፣ ቀርጾ ፣ በፍጹምነት ፣ ለማበርከት ፣ የቻለ ፣ ደራሲ ፤ በዓለማችን ፣ ላይ ፣ ማለፉ፣ ያጠራጥራል።እርግጥ ፣

ነው ፤ እንዳንድ ፡ ባለቅኔዎች ፤ እንደዚህ ፡ የመሰለውን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሥቃይና ፡ ኃዘን ፤ በከዋክብት ፡ መርገፍ ፤ በጨረቃ ፡ መጥቆር ፤ በፀሐይ ፡ መጨለም ፤ በመላእክት ፤ ዋይታ ፤ በወፎች ፡ ልቅሶ ፡ እየመሰሉ ፡ ለማስረዳት ፡ ሞክረዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሁሉም ፡ የሚሻለው ፤ የእንባቢ ዎች ፡ የሐሳብ ፡ ግምት ፡ እንደሆነ ፡ አይካድም ። ስለዚህ ፡ የጣዘሱን ፡ ስሜት ፤ ለሕሊናችን ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ፡ ትተን የአበባን ፡ አሻሻት ፡ በአጭሩ ፡ ብንመለከት ፡ ይቀላል ።

አበባ ፡ ከሦስርታል ፡ ከወጣች ፡ በኋላ ፤ ወደምታውቃ ቸውና ፡ ወዳሚያውዳት ፡ መንደሮች ፡ ለመሔድ ፡ ችውም ። ባልንጀሮችዋ ፡ ከነበሩት ፡ አንዳንዶች በመጠኑ ፡ ሳይረዱዋት ፡ እንደማይቀሩ የሚታመን ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ ለዘለቄታው ፡ እንደማይደግፍዋት ፡ እውቅ ፡ ነው ። በጨንነት ፡ ላይ ፡ እንኳ ፡ ያለበትን ፡ ስድብና ፡ ፈዝ፤ እሹሮርና ፡ እንካሰላንትያ ፡ ስታስታውስ ፤ አሁንማ ፡ ያ ፡ ጉዶው ፡ አካልዋ ፡ እንዴት ፡ ያል ፡ አቀባበል ፡ እንደሚጠ ባበቀው ፡ በመገመት ፡ ሰውነቷ ፡ ስትጥጥ ፡ ይል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፤ የሴት ፡ አዳሪዎችን ፡ እጅና ፡ ሥላቅ ፡ አይቶ ፡ ከመኖር ፤ የልመና ፡ እንጀራን ፡ መረጠች ። በምድር ፡ ላይ፡ ለተቀጣችበት ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፤ ምናልባት ፡ ሰግያ ዊውን ፡ ይቅርታ ፡ እንድታገኝ ፡ ወደነዳም ፡ ለመግባት ም ፡ አስባ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰውነቷ ፡ ጠና ፡ እስኪል ና ፡ መንፈሶዋም ፡ እስኪበረታ ፡ ድረስ ፡ በጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ አረፈች ።

የምዕዋት ፡ እንጀራ ፤ እንኳንስ ፤ ለወጣት ፡ ሚንፈስና ፡ ለሽጀ ፡ ሽማግሌም ፡ ቢሆን ፡ እንደሚመር ፡ ሊታመን ፤ አበባ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ የውርደት ፡ ሰቀቀን ፡

እንደመታት ፡ ለመገመት ፡ አያዳግትም ። በየመንደሩ ፤ እየዞረች ፡ መቀፈፍ ፡ ይቅርና ፤ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጣ ፡ በምትመጸወትበት ፡ ጊዜ ፡ አፍዋን ፡ ከፍታ ፡ ለመጠየቅ ፡ አትሞክረውም። ብታገኝ፡ አገኘች ። ብታጣም ፡ ግድ፡ አልነ በራትም ። ለመንቀሳቀስ ፡ እስከቻለች ፡ ድረስ ፡ የራቡን ፡ ስሜት ፡ በጭከና ፡ እደንዝዛው ፡ ነበር ። ብዙውን ፡ ሰዓት ፡ የምታሳልፈው ፤ ከዓጸደ ፡ ቤተክርስቲያኑ ፡ ሥር ፡ ተኮራም ታ ፡ በመጸለይና ፡ ፈጣሪዋን ፡ በመለመን ፡ ነበር ። ወደመን ፈሳዊና ፡ ወደንስሐ ፡ በማዘንበል ፤ ለምድራዊው ፡ ጣጣ ፡ ድርሻ ፡ ልትሰጠው ፡ አልፈቀደችም ።

በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ እንዳለለፈች ፤ ድንገተኛ ፡ የብርድ ፡ ሕመም ፡ አድሮባት፤ ከገመም ተኛነት፡ ያልጠናውን፡ ሰውነቷን ፡ ሦስት ፡ ቀኖች ፡ ያህል፡ በትኩሳት ከቀቀለው ፡ በኋላ ፡ ከዚች ፡ ዓለም ፡ ጣጣ ፡ አገላገላት ። ጊዜዋ ፡ እንደተፈጸመ ፡ በማወቅ ፤ በመጨረሻ ፡ ሰዓቶች ፡ ያደረሰችው ፡ ጸሎትም ፤ ‘‘አምላኬ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ። ሣህሉም ፡ አትቀየመኝ’’የሚል ፡ ነበር ።

አበባ ፤ ሰግያዊውን ፡ ይቅርታ ፡ ለመቀበልዋ ፡ አንጻ ችም ፡ ማስረጃ ፡ ባይኖረን ፤ ከሣህሉ ፡ ጋር ፤ ከመቃብር ፡ ወዲህ ፡ ማዶ ፡ እንዲገናኙ ፡ የቸርነቱ ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑን ፡ ስናይ ፡ ተስፋ ፡ እናደርግላታለን ። ከሣህሉ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ በደልዋ ፡ ተፍቆላታል ።

የመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ካህ ናት ፤ በፈጣሪ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ እየተገረመ ፤ መልካም ጸሎተ ፡ ፍትሐት ፡ አድርሰውላታል ። ቤተ፡ክርስቲያን፡ ለመሳለም ፡ ተሰብስቦ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብም ፡ የሣህሉን ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ ሲሰማ ፡ አንዳንድ ፡ ዘለላ ፡ ፅንባ ፡

አልነፈጋትም ። በጠቅላላው ፤ እንደአንዲት ፡ ለማኝ ፡ ላይሆን ፡ ከፍተኛ ፡ ሥርዓተ ፡ ቀብር ፡ ተደርጉላታል ።

ግሀሉ ፤ እስከ፡ሰባት ፡ ቀን፡ ድረስ፡ ጸሎተ፡ቅዳሴ፡ ከሴፈ ጸሎት ፡ በኋላ ፤ ወደአገሩ ፡ ተመልሶ ፤ ከዚያም ፡ ትልቅ ፡ መሰናዶ ፡ በማዘጋጀት ፡ እርሙን ፡ በሚገባ ፡ አወጣ ። ዘመድ ፤ አዝማድ ፤ ወዳጅ ፡ ጉረቤት ፤ የሚያውቃትም ፡ የማያውቃትም ፤ በለፋፊ ፡ ታድሞ ፡ በመርገዶ ፡ ዋይታ ፡ ሲረገድ ፡ ሰነበተ ። አስረስም ፡ አባቱ ፡ ሲያለቅስ ፡ በመመልከቱ ፡ በሕፃን ፡ ሰሜቱ ፡ አብሮ ፡ አልቅሷል ።

ይህ ፡ በሆነ ፡ ከጥቂት ፡ ሳምንቶች ፡ በኋላ ፤ አንድ ፡ ቀን ግሀሉ ፤ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ምሥጢራዊ ፡ ቀይታ ፡ በማድረግ ፤ የአብባን ፡ ፎቶግራፍ ፡ ከግጥን ፡ አውጥቶ ፡ "እናትህ ፡ ይህች ፡ ነበረች—እንግዲህ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ስለርሷ ፡ እንዳችም፡ነገር፡እንዳትጠይቀኝ፡" አለና፡ አስረዳው። አስረስ ም፡ፎቶግራፉን ፡ባለንግታ፡ እየተመለከተ፡ "አባባ ፤ ቆንጆ፡ ናት ። ከነከበደ ፡ እናቶች ፡ ታሞራቂች ። ትበልጣለችኮ,, ሲል ፡ በኩራት ፡ ተናገረ ። ፎቶግራፉ ፤ ከተጫን ፡ ፎት ፡ ወዲያው ፡ እንደወጣች ፡ የታሳለችው ፡ ስለሆነ ፤ ያ ፡ የመጣትኑት ፡ ለዜትዋ ፡ እንዳለ ፡ ነበር ። ቆንጆናዋ ፡ አይጠ ረጠርም—በርግጥ ፡ ውብ ፡ ነበረች—

ተፈጸመ ።